ያልታተሙ የሰበር ውሳኔዎች

ቅፅ - 1

በዳንኤል ፍቃዱ (ጠበቃና የህግ አማካሪ) ተሰብስቦ በአንድ ተቀናበረ



የሰ.መ.ቁ.203746
መስከረም 27 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግስቱ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- ታሪኩ ኬዶ ኬሪ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካችና በዚህ መዝገብ ያልቀረቡ ሌሎች 9 ተከሣሾችን ጨምሮ ያቀረበው የእርስ በእርስ ጦርነት የማነሳሳት ወንጀል የአሁን አመልካች በተከሰሰበት 5 ክሶች እንዲከላከል ብይን ሰጥቶ ክስና ማስረጃውን አልተከላከልክም ተብሎ ጥፋተኛ ተደርጐ በ16 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ መወሰኑ እና በይግባኝም ውሣኔው ያለመታረሙ የሰር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ ሲሉ አቤቱታ በማቅረባቸው መነሻነት ነው።

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ላይው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካችን 9ኛ ተከሣሽ በማድረግ፣ ሌሎች 9 ተከሣሾችን ጨምሮ በአጠቃላይ 6 ክሶች የቀረቡባቸው ሲሆን፣ አመልካች ግን 6ኛ ክስ ላይ አልተጠቀሰም።

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እሱም የነበረ መሆኑን፣ ዳኜ ፈይራ የተባለው ሰው ተገድሎ መገኘቱን ማን እንደገደለው ግን እንደማያውቅ፣ አመልካች ንብረት ማውደሙን እና ወደ ተጠለሉ ሰዎች እየመራ የወሰደ መሆኑን መስክሯል። 7ኛ የዐቃቤ ህግ ምስክር በበኩሉ የአሁን አመልካችን በችሎት ለይቶ ማሳየቱን፣ በጊዜው የኦሮሞ ልጆችን ሲያሯሩጥ የነበረ መሆኑን ማሳ ውስጥም ሰው ሞቶ መገኘቱን እና በተጠለሉ ሰዎች ላይም ጉዳት የደረሰ መሆኑን አውቃለሁ ሲል መስክሯል።

ፍ/ቤቱም የቀረበውን ክስ እና ማስረጃን መርምሮ **በ1ኛ** ክስን አስመልክቶ የቀረበው ማስረጃ የእርስ በእርስ ጦርነት ድርጊትን ሊገልጽ የሚችል አይደለም በሚል የቀረበውን ክስ ወደ **አምባጓሮ ወይም በጠብ ተካፋይ** ሆኖ መገኘትን የሚያሳይ ነው በማለት ድንጋጌውን ወደ 577/3/ በመቀየር አመልካችን ጨምሮ 1፣2፣5፣7፣10ኛ ተከሣሾች እንዲከላከሉ፣ **በ2ኛ** ክስ አመልካችን ጨምሮ 2ኛ፣5ኛ፣7፣8ኛ፣ እና 10 የስር ተከሣሾች **በ539/1/ሀ/ ስር** እንዲከላከሉ፣**3ኛ** ክስን አስመልክቶ በድርጊቱ ሰው ያልሞተ መሆኑ ስለተረጋገጠ በሚል የቀረበውን ድንጋጌ ወደ **690/1/ለ/** በመቀየር አመልካችን ጨምሮ 1ኛ፣2ኛ፣5ኛ፣7ኛ፣8ኛ እና 10 የስር ተከሣሾች እንዲከላከሉ፣**4ኛ** ክስን አስመልክቶም ድንጋጌውን በመቀየር በ556/2/ሀ ስር አመልካችን ጨመሮ 1ኛ፣2ኛ፣5ኛ፣8ኛ እና 10ኛ የስር ተከሣሾች እንዲከላከሉ፣ 5ኛ ክስንም እንዲሁ ወደ 556/2/ሀ በመቀየር አመልካችን ጨምሮ ሌሎች ተከሣሾች እንዲከላከሉ ብይን ሰጥቷል። ከዚህ ውጪ ያሉ የስር ተከሣሾችን መከላከል ሳያስፈልጋቸው ክቀረበባቸው ክስ በነፃ አሰናብቷል።

በዚሁ መሠረት አመልካች የመከላከያ ማስረጃውን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ክስና ማስረጃውን አልተከላከለም በሚል እንዲከላከል ብይን በተሰጠበት የህግ ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ ነው ሲል የጥፋተኝነት ውሣኔ በመስጠት ቅጣቱን አስልቶ በ16/ አስራ ስድስት ዓመት/ ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል።

አመልካች በስር ፍ/ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታውን ያቀረበ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል። የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሣኔ በመቃወም ነው።

አመልካች መጋቢት 1 ቀን 2013 ዓ.ም. በጠበቃው አማካይነት የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን፣ ይዘቱም በአጭሩ፡- አመልካች በተከሰሰባቸው የወንጀል አይነቶች ላይ የወ/ሕ/አ/35 ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው ያለመሆኑን፣ በአመልካች ላይ በተጠቀሰው ከባድ ወንጀል ቅጣቱም እድሜ ልክ ወይም ሞት በሚያስቀጣ ላይ በህብረቱ ውስጥ ተገኝተህል በሚል ምክንያት ብቻ አመልካች ምን እንዳደረገ ተለይቶ ባልተከሰሰበት እና ባልተመሰከረበት ጥፋተኛ ተደርጉ ቅጣት መጣሉ፣ ዳኜ ፈየራ የተባለው ሰው በተገደለበት በ6/1/2011 ዓ.ም. አመልካች በቦታው የነበረ ስለመሆኑ ባልተመሰከረበት፣ የዐቃቤ ሕግ 1ኛ፣2ኛ፣4ኛ፣ ምስክሮች አመልካች ከላይ በተጠቀሰው ቀን እንደሌለ መስክረው ባለበት፣ 5ኛ፣5ኛ፣7ኛ፣8ኛ፣10ኛ ምስክሮችም በአመልካች ላይ የመሰከሩት ነገር በሌለበት፣ በ3ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክርም ላይ ከአመልካች ጋር ጠበኛ በመሆኑ እንዳይመሰክር አመልክተን እያለ ጥፋተኛ መደረጉ፣ ተመስክሮበታል እንኳን ቢባል በወ/ሕ/አ/540 መሆን

ሲገባው በ2ኛ ክስ 539/1/ሀ ጥፋተኛ ተደርጐ መቀጣቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሆኑን ስለሚያሳይ ስህተቱ እንዲታረምልኝ ሲል ጠይቋል፡፡

አቤቱታው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች በወ/ሕ/አ/ 35/32/1/ሀ እና 577/3/፣ 539/2/ሀ፣690/1/ለ/ እና 556/2/ሀ/ን ተላልፎ ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በስር ፍ/ቤት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ የተወሰነበትን አግባብነት ከተጠቀሰው ድንጋጌና ከወንጀል ህግ አንቀጽ 23/2/ አንፃር ለመመርመር መዝገቡ ለችሎቱ እንዲቀርብ በመታዘዙ ሊቀርብ ችሏል፡፡

ለተጠሪ መጥሪያ እንዲደርሰው ተደርጐም በ22/11/2013 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡-እንደ አድማና አምባንሮ የመሳሰሉ ወንጀሎች በአንቀጽ 35 2ኛ ሃሣብ አገላለጽ ከዐ/ሕግ የሚጠበቀው በህብረቱ ውስጥ ተከሣሽ መገኘቱን እንጂ ወንጀል አለመፈፀሙን የማስረዳት ሸክም ወደ ተከሣሽ የሚዞር መሆኑን፣ ያቀረብነውን ክስ ከጥርጣሬ በዐዳ መልኩ ያስረዳን በመሆኑ፣ ዳኜ ፈየራ የተባለው ሰው ግድያ ላይ አመልካች ከሌሎች ጋር አብሮ ስለመኖሩ በምስክር ያረጋገጥን መሆኑን፣ 3ኛ፣4ኛ እና 7ኛ ምስክሮች የኦሮሞ ወጣቶችን አመልካች ከሌሎች ጋር በመሆን እያባረረ ወደ በቀለ ኢዶ የጤፍ ማሳ የወሰዱ መሆኑ፣ ማሳ ውስጥም ዳኜ ፈየራ ሞቶ መገኘቱ መመስከሩን፣ የወ/ሕ/አ/539/1/ሀ ወደ 540 ይቀየርልኝ ያለውንም አስመልክቶ አመልካች ከሌሎች ጋር በመስማማት ድርጊቱ የፈፀመ በመሆኑ ድንጋጌውን የሚያቋቁም ከሆነው አንዱ የተሟላ በመሆኑ ሊቀየር የሚገባው አለመሆኑን፣ በማንሳት የስር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ የሰጠው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔ ተገቢ በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ይደረግልኝ ብሏል፡፡

የአመልካች ጠበቃም የቀደመው የሰበር አቤቱታን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገብ ተያይዞ የግራ ቀኙ የጽሁፍ ልውውጥ በዚሁ ተጠናቋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭር በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበውን አቤቱታ መልስ እና የመልስ መልስ በስር ፍ/ቤቶች ከተሰጠው ውሣኔ እና አጠቃላይ ከማስቀረቢያ ነጥቡ አኳያ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

የክርክሩ ሂደት የሚያሳየው በአመልካች ላይ ዐቃቤ ህግ 5 ክሶችን ጠቅሶ ከሌሎች ተከሣሾች ጋር ወንጀል ፈጽሟል ሲል ክስ የመሰረተበት መሆኑን፣ የተጠቀሱት ክሶችም 240/3፣ ለጦርነት የማነሳሳት ወንጀል፣539/1/ሀ/ ከባድ የሰው ግድያ፣690 በንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ፣555/ለ/ በሰው አካል ላይ ከባድ ጉዳት ማድረስ ወንጀል ፈጽሟል ሲል ክስ ያቀረበ ሲሆን አመልካች ክሱን ክዶ የተከራከረ በመሆኑ ምስክሮች ተሰምተው ለጦርነት የማነሳሳት ወንጀሉ ድንጋጌን እና በአካል ላይ ከባድ ጉዳት ማድረስ ወንጀል ድንጋጌን ወደ አምባንሮ እና ቀላል አካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል በመቀየር ሌሎቹ ክሶች በነበሩበት ሁኔታ አመልካች እንዲከላከል ፍ/ቤቱ ብይን የሰጠ በመሆኑ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ በማድረግ ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በአጣሪ ችሎቱ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በጭብጥነት ተይዞ ሊመረመር የሚገባው ዐቃቤ ሕግ እንዳቀረበው ክስ በማስረጃ ስለማስረዳት አለማስረዳቱና አስረድቷል ከተባለም አመልካች ክሱና ማስረጃውን ተከላክሏል ወይንስ አልተከላከለም የሚለውን እና ተጠቅሰው የቀረቡት ድንጋጌዎች በተደራራቢ ክስ የመቅረባቸውን አግባብነት ከወ/ሕ/አ/23/2/ /35 ፣60፣61 እና 141፣577/3/፣ 690 ድንጋጌዎች ጋር ሊመረመር የሚባው ሆኖ ተገኝቷል።

የወ/ሕ/አ/23/2/ በግልጽ የሚደነግገው፡- " አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው።" በሚል ነው።

ከወንጀል ጉዳዮች የክስ ሂደት ጋር በተገናኘ ዓቃቤ ሕግ ሊያከናውናቸው ከሚገቡ ተግባራትና ኃላፊነቶች ዋናው የተከሰሰን ሰው የወንጀል ድርጊቱን በቀረበው ክስ አይነት ስለመፈፀሙ በበቂና አሳማኝ ማስረጃ የማስረዳት ሸክሙን መወጣት ያለበት ስለመሆኑ ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 141 እና 142/1/ ድንጋጌ መረዳት እንችላለን።

የወ/ሕ/አ/577/3/ ፡- " በአምባንሮ ወቅት ከነበረው ሁኔታ የተነሳ በተለይም በጠበኞች መካከል በነበረው ቂም፣የጠብ ማጫር ወይም የስካር ሁኔታ ወይም የጦር መሣሪያዎችን፣ ድንጋዮችን ወይም ማቁሰል ወይም መግደል የሚችሉ ሌሎች ነገሮችን የያዙ ወይም እነዚሁ ነገሮች የተሰጧቸው በመሆኑ በጠቡ መካከል ሰው የቆሰለ ወይም የተገደለ እንደሆነ ቅጣቱ እስከ ከፍተኛው መደበ ቅጣት ሊደርስ ይችላል።" በሚል ይደነግጋል።

በመሰረቱ ተደራራቢ ወንጀሎች በአጠቃላይ በአንድ ጊዜ(ሀሳባዊ መደራረብ) ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ጊዜያት የተፈፀሙ ድርጊቶችን(ቁሳዊ መደራረብ) የሚመለከቱ ሲሆኑ መደጋገም የቁሳዊ መደራረብ መለያ ባህሪ በመሆኑ ተመሳሳይ ድርጊቶች በተለያዩ ጊዜያት ቢፈፀሙ ወይም የተለያዩ ድርጊቶች በተለያዩ ጊዜ ተፈፅመው ቢገኙ ቁሳዊ መደራረብ አለ ለማለት የሚቻል ሲሆን፣ በአንድ ነጠላ ድርጊት ከአንድ በላይ የሆኑ ወንጀሎች መፈፀማቸው የሀሳባዊ መደራረብ መለያ ባህሪ መሆኑን ከወ/ህ/አ.60(ሀ)እና(ለ) ድንጋጌ ይዘት ለመረዳት ይቻላል።

ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ላይ ዐቃቤ ሕግ ጠቅሶ ያቀረበውን ክስ ስንመለከት በፍ/ቤቱ ባይለወጥ ኑሮ 1ኛው ክስ የእርስ በእርስ ጦርነት ማነሳሳት የነበረ ሲሆን ይህን ግን የስር ፍ/ቤት የቀረበው ክስ እና ማስረጃ የተጠቀሰውን መስፈርት አያሟላም በሚል ወደ አምባንሮ ድንጋጌ የቀየረው መሆኑን ነው።

ከላይ እንደተመለከትነው የወ/ሕ/አ/577/3/ ተጠቅሶ አመልካች ጥፋተኛ የተባለ ሲሆን አመልካች በድንጋጌው ጥፋተኛ ሊደረግ የበቃው የወ/ሕ/አ/35 እና 32/1/ሀ ተጠቅሶ ከሌሎች ጋር በህብረት ወንጀሉን ፈጽሟል በሚል በመሆኑ የወ/ሕ/አ/35 በግልጽ የሚደነግገው ደግሞ አድማና አምባንሮ በተደረጉ ጊዜ በህብረቱ ውስጥ መገኘቱ የተረጋገጠበት ሰው የማይቀጣው በወንጀሉ ተካፋይ አለመሆኑን ሊያስረዳ ከቻለ ብቻ መሆኑን ይደነግጋል። በመሆኑም አመልካች አምባንሮው መፈፀሙ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ቁጥራቸው ትንሽ ይሁኑ እንጂ በቀረቡት ምስክሮች በዚህ ህብረት ውስጥ ስለመገኘቱ የመሰከሩበት በመሆኑ

አመልካች አብረውት የተከሰሱት ሰዎች ድንጋይ፣ ዱላ እና ሌሎች ማቁሰል የሚችሉ መሳሪያዎችን በመያዝ እየፎከሩ የኦሮሞ ልጆች ላይ ጥቃት ሲያደርሱ እሱም የተጠለሉ ሰዎች ያሉበትን ቦታ ይመራ የነበረ መሆኑን፣ የኦሮሞ ልጆችን ያባርር የነበረ መሆኑን፣ እንዲሁም መስከረም 6 ቀን 2011 ዓ.ም. በነበረው ረብሻ ላይ የነበረ ስለመሆኑ እና በዚህ የአመልካቾች ድርጊት የአንድ ሰው ህይወት ያለፈ ንብረትም የወደመ መሆኑ በምስክሮች በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጧል።

አመልካች ከላይ በተጠቀሰው ቀን ሰዓትና ቦታ በአምባጓሮው መካከል ስላለመኖሩ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ላይ ጥርጣሬን በሚፈጥር መልኩ ባቀረባቸው ማስረጃዎች አልተከላከለም። በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የቀረበውን 1ኛ ክስ ወደ 577/3/ ቀይሮ ጥፋተኛ ማድረጉ ተገቢ እንጂ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም።

ነገር ግን የስር ፍ/ቤት የወ/ሕ/አ/577/3/ ወንጀል ተፈጽሟል ብሎ ያመነ ከመሆኑ አንፃር ዐቃቤ ሕግ የወ/ሕ/አ/539/1/ሀ/ ጠቅሶ በዛው በተፈጠረ አምባጓሮው ድርጊት ምክንያት ሰው የሞተ መሆኑን በመጥቀስ አመልካች የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት ያቀረበውን ክስ ድርጊቱ የተደራራቢ ወንጀልን መስፈርት የማያሟላ መሆኑን በመረዳት 2ኛው ክስ በ1ኛው ክስ ውስጥ የሚጠቃለል ነው ብሎ መወሰን ሲገባው በአንድ ወንጀል የመስራት ሃሣብ የተፈፀመን ድርጊት ወንጀሉ እንደተደራረበ አድርጐ በ2ኛ ክስ ጥፋተኛ ማለቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል።

መስከረም 7 ቀን 2011 ዓ.ም. አመልካችን ጨምሮ የስር ሌሎች ተከሣሾች የወ/ሕ/አ/35/32/1/ሀ/ እና 690/1/ለ/ ተላልፈው በተለያዩ ሰዎች ንብረት ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን አስመልክቶ በአመልካች ላይ ድርጊቱን ስለመፈፀሙ በማስረጃ የተረጋገጠበት በመሆኑ እንዲሁም ወንጀሉ የተፈፀመበት ቀን አምባጓሮ ከተፈፀመበት ቀን የሚለይ በመሆኑ በዚህ ድንጋጌ አመልካችን ጥፋተኛ በማድረግ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለ በመሆኑ ሊፀና የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም በስር ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ የተፈፀመው መሠረታዊ የህግ ስህተት ሊታረም የሚገባው በመሆኑ የበላይ ፍ/ቤትም የስር ፍ/ቤትን የህግ ስህተት ሳያርም ማለፉ ተገቢ ባለመሆኑ ውሣኔውን በማሻሻል ተከታዩን ወስነናል።

ውሳኔ

1) የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 188605 በ27/5.2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 227015 ጥቅምት 24 ቀን 2012 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ እና ህዳር 30 ቀን 2012 ዓ.ም. የተሰጠው የቅጣት ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሻሽሏል።
2) አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ሊወሰንበት የሚገባው በወ/ሕ/አ/35፣32/1/ሀ እና 577/3 እና 690/1/ለ/ በአምባጓሮ እና በንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል ነው ብለን ወስነናል። አመልካች በወ/ሕ/አ/539/1/ሀ እና 556/2/ሀ ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ሊወሰንበት አይገባም ብለን ወስነናል።

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

3) አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወ/ሕ/አ/577/3/ የአምባንሮ ወንጀል ድንጋጌ፡- “ በአምባንሮ ወቅት ከነበረው ሁኔታ የተነሳ በተለይም በጠበኞች መካከል በነበረው ቂም፣የጠብ ማጫር ወይም የስካር ሁኔታ ወይም የጦር መሣሪያዎችን፣ ድንጋዬችን ወይም ማቁሰል ወይም መግደል የሚችሉ ሌሎች ነገሮችን የያዙ ወይም እነዚሁ ነገሮች የተሰጧቸው በመሆኑ በጠቡ መካከል ሰው የቆሰለ ወይም የተገደለ እንደሆነ ቅጣቱ እስከ ከፍተኛው መደበኛ ቅጣት ሊደርስ ይችላል።” በሚል ይደነግጋል።

በንብረት ላይ ከባድ ጉዳት ማድረስ ወንጀልን የሚደነግገውና አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወ/ሕ/አ/690/1/፡- “ ወንጀሉ በወንጀል ክስ አቅራቢነትና ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና መቀጮ ሊያስቀጣ በሚችል ፡- ለ/ ወንጀሉ የተፈፀመው በዛቻ፣በኃይል ወይም በብዙ ሰዎች ይልቁንም ሁከት፣ የሥራ መዘጋት ወይም የሥራ ማቆም አድማ በተነሳ ጊዜ በሠራተኞች ወይም በአሰሪዎች እንደሆነ----” በሚል ይደነግጋል።

ከላይ በተገለፀው ድንጋጌ መሠረት በተፈፀመው የአምባንሮ ወንጀል ምክንያት ሰው የተገደለ እንደሆነ አጥፊው በወ/ሕ/አ/577/3/ ስር በተደነገገው መሠረት ቅጣቱ እስከ ከፍተኛው መደበኛ ቅጣት ሊደርስ ይችላል”፡ ይህም ማለት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 539/1/ ስር እንደተደነገገው ሰው በመግደል ወንጀል ከፍተኛ መደበኛ ቅጣት ፅድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም ሞት ነው። አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 577/3/ ስር በሞት ወይም በእድሜ ልክ እስራት ሊያስቀጣ በሚችል ወንጀል ጥፋተኛ ስለተባሉ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 690/1/ ስር ጥፋተኛ የተባሉበት ቅጣት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 184/1/ሀ/ መሠረት ከፍተኛው መደበኛ ቅጣት ውስጥ የተጠቃለለ ነው።

በመሆኑም የሞት ቅጣት ወይም የእድሜ ልክ እስራት ቅጣት በሌሎች ተደራራቢ ወንጀሎች ምክንያት ሊጣሉ የሚገባቸውን የቅጣት ዓይነቶች ሁሉ አካቶ የሚይዝ ስለመሆኑ በወ/ሕ/አ/ 184/1/ሀ/ ስር የተደነገገ በመሆኑ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበትን ተደራራቢ ወንጀል ማለትም የወ/ሕ/አ/690/1/ለ/ ቅጣቱ ሲሰላ ታሳቢ አይደረግም ብለን ወስነናል።

4) አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ የቅጣት መነሻው እድሜ ልክ እስራት በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት ደረጃ 38 ተይዞ ቅጣቱ መሰላቱ እና ቅጣት መወሰኑ ተገቢ ነው ብለን ወስነናል።

ሆኖም ግን በስር ፍ/ቤት ከተያዘው 3 የቅጣት ማቅለያ በተጨማሪ ከአጠቃላይ ክርክሩ እንደተገነዘብነው አመልካች ይህን ድርጊት እንዲጸትም የገፋፋው አስቀድሞ በጋሞዎች ላይ ተፈጽሞ የነበረው ጉዳት መሆኑን መረዳት የሚቻል በመሆኑ ቅጣቱም ሊጣል የሚገባው

ፍትህን ሊያሰፍን በሚችል መልኩ ሆኖ ስላገኘነው ይህን ወንጀል ለመፈፀም ያነሳሳውን ምክንያት እንደ አንድ የቅጣት ማቅለያ በመውሰድ 4 የቅጣት ማቅለያ እንዲያገና ከተያዘው የቅጣት መነሻ ደረጃ ላይ መቀነስ ተገቢ ነው ብለን የቅጣት ደረጃውን ወደ ደረጃ 34 ዝቅ አድርገን በ15/ አስራ አምስት/ ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ተደርጐ ቅጣቱ ተሻሽሎ ተወስኗል።

ትዕዛዝ

- የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች እና አመልካች ለታሰረበት ማረሚያ ቤት እንዲደርስ ታዟል።
- አመልካች የታሰረበት ማረሚያ ቤትም አመልካች ከዚህ ቀደም በዚህ ጉዳይ የታሰረው ታሳቢ ተደርጐ በተሻሻለው ውሣኔ መሠረት ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ታዟል።
- የውሣኔው ግልባጭ አመልካች ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት በፍ/ቤቱ መልእክት ክፍል በኩል እንዲደረስ ታዟል።
- መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ/መ/ቁ. 104131

መጋቢት 27 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ

መ/ስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- ፓስተር ሚሊዮን ጎንጤ ጠበቃ መስፍን ጌታቸው ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አብዱልቃድር አብዱራህማን - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የንብረት ክርክርን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘት ባጭሩ በሰበታ ከተማ ቀበሌ 04 የሚገኝ በካርታ ቁጥር ሰ/23802/2001 የሚታወቅ አዋሳኙ በሰሜን መንገድ፣ በሌሎች አቅጣጫዎች ምሪት ከሆነ 500 ካ.ሜ ይዞታቸው ላይ አቶ ሽምሱ አወል ከወኪላቸው አቶ ሀሰን አህመድ ጋር በ16/02/02 በተደረገ ውል ሽጠውልኝ በስሜ አዙሬ በእጅ አስገብቼ ስጠቀምበት የነበረውን ቤት ተከሳሽ በቤቱ ካስቀመጥኩት አቶ ሀሽም ሁሴን

ላይ በኃይል የቤቱን ቁልፍ ተቀብሎ ገብቶ ይዞት ስለሚገኝ ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ቀን ድረስ በወር ብር 300.00 ኪራይ ታስቦ የአስራ ሰባት ወራት ኪራይ ብር 5700.00 ከፍለው ቤቱን እንዲለቁ እንዲወሰን ዳኝነት የተጠየቀበት ነው።

የአሁን አመልካች በበኩላቸው ይዞታውን የሸጡላቸው አቶ ዳንኤል ኃይሉ በ1999 ዓ/ም ከመንግስት በሊዝ ያገኙት እና ሰርቪስ ቤት ሰርተውበት የነበረ መሆኑን፣ የገዙትም በውል አዋዋይ ፊት በብር 270000.00 መሆኑንና የግንባታ ፈቃድ በመውሰድ ግንባታ እያካሂዱበትም እንደሚገኙ፣ የካርታ ቁጥሩም L/1232/200 መሆኑን፣ የከሳሽ ካርታ የተለየ ቁጥር በመሆኑ ሌላ ቦታ ሊሆን እንደሚችል፣ ከሳሽ ገዛሁ ያሉበት ውል በህግ ፊት ተቀባይነት እንደለሌው እና ካርታውንም እንደሚጠራጠሩ በመግለጽ መልስ ሰጥተዋል።

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ ቤቱን በሃይል እንዳልያዙ ያልገለጹ መሆኑ፣ የክፍሉ አስተዳደር በሁለቱም ተከራካሪዎች ፋይል ውስጥ ቦታውን የሚገልጽ ሳይት ፕላን ስለሌለ ከሁለቱ ካርታዎች መካከል የትኛው ካርታ አሁን ክርክር ባስነሳው መሬት ላይ እንደተሰጠ ለማወቅ አስቸግሮናል በማለት የገለጸ በመሆኑ፣ ፍርድ ቤቱ እንደተመለከተው በክሱ ከተጠቀሰው አዋሳኝ ጋር በአራቱም አቅጣጫ የሚመሳሰለው የከሳሽ ካርታ ሲሆን ተከሳሽ በውል ግዥ የፈጸመበት መሬት አዋሳኝ በደቡብ መንገድ የሚዋሰነው መሆኑን የሚገልጽ በመሆኑ፤ የተሻለ ክብደት ያለው የከሳሽ ማስረጃ ነው በማለት ተከሳሽ አከራካሪውን ንብረትና ይዞታ ለቀው ለከሳሽ እንዲያስረክቡ እና ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ እስከሚለቁ ድረስ በወር ብር 300.00 ታስቦ ከወለድ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍሉ ወስኗል።

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ጉዳዩን በይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኝ ሰሚው ችሎት ግራ ቀኙን አከራክሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔን አጽንቷል። የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ችሎት በበኩሉ አመልካች ንብረቱ እንዲለቁ የተሰጠውን ውሳኔ በመጽናት የቤት ኪራይ ገንዘቡን በተመለከተ አሻሽሎ በተጠየቀው ዳኝነት መሰረት ብር 5700.00 ከነወለዱ እንዲከፍል ወስኗል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው። አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ክስ የቀረበበትን ቤትና ቦታ በሊዝ ስርዓት ካገኙት አቶ ዳንኤል ኃይሉ ላይ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በኩል በተደረገ ውል የገዙትና በእጃቸው ይዘው ከመንግስት በተሰጣቸው የግንባታ ፈቃድና ፕላን መሰረት ግንባታ እያከናወኑበት ያለ መሆኑን፣ ልዩ ልዩ ክፍያዎችን በስማቸው የከፈሉ እና በስማቸው የሊዝ ስሪት ካርታ ተሰርቶ የተሰጣቸው መሆኑን፣ ካርታው

ክርክር የተነሳበትን ቦታ በትክክል የሚያመለክት እስከሆነና ይህ ሳይሰረዝ ጸንቶ እስካለ ድረስ የቦታ አቀማመጥ የአዋሳኝ ልዩነት አለ መባሉ በምንም መልኩ አመልካች ባለይዞታ መሆናቸው ተረጋግጦ የተሰጠውን ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ዋጋ አልባ ሊያደርግና የይዞታ መብታቸውን መና ሊያስቀር እንደማይችል በመግለጽ እንዲሁም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ ንብረታቸው መሆኑንና በሃይል ተግባር ያልያዙ ስለመሆኑ ማስረጃ ይሆን ዘንድ እማኞችንም ዘርዝረው ያቀረቡ ቢሆንም የስር ፍርድ ቤት ያለ በቂ ምክንያት ምስክሮችን እንኳ ሳይሰማ ህጋዊ የሊዝ ባለይዞታና ባለንብረት የሆኑበትን ለቀው እንዲያስረክቡ እና ኪራይ እንዲከፍሉ የተሰጠው ውሳኔ ህግን መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ እንዲሻር ጠይቀዋል።

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ክርክር የተነሳበት የከተማ ቦታ መንግስት በሊዝ ክፍያ የሚያስተላልፈው መሆኑ ተረጋግጦ እያለ፤ አመልካችም በሊዝ ክፍያ ከመንግስት ካገኘ ሰው ገዝተው እየሰሩ መሆኑ እየታወቀ፤ የሊዝ ይዞታ ማረጋገጫም እያላቸው፤ ካርታውም ህገ ወጥ ነው ሳይባል፤ የቦታ አቀማመጥ ልዩነት አለ የሚል ምክንያት ተሰጥቶ በሊዝ ካልያዘ ሰው ገዛሁ ለሚሉት ተጠሪ እንዲያስረክቡ የመወሰኑን አግባብ ለማጣራት ሲባል አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል።

በዚህ መሰረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ቀርበው በሰጡት መልስ አቶ ዳንኤል በሊዝ ከመንግስት ያገኙት መሬት አሁን ክርክር የተነሳበትን መሬት አለመሆኑን፤ አመልካች በይዞታው ፕላንና የግንባታ ፈቃድ ተሰጥቶኝ ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ ግንቦታ ፈጽሚያለሁ ቢሉም የፈጸሙት ግንባታ ጅምር መሰረት ከመሆኑም በላይ ፈቃድና ፕላኑ ክርክር ለተነሳበት ቦታ የተሰጠ መሆኑ ስላልተረጋገጠ፤ በተጠሪ ይዞታ ላይ ካርታ ስላሰሩ ብቻ መብት የማይሰጣቸውና ደንብ ከሚፈቅደው ውጭ የተሰራ ስለሆነም በፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1195 እና 1196/ሀ/ መሰረት በካርታ የሚኖረውን የባለይዞታነት ግምት የሚያሰጥና ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፤ የሰው ምስክሮች አለመስማማቱም በፍትህ ላይ ያደረሰው ጉዳት የሌለና በጉዳዩም የሚያመጣው ለውጥ ባለመኖሩ ውሳኔው ሊነቀፍ የሚገባው አለመሆኑን፤ ለተጠሪ የሸጡላቸው አቶ ሽምሱ አወል በምሪት ያገኙት መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ በምን ስሪት እንደያዙት አልተረጋገጠም እንዲሁም የሊዝ ስሪት የተሻለ መብት ያረጋግጣል ተብሎ የቀረበው ክርክር ተቀባይነት እንደሌለው፤ በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤቶች የቀረቡትን በቂ ማስረጃዎች በአግባቡ መዝነው ያሳለፉት ውሳኔ በመሆኑ የሚነቅፍ አይደለም ተብሎ ቅሬታው ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል። አመልካችም ክርክርራቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል።

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል። እንደመረመርነው የስር

ፍርድ ቤቶች አከራካሪውን ይዞታና ንብረት በተመለከተ ውሳኔ ላይ የደረሱት ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ስለመሆን አለመሆኑ በመመልከት ለተያዘው ጉዳይ እልባት መስጠት ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል።

ከክርክሩ መረዳት እንደሚቻለው ሁለቱም ወገኖች ይዞታውን በህጉ አግባብ ከአስተዳደርሩ አግኝተዋል ከሚሏቸው ሰዎች የገዙ መሆኑንና ለይዞታው ተገቢውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ያገኙት መሆኑን በማንሳት ተከራክረዋል።

በመሰረቱ አንድ ሰው አንድ ንብረት ለሌላ ሰው በህጋዊ መንገድ ሊያስተላልፍ የሚችለው በንብረቱ ላይ በሕጉ ጥበቃ የሚደረግለት መብት ሲኖረው ብቻ መሆኑ የሚታወቅ ነው። ይህም ማለት በህግ ጥበቃ የማይደረግለት ወይም የሌለ መብት ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ሊተላለፍ አይችልም። ይህ ተቀባይነት ያለው የህግ መርህ ነው። በሌላም በኩል በፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1195 እንተደነገገው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የምስክር ወረቀት ሲሰጥ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ባለሃብት ሁኖ ሊገመት እንደሚገባ ተመልክቷል። ይህን ማስረጃ የያዘ ሰው ደግሞ በሕግ ጥበቃ የተደረጉትን መብት በሕጋዊ መንገዶች ለሌላ ለማስተላለፍ ስለሚችል ሃብቱን በሕጉ አግባብ ከሰጠ ተግባሩ ሕጋዊ ውጤት ይኖረዋል። ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሕ*ቁጥር 1195 ስር የተመለከተው የሕግ ግምት ፍፁም የሆነ ወይም ደምዳሚ ማስረጃ አይደለም። ግምቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ስር የተመለከቱት ሁኔታዎች ስለመኖራቸው በማናቸውም ማስረጃ በአግባቡ በማረጋገጥ ሊስተባበል የሚችል የሕግ ግምት ነው። በመሆኑም አንድ ሰው በአስተዳደር አካል የተሰጠ ካርታ በመያዙ ብቻ በካርታው የተጠቀሰው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሕጋዊ ባለሃብት እንደሆነ ሕጉ ግምት ቢወስዱለትም ይህ ግምት ግን ካርታው የተሰጠበትን አግባብ ከደንቡ፣ ከአሰራሩና ከስልጣኑ ውጪ እንዲሁም በማይረጋ የምስክር ወረቀት መሰረት ማስረጃው ተሰጥቶ ከሆነ ይህንኑ በማንኛውም ማስረጃ በማረጋገጥ የሕጉን ሕሊናዊ ግምት ማፍረስ እንደሚቻል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል። ከዚህም ሌላ ሊሰረዝ ሲገባ የአስተዳደሩ ክፍል ሳይሰርዘው የቀረውን ካርታ /የባለሃብትነት ምስክር ወረቀት/ በማመን በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ አንድ መብት ያገኘ ሰው ለሚደርስበት ጉዳት አስተዳደሩ ኃላፊነት እንደሚኖርበት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1197 ስር ተደንግጓል። የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004 የከተማ ቦታ በሉዝ እንዲይዝ ተፈቅዶለት አግባብ ካለው የአስተዳደሩ አካል ጋር የሊዝ ውል የተፈራረመ እና የሊዝ ይዞታ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የሊዝ መብቱን የሚያስተላልፍበት እንዲሁም የሊዝ ይዞታው የሚቋረጥበት ዝርዝር ድንጋጌዎች ይዟል።

በተያዘው ጉዳይ በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ እነዚህን የሕጉን ግልፅ ድንጋጌዎች እና መርሆች መሰረት ባደረገ መልኩ በሕጉ ጥበቃ የሚደረግለት መብት ካለው ሰው የተላለፈለት ተከራካሪ ወገን የትኛው ስለመሆኑ፤ ከሕግ እና ደንቡ ውጭ የተሰጠ ካርታ ስለመኖሩ፤ ከሕግ እና ደንቡ ውጭ የተሰጠ ካርታ ቢኖር ኃላፊነቱን ስለሚወስደው አካል እና በአከራካሪው ይዞታ ላይ በሰፈረው ንብረት ስለሚኖረው ውጤት ሁሉ አግባብነት ባለው ማስረጃ በዝርዝር ተጣርቶ ውሳኔ ሊሰጥበት ሲገባ በዚህ አግባብ ታይቶ አለመወሰኑን ተረድተናል። አከራካሪውን ይዞታ በከተማው ክልል የሚገኝ ተለይቶ የማታወቅ መሬት ስለመሆኑ እስከታወቀ ድረስ ፍርድ ቤቱ የቀድሞውን ትክክለኛ ባለይዞታ፤ ይዞታውን ያገኘበት መንገድና፤ ያስተላለፈበትን ሁኔታ ሁሉ ከግራ ቀኙ ተከራካሪዎች ከሚቀርቡት ማስረጃዎች እና ይዞታውን የሚመለከቱ ማህደሮችን ከተገቢው አካል በማስቀረብ፤ እንዲሁም ስለጉዳዩ ሙያዊ ምስክርነት ሊሰጡ የሚችሉ የሙያ ምስክሮችን በመስማት ውሳኔ ላይ መድረስ እየተቻለ እንዲህ ዓይነት እና ተመሳሳይ ጥረት ሳይደረግ፤ ተከራካሪዎቹ ዘርዝረው ያቀረቧቸው ማስረጃዎች እንኳ ያለምክንያት ተጠቃለው ሳይሰሙ፤ በአንድ አዋሳኝ በኩል ልዩነት ታይቷል ተብሎ ውሳኔ ላይ መደረሱ የክርክር አመራር ስርዓቱን እና ከላይ የተጠቀሱትን የሕጉን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የተከተለ አይደለም። ግራ ቀኙን የሚያለያያቸው ፍሬ ነገር ተገቢው ትጋት ተደርጎበት በማስረጃ በአግባቡ እንዲጣራ ሳይደረግ የሚሰጥ ውሳኔ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ሊባል የሚችል ባለመሆኑ ውሳኔው የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል። ተከታዩንም ወስነናል።

ው ሳ ኔ

1. በፌንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0622 ጥቅምት 26 ቀን 2005 ዓ.ም፤ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 141261 በ17/07/05 ዓ.ም፤ እንዲሁም በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 164113 በ23/10/2006 ዓ.ም የተሰጡት ውሳኔዎች በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሰረት ተሽረዋል።
2. የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ አከራካሪው ይዞታ በምሪት ወይም በሊዝ በሕጋዊ መንገድ አስቀድሞ የተሰጠው ለማን ነው፤ ይህን ይዞታ በሕጉ አግባብ በሽያጭ ለማስተላለፍ መብት ኑሮት ያስተላለፈው ማን ነው፤ ከሕግ ውጪ የተሰጠ ካርታ ቢኖር ኃላፊነቱን ስለሚወስደው አካል እና በአከራካሪው ይዞታ ላይ በሰፊው ንብረት የሚኖረውን ውጤት እንዲሁም ክክርክሩ የሚነሱ ሌሎች ነጥቦች በግራ ቀኙ ማስረጃ እና ተገቢነት ባለው ማስረጃ ሁሉ በማጣራት እንዲወሰን ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 343/1/ መሰረት መልሰናል። የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው።

3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።
መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ

ሰ/መ/ቁ. 105332

28 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች አቶ ገብረመድህን ግዛቸው አልቀረቡም

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ መሰረት መኮንን አልቀረቡም

2. አቶ ፍቅርሰው አድማሱ አልቀረቡም

መዝገቡ መርምረን የሚከተለው ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 80678 ሚያዝያ 1 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ብይንና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 139926 ሰኔ 17 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የስራ ውል ከህግ አግባብ ውጭ ተቋርጧል በሚል መንገድ የቀረበ ክስ የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል

1. የክርክር መነሻ አመልካች ኪንግ ማክሬል ካሬና ሬስቶራንት በሚል መጠሪያ በሚታወቀው የንግድ ድርጅት ውስጥ እንዲሰራ ሁለተኛ ተከሳሽ /ሁለተኛ ተጠሪ/ ያቀረበውና ሰኔ 24 ቀን 2005 ዓ.ም ሁለተኛ ተከሳሽ ከስራ ያባረረው መሆኑን ገልፆ፣ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሰረት መብቱ እንዲከበርለት ሀምሌ 29 ቀን 2005 ዓ.ም የተባለ ክስ አቅርቧል፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ ከከሳሽ ጋር የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት የለኝም፡፡ የኪንግማክሬል ካፌና ሬስቶራንት ባለቤት አይደለሁም የከሳሽም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አሰሪ አይደለሁም የሚል የክስ መቃወሚያ በማቅረቡ ከሳሽ /አመልካች/ የካቲት 21 ቀን 2006 ዓ.ም ክሱን በማሻሻል በሁለቱ ተጠሪዎች ላይ ክሱን በማቅረብ ፍርድ ቤቱ ከሁለቱ ሰዎች ማንኛቸው ለስራ ውሉ ከህግ አግባብ ውጭ መቋረጥ ኃላፊ እንደሆኑ ለይቶ እንዲወሰንለት ጥያቄ አቅርቧል፡፡

2. ተጠሪ ክሱን አሻሽሎ ካቀረበ በኋላ አንደኛ ተጠሪ ቀርቦ ከሳሽ የማይመለከተውን ሁለተኛ ተከሳሽ ይዘው ክስ አቅርቦ የቆየ መሆኑን ገልፆ በእኔ በድርጅቱ ባለቤትና አሰሪው ላይ ክስ ያቀረበው የስራ ውሉ ከተቋረጠ ከስድስት ወር በኋላ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ አቅርባለች የስር ፍ/ቤት ሁለተኛውን ተከሳሽ ያሳደገችው አንደኛ ተከሳሽ እንደሆነች የገለፀች መሆኗንና ሁለተኛ ተከሳሽ የንግድ ድርጅቱን

ስትከፍት የተወሰነ ገንዘብ ያረዳትና ያንግድ ድርጅቱን ያየከፈተላት መሆኑን ከሳሽንም ያቀረጠረዉ ሁለተኛ ተከሳሽ መሆኑን ግራ ቀኙ ባደረጉት ክርክር እንደተገለፀ፤ በዉሣኔዉ አስፍሮ ይህም ሁለተኛ ተከሳሽ የድርጅቱ ባለቤት ወይም ሥራ እስኪያጅ መሆኑን ያማያሳይ በመሆኑ ከሳሽ በሁለተኛዉ ተከሳሽ ላይ ክስ በማቅረብ የምችልበት መብትና ጥቅም የለዉም አንደኛ ተከሳሽ ያቀረበችዉን ይርጋ መቀወሚያ በተመለከተ ካሳሽ ሀምሌ 29 ቀን 2005 ዓ.ም ክስ ያቀረበዉ ጉዳዩ በማይመለከተዉ በሁለተኛዉ ተከሳሽ ላይ ነዉ ከሳሽ በድርጅቱ ባለቤት በአንደኛ ተከሳሽ ላይ ክስ ያቀረበዉ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162(3) የተደነገገዉ ያስድስት ወር የይርጋ የጊዜ ገደብ ካለፈ ቦኋላ የካቲት 21 ቀን 2006 ዓ.ም አሻሽሎ ባቀረበዉ ክስ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነዉ በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ብይን ቅርበመመሰንት ይግባኝ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሣኔ አፅንቶታል፡፡

3. አመልካች መስከረም 13 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች የሥራ ዉልከተዋዋልኩትና ከቀጠረኝ ሁለተኛ ተጠሪ ላይ በወቅቱ የክስ ማመልከቻዉን አቅርበዉ አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ ዘመዳሞች እንደሆነና ሁለተኛ ተጠሪ የድርጅቱን ሥራ በማስተዳደር የንግድ ስራዉን በመምራት አስተዋፅኦ ያለዉ መሆኑ አልተካደም ይህ ብሆነ የመጀመሪያዉ ሀምሌ 29 ቀን 2005 ዓ.ም የቀረበዉት ክስ የይርጋ የጊዜ ገደብ መቀጠሩን የማይቋርጠዉን ሆኖ እያለ፤ አንደኛ ተጠሪን የከሰሰዉ የካቲት 21 ቀን 2006ዓ.ም በሚል ምክንያት ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የሰጡት ብይን መሠረታዊ የሐግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንድታረምልኝ በማለት አመልክቷል ተጠሪዎች ጥር 22 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡ ተጠሪዎች አመልካች የንግድ ድርጅቱን ባለንብረት አጣርቶ ክስ ማቅረብ ሲገባዉ የማይመለከተዉን ሰዉ ክሶ አንደኛ ተጠሪን በሕጉ የተመለከተዉ ስድስት ወር ካለፈ በኋላ በክስ አካቲቶ ክሱን አሻሽሎ የቀረበ በመሆኑ ክስ በይርጋ ቀሪ ነዉ መባሉ ተገቢ በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የካቲት 24 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀዉ ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ክሱ በይርጋ ቀሪ ነዉ በማለት ዉድቅ ማድረጋቸዉ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ኪንግ ማርኬል ካፌና ሬስቶራንት በሚል ስያሜ በሚታወቀው የንግድ መደብር ሠራተኛ ሆኖ መምራቱንና አመልካችንም በሠራተኝነት፤የቀጠረው ሁለተኛው ተጠሪ እንደነበር፤ አንድኛ ተጠሪ ሁለተኛ ተጠሪን ያሣደገችው መሆናና አንደኛ ተጠሪ ካፌና ሬስቶራንቱን ስትከፍት ሁለተኛው ተጠሪ በገንዘብ የረዳት መሆኑ፣ የንግድ መደብሩ አንደኛ ተጠሪ ስም የንግድ ፈቃድ ያወጣለትና የንግድ ድርጅቱ ለባቤት አንደኛ ተጠሪ መሆኗ የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው አረጋግጦ ያሰፈረው ፍሬ ነገር ነው። ከዚህ በተጨማሪ ሁለተኛ ተጠሪ የንግድ ሥራውን እንድንሠራ ከአንደኛ ተጠሪ በሰነድ የተሰጠው የውክልና ሥልጣን የሌለና በሕግ አግባብ የንግድ መደብሩ ሥራ አስኪያጅ ያለመሆኑና ነገር ግን አንደኛ ተጠሪ የምትሠራውን የኮፌና ሬስቶራንት ሥራ በመምራት በኩል በተግባር ተጨባጭ እገዛ ሲያደርግ የነበረ መሆኑ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመረዳት ይቻላል።

6. ይህም በመሆኑ አመልካች የካፌውና ሬስቶራንቱ ባልተቤት ሁለተኛ ተጠሪ ነው በሚል እምነት ሀምሌ 29 ቀን 2005 ዓ.ም የሥራ ውሉ ከሕግ አግባብ ውጭ የተቋረጠ መሆኑን ገልፆ ክስ አቅርቧል። ይህም አመልካች በሁለተኛው ተጠሪ ላይ ክስ ያቀረበው የንግድ መደብሩ ባለቤትና እርግጠኛ አሠሪው ሁለተኛው ተጠሪ ነው በሚል እምነትና ቅን ልቦና መሆኑን የሚያሳይ ነው የቅን ልቦና በይርጋ ስህተት ምክንያት ተከሳሽ መሆን በማይገባው ሰው ስም ክስ ያቀረበ በሆነ ጊዜ የተገቢው ሰው ስም በተከሳሽነት እንዲተካ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ መስጠት እንደሚችል በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 40 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገ ሲሆን ይህም ሲሆን ክሱ ተሻሽሎ በተተኪነት በሚገባው ሰው እንዲደርስ ሊደረግ እንደሚችል የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 40 ንዑስ አንቀፅ 3 ይደነግጋል ፍርድ ቤቱ ከሳሽ የተከሳሽን ስም የተሳሳተው በቅን ልቦና መሆኑን በማመን ክሱን በማሻሻል በገዳዩ ትክክለኛ ተከሳሽ መሆን ያለበትን ሰው እንድተካ ወይም እንድጨምር ከፈቀደለት ከሳሽ በስህተት የተከሳሽን ስም ሣያካትት ክስ ካቀረበበት ጊዜ ጀምሮ የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚያቋርጠው መሆኑን በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ 40 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 3 ድንጋጌና ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 164 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ በጣምራ በማየት ለመረዳት ይቻላል።

7. ከዚህ አንፃር በአንደኛ ተጠሪና በሁለተኛ ተጠሪ ባለቸው ቅርብ ግንኙትና ሁለተኛ ተጠሪ የአንደኛ ተጠሪ ካፌና ሬስቶራንት የንግድ ሥራ በሚያደርገው ንቁ ተሣትፎ ምክንያትና አመልካችንም የቀጠረው ሁለተኛ ተጠሪ በመሆኑ ምክንያት ፤ ሶስተኛ ተጠሪ የንግድ መደብሩ ባለቤትና አሠሪ ነው በሚል ቅን ልቦና ተነስቶ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ክስ ካቀረበበት ሀምሌ 29 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ ጉዳዩ እስከተወሰነበት

ጊዜ ድረስ የይርጋ የጊዜ ገደቡ መቆጠሩ የሚቋረጥ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር40 ንዑስ አንቀፅ1 እና ንዑስ አንቀጽ3 መሠረት ክሱን በማሻሻልና የአንደኛ ተጠሪን ስም በተከሳሽነት ጨምሮ የካቲት 21 ቀን2006 ዓም ያቀረበውን ክስ ብቻ በማመልከት ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የሰጠውን ብይን ሣያርም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ማጥናቱ ከላይ የገለጽናቸውን የህግ ድንጋጌዎች ይዘት እጋዊ ውጤት ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሸሯል
2. አመልካች ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 40 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ3 እደዚሁም የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 164 ንዑስ አንቀጽ1 መሠረት ውሣኔ ሰጥተናል፡፡
3. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችንና የአንደኛ ተጠሪን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ውሣኔ እዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁጥር 341(1) መሠረት መልሱን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ በየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/መ

ሰ/መ/ቁ. 105332

28 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች አቶ ገብረመድህን ግዛቸው አልቀረቡም

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ መሰረት መኮንን አልቀረቡም

2. አቶ ፍቅርሰው አድማሱ አልቀረቡም

መዝገቡ መርምረን የሚከተለው ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 80678 ሚያዝያ 1 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ብይንና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 139926 ሰኔ 17 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የስራ ውል ከህግ አግባብ ውጭ ተቋርጧል በሚል መንገድ የቀረበ ክስ የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል

1. የክርክር መነሻ አመልካች ኪንግ ማክሬል ካሬና ሬስቶራንት በሚል መጠሪያ በሚታወቀው የንግድ ድርጅት ውስጥ እንዲሰራ ሁለተኛ ተከሳሽ /ሁለተኛ ተጠሪ/ ያቀረበውና ሰኔ 24 ቀን 2005 ዓ.ም ሁለተኛ ተከሳሽ ከስራ ያባረረው መሆኑን ገልፆ፣ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሰረት መብቱ እንዲከበርለት ሀምሌ 29 ቀን 2005 ዓ.ም የተባለ ክስ አቅርቧል፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ ከከሳሽ ጋር የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት የለኝም፡፡ የኪንግማክሬል ካፌና ሬስቶራንት ባለቤት አይደለሁም የከሳሽም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አሰሪ አይደለሁም የሚል የክስ መቃወሚያ በማቅረቡ ከሳሽ /አመልካች/ የካቲት 21 ቀን 2006 ዓ.ም ክሱን በማሻሻል በሁለቱ ተጠሪዎች ላይ ክሱን በማቅረብ ፍርድ ቤቱ ከሁለቱ ሰዎች ማንኛቸው ለስራ ውሉ ከህግ አግባብ ውጭ መቋረጥ ኃላፊ እንደሆኑ ለይቶ እንዲወሰንለት ጥያቄ አቅርቧል፡፡

2. ተጠሪ ክሱን አሻሽሎ ካቀረበ በኋላ አንደኛ ተጠሪ ቀርቦ ከሳሽ የማይመለከተውን ሁለተኛ ተከሳሽ ይዘው ክስ አቅርቦ የቆየ መሆኑን ገልፆ በእኔ በድርጅቱ ባለቤትና አሰሪው ላይ ክስ ያቀረበው የስራ ውሉ ከተቋረጠ ከስድስት ወር በኋላ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ አቅርባለች የስር ፍ/ቤት ሁለተኛውን ተከሳሽ ያሳደገችው አንደኛ ተከሳሽ እንደሆነች የገለፀች መሆኗንና ሁለተኛ ተከሳሽ የንግድ ድርጅቱን

ስትከፍት የተወሰነ ገንዘብ ያረዳትና ያንግድ ድርጅቱን ያየከፈተላት መሆኑን ከሳሽንም ያቀረጠረዉ ሁለተኛ ተከሳሽ መሆኑን ግራ ቀኙ ባደረጉት ክርክር እንደተገለፀ፤ በዉሣኔዉ አስፍሮ ይህም ሁለተኛ ተከሳሽ የድርጅቱ ባለቤት ወይም ሥራ እስኪያጅ መሆኑን ያማያሳይ በመሆኑ ከሳሽ በሁለተኛዉ ተከሳሽ ላይ ክስ በማቅረብ የምችልበት መብትና ጥቅም የለዉም አንደኛ ተከሳሽ ያቀረበችዉን ይርጋ መቀወሚያ በተመለከተ ካሳሽ ሀምሌ 29 ቀን 2005 ዓ.ም ክስ ያቀረበዉ ጉዳዩ በማይመለከተዉ በሁለተኛዉ ተከሳሽ ላይ ነዉ ከሳሽ በድርጅቱ ባለቤት በአንደኛ ተከሳሽ ላይ ክስ ያቀረበዉ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162(3) የተደነገገዉ ያስድስት ወር የይርጋ የጊዜ ገደብ ካለፈ ቦኋላ የካቲት 21 ቀን 2006 ዓ.ም አሻሽሎ ባቀረበዉ ክስ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነዉ በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ብይን ቅርበመመሰንት ይግባኝ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሣኔ አፅንቶታል፡፡

3. አመልካች መስከረም 13 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች የሥራ ዉልከተዋዋልኩትና ከቀጠረኝ ሁለተኛ ተጠሪ ላይ በወቅቱ የክስ ማመልከቻዉን አቅርበዉ አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ ዘመዳሞች እንደሆነና ሁለተኛ ተጠሪ የድርጅቱን ሥራ በማስተዳደር የንግድ ስራዉን በመምራት አስተዋፅኦ ያለዉ መሆኑ አልተካደም ይህ ብሆነ የመጀመሪያዉ ሀምሌ 29 ቀን 2005 ዓ.ም የቀረበዉት ክስ የይርጋ የጊዜ ገደብ መቀጠሩን የማይቋርጠዉን ሆኖ እያለ፤ አንደኛ ተጠሪን የከሰሰዉ የካቲት 21 ቀን 2006ዓ.ም በሚል ምክንያት ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የሰጡት ብይን መሠረታዊ የሐግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንድታረምልኝ በማለት አመልክቷል ተጠሪዎች ጥር 22 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡ ተጠሪዎች አመልካች የንግድ ድርጅቱን ባለንብረት አጣርቶ ክስ ማቅረብ ሲገባዉ የማይመለከተዉን ሰዉ ክሶ አንደኛ ተጠሪን በሕጉ የተመለከተዉ ስድስት ወር ካለፈ በኋላ በክስ አካቲቶ ክሱን አሻሽሎ የቀረበ በመሆኑ ክስ በይርጋ ቀሪ ነዉ መባሉ ተገቢ በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የካቲት 24 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀዉ ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ክሱ በይርጋ ቀሪ ነዉ በማለት ዉድቅ ማድረጋቸዉ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ኪንግ ማርኬል ካፌና ሬስቶራንት በሚል ስያሜ በሚታወቀው የንግድ መደብር ሠራተኛ ሆኖ መምራቱንና አመልካችንም በሠራተኝነት፤የቀጠረው ሁለተኛው ተጠሪ እንደነበር፤ አንድኛ ተጠሪ ሁለተኛ ተጠሪን ያሣደገችው መሆናና አንደኛ ተጠሪ ካፌና ሬስቶራንቱን ስትከፍት ሁለተኛው ተጠሪ በገንዘብ የረዳት መሆኑ፣ የንግድ መደብሩ አንደኛ ተጠሪ ስም የንግድ ፈቃድ ያወጣለትና የንግድ ድርጅቱ ለባቤት አንደኛ ተጠሪ መሆኗ የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው አረጋግጦ ያሰፈረው ፍሬ ነገር ነው። ከዚህ በተጨማሪ ሁለተኛ ተጠሪ የንግድ ሥራውን እንድንሠራ ከአንደኛ ተጠሪ በሰነድ የተሰጠው የውክልና ሥልጣን የሌለና በሕግ አግባብ የንግድ መደብሩ ሥራ አስኪያጅ ያለመሆኑና ነገር ግን አንደኛ ተጠሪ የምትሠራውን የኮፌና ሬስቶራንት ሥራ በመምራት በኩል በተግባር ተጨባጭ እገዛ ሲያደርግ የነበረ መሆኑ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመረዳት ይቻላል።

6. ይህም በመሆኑ አመልካች የካፌውና ሬስቶራንቱ ባልተቤት ሁለተኛ ተጠሪ ነው በሚል እምነት ሀምሌ 29 ቀን 2005 ዓ.ም የሥራ ውሉ ከሕግ አግባብ ውጭ የተቋረጠ መሆኑን ገልፆ ክስ አቅርቧል። ይህም አመልካች በሁለተኛው ተጠሪ ላይ ክስ ያቀረበው የንግድ መደብሩ ባለቤትና እርግጠኛ አሠሪው ሁለተኛው ተጠሪ ነው በሚል እምነትና ቅን ልቦና መሆኑን የሚያሳይ ነው የቅን ልቦና በይርጋ ስህተት ምክንያት ተከሳሽ መሆን በማይገባው ሰው ስም ክስ ያቀረበ በሆነ ጊዜ የተገቢው ሰው ስም በተከሳሽነት እንዲተካ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ መስጠት እንደሚችል በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 40 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገ ሲሆን ይህም ሲሆን ክሱ ተሻሽሎ በተተኪነት በሚገባው ሰው እንዲደርስ ሊደረግ እንደሚችል የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 40 ንዑስ አንቀፅ 3 ይደነግጋል ፍርድ ቤቱ ከሳሽ የተከሳሽን ስም የተሳሳተው በቅን ልቦና መሆኑን በማመን ክሱን በማሻሻል በገዳዩ ትክክለኛ ተከሳሽ መሆን ያለበትን ሰው እንድተካ ወይም እንድጨምር ከፈቀደለት ከሳሽ በስህተት የተከሳሽን ስም ሣያካትት ክስ ካቀረበበት ጊዜ ጀምሮ የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚያቋርጠው መሆኑን በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ 40 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 3 ድንጋጌና ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 164 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ በጣምራ በማየት ለመረዳት ይቻላል።

7. ከዚህ አንፃር በአንደኛ ተጠሪና በሁለተኛ ተጠሪ ባለቸው ቅርብ ግንኙትና ሁለተኛ ተጠሪ የአንደኛ ተጠሪ ካፌና ሬስቶራንት የንግድ ሥራ በሚያደርገው ንቁ ተሣትፎ ምክንያትና አመልካችንም የቀጠረው ሁለተኛ ተጠሪ በመሆኑ ምክንያት ፤ ሶስተኛ ተጠሪ የንግድ መደብሩ ባለቤትና አሠሪ ነው በሚል ቅን ልቦና ተነስቶ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ክስ ካቀረበበት ሀምሌ 29 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ ጉዳዩ እስከተወሰነበት

ጊዜ ድረስ የይርጋ የጊዜ ገደቡ መቆጠሩ የሚቋረጥ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር40 ንዑስ አንቀፅ1 እና ንዑስ አንቀጽ3 መሠረት ክሱን በማሻሻልና የአንደኛ ተጠሪን ስም በተከሳሽነት ጨምሮ የካቲት 21 ቀን2006 ዓም ያቀረበውን ክስ ብቻ በማመልከት ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የሰጠውን ብይን ሣያርም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ማጥናቱ ከላይ የገለጽናቸውን የህግ ድንጋጌዎች ይዘት እጋዊ ውጤት ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሸሯል
2. አመልካች ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 40 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ3 እደዚሁም የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 164 ንዑስ አንቀጽ1 መሠረት ውሣኔ ሰጥተናል፡፡
3. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችንና የአንደኛ ተጠሪን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ውሣኔ እዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁጥር 341(1) መሠረት መልሱን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ በየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/መ

የሰ/መ/ቁ.155880

ሰኔ 28 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች - መዓዛ አሸናፊ

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች - አግሪኮም ኢንተርናሽናል ኩባንያ -ጠበቃ አለሙ ደነቀው ቀረቡ

ተጠሪ-የኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን-ጠበቆች ሜሮን ሰለሞን እና ዶ/ር ዘውድነህ በየነ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስንዴ ግዢ ውልን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተደረገው ግራ ቀኙ እ.ኤ.አ ኖቨንበር 25/2011 ባደረጉት ስምምነት መሰረት አለመግባባታቸውን በኢትዮጵያ መሰረታዊ ህግ (Substantive Law) እንዲሁም በ Grain and Feeds Trading association (GAFTA) የሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 125 (GAFTA Rules NO. 125) መሰረት በሚቋቋም የግልግል ዳኝነት አካል በእንግሊዝ ሃገር ለመቋጨት በተስማሙት መሰረት ነው፡፡

1. የአሁን ተጠሪ ለግልግል ጉባኤው ባቀረበው ክስ 200,000 ሜትሪክ ቶን ስንዴ ለማቅረብ አመልካች የውል ግዴታ ገብቶ ማቅረብ ባለመቻሉ ጥቅምት 9/2005 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ ሰጥቼ ውሉን በማቋረጥ ሌላ ግዢ ፈጽሜያለሁ፤ ስለሆነም በፈፀምኩት አዲስ ግዢ ምክንያት ለ 11,549,000.00 (አስራ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ) የአሜሪካ ዶላር ተጨማሪ ወጪ ተዳርጌያለሁ፤ ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡
2. አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ ስንዴውን ለማቅረብ ያልቻልኩት ስንዴውን ለማቅረብ የሚያስፈልገውን የባንክ የመተማመኛ ሰነድ (L/C) ተጠሪ አስተካክሎ በወቅቱ ለማቅረብ ባለመቻሉ በራሱ ጥፋት ነው፤ የራሱን ግዴታ ባልተወጣበት ሁኔታ ውሉን ለማቋረጥም ሆነ ኪሳራ ለመጠየቅ አይችልም፤ ከዚህም ሌላ ውሉ በሚተዳደርበት በኢትዮጵያ ህግ መሰረት ተገቢው ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ተጠሪ ውሉን ሊያቋርጥ አይችልም፤ ስለሆነም ካሳ እንድከፍል ሊጠይቀኝ አይችልም፤ ይህ የሚታለፍ ቢሆንና የደረሰ ጉዳት አለ ከተባለ ተጠሪ ሊጠይቅ የሚችለው ለ200,000 ሜትሪክ ቶን የዋጋ መጠን በተሰጠው የመልካም ሥራ አፈፃፀም ሰነድ (Performance Bond) ማለትም 5,855,000.00 (አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃምሳ አምስት ሺህ) የአሜሪካን ዶላር ብቻ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

3. ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የግልግል ጉባኤ ክርክርና ማስረጃውን መርምሮ ተጠሪ ውሉን ያቋረጠው በአግባቡ ነው፤ ውሉን ለማቋረጥ የተሰጠው ማስጠንቀቂያም የኢትዮጵያ ህግ የሚጠይቀውን የሚያሟላ ነው፤ እንዲሁም ተጠሪ የጠየቀውን የካሳ መጠን የማይከፍልበት ምክንያት የለም በማለት አመልካች ለተጠሪ 11,549,000.00 (አስራ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ) የአሜሪካ ዶላር እንዲከፍል የካቲት 20/2010 ዓ.ም ባሳለፈው ፍርድ ወስኗል።
4. የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው። አመልካች መጋቢት 18/2010 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ ውሳኔው የተሰጠው በኢትዮጵያ ህግ ላይ ተመስርቶ መሆኑንና ውሳኔውም የመጨረሻና በሁለቱ ወገኖች ላይ ተፈፃሚነት ያለው መሆኑ መደንገጉን፤ እንዲሁም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 42239 ከሰጠው ውሳኔ አንጻር ጉዳዩን ተቀብሎ ለመዳኘት እንደሚችልና ህገመንግስታዊ ሥልጣን ያለው መሆኑን ጠቅሶ ማመልከቻውን አቅርቧል።
5. አመልካች በሰበር ማመልከቻው በ09/02/2005 ዓ.ም ተሰጠ የተባለው ማስጠንቀቂያ በ16/02/2005 ዓ.ም ከተጠሪ በተላከ መልዕክት የተነሳና የተሰረዘ በመሆኑ፤ ይህም ባይሆን ማስጠንቀቂያው የተሰጠው ተጠሪ የራሱን ግዴታ ሳይወጣና በቂ ጊዜም ሳይሰጥ የፍትሐብሔር ህጉንና የሰበር ውሳኔዎች ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች ሳያሟላ ስለሆነ በአግባቡ ባልተቋረጠ ውል ላይ ተመስርቶ አመልካች 11,5490,00.00 (አስራ አንድ ሺህ አምስት መቶ አርባ ዘጠኝ) የአሜሪካ ዶላር እንዲከፍል የተሰጠው የግልግል ጉባኤ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል። ይህ የሚታለፍ ከሆነም ለደረሰው ጉዳት መከፈል ያለበት ለ 200,000 ሜትሪክ ቶን ስንዴ ግራቀኙ ካደረጓቸው ውሎች ተለይቶ በተሰጠው የፐርፎርማንስ ቦንድ ገንዘብ መጠን ማለትም 5,855,000.00 (አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃምሳ አምስት ሺህ) የአሜሪካን ዶላር ብቻ ነው ተብሎ እንዲወሰን አመልክቷል።
6. የሰበር ማመልከቻው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ የግልግል ጉባኤው የሰጠው ውሳኔ ተዋዋይ ወገኖች ውሉን በተናጠል ለመሰረዝ (Unilateral Cancillation of Contract) ስለሚችሉበት አግባብ በሰበር መዝገብ ቁጥር 57280 ከተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አኳያ ተገቢነቱን መርምሮ ለመወሰን በሚል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል።
7. ተጠሪ መስከረም 22/2011 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቀረበውን ጉዳይ ለማየት ስልጣን የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና በፍሬነገሩም መልስ ሰጥቷል።
8. ተጠሪ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የሌለው ስለመሆኑ ባቀረበው የመቃወሚያ ክርክር የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫ ኢትዮጵያ ውስጥ ባልሆነ የግልግል ዳኝነት የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ ለኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ጉዳዩ እንዲታይ የሚቀርብበት የህግ መሰረትም ልምድም የለም፤ የግልግል ዳኝነቱ ውሳኔ እንደ ኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔ ሆኖ እንዲቆጠር በተዋዋዮች መካከል የተደረገ ስምምነት ስለሌለ ውሳኔውን በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እንደተሰጠ ውሳኔ ቆጥሮ በመሰረታዊ የህግ ስህተት ስም ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የሚደረግበት የህግ መሰረት የለም፤ ጉዳዩ በሰበር እንዲታይ የሚቀርብበት የህግ አግባብ የለም እንጂ አለ እንኳ ቢባል ሊቀርብ

ይገባ የነበረው የግልግል ዳኝነቱ ህጋዊ መቀመጫ ሆኖ በተመረጠውና በተዋዋይ ወገኖች ተቀባይነትን ባገኘው እ.ኤ.አ በ1996 በፀደቀው የዩናይትድ ኪንግደም የአርቢትሬሽን ህግ መሰረት ለለንደን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የንግድ ችሎት ብቻ ነበር፤ አመልካች የግልግል ዳኝነት አካሉ የመጀመሪያ ጉባኤ (First Tier Tribunal) በሰጣቸው ውሳኔዎች ቅር በመሰኘት ከአንዴም ሁለት ጊዜ የይግባኝ አቤቱታውን ለለንደን የከፍተኛው ፍርድ ቤት ንግድ ችሎት አቅርቦ ውድቅ ተደርጎበታል፤ አመልካች እ.ኤ.አ. በፌብሪዋሪ 27 ቀን 2018 በአምስት ዳኞች የተላለፈውን የ GAFTA የግልግል ዳኝነት የይግባኝ ጉባኤ የመጨረሻ ውሳኔ ቀሪ እንዲደረግ፣ እንዲሻር ወይም እንዳይፈፀም ለማድረግ አቤቱታውን ማቅረብ የነበረበት የግልግል ጉባኤው መቀመጫ ሀገር ህግ በሚፈቅደው መሰረት ሥልጣን ላለው ለለንደኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ንግድ ችሎት ነበር፤ ስለሆነም ይህ የሰበር አቤቱታ ስልጣን ለሌለው ፍ/ቤት የቀረበ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል። አመልካች በሰ/መ/ቁ 42239 የተሰጠውን ውሳኔ በመጥቀስ አቤቱታውን ያቀረበ ቢሆንም በሁለቱ መዛግብት ክርክር ያስነሳው ጉዳይ፣ የውሉ ሁኔታዎች እና የግልግል ጉባኤው መቀመጫ ፈጽሞ የተለያየ በመሆኑ በሰ/መ/ቁ 42239 የተሰጠው ገዢ ትርጉም በዚህ መዝገብ ላይ ተፈጻሚ ሊሆን አይገባም፤ ሰበር ችሎቱ የመጨረሻና ይግባኝ የማይባልባቸው ናቸው የተባሉ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎችን ተቀብሎ ማየት የሚችለው የመጨረሻውን የግልግል ዳኝነት ወሳኔ ያስተላለፈው የግልግል ዳኝነት አካል ህጋዊ መቀመጫ (Juridical or Legal Seat) በኢትዮጵያ ከሆነ ብቻ ነው፤ ከዚህም ሌላ ተዋዋይ ወገኖች ውሳኔያቸውን የሚገዛው መሰረታዊ (የሥረ ነገር) ህግ (Substantive Law) የኢትዮጵያ ህግ በመሆኑና የኢትዮጵያ ህግ ሲተረጎም ደግሞ መሰረታዊ ስህተት ከተፈጸመበት ሊያቃና የሚችለው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ነው ከሚል ግንዛቤ የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፤ በግራቀኙ የተመረጠው መሰረታዊ ህግ የኢትዮጵያ ህግ ቢሆንም ክርክር ሂደቱን የሚገዛው የሥነ ሥርዓት ህግ ደግሞ የግልግል ዳኝነት አካሉ (የ GAFTA የአርቢትሬሽን የሥነ ሥርዓት ህግ) ህጋዊ መቀመጫ ሀገር ህግ በመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት "መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል" የተባለውን የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ውሳኔ የማየት ሥልጣን የለውም። በተዋዋይ ወገኖች የአርብትሬሽን የሥነ ሥርዓት ህጎች የሚወሰኑትም ከፍርድ ቤቶች ጣልቃ ገብነት ለመራቅ ሲባል ነው። በሌላም በኩል አመልካች በአቤቱታው የገለፀው ጥቅምት 9/2005 ዓ.ም የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ጥቅምት 16/2005 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ተነስቷል? ወይስ አልተነሳም? የሚለው ክርክር ማስረጃን የሚመለከት በመሆኑና ውሳኔም የተሰጠው ማስረጃዎቹ ታይተው በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው ክርክር የህግ ክርክር አይደለም ለሰበር ችሎቱ በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሊታይ የሚችል አይደለም ተብሎ ውድቅ ይደረግልን በማለት መቃወሚያውን አቅርቧል።

9. ተጠሪ ከዚህም ሌላ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ዝርዝር መልስ ሰጥቷል። የመልሱ ይዘት ባጭሩ ሲታይ በተጠሪ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ አልተነሳም፤ በግራ ቀኙ መካከል በተገባው ውልና የውል ማራዘሚያ መሰረት አመልካች ሥንዴውን ማቅረብና ማጠናቀቅ የነበረበት ጊዜ ባለማቅረቡ ተጠሪ ጥቅምት 13/2005 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል፤ ከዚህ በኃላ በአመልካች በቀረበ ጥያቄ መሰረት ተጠሪ ጥቅምት 16/2005 ዓ.ም የጻፈው ደብዳቤም ማስጠንቀቂያውን ያለቅድመ ሁኔታ አንስቻለሁ የሚል ሳይሆን ቅድመ ሁኔታዎችን በግልጽ አስቀምጦ ሁኔታዎች ከተሟሉ ብቻ

ማስጠንቀቂያው ሊቀር እንደሚችል ገልጾ ነው፤ አመልካች ሁኔታዎችን ያላሟላ መሆኑንና ጥቅምት 13/2005 ዓ.ም የተሰጠው ማስጠንቀቂያ የፀና ስለመሆኑ የግልግል ዳኝነት ጉባኤው አጣርቶ ውሳኔ ሰጥቶበታል፤ ስለሆነም ማስጠንቀቂያው ተነስቷል ወይም ተሰርዟል በማለት ያቀረበው ክርክር የውልም ሆነ የህግ መሰረት የሌለው ነው። የተሰጠው ማስጠንቀቂያም በፍትሐብሔር ህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እንዲሁም በሰ/መ/ቁ 57280 የተሰጠውን የህግ ትርጉም ባሟላ መልኩ የተደረገ ነው። በአጠቃላይ ተጠሪ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ህጋዊ ግዴታ ባይኖርበትም ተጠሪ በአግባቡ ህጉን የተከተለ ማስጠንቀቂያ የሰጠ በመሆኑና የግልግል ዳኝነት ጉባኤው ማስረጃዎችን መርምሮ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ያልተነሳ መሆኑን በማረጋገጥ እንዲሁም ተጠሪ የሚጠበቅበትን የውል ግዴታ ቢወጣም አመልካች ግን ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑን በማስረጃ አረጋግጦ የወሰነ በመሆኑ ቅሬታው ውድቅ ይደረግ። የመልካም ሥራ አፈጻፀም ዋስትና (ቦንዱ) በተመለከተም በአመልካች አቤቱታ የተጠቀሰው መጠን ስህተት ነው፤ በውሉ አንቀጽ 13 እንደተቀመጠው የመልካም ሥራ አፈጻፀም ዋስትናው የሚገባው የውሉን ዋጋ 10% መሆኑን ስለሚደነግግ ይህ ሲሰላ 14,637,500.00 የአሜሪካ ዶላር ይሆናል፤ አመልካች የ200,000 ሜትሪክ ቶን ስንዴ ዋጋን መሰረት በማድረግ ያስቀመጠው የዋስትና ገንዘብ መጠን የተሳሳተ እና የውል መሰረት የሌለው ነው፤ ውሉ የመልካም ሥራ አፈጻፀም ዋስትና (ቦንድ) መጠኑን ሲያስቀምጥ የዋሱን ኃላፊነት መጠን ለመገደብ እንጂ የጉዳቱን መጠን ለመገደብ እንደሆነ ያስቀመጠው ነገር የለም፤ ከቦንዱ በላይ ጉዳት ቢደርስ ተጨማሪ ካሳ መጠየቅ አይቻልም የሚል መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ ነገርም የለም፤ በተጨማሪም በውሉ አንቀጽ 17 ላይ liquidated damage የተቀመጠ ሲሆን ይህም በአንቀጽ 13 ላይ የተቀመጠው የጉዳት ካሳ የመልካም ሥራ አፈጻፀም ዋስትና ሰነድ የጉዳት መጠኑን በአጠቃላይ ለመገደብ የተቀመጠ እንዳልሆነ የሚያሳይ ነው። በአጠቃላይ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ የግልግል ጉባኤው ውሳኔ እንዲፀና በማለት ተከራክሯል።

10. አምልካች ጥቅምት 23/2011 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ በመቃወሚያው ላይ የበኩሉን ክርክር አቅርቧል። በዚህም መሰረት የጋፍታ የግልግል ጉባኤ (ቦርድ) የሰጠው ውሳኔ ጉዳዩ የሚዳኝበትን የኢትዮጵያ ህግ የጣሰ ነው በማለት የቀረበን ቅሬታ በኢትዮጵያ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 እና በአዋጅ ቁጥር 454/97 መሰረት ለማየት ሥልጣን ያለው ሰበር ሰሚው ችሎት ነው፤ ሁለቱ ወገኖች ጉዳያቸውን በኢትዮጵያ መሰረታዊ ህግ (substantive law) መሰረት ለመገዛት ፈቃደኛነታቸውን በውል ከገለፁ የኢትዮጵያን ህግ አስመልክቶ ክርክር ቢነሳ ጉዳዩ ከሰበር ሰሚው ስልጣን ውጪ የሚሆንበት የህግ መሰረት የለም፤ ይህ ያልተገደበ የሰበር ስልጣን ፍርዱ በየትም ቦታ ቢሰጥ ወይም ውሳኔ የሰጠው አካል የተከተለው ሥርዓት (Procedure) ምንም ይሁን የተሰጠው ውሳኔ የኢትዮጵያ የህግ መስፈርቶችን አያሟላም የሚል ጥያቄ ከተነሳ ውሳኔ የሚሰጠው በህግ ስልጣን የተሰጠው ሰበር ሰሚ ችሎት ብቻ ነው፤ ተዋዋዮች በአንድ የግልግል ተቋም አማካኝነት በተወሰነ ሃገር ለመዳኘት ፈቃድ መስጠታቸው የግልግል ተቋሙ የሚመራበትን ሥርዓት (procedure) መቀበላቸውን ከሚያረጋግጥ በቀር መሰረታዊውን ህግ በተመለከተ ያላቸውን መብት ተነፍገዋል ማለት አይደለም። አመልካች በተለያዩ ጊዜያት ይግባኝ ሲያቀርብ የነበረው ለለንደኑ

ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው አሁንም በዚያው መሰረት ሊያቀርብ ይገባል ተብሎ በተጠሪ በኩል የቀረበውን ክርክር በተመለከተም ፍሬ ነገርን ወይም መሰረታዊ (የስረ ነገር) የህግ ስህተትን አስመልክቶ ለለንደን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረብነው አንዳችም ይግባኝ የለም፤ በርግጥ ጉዳዩ በግልግል ጉባኤ በመታየት ላይ እያለ ሁለት የሥነ ሥርዓት ጥያቄዎች ላይ በመመስረት አቤቱታ ለለንደን ፍርድ ቤት አቅርበናል፡- ይኸውም በመጀመሪያ ጉዳዩ ለግልግል ጉባኤ በቀረበበት ወቅት የአቤቱታ ማቅረቢያው ጊዜ አልፏል በማለት፣ ሁለተኛ ደግሞ ክርክሩ አልቆ ውሳኔውን ከመስማታችን በፊት ተዋዋይና ከሳሽ ወገን የነበረው የኢትዮጵያ አህል ንግድ ድርጅት አስቀድሞ ፈርሶ እያለ በፈረሰው ድርጅት ሥም ሲካሄድ የነበረው ክርክር እንደተካሄደ ሊቆጠር አይገባም በማለት የቀረበ የሥነ ሥርዓት ተቃውሞ ነው፤ የዚህ አይነት የሥነ ሥርዓት ተቃውሞ ደግሞ ክርክሩ የሚካሄድበትን ሥርዓት መሰረት በማድረግ በይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት መቅረቡ በአግባቡ ነው። ስለሆነም ተጠሪ ያቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ብሏል። ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም አመልካች የቀደመ ክርክሩን በማጠናከር ውሉ የተቋረጠው ያላግባብ ስለሆነ የግልግል ጉባኤው ውሳኔ ውድቅ እንዲደረግ፤ ይህ የሚታለፍ ከሆነም የካሳው መጠን በመልካም ሥራ አፈጻፀም ቦንዱ ላይ የተቀመጠው የገንዘብ መጠን 5,855,000.00 (አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃምሳ አምስት ሽህ) የአሜሪካን ዶላር ነው ተብሎ እንዲወሰን ጠይቋል።

11. የጉዳዩ አመጣጥና የግራቀኙ የጽሁፍ ክርክር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያው ላይ ክርክራቸውን በቃል ሰምቷል። ጉዳዩንም የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል።
12. እንደመረመርነው በሰበር አጣሪ ችሎቱ እንዲታይ የተያዘው ጭብጥ ፍሬ ጉዳዩን የተመለከተ ቢሆንም ከዚህ በፊት የችሎቱን ምላሽ የሚጠይቀው ነጥብ የአሁን ተጠሪ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ተቀብሎ ለመወሰን ስልጣን የለውም በማለት ያቀረበው ክርክር ነው። ይህን ጭብጥ ለመመለስ ግራቀኙ በገቡት ስምምነት መሰረት ጉዳዩ በግልግል ጉባኤ ውሳኔ ያገኘበትን አግባብ እና የተሰጠውን ውሳኔ ተፈጥሮ፤ መሰል የአማራጭ ሙግት መፍቻ ዘዴዎችን በመጠቀም በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ ለመደበኛ ፍርድ ቤቶች አቤቱታ የሚቀርብበትን ሁኔታ፤ እንዲሁም በሀገራችን የተዘረጋው የሰበር ስርዓት አላማና የህጉን ማእቀፍ መመልከቱ ተገቢ ነው።
13. በሀገር ውስጥ የግልግል ጉባኤ የመጨረሻ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ተከራካሪዎቹ ጉዳያቸውን ወደ ፍርድ ቤት በመውሰድ ይግባኝ የሚሉበትና ውሳኔው እንዲሻር ማመልከቻ የሚቀርብበት ሂደት በሥነ ሥርዓት ህጉ ተመልክቷል። ከፍትሐብሄር ሥነ ሥርዓት ህጉ ግልጽ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መረዳት እንደሚቻለው የግልግል ውሳኔው እንዲሻር የሚቀርበውን ማመልከቻ በመቀበል እንዲሁም የአፈፃፀም ክርክሩን በመወሰን ፍርድ ቤቶች የግልግል ዳኝነት ሂደትን ይቆጣጠራሉ። ፍርድ ቤቶች የግልግል ዳኛ በመሾም፣ በመሻር፣ ጉዳይን ወደ ግልግል በመምራት እንዲሁም ውሳኔ ከተላለፈ በኋላ ፍርዱን ሊመረምሩ የሚችሉበት ሁኔታ በህጉ ተደንግጓል። በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ ከአንቀጽ 350 እስከ 354 ስለ ይግባኝ፤ ከአንቀጽ 355 እስከ 356 ብይኑ ስለሚሻርበት እና ማመልከቻው ስለሚቀርብበት ሁኔታ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ፍርድ ቤቶች የግልግል ዳኝነቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ማሳካቱና እና

በህጉ አግባብ ጉዳዩን መርቶ መወሰኑን እንዲያረጋግጡ የሚያስችሉ ናቸው። በአንፃሩ እነዚህ ድንጋጌዎች በውጪ ሀገራት የተሰጡ የግልግል ዳኝነቶችን በቀጥታ ይመለከታሉ ባይባልም የሥነ ሥርዓት ህጉ ከአንቀጽ 456 እስከ 461 ድረስ ከውጪ አገር ስለሚመጡ የግልግል ውሳኔዎች አፈፃፀም ሂደትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ይዟል።

14. በሌላ በኩሉ በዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ያለው ልምድ እና የዳበረ የግልግል ዳኝነት ህግጋት ያላቸው የበርካታ ሀገራት ህጎች እንዲሁም አለማቀፍ ስምምነቶች እንደሚያረጋግጡት የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች እንደመደበኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተቆጥረው የግልግል ውሳኔዎችን በፍርድ ውሳኔ ለማስቀረት (seating aside) ወይም ለማሰረዝ (annulment) አቤቱታ ሊቀርብ የሚችለው በተዋዋይ ወገኖች መካከል ይኸው በስምምነት ሲደገፍ፣ ተዋዋይ ወገኖች በመረጡት የግልግል ዳኝነት የሥነ ሥርዓት ህግ (Institutional Arbitration Rule) ይኸው ሲደገፍ፣ እንዲሁም የግልግል ዳኝነቱ ህጋዊ መቀመጫ ሀገር (Juridical or Legal Seat) ህግ ይህንኑ የሚደግፍ ሲሆን ነው። በተያዘው ጉዳይ የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫ በእንግሊዝ ሀገር መሆኑ እንዲሁም ግራቀኙ ባደረጉት ስምምነት ውስጥ የግልግል ዳኝነቱ ውሳኔ እንደ ኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሆኖ እንዲቆጠር የተደረገ ስምምነት አለመኖሩ አላከራከረም። የተመረጠው የግልግል ዳኝነት መቀመጫ ሀገር ህግም ቢሆን በግልግል ጉባኤው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ በዚያው ሀገር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ እንዲቀርብ የሚፈቅድ ነው። ስለሆነም የግልግል ጉባኤው ውሳኔ እንዲሻር/እንዲሻሻል አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት በቀጥታ የቀረበው ይህን የሚፈቅድ ህግ እንዲሁም የተዋዋይ ወገኖች ሥምምነት በሌለበት ነው።

15. ከዚህ ጋር በተያያዘ አመልካች የግልግል ዳኝነት አካሉ የመጀመሪያ ጉባኤ (First Tier Tribunal) በሰጣቸው ውሳኔዎች ቅር በመሰኘት ከአንዴም ሁለት ጊዜ የይግባኝ አቤቱታውን ለለንደን የከፍተኛው ፍርድ ቤት ንግድ ችሎት አቅርቦ ውድቅ ተደርጎበታል፤ በመጨረሻው ውሳኔ ላይም ቅሬታው ሊቀርብ የሚገባ በዚሁ አግባብ ነው በማለት ተጠሪ የተከራከረ ሲሆን አመልካች በሰጠው መልስ ሁለት ጊዜ የይግባኝ አቤቱታ ለለንደን የከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቦ እንደነበር ሳይክድ ያቀረበው ይግባኝ የስነ ሥርዓት ጉዳዮችን በተመለከተ ብቻ እንደነበርና ፍሬ ነገርን ወይም መሰረታዊ (የስረ ነገር) የህግ ስህተትን አስመልክቶ ለለንደን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ይግባኝ እንደሌለ ተከራክሯል። እንደሚታወቀው በአንድ በተሰጠ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የማለት መብት መሰረታዊ መብት ሆኖ የሚቆጠር ሲሆን የይግባኝ መብቱ ዝርዝር አፈፃፀም ግን የሚወሰነው በሥነ ሥርዓት ህጎች ነው። ስህተቱ የሥነ ሥርዓትም ሆነ የፍሬ ነገር ቢሆን ሊሰማና ሊታረም የሚችለው ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ባለው የሥነ ሥርዓት ደንብ እየተመራ ነው። ስለሆነም የግልግል ዳኝነቱ አካል የሚመራበት ሥነ ሥርዓት ላይ ግራ ቀኙ ስምምነት አድርገው በዚሁ አግባብ ሁለት ጊዜ የይግባኝ አቤቱታ ለለንደኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መቅረቡ ባላከራከረበት ሁኔታ አመልካች ፍሬ ነገርን ወይም መሰረታዊ የህግ ስህተትን አስመልክቶ ለመደበኛው ፍርድ ቤት ያቀረብኩት ቅሬታ የለም በማለት ያቀረበው ክርክር የሥምምነታቸውን ይዘት እና ጉዳዩ የሚገዛበትን ህግና ልምድ የተከተለ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም።

16. በሌላ በኩል አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ሁለቱ ወገኖች ጉዳያቸውን በኢትዮጵያ መሰረታዊ ህግ (substantive law) መሰረት ለመገዛት ፈቃደኛነታቸውን በውል ከገለፁ የኢትዮጵያን ህግ አስመልክቶ ክርክር ቢነሳ ጉዳዩ ከሰበር ሰሚው ስልጣን ውጪ የሚሆንበት የህግ መሰረት የለም፤ ይህ የሰበር ስልጣን ፍርዱ በየትም ቦታ ቢሰጥ ወይም ውሳኔ የሰጠው አካል የተከተለው ሥርዓት (Procedure) ምንም ይሁን የተሰጠው ውሳኔ የኢትዮጵያ የህግ መስፈርቶችን አያሟላም የሚል ጥያቄ ከተነሳ ውሳኔ የሚሰጠው ሰበር ሰሚ ችሎቱ ብቻ ነው በሚል ነው። ለዚህ ክርክራቸው መሰረት የሚያደርጉትም በሰ/መ/ቁ 42239 የተሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም እና የህገ መንግስቱን አንቀጽ 80 እንዲሁም የአዋጅ ቁጥር 454/97 ድንጋጌን ነው። በእርግጥ በኢትዮጵያ ሁኔታ በግልግል ጉባኤ የሚሰጥ የመጨረሻ ውሳኔ አስገዳጅና ይግባኝ የማይባልበት ስለመሆኑ በተከራካሪዎች ስምምነት የተደረገበት ቢሆን ጉዳዩ በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለው ነጥብ አከራካሪ ሆኖ ይታያል። የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በጉዳዩ ላይ አስቀግሞ ሰጥቶት የነበረውን አስገዳጅ ትርጉም በፓናል ችሎት በመለወጥ ትርጉም ሰጥቷል። በሰ/መ/ቁ 42239 *ብሔራዊ ማዕድን ኮርፖሬሽን ኃ/የተ/የግል ኩባንያ* እና *ዳሂ ድሪሊ ንግ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ* መካከል በተደረገው ክርክር ሰበር ችሎቱ የግልግል ውሳኔን የመጨረሻነት እንዲሁም በግልግል ዳኝነት አካላት የተሰጡ ውሳኔዎችን በተመለከተ ፍርድ ቤቶች ሊኖራቸው የሚገባውን ሚና አስመልክቶ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶ ወስኗል። በዚህም መሰረት "..... *አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች በኢትዮጵያ የህግ ስርዓት ውስጥ ተካተው የሚገኙ ሲሆን እነዚህን የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ፍርድ ቤቶች የሚያበረታቱበት አጋጣሚ እንዳለ ሁሉ የሚቆጣጠሩበት ሁኔታ መኖሩን.....፤ ከዚህ አኳያ አንድ ጉዳይ ለሰበር የመቅረቡ ሁኔታ በህገ መንግስቱ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠ ሥልጣን በመሆኑ የሰበር ስርዓቱ ሊጫወተው ከተፈለገው ዐቢይ ዓላማ አንፃር ሲታይ ጉዳያቸው በግልግል ዳኝነት እንዲታይላቸው የተስማሙ ወገኖች የግልግል ዳኝነቱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ነው በማለት ስለተስማሙ ብቻ ጉዳዩ በሰበር ሥርዓቱ እንዳይታይ ፍላጎት አሳይተዋል ተብሎ መሰረታዊውን የህግ ስህተት ላለማሳረም ምክንያት ሊሆን የሚቸል አይደለም....*" በማለት የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ)፣ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10፣ እና አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በማድረግ ወስኗል። ነገር ግን ሊታይ የሚገባው ይህ ውሳኔ ለተያዘው ጉዳይ ያለው ተገቢነትና አስገዳጅነት ነው። ከውሳኔው መገንዘብ እንደሚቻለው በጉዳዩ ላይ በሰበር ችሎቱ ውሳኔ የተሰጠው የግልግል ችሎቱ መቀመጫ እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑን ተከትሎ በመሆኑ አሁን በእጃችን ካለው ጉዳይ ጋር የተገናኘ አይደለም። በተያዘው ጉዳይ ግራቀኙ ባደረጉት የግሸ እና ሽያጭ ውል የግልግል ዳኝነት መቀመጫውን በእንግሊዝ ሀገር ለንደን ከተማ ያደረገ የግልግል ተቋም የመረጡ ሲሆን በ Grain and Feeds Trading association (GAFTA) የሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 125 (GAFTA Rules NO. 125) መሰረት ለመዳኛትም ተስማምተዋል። በሰ/መ/ቁ 42239 የተሰጠው ውሳኔ ደግሞ ይህን መሰረት አድርጎ የተሰጠ ባለመሆኑ ከተያዘው ጉዳይ ጋር የሚገናኝ አይደለም። ተመሳሳይ የፍሬ ነገር ወይም የህግ ክርክሮች በሌሉበት ሁኔታ አስቀድሞ የተሰጠ የሰበር ውሳኔ በጉዳዩ ላይ ተፈፃሚ እንዲሆን የሚደረግበት የህግ አግባብ እንደሌለም ከአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(4) ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል።

17. በሌላ በኩል የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የግልግል ጉባኤ ውሳኔ (APPEAL AWARD NO: 4496 & 4515) መግቢያ ላይ በተራ ቁጥር 1.4 ሥር የሚከተለው ተመልክቷል፡-

> "As the seat of the arbitration is in England and an Award subject to English procedural and Ethiopian substantive law, it therefore follows that it is an English Award for the purpose of recognition and enforcement under the terms of the 1958 New York Convention on the Recognition and Enforcement of Foreign Arbitral Awards"

የዚህ የአማርኛ ትርጉምም እንደሚከተለው ይነበባል፡-

> "የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫ ቦታ እንግሊዝ ሀገር በመሆኑና የዳኝነቱ ሂደት የሚመራው በእንግሊዝ የሥነ ስርዓት ህግ፣ የውሉን ይዘት በተመለከተ ግን ተፈፃሚው የኢትዮጵያ ህግ በመሆኑ፤ የግልግል ውሳኔው እንደ እንግሊዝ አገር ውሳኔ ተቆጥሮ ውሳኔው ዕውቅና የሚያገኝውና ተፈፃሚም የሚሆነው ከአንድ አግር ውጪ የተሰጠን ውሳኔ አፈፃፀም በተመለከተ በ1958 የወጣው የኒዮርክ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ነው"

18. ከዚህ የግልግል ጉባኤ ውሳኔ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለው የግልግል ውሳኔው ከአንድ አገር ውጪ የተሰጠ ውሳኔ (በእንግሊዝ) ተደርጎ የሚወሰድና ውሳኔው ዕውቅና የሚያገኝውና ተፈፃሚም የሚሆነው በ1958 የወጣው የኒዮርክ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን መሰረት ስለመሆኑ ነው። ስለሆነም ለሰበር ክርክሩ አወሳሰን ሲባል ይህ የግልግል ጉባኤው ውሳኔ ተፈጥሮና በ1958 የወጣው የኒዮርክ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን በሀገራችን የህግ ሥርዓት ያለውን ቦታ በአግባቡ መመርመር ይጠይቃል።

19. ከሀገር ውጪ የሚሰጡ የግልግል ውሳኔዎችን በሃገራት ውስጥ በማስፈፀም ረገድ እ.ኤ.አ በ1958 የወጣው ለግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች ዕውቅና መስጠትና ማስፈፀምን የሚመለከት የኒውዮርክ ኮንቬንሽን (The New York Convention on the Recognition and Enforcement of Arbitral Awards) እንደ ትልቅ ስኬትና እመርታ ይወሰዳል። በርካታ የዘርፉ ተመራማሪዎች እንደሚመሰክሩለትም ከሁሉም ሃገራት ፍላጎት ጋር በሚስማማ መልኩ የግልግል ውሳኔዎች በቀላሉ የሚፈፀሙበትን መንገድ ዘርግቷል ተብሎ ይታመናል። በሃገራችንም ከኢኮኖሚው እድገት ጋር ተያይዞ ድንበር ተሻጋሪ የንግድ ልውውጦች እየተጠናከሩ በመሆኑና ግዙፍ ኩባንያዎች የገበያ አድማሳቸውን በማስፋት ወደ ሃገራችን በማቅናት መዋዕለ ንዋያቸውን እያፈሰሱ በመሆኑ ይህን ዘላቂ ለማድረግ፤ በተለይም ኢትዮጵያ የዓለማቀፉ የንግድ ማህበር (World Trade Organization) አባል ለመሆን በምታደርገው ጥረት አንዱ መመዘኛ ተደርጎ የሚወሰድ በመሆኑ፤ እንዲሁም አለመግባባቶች በግልግል መቋጨታቸው ከሚኖረው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አንፃር ሃገራችን የኒውዮርኩን ኮንቬንሽን ለማጽደቅ በሂደት ላይ መሆኗ ይታወቃል።

20. የኒዮርኩ ኮንቬንሽን እስካሁን በሃገራችን አልፀደቀም ማለት ግን በህግ ሥርዓታችን ውስጥ ምንም ቦታ አልተሰጠውም ማለት እንዳልሆነ ተገቢነት ያላቸውን ድንጋጌዎች በማየት መገንዘብ ይቻላል። በሀገራችን ውስጥ በግልግል ጉባኤዎች የሚሰጡ ውሳኔዎች የሚፈፀሙት የፍርድ ውሳኔዎች በሚፈፀሙበት መንገድ ስለመሆኑ

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 319 በግልጽ ተደንግጓል። በሌላ በኩል ከውጪ ሀገር የሚመጡ የግልግል ውሳኔዎች የሚፈፀሙበት ራሱን የቻለ ሥርዓት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ ከአንቀጽ 456 እስከ 461 ተደንግጎ ይገኛል።

21. ከኒዮርኩ ስምምነት ይዘትና ከሃገራችን ህጎች መገንዘብ እንደሚቻለው በውጭ ሃገራት የሚሰጡ የግልግል ውሳኔዎችን በማስፈፀም ረገድ የኢትዮጵያ ህግ ከኒዮርክ ስምምነት *ጋር* ተመሳሳይነት አለው። መመሳሰሉን ለማሳየት የሚከተሉትን ነጥቦች በማነፃፀር ማንሳት ይቻላል፡-
    - የስምምነቱ አንቀጽ 1(3) ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 458(ሀ) እና 461(1)(ሀ)
    - የስምምነቱ አንቀጽ 3 ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 461(1) ይዘት *ጋር*
    - ከኒውዮርኩ ስምምነት በዋናነት የሚጠቀሱት በአንቀጽ 5 *ሥር* የተጠቀመጡት *ሁኔታዎች* ሲሆኑ እነዚህ ሁኔታዎች ከኢትዮጵያ ህግ *ጋር* በእጅጉ የሚመሳሰሉ መሆኑን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 461(1)(ለ)-(ሠ) ከተዘረዘሩት *ጋር* በማነፃፀር መረዳት ይቻላል።
22. በዚህ መልኩ በኒውዮርክ ስምምነት እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 461 መካከል የቃል በቃል መመሳሰል እንዴት ሊፈጠር ቻለ የሚለውን በአግባቡ ማየትም ያስፈልጋል። በኒውዮርክ ስምምነት እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ መካከል ላለው መመሳሰል በምክንያትነት የሚጠቀሰው የሥነሥርዓት ህጉ የወጣው የኒውዮርኩ ስምምነት በወጣ በጥቂት አመታት ውስጥ መሆኑ ነው። የሥነ ሥርዓት ህጉ እ.ኤ.አ በ08/10/1965 የወጣ ሲሆን የኒዮርክ ስምምነት ለፊርማ ክፍት የሆነው እ.ኤ.አ በ31/12/1958 ነው። ከዚህ በመነሳት ህግ አውጭው በውጪ ሃገራት የተሰጡ የግልግል ውሳኔዎችን ለማስፈፀም እንዲሁም አፈፃፀሙን ለመቃወም ሊጠቀሱ የሚችሉ ምክንያቶችን ከኒዮርክ ስምምነት ሊወስድ መቻሉ ይታመናል።
23. ስለሆነም በተያዘው ጉዳይ ግራቀኙ ያደረጉትን ስምምነት ተከትሎ የግልግል ጉባኤው የሰጠው ውሳኔ እንደ እንግሊዝ አገር ውሳኔ የተቆጠረ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ለማሳረም በሚል ለዚህ ፍርድ ቤት መቅረቡ ተገቢ ባይሆንም ውሳኔው ዕውቅና የሚያገኘውና ተፈፃሚም የሚሆነው ከአንድ አገር ውጪ የተሰጠን ውሳኔ አፈፃፀም በተመለከተ በ1958 በወጣው የኒዮርክ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን መሰረት በመሆኑ በዚህ አግባብ አቤቱታ ሊቀርብና ሊስተናገድ አይገባም ማለት ግን አይሆንም።
24. በአጠቃላይ ግራቀኙ ወገኖች በ Grain and Feeds Trading association (GAFTA) የሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 125 (GAFTA Rules NO. 125) መሰረት በሚቋቋም የግልግል ዳኝነት አካል በእንግሊዝ ሃገር ክርክራቸውን ለመቋጨት የተስማሙ በመሆኑና የግልግል ዳኝነቱ ውሳኔ የተሰጠውም ይህን ስርዓት ተከትሎ በመሆኑ፤ አመልካቹም በግልግል ጉባኤው ውሳኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታውን በውል ስምምነታቸው እና በህግ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ለንደን ለሚገኘው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅሬታውን በየጊዜው ያቀርብ እንደነበር የተረጋገጠ በመሆኑ፤ አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ሰበር ችሎት ለማቅረብ በዋቢነት በጠቀሰው የሰ/መ/ቁ 42239 የተሰጠው የህግ ትርጉም የግልግል ጉባኤው መቀመጫ በተዋዋዮች በስምምነት ወይም ከህግ በተሰጠ ስልጣን በውጪ ሀገር እንዲሆን ተደርጎ በውጪ ሀገር የተሰጠ ፍርድን የሚመለከት ባለመሆኑ፤ እንዲሁም ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰበር ችሎት በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 (በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 እንደተሻሻለ) የተሰጠው መሰረታዊ የህግ ስህተትን የማረም ስልጣን የተያዘውን ጉዳይ የሚመለከት ባለመሆኑ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አመልካችና ተጠሪ እ.ኤ.አ ኖቨንበር 25/2011 ባደረጉት ስምምነት መሰረት አለመግባባታቸውን በ Grain and Feeds Trading association (GAFTA) የሥነ ሥርዓት ህግ 125 (GAFTA Rules NO. 125) መሰረት በሚቋቋም የግልግል ዳኝነት አካል በእንግሊዝ ሃገር ለመቋጨት በተስማሙት መሰረት የተቋቋመው ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ (APPEAL AWARD NO: 4496 & 4515) በኢፌዴሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ታይቶ እንዲታረም የቀረበው የሰበር ማመልከቻ በግራቀኙ የተደረገውን ስምምነት እና ህጉን መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244(2)(ሀ) እና 245(2) መሰረት ወስነናል፡፡
2. አመልካች ለዳኝነት ከከፈለው ብር 1,605,760.10 (አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰምስት ሺህ ሰባት መቶ ስድሳ ብር ከአስር ሳንቲም) ላይ በደንቡ መሰረት የሚቀነሰው ሂሳብ ከተቀነሰ በኃላ ቀሪው ገንዘብ ለአመልካች እንዲመለስ ብለናል፡፡ የፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር ይህን ተከታትሎ ያስፈጽም፡፡
3. ውሳኔው ሀምሌ 5/2011 ዓ.ም በችሎት ተነቧል፡፡
4. በዚህ ችሎት ስለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የልዩነት ሀሳብ

ውል የተዋዋዩ ወገኖችን ነፃነት የሚያሳይ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን ተዋዋይ ወገኖች ውል በሚያደርጉበት ጊዜ ውሉ ህግን እና ሞራልን የሚቃረን መሆን ሊቃረን አይገባም።

አመልካችና ተጠሪ ጉዳያቸውን በግልግል ለማሳየት መስማማታቸው የዳኝነቱ አገር እና የስነ ስርአት ህግ መምረጣቸው ጤናማ የውል ስምምነት ሲሆን ነገር ግን ከተዋዋዩች አንዱ የኢትዮጵያ መንግስት መ/ቤት ሆኖ የተዋዋሉበት ነገር ለኢትዩጵያ ሆኖ የተዋዋሉበት ነገር ለኢትዩጵያ እና ህዝቦቿ ጥቅም እንዲሰጥ መሆኑ ተረጋግጦ አለ እንዲሁም የሚፈፀመውም በኢትዮጵያ ሆኖ አመልካችን እንደ አንድ ተዋዋይ ግለሰብ በማሰብ የኢትዮጵያ ፍ/ቤት በማንኛውም ደረጃ ገዳዩ ቢቀርብለት የማየት ስልጣን እንደሌለው አድርጎ መዋዋል ህግን እና ሞራልን የሚጋፋ እንዲሁም ብሄራዊ ጥቅምን የሚጎዳ ከመሆኑም በላይ በውጭ አገር የተሰጠው ፍርድ የኢትዮጵያ መሰረታዊ ህግ ግድፈት በተፈፀመበት ጊዜ በኢትዮጵያ ፍ/ቤት አይታይም አይልም እንጂ የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫም ሆነ የሚመራበት ስነ ስርአት ህግ በኢትዮጵያ ባለመሆኑ እና የሚሰጠው ፍርድም የለንደን ፍርድ እንደሆነ መቆጠሩ በኢትዮጵያ ፍ/ቤት ፍርዱ ላይ መሰረታዊ የህግ ጥሰት ተፈጽሟል የሚል ወገን አቤቱታ ሲያቀርብ ፍ/ቤቱ የማየት ስልጣን የለውም የሚባል ከሆነ ኢትዮጵያን በራሷ ጥቅም ላይ ጉዳይዋን እንዳታይ ያገለለ ከመሆኑ አንፃር ውሉ በራሱ ለህግና ለሞራል ተቃራኒ የሆነ ውል በመሆኑ ከመነሻው ተቀባይነት ማግኘት ያልነበረበት ውል ነው ባይ ነኝ።

በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ጉዳዩ በግልግል እንዲታይ፣ መስማማታቸው በስምምነታቸው መሰረትም የግልግል ዳኝነቱ ሀጋዊ መቀመጫ አገር ለንደን መሆኑን እና ግልግሉ ሚመራበትን የስነ ስርአት ህግ የመረጡ መሆኑ እና ውሳኔው በኢትዮጵያ እንደተሰጠ ፍርድ እንደማይቆጠር በመስማማታቸው ላይ ልዩነት እንደሌላቸው ተረድቻለሁ።

ነገር ግን በዚህ መልኩ ተዋዋይ ወገኖች የተዋዋሉ መሆኑ እና በተለይ መንግስት በሚያስተዳድረው መ/ቤት የተወከሉ የስራ ኃላፋዎች ጉዳዩ በውጭ አገር እንዲታይ እና በውጭ አገር ህግም እንዲመራ የተስማሙበትን ልዩ ምክንያት ሳያስቀምጡ በአገር ጥቅም ላይ ስምምነት በማድረጋቸው ብቻ የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች በተለይም የሰበር ሰሚ ችሎቱ ስልጣን የለውም ለማለት የሚቻልበት አግባብ ተገቢነት ያለው አይደለም።

ግራ ቀኙ የስነ ስርአት ግድፈት ሲፈጽም ለለንደን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ማለት የሚችሉ መሆኑ የተዋዋሉ በመሆኑ አመልካች በለንደን በስነ ስርአት ጉዳይ ላይ ይግባኝ ማለቱን አልካደም፣ ተጠሪም በስነ ስርአት ጉድለት ብቻ ሳይሆን በፍሬ ነገር ላይም ይግባኝ ብሏል ቢልም በምን አይነት ፍሬ ነገር ላይ ይግባኝ እንዳለ ባልገለፀበት እና በአብብላጫው ድምጽ እንደተገለጸው ሁለት ጊዜ ለለንደን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ የተባለው በስነ ስርአት ግድፈት ላይ መሆኑ የሚያስረዳ ሆኖ እያለ በፍሬ ጉዳይ ላይ ይግባኝ እንዳለ በመቁጠር በስምምነቱ መሰረት ጉዳዩ የሚታየው በለንደን አገር እና በለንደን ፍ/ቤት ብቻ ነው መባሉ ሌላው ጉዳይ ነው።

እንዲሁም ክርክር ያስነሳው ጉዳይ ሰንዴን ወደ ኢትዮጵያ ለማስመጣት ሆኖ ስንዴውን የሚጠቀሙት ኢትዮጵያውያን ሆነው እያለ እንዲሁም የግልግል ጉባኤው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ለዛው አገር ከፍተኛ ፍ/ቤት አቤቱታ የሚቀርብ መሆኑን ይግለጽ እንጂ በኢትዮጵያ ፍ/ቤት የሰበር ስልጣንን በሚያስቀር መልኩ ስለመዋዋላቸው የሚያሳይ ነገር ሳይኖር አመልካች ቀደም ሲል በስነ ስርአት ግድፈት ምክንያት ለከፍተኛ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ለዛው ይግባኙን ላየው ፍ/ቤት ደግሞ አቤቱታ እንዲያቀርብ ስምምነቱን ማድረጉ በራሱ ኢትዮጵያ ምንም አይነት ተሳትፎ እንዳይኖራት ተደርጎ ውል የተደረገ መሆኑን ከማሳየቱም በላይ አመልካች በኢትዮጵያ የሚገኝ የመንግስት ተቋም እንደመሆኑ መጠን በኢትዮጵያ መሰረታዊ የሆኑ ህጎች የመዳኘት መብት ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ እና አመልካች ውል ውስጥ ሲገባ ማንኛውንም መብት የተወ መሆኑን ባልገለጸበት ሁኔታ የአመልካቾች ጥያቄም የኢትዮጵያ መሰረታዊ ህግ ተጥሶብናል በሚል አቤቱታ አቅረበው ባለበት፣ በስምምነታቸውም የስነ ስርኣት ግድፈት ሲኖር ይግባኝ ማለት እንደሚችሉ እንጂ መሰረታዊ ህግ ሲጣስ ለለንደን ፍ/ቤት ይግባኝ ይላሉ ተብሎ ውል ባልተገባበት ሁኔታ በተለይ ተዋዋይ ወገኖች መንግስታዊ አካላት ከሆኑ የሚዋዋሉትን ውሎች የመንግስትን እና የአገሪቱን ጥቅም በሚያስጠብቅ ሁኔታ መዋዋል ያለባቸው መሆኑ ስለታመነበት የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግን ለማቋቋም እና ስልጣኑን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀጽ 6/4/ለ/ መሰረት የፌዴራል ጠ/ዐቃቤ ህግ ውሎችን እንዲመረምር መደረጉ ከብሄራዊ ጥቅም አንፃር በራሱ በዚህ መልኩ የሚፈፀሙ ውሎች በአገር ጥቅም ላይ ጉዳትሊያድርሱ የሚችሉ ከመሆኑ አኳያም ሲታሰብ የአገሪቱ የመጨረሻ የሆነው ፍ/ቤት በውጭ አገር የተሰጠን ፍርድ የግልግል ዳኝነቱ አገር በመመረጡ እና የስነ ስርአት ህጉ በመመረጡ እንዲሁም ፍርዱ በኢትዮጵያ እንደተሰጠ ፍርድ ይቆጠራል በሚል በውሉ ባለመገለፁ መሰረታዊ የህግ ጥሰት እንዲታረም የቀረበን አቤቱታ ባለመቀበል ፍ/ቤቱ ስልጣን የለውም ተብሎ በአብላጫው የተሰጠው ፍርድ ተገቢ አይደለም በማለት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለው ተብሎ ብይን ተሰጥቶ ወደ ዋናው ጉዳይ ተገብቶ ሊመረመር ይገባ ነበር በማለት ስሜ በተራ ቁጥር 5 ስር የተሰየምኩት የችሎት ዳኛ በአብላጫው ድምጽ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 161597

ግንቦት 27 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- ወ/ሮ ፍሬህይወት ገበየሁ

ተጠሪ፡- አቶ ዘሪሁን ተፈራ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በውጪ ሀገር የተሰጠ ፍርድ የሚፈፀምበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በቀን 19/07/2009 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት የአፈፃፀም አቤቱታ የአሜሪካን የዲስትሪክት ፍ/ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረውን የባልና ሚስት ፍቺና ንብረት ክፍፍል ክርክር መርምሮ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በቀን 1/02/2013 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ መሠረት ተጠሪ እንዲፈፅሙ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ በውጪ ሀገር የተሰጠ ፍርድ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲፈፀም ሊሟሉ ከሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች አንዱ እንዲፈፀም የተጠየቀውን ፍርድ የሰጠው ፍርድ ቤት የሚገኝበት ሀገር በኢትዮጵያ የተሰጠውን ፍርድ የሚፈፅም መሆኑ ሲረጋገጥ በመሆኑ ይህንኑ መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች የሚሰጡት ውሳኔ በአሜሪካን ፍርድ ቤቶች የሚፈፀሙ ስለመሆን አለመሆኑ እንዲሁም ይህንኑ በተመለከተ የሁለቱ ሀገራት የሁለትዮሽ ስምምነት ስለመኖር አለመኖሩ ለፍ/ቤቱ እንዲገለፅ ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በቀን 01/03/2010 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቶ በቀን 10/04/2010 ዓ.ም በተፃፈ ምላሽ በሁለቱ ሀገራት መካከል ፍርድን ለማስፈፀም የሚያስችል ስምምነት አለመኖሩ የተገለፀ በመሆኑና የኢትዮጵያ ፍርዶችም

በአሜሪካን ሀገር የማይፈፀሙ ስለመሆኑ በቀን 27/04/2010 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ስለተገለፀ አመልካች ያቀረቡት የፍርድ ይፈፀምልኝ አቤቱታን አልተቀበልኩትም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኙት አመልካች ይግባኛቸውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቢያቀርቡም የይግባኝ አቤቱታቸው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም እነዚህ በስር ፍርድ ቤት የተሰጡትን ውሳኔዎች ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች በጠበቃቸው አማካኝነት ሐምሌ 18 ቀን 2010 ዓ.ም በተፃፈ 03 ገፅ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈፅመዋል ያሏቸውን ስህተቶች ዘርዝረው በማቅረብ እንዲታረሙላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት በሁለቱ ሀገሮች መካከል የአንዱን ሀገር ፍርድ እንዴት እንደሚፈፀም የጋራ ስምምነት የለም ተብሎ ተረጋግጦ እያለ በተዘረጋለት ስርዓት ጉዳያችንን ሊያስተናግድ ሲገባ "የተለየ ስምምነት ከሌለ..." የሚለውን ሀረግ በስህተት በመተርጎም ፍርዱ ሊፈፀም አይገባም በማለት መወሰኑ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪው ተመርምሮ አመልካች በአሜሪካን ሀገር ፍ/ቤት የተሰጠዉን ውሳኔ መሠረት አድርገው በኢትዮጵያ ፍ/ቤት ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስ በሁለቱ ሀገራት መካከል ፍርድን ለማስፈፀም የሁለትዮሽ ስምምነት የለም ተብሎ ውድቅ የመደረጉን አግባብ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 256 እና ተከታዮቹ አንፃር ለማጣራ መዝገቡ ለሠበር ችሎት ቀርቧል፡፡ በጉዳዩ ላይ አመልካች መልስ እንዲሰጥበት በጋዜጣም ጭምር ጥሪ ቢደረግለትም ሊቀርባ ባለመቻሉ መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፎ ክርክሩ በሌለበት እንዲቀጥል ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ከተያዘው ጭብጥና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ ይህ ጉዳይ በዉጭ አገር የተሰጠ ፍርድ የሚፈጸምበትን ሁኔታ የሚመለከት ነዉ፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ የተመለከተው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ በሁለት ዓብይት ምዕራፎች የተመለከተ ሲሆን፣ በምዕራፍ 1 ላይ የተመለከተው በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የተሰጠን ፍርድ በማስፈፀም ረገድ ተፈጻሚነት ያላቸው ድንጋጌዎች ሲሆን፣ በምዕራፍ 2 (ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 456 እስከ 461 የተጠቀሱት ድንጋጌዎች) ደግሞ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ ወይም ብይን የሚፈፀምበትን ሁኔታ

የሚመለከቱ ናቸው። በውጭ አገር የተሰጠን ፍርድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ከማስፈጸም ጋር በተያያዘ መሠረቱ (principle) በህጉ አንቀጽ 456 ላይ የተመለከተ ሲሆን፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 1 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ "በኢንተርናሲዮናል ስምምነት በተለየ እንዲፈጸም የሚደረግ ልዩ ህግ ከሌለ በቀር ከኢትዮጵያ ዉጪ የተሰጠ የፍርድ ዉሳኔ ወይም ብይን የሚፈጸመዉ በዚህ ህግ በተመለከተዉ ድንጋጌ መሠረት ነዉ" በማለት የሚያስቀምጥ ሲሆን፣ የድንጋጌዉ የእንግሊዝኛ ትርጉምም "Unless otherwise expressly provided by international law conventions, foreign judgments may not be executed in Ethiopia except in accordance with the provisions of this chapter" በማለት ያስቀምጣል። የዉጭ አገር ፍርድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ሊፈጸሙ የሚችሉባቸዉ ሁኔታዎችም በህጉ አንቀጽ 458 ላይ ተመልክተዋል። እነዚህም ሁኔታዎች እንዲፈጸም የተጠየቀዉን ፍርድ የወሰነዉ ፍርድ ቤት የሚገኝበት አገር በኢትዮጵያ የተሰጠዉን ፍርድም የሚያስፈጽም መሆኑ ሲረጋገጥ፤ ፍርዱ የተሰጠዉ በህግ በተቋቋመ ፍርድ ቤት መሆኑ ሲታወቅ፤ የፍርድ ባለዕዳዉ ቀርቦ መቃወሚያዉን ለማሰማት መብት የተሰጠዉ መሆኑ ሲረጋገጥ፤ ፍርዱ የመጨረሻና ተፈፃሚነት ያለዉ መሆኑ ሲታወቅ እና የፍርዱ መፈጸም ለህዝብ ሞራልና ጸጥታ ተቃራኒ ያለመሆኑ ሲታወቅ ስለመሆኑ በድንጋጌዉ ላይ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል።

ከእነዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለዉ፣ በውጭ አገር የተሰጠ ፍርድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ሊፈጸም የሚችለዉ በመርህ ደረጃ በኢትዮጵያ እና ፍርዱን በሰጠዉ ፍርድ ቤት አገር መካከል ይህን አስመልክቶ የተደረገ ስምምነት (bilateral agreement) መኖሩ ሲረጋገጥ ሲሆን፣ በልዩ ሁኔታ በህጉ አንቀጽ 458 ስር የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተዉ ሲገኙ ነዉ። በመሆኑም በህጉ አንቀጽ 458 የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸዉ ከተረጋገጠ ምንም እንኳ የዉጭ አገር ፍርድ የሚፈጸምበትን ሁኔታ በተመለከተ የተደረገ የሁለትዮሽ ስምምነት ባይኖርም፣ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ፍርዱን ተቀብለዉ ማስፈጸም የሚችሉ መሆኑን ነዉ። ስለሆነም በዉጭ አገር የተሰጠን ፍርድ እንዲያስፈጽም ዳኝነት የቀረበለት የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት በቅድሚያ እንዲያጣራ የሚጠበቅበት ለአፈፃፀም የቀረበዉን ፍርድ በሰጠዉ ፍርድ ቤት አገር እና በኢትዮጵያ መካከል የፍርድ አፈፃፀምን አስመልክቶ የተደረገ የሁለትዮሽ ስምምነት መኖር አለመኖሩን፣ ስምምነት የሌለ መሆኑ ከተረጋገጠ በህጉ አንቀጽ 458 ላይ የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች የተሟሉ መሆን አለመሆኑን ነዉ።

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ፣ ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ፣ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች የቀረበዉን የአፈፃፀም ጥያቄ ዉድቅ ያደረገዉ፣ ከፍርድ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ እና በአሜሪካን ሀገር መካከል የተደረገ የሁለትዮሽ ስምምነት አለመኖሩንና በኢትዮጵያ የተሰጡ ፍርዶች በአሜሪካ የማይፈጸሙ ስለመሆኑ የኢፌዲሪ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከጻፈለት ደብዳቤ ማረጋገጡን ነዉ፡፡ ይሁንና ከላይ እንደተገለጸዉ የሁለትዮሽ ስምምነት መኖር ብቸኛዉ ቅድመ ሁኔታ አይደለም፡፡ በመሆኑም የአሜሪካን አገር ፍርድ ቤቶች በኢትዮጵያ የተሰጡትን ፍርዶች የሚፈጽሙ መሆን ያለመሆኑን ጨምሮ ሌሎች በህጉ አንቀጽ 458 ላይ የተጠቀሱት ቅድመ ሁኔታዎች በተጨባጭ ማስረጃ ሊረጋገጡ የሚገባቸዉ ናቸዉ፡፡ የአሜሪካን አገር ፍርድ ቤቶች በኢትዮጵያ የሚሰጡትን ፍርድ የሚፈጽሙ መሆን ያለመሆኑና ሌሎች በህጉ የተመለከቱት ሁኔታዎች ፍርድ ቤቱ የአፈፃፀም አቤቱታዉን ተቀብሎ ለማስተናገድ ስልጣን ያለዉ መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ ሊረጋገጡ የሚገቡ መሠረታዊ የፍሬ ነገር ጭብጦች በመሆናቸዉ እና ፍሬ ነገሩን ለማስረዳት ሊቀርብ የሚገባዉ የማስረጃ ዓይነት በህግ ተለይቶ የተወሰነ እስካልሆነ ድረስ፣ ፍርድ ቤቱ ማናቸዉንም ማስረጃ በማስቀረብ እና በመመርመር እነዚህን ፍሬ ነገሮች የማረጋገጥ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ ይህ በመሆኑም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት እነዚህን ፍሬ ነገሮች በዚህ መልኩ አጣርቶ መወሰን ሲገባዉ፣ ከኢፌዲሪ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቀረበዉን ደብዳቤ ብቻ መሠረት በማድረግ የሰጠዉ ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 193868 በቀን 14/06/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 156444 በቀን 30/08/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተዘግቶ የነበረዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ፣ የአሜሪካን አገር ፍርድ ቤቶች በኢትዮጵያ የተሰጠዉን ፍርድ የማስፈጸም ልምድ ያላቸዉ መሆን ያለመሆኑን ሌሎች በህጉ አንቀጽ 458 ላይ የተመለከቱትን ሁኔታዎች አመልካች በሚያቀርቡትና ስለጉዳዩ ማስረዳት የሚችል ማንኛዉንም ማስረጃ በማስቀረብ እና

በመመርመር ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ እንዲሰጥ መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 343(1) መሠረት ተመልሶለታል፡፡

3. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ.161780

ሀምሌ 30 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች - መዓዛ አሸናፊ

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ኑረዲን ከድር

አመልካቾች - 1ኛ. አቶ ተረፈ በቀለ

2ኛ. አቶ ተሻለ በቀለ

ተጠሪ - ወ/ሮ ውድነሽ ዳዲ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 153643 ሚያዚያ 26 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ክርክሩ የጀመረው ተጠሪ በአመልካቾች ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

ተጠሪ ታህሳስ 26/2008 ዓ.ም ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- ከ1ኛ አመልካች ጋር ሚያዚያ 9/1991 ዓ.ም ጋብቻ ፈጽመን ስንኖር ከቆየን በኃላ ጋብቻችን ከመጋቢት 2006 ዓ.ም ጀምሮ በአሜሪካን ሀገር ፍርድ ቤት በተሰጠ ፍርድ ፈርሷል፤ ይህን ተከትሎ በአሜሪካን ሀገር ያፈራነውን ንብረት ክፍፍል አድርገናል፤ ከ1ኛ አመልካች ጋር ኢትዮጵያ ወስጥ ቡራዩ ከተማ ከታ ቀበሌ የቤት ቁጥር አዲስ የሆነ የማህበር ቤት በጋራ አፍርተናል፤ ይህን ቤት በተመለከተ በመ/ቁ 161852 በፌዴራሉ 7ኛ ፍ/ብሔር ችሎት ክስ የመሰረትኩ ሲሆን 1ኛ አመልካች የጋራ ቤታችን የሆነውን ይህን ቤት ዘመኑ ካልታወቀ ጊዜ ጀምሮ ወንድሙ ለሆነው ለ2ኛ አመልካች በስጦታ መስጠቱን በ23/11/2007 ዓ.ም ለፍርድ ቤቱ ጽፎ ባቀረበው መልስ ያረጋገጠ በመሆኑ በአመልካቾች መካከል የተደረገው ስጦታ ውል እንዲፈርስ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካቾች ለክሱ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር መልስ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ በመቀወሚያው ላይ ያቀረቡትን ክርክር ከሰማ በኃላ አመልካቾችን የይርጋ መቃወሚያ ተቀብሎ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ውሳኔ የስጦታ ውል የተከናዋነው በቀን 29/07/1991 ዓ.ም ሲሆን ተጠሪ ክስ ያቀረቡት ደግሞ የስጦታ ውሉ ከተደረገ ከ16 ዓመት በኃላ ታህሳስ 26/2008 ዓ.ም ነው፤ ይህም

በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 69 ስር የተመለከተውን የሁለት ዓመት ጠቅላላ የይርጋ ጊዜ ካለፈ በኃላ በመሆኑ የዳኝነት ጥያቄው በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ክርክሩን መርምሮ ጋብቻው በተደረገበትና እና በስጦታ ውሉ መካከል ያለው ጊዜ የ 1 ወር በመሆኑ ለጉዳዩ አወሳሰን ይረዳ ዘንድ የስጦታ ውሉ እውነተኛነት በቅድሚያ መረጋገጡ ተገቢ ነው፤ ስለሆነም ይዞታው ለ1ኛ አመልካች በማህበር ተደራጅተው የተሰጣቸው መቼ እንደሆነና ለማህበሩ ይዞታው መቼ እንደተሰጠ፤ ቤቱ መቼ ተሰርቶ እንደተጠናቀቀና ለ17 ዓመት በማን ስም ቤቱ እንደሚታወቅ፤ ውክልና ባልና ሚስቱ ሲሰጡ ቆይተዋል የተባለ በመሆኑ ለምን አላማ ውክልና ሲሰጥ እንደነበር እንዲሁም የስጦታ ውሉን ህጋዊነት ጭምር ለማጣራት የሚያስችሉ ማስረጃዎችን 1ኛ አመልካች ከተደራጁበት የቤት ስራ ማህበር በመጠየቅ፣ ማህደሩን በማስቀረብ፣ የማህበራት ማደራጃ የክርክሩን ቤት በማን ስም እንደሚያውቀው በመጠየቅ፣ እንዲሁም ቤቱ ከሚገኝበት የቡራዩ ከተማ አስተዳደር በማጣራትና ሌሎች በግራቀኙ የቀረቡ ማስረጃዎችን በመመርመር ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል ብሏል፡፡ በአጠቃላይ ባልተጣራ ክርክር ክሱ በይርጋ ይታገዳል ተብሎ ውድቅ መደረጉ ተገቢ አይደለም በማለት ውሳኔውን ሽሮ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የክስ መቃወሚያውን ለመወሰን የሚረዳውን ማስረጃ አስቀርቦ በመመርመር ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341(1) መሰረት መልሶለታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡ አመልካቾች ሀምሌ 23 ቀን 2010 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ የግባኝ ሰሚው ችሎት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ያሳለፈውን ውሳኔ ተገቢነት ለማጣራት ሲባል ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ታህሳስ 19/2011 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በሰጠው ፍርድ አግባብ እንዲወሰን የጠየቁ ሲሆን አመልካቾችም ክርክራቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩ ለምርመራ የተቀጠረው በዚህ ሁኔታ ነው፡፡

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለፅነው የክርክሩን አመጣጥ ነው፡፡ ጉዳዩን አግባብነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው የስር ፍርድ ቤት በአመልካቾች መካከል የተደረገው የስጦታ ውል የተከናዋነው በቀን 29/07/1991 ዓ.ም በመሆኑና ተጠሪ ክስ ያቀረቡት ውሉ ከተደረገ ከ16 ዓመት በኃላ ታህሳስ 26/2008 ዓ.ም በመሆኑ በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 69 ስር የተመለከተው የሁለት ዓመት ጠቅላላ የይርጋ ጊዜ ካለፈ በኃላ የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የወሰነ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ችሎት

በበኩሉ ውሳኔ የተሰጠው መቃወሚያውን ለመወሰን የሚረዳው ማስረጃ እንዲቀርብ ተደርጎ ሳይመረመር ነው በማለት ውሳኔውን ሽሮ የስር ፍርድ ቤት ማስረጃውን አስቀርቦ በመመርመር ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን መልሶለታል፡፡

ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244 እና 245 ድንጋጌዎች መረዳት እንደሚቻለው ለክሱ የተለያየ መቃወሚያ ሲቀርብ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ ሌላው ተከራካሪ ወገን በጉዳዩ ላይ የሚያቀርበውን ክርክር ከሰማ በኋላ ውሳኔ ለመስጠት ተገቢ መስሎ የሚገምተው ማስረጃ እንዲቀርብለት በማድረግ መቃወሚያው በተገቢና በቂ ማስረጃ መደገፉን በመመርመር ተገቢ መስሎ የታየውን ብይን ሊሰጥ ይገባል፡፡ ከዚህ የህጉ ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻለው መቃወሚያው ተቀባይነት አግኝቶ ክሱ ውድቅ እንዲሆን ሊወሰን የሚችለው መቃወሚያው በተገቢና በቂ ማስረጃ መደገፉ ሲረጋገጥ መሆኑን ነው፡፡

ስለሆነም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መቃወሚያው ላይ የተወሰነው መቃወሚያውን ለመወሰን ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ ሳይደረግ መሆኑን በማረጋገጥ የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ ሽሮ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ ተደርጎ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለስር ፍርድ ቤት መመለሱ ክርክሩ የሚመራበትን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአጠቃላይ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 153643 ሚያዚያ 26 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የተሰጠ የዕግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ.መ.ቁ 173967

መጋቢት 28 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፦ እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሾሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም፡፡

አመልካቾች፦ አቶ አማኑኤል ገ/ጊዮርጊስ

ተጠሪዎች፦ የትግራይ ክልል ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤሕግ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 07 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሰሜን ምዕራባዊ ዞን የሸሬ እንዳስላሴ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 22620 መጋቢት 05 ቀን 2011 ዓ.ም አመልካች በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ሊነሳ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ በወንጀል ጉዳይ በሌለሁበት ታይቶ የተሰጠ ውሳኔ ይነሳልኝ በሚል የቀረበን ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ አመልካች የአዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 4/5 ድንጋጌን በመተላለፍ ሕገወጥ ማንቀሳቀሻ በተጭበረበረ ሰነድ መስራት ወንጀል ፈጽሟል በማለት ያቀረባቸውን ስድስት ክሶች የተመለከተው በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሰሜን ምዕራባዊ ዞን የሸሬ እንዳስላሴ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ተፈልጎ በአድራሻው ሊገኝ ስላልቻለ በመቃልህ ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ስላልቀረበ በሌለበት ጉዳዩን በማየት በተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ በማለት በ18 ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች ውሳኔውን ለሰጠው ፍ/ቤት ባቀረበው አቤቱታ በሌለበት ታይቶ የተሰጠውን ውሳኔ ያወቀው በቀን 23/05/11 ዓ/ም በሕመም ምክንያት አዲስ አበባ በነበሩበት ጊዜ መሆኑን፤ በጊዜ ቀጠሮ ጊዜ ዋስ የሆንዋቸው ግለሰብ በሸሬ ከተማ የሚገኙ ቢሆነም አመልካችን እንዲያቀርቡ ያልተጠየቁ መሆኑን፤ በሌለበት ጉዳያቸው እንዲታይ የተደረገው ከትግራይ ክልል ውጪ ሸፋን በሌለው በመቃልሕ ጋዜጣ

መሆኑን በመግለጽ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ፍርድ ተሰርዞ ጉዳያቸው ባሉበት እንዲታይ አቤቱታ አቅርበዋል።

ፍ/ቤቱም ተጠሪ በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጥበት ካደረገ እና የአመልካችን ምስክሮች ከሰማ በኋላ በኋላ ምስክሮቹ አመልካች በሐምሌ ወር 2008 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ሄዶ የታከመ እና ኒሞኒያ የተገኘበት መሆኑን፤ በኋላም እስከ 2009 ዓ/ም ድረስ ቆይቶ ለስራ ወደ ዱባይ የሄደ እና በ2010 ዓ.ም ወደ መቀሌ ተመልሶ እስከ ሚያዝያ ወር ድረስ ይኖር እንደነበር አስረድተዋል፤ ይህንኑ የሚያሳይ የሕክምና ማስረጃም ቀርቧል፤ አመልካች መጀመሪያ ክስ ቀርበባት በመደበኛ መጥሪያ እንዲቀርብ ፖሊስ በቀጠሮ እንዲቀርብ ያዘዘው መሆኑን ለፍ/ቤቱ በጻፈው ምላሽ አሳውቋል፤ አመልካች የክስ ቻርጅ ደርሶት በመጥሪያ ሳይቀርብ በመቅረቱ ፖሊስ በእስር እንዲያቀርበው ከታዘዘ ጠፍቶ እንደተሸሸገ መረዳት ይቻላል፤ የክፍሉ አስተዳደር ጽ/ቤት አመልካች በአድራሻው እንደሌለ የገለጸ በመሆኑ አመልካች በመቃልህ ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለታል፤ አመልካች ባስመዘገበው ቀበሌ እንደሌለ ተረጋግጦ ፍ/ቤቱ በምትክ መጥሪያ አጠራር ስርዓት አመልካችን በሚጠቅም መንገድ የጋዜጣ ጥሪ ያደረገለት እና ያልቀረበ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የፈጸመው የስነ ስርዓት ስሕተት የለም በማለት የአመልካች አቤቱታው ውድቅ በማድረግ ወስኗል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት ፖሊስ መጥሪያ ሰጥቸዋለሁ ብሎ ወረቀት ስለጻፈ መጥሪያ ደርሶሃል ቢልም ፖሊስ አልነገረኝም፤ አመልካች የፈረምኩበትንም ማስረጃ አላቀረበም፤ ፖሊስ ነግሬዋለሁ ብቻ ማለቱ እንደነገረኝ ማረጋገጫ አይደለም፤ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 125 በግልጽ እንደተደነገገው ተከሳሽ በእስር እንዲቀርብ ትዕዛዝ የሚሰጠው ተከሳሹ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ መጥሪያ እንደደረሰው ማረጋገጫ ከቀረበ በኋላ ነው፤ ፖሊስ በእስር እንዲያቀርበኝ በፍ/ቤት ሲታዘዝ በእስር እያቀረብኩት ነው ብሎ በቀን 3/01/2009 ምላሽ የሰጠ ቢሆንም ይህን ምላሽ የሰጠው አመልካችን ሳይዝ ነው፤ ፖሊስ የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ለአመልካች ነግሬአለሁ ባለበት ሰዓት አመልካች በሸሬም ከተማ ሆነ በትግራይ ክልል አልነበርኩም፤ አመልካች በወቅቱ አዲስአበባ ውስጥ እንደነበርኩ ባቀረብኳቸው ማስረጃዎች ያስረዳሁ ቢሆንም የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት ይህን ማስረጃ ሳይመዝን አልፎታል፤ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የአመልካች ማስረጃዎች በአግባቡ ሳይምን የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት መጥሪያ ለአሁን አመልካች በቀጥታ መድረሱ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ፖሊስ አመልካች ወደ ፍ/ቤት እንዲቀርብ ነግሬዋለሁ በማለት ሪፖርትe

ማድረጉን መሠረት በማድረግ እና በጋዜጣ መጥሪያ መውጣቱን በቂ አድርጎ በሌለበት የተሰጠው ውሳኔ ሊነሳ አይገባም በማለተ የመወሰኑን አግባብነት ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 125 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል። ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ፖሊስ ለፍ/ቤቱ በሰጠው ምላሽ አመልካች በቀጠሮው ቀን እንዲቀርብ የተነገረው መሆኑን ምላሽ ገልጿል፤ ፍ/ቤቱም አመልካች እንዲቀርብ መጥሪያ ደርሶት ሳላልቀረበ ታስሮ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ የክፍሉ አስተዳደር ጽ/ቤት አመልካች ባስመዘገበው አድራሻ እንደሌለ በመግለጽ ምላሽ ልኳል፤ አመልካች በመቃልህ ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ሊቀርብ ሳላልቻለ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተላልፎበታል፤ ፖሊስ የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ለአመልካች እንደነገረው ምላሽ የሰጠ በመሆኑ መልስ የላከ በመሆኑ አመልካች ከፍትሕ ራሱን ደብቆ ተሸሽጎ እንደነበር የሚያመለክት ነው፤ አመልካች በሕክምና ላይ እንደቆየ ለማሳየት ያቀረባቸው ማስረጃዎች ጉንፋን እና ኒሞንያ በሽታ እንዳለበት ከሚያሳዩ በቀር በጤና ጣቢያው ተኝቶ ታካሚ እንደነበር አያሳዩም፤ አመልካች በትግራይ ክልል ባሉ ሆስፒታሎች ሕክምና ማግኘት ይችል ነበር፤ የአመልካች ምስክሮች ዘመዶቹ በመሆናቸው ገለልተኛ ምስክሮች አይደሉም፤ የሰር ፍ/ቤት መጥሪያ አደራረስን አስመልክቶ የፈጸመው የስነስርዓት ስሕተት ስለሌለ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው። አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል።

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል።

አመልካች ካቀረበው አቤቱታ እና የሰር ፍ/ቤት ለውሳኔው መሠረት ካደረጋቸው ነጥቦች አንጻር የዚህን ችሎት ምላሽ የሚፈልገው የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ የሰር ፍ/ቤት አመልካች በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳለት እና ጉዳዩ ባለበት እንዲታይ ያቀረበውን አቤቱታ ፖሊስ የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ለአመልካች የነገረው መሆኑን አሳውቋል፤ የክፍሉ አስተዳደር አመልካች ባስመዘገበው አድራሻ የሌለ መሆኑን በመግለጽ ምላሽ ሰጥቷል፤ ፍ/ቤቱ አመልካችን በሚጠቅም መልኩ በምትክ መጥሪያ አደራረስ በመቃልህ ጋዜጣ እንዲጠራ አድርጎ አመልካች ባለመቅረቡ በሌለበት እንዲታይ ማድረጉ የፈጸመው የስነስርዓት ስሕተት የለም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው።

በመሠረቱ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 161 የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው አንድ ክስ ተከሳሽ በሌለበት ነገሩ እንዲሰማ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ የሰጠ እንደሆነ የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ተከሳሹ የተከሰሰበት ወንጀል ዝርዝር፤ ነገሩ እንዲሰማ በተቀጠረበት ቀን ተከሳሹ ሳይቀርብ ቢቀር በሌለበት የሚፈረድ መሆኑን የሚገልጽ የመጥሪያ ማስታወቂያ በጋዜጣ እንዲወጣ ወይም ለተከሳሹ የሚደርስ መስሎ ከታየዉ መጥሪያዉ የሚደርስበትን ሌላ መንገድ ፍርድ ቤቱ ሊያዝ እንደሚችል በዚሁ ሕግ ቁጥር 162 ላይ በግልጽ ተመልክቷል። በዚህ ድንጋጌ መሠረት የሚደረግ የጋዜጣ ጥሪም ጉዳዩን አመልካች በሌለበት ለማየት የሚያስችል ቅድመ ሁኔታ ነው። ይህን ሥርዓት ተከትሎና በዚሁ ሕግ ቁጥር 163(3) መሠረት እንደ ማንኛዉም ደንበኛ ክስ ታይቶ ፍርድ የተሰጠ እንደሆነ በሕጉ ቁጥር 197 እስከ 202 በተመለከቱት ምክንያቶች ፍርዱ ዉድቅ እንዲደረግ ተከሳሹ ማመልከቻ ማቅረብ እንደሚችል በቁጥር 164 ተመልክቷል። ተከሳሹ በሌለበት የተሰጠው ፍርድ ውድቅ ተደርጎ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ያቀረበው ማመልከቻ የሚፈቀደው እንዲቀርብ መጥሪያ ያልደረሰዉ እንደ ሆነ ወይም ራሱ ወይም ጠበቃዉ ከዐቅም በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት መቅረብ አለመቻሉን ያስረዳ እንደ ሆነ ነዉ በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 199 ላይ ተደንግጓል።

በያዝነው ጉዳይ የሰር ፍ/ቤት ፖሊስ የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ለአመልካች የነገረው መሆኑን ለፍ/ቤቱ ያሳወቀ መሆኑን እና የክፍሉ አስተዳደር አመልካች ባስመዘገበው አድራሻ የሌለ መሆኑን በመግለጽ ምላሽ የሰጠ መሆኑን በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ በግልጽ ሰፍሯል። በአመልካች ላይ የቀረበው ክስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 161 ላይ በተመለከቱት ሁኔታዎች በሌለበት የሚታይ ከመሆኑ አኳያ ፍ/ቤቱ በቀጣይነት አመልካች በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግለት ትዕዛዝ መስጠቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 162 አግባብ የተሰጠ በመሆኑ በዚህ ረገድ ፍ/ቤቱ የፈጸመው ስሕተት የለም። ሆኖም ፍ/ቤቱ ለተከሳሽ የጋዜጣ ጥሪ ያስተላለፈው በመቃለህ ጋዜጣ ከመሆኑ አኳያ ተከሳሹ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ፍርድ እንዲነሳለት የሚያቀርበው ማመልከቻ ስለሚፈቀድባቸው ምክንያቶች አስመልክቶ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 199 (ሀ) ላይ "መጥሪያዉ ያልደረሰዉ እንደሆነ" በማለት ከተቀመጠው መስፈርት እና የተከሰሱ ሰዎች በሕገመንግስቱ ከተጠበቁላቸው መሠረታዊ መብቶች ገር በማገናዘብ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባ የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ ነው።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 20/4 የተከሰሱ ሰዎች ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ሲታይ በችሎት ተገኝተው የቀረበባቸውን ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረበባቸውን ምስክሮችን የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቹ ቀርበዉ እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው። ከዚህ ሕገ-መንግስታዊ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ የወንጀል ጉዳዮች ተከሳሽ በተገኘበትና የመከላከል መብቱ በተጠበቀበት ሁኔታ ማካሄድ መርሁ ሲሆን ልዩ ሁኔታው ደግሞ

በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 161 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት አንድ ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት ታይቶ በተወሰነ ጊዜ በመርሀ የተቀመጠዉን የተከሳሽን የመከራከር መብት ለማረጋገጥ ሲባል ፍርዱ እንደገና ተነስቶ ጉዳዩ እንደገና የሚታይበት ስርዓት በቁጥር 197 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የተቀመጠ በመሆኑ በተቻለ መጠን ተከሳሹ በእርግጠኝነት መጥሪያ ደርሶት በችሎት የመገኘትና የመከራከር መብቱን አዉቆ መተዉ እስካልተረጋገጠ ድረስ ይህ መብቱ ሊነፈግ አይገባም። በመሆኑም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 199 (ሀ) ላይ "መጥሪያዉ ያልደረሰዉ እንደሆነ" በሚል የተቀመጠውን መሰፈርት መሠረት በማድረግ ተከሳሹ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ፍርድ እንዲነሳ ባመለከተ ጊዜ ክሳሽ የሆነው ዓቃቤሕግ ተከሳሹ የፍ/ቤቱን መጥሪያ ሰምቶ ያልቀረበ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ሲሆን ፍ/ቤቱም ይህንን የማረጋገጥ ሀላፊነት አለበት።

ስለሆነም ከላይ ከተገለጹት ድንጋጌዎች እና ምክንያቶች አንጻር የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 199(ሀ) ተከሳሹ በትክክል መጥሪያ ደርሶት የመከራከር መብቱን አዉቆ በመተዉ መቅረቱ አሻሚ ባልሆነ መልኩ ዐ/ሕግ በሚያቀርበዉ በቂ ማስረጃ ካልተረጋገጠ በቀር ማወቅ ነበረበት ወይም ሊያዉቅ ይችላል የሚል ግምት በመዉሰድ ተከሳሹ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ ባለበት እንዲታይ ያቀረበዉ ማመልከቻ ዉድቅ ሊደረግ አይገባም።

በተያዘዉ ጉዳይ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ያደረገዉ አመልካች በአገር ዉስጥ አለመኖሩ ተረጋግጦ በምትክ መጥሪያ አጠራር ስርዓት በመቃልህ ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ያልቀረበ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩን አይቶ መወሰኑ የፈጸመው የስነስርዓት ስሕተት የለም በሚል ነዉ። ሆኖም አመልካች ጥሪ የተደረገለት በክልሉ ብቻ ተደራሽ በሆነው መቃልህ ጋዜጣ እንጂ ሐገር አቀፍ ስርጭት ባለው ጋዜጣ አይደለም፤ ዓቃቤሕግ ባቀረበው ክርክርም ለአመልካች ጥሪ የተላለፈበት መቃልህ ጋዜጣ ሐገር ዓቀፍ ስርጭት ያለው ስለመሆኑ አላረጋገጠም፤ ይልቁንስ አመልካች ባቀረባቸው ማስረጃዎች በጤና ችግር ምክንያት ከክልሉ ውጪ እንደነበር በኋላም በስራ ምክንያት ከኢትዮጲያ ውጪ እንደነበር አስረድቷል። አንድ ተከሳሽ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ክስ የቀረበበት ስለመሆኑ አውቋል የሚል ግምት ሊወሰድ የሚገባው ሐገር አቀፍ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ጥሪ የተደነገለት መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ እንጂ በክልሉ ብቻ ተደራሽ በሆነው ጋዜጣ ብቻ ጥሪ መደረጉ ተከሳሹ ክስ እንደቀረበበት አውቋል የሚል ግምት የሚያስወስድ አይደለም።

በመሆኑም የስር ፍ/ቤት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 162 ተከሳሹ በሌለበት ነገሩ እንዲሰማ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ለመስጠት የሚችልበትን ቅድመ ሁኔታ መነሻ በማድረግ ሐገራዊ ስርጭት በሌለው መቃልህ ጋዜጣ ለአመልካች ጥሪ ማስተላለፉን ለአመልካች መጥሪያ እንደደረሰው ማረጋገጫ አድርጎ በመውሰድ እና

መጥሪያ ደርሶታል የሚል ግምት በመውሰድ አመልካች በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ ባለበት እንዲታይ ያቀረበውን ማመልከቻ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 199(ሀ) ድንጋጌ ይዘትና በሕገመንግስቱ ለተከሰሱ ሰዎች የተጠበቁላቸውን መሠረታዊ መብቶች ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል። ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

ውሳኔ

1. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ምዕራብ ዞን የሸሬ እንዳስላሴ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 22620 መጋቢት 15 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና መጋቢት 19 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ እንዲሁም መጋቢት 05 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሸሯል።
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት የስር ፍ/ቤት አመልካች በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ ባለበት እንዲታይ ያቀረበውን ማመልከቻ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው በማለት ክርክሩ አመልካች ባለበት ታይቶ ውሳኔ እንዲያገኝ በማለት ወስነናል።
3. የሸሬ እንዳስላሴ ከፍተኛ አመልካች ባለበት ክርክሩን ቀጥሎ ተገቢውን እንዲወስን በማለት ጉዳዩ ተመልሶለታል።

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል። ይመለስ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ/መ/ቁ. 175142

ቀን ፡- ግንቦት 24 ቀን 2012 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሠሜን ሪጅን ሑመራ ዲስትሪክት

ተጠሪ ፡- አቶ ወሉ ገ/ሔር

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ተከሳሽ ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በቃፍታ ሑመራ ወረዳ ማይ ከድራ ከተማ ቀጠና 02 በምኖርበት ቤት የካቲት 18 ቀን 2009 ዓ/ም በአመልካች የተዘረጋ የኤሌክትሪክ መሥመር በተነሳ የእሳት ቃጠሎ መኖሪያ ቤቴ ስለወደመ ግምቱ ብር 49,500.00 ካሣ እንዲከፈለኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች የሠጠው መልስ ተጠሪ ለጉዳቱ ሊጋለጡ የቻሉት ከአመልካች ድርጅት ኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ደምበኛ የሆኑ አቶ ማማይ ተገኝ ለግል ቤታቸው ሊጠቀሙበት ከተሠጣቸው ኤሌክትሪክ ሀይል፤ ከሕግ ውጭ ከቆጣሪው ስበው ሲጠቀሙ አደጋው ከወ/ሮ አከዛ ተስፋይ ቤት ውስጥ በራሳቸው ችግር ምክንያት የተፈጠረ ስለሆነ ልንጠየቅ አይገባም፡፡ የተዘረጋው መስመር ደረጃውን የጠበቀ በመሆኑና ጥፋት ስላልፈጸምን ለክሱ ኃላፊነት የለብንም በማለት ተከራክሯል፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ/መ/ቁ. 175142

የምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሑመራ ምድብ ችሎት የግራቀኙን ማስረጃ በመስማትና የፎረንሲክ ምርመራ ውጤቱን በመመልከት የቃጠሎ አደጋው ከወ/ሮ አከዛ ቤት መነሳቱ አልተረጋገጠም፡፡ ቢረጋገጥ እንኳን ተጠሪ ጥፋት የሌለባቸው በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 2086 መሠረት አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊነት አለበት፡፡ በመኖሪያ ቤታቸው ላይ ለደረሠው ጉዳት ካሣ ብር 42,700.00 ከወጭና ኪሣራ ብር 3,500.00 ጋር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ አመልካች ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ የአመልካችን ይግባኝ ባለመቀበል ሠርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ከተጠሪ ጋር የውል ግንኙነት የለንም፡፡ በፎረንሲክ ምርመራ አደጋው የተነሳው ከወ/ሮ አከዛ ቤት ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ ለክሱ ኃላፊ ልንባል ስለማይገባ ውሳኔው ይሻርልን፤ አላግባብ የኤሌክትሪክ ሀይል ያከፋፈሉት አቶ ማመይ ተገኘ ጣልቃ እንዲገቡ ጠይቀንም መታለፉ ስህተት ያለበት ነው የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ አመልካች ለተጠሪ ቆጣሪ ያልሠጠና በራሳቸው ጊዜ ከሌላ ሠው ስበው ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለብኝም በማለት እየተከራከረ ለክሱ ኃላፊ መሆኑ ከፍ/ሕ/ቁ. 2086(2) እና 2098(1)(2) አኳያ ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ አዟል፡፡ የተጠሪ መልስ የአመልካች መስመር ተቆርጦ ወደ መኖሪያ ቤት ወድቆ የተነሳ ቃጠሎ ነው፡፡ ጥፋቱ የእኔ የተበዳይ ስለመሆኑ እስካላረጋገጠ ድረስ ለጉዳቱ አመልካች ተጠያቂ ነው፡፡ ያጠፋሁት ጥፋት ደግሞ ስለሌለ ውሳኔው ተገቢ ነው ብለዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታውን አጠናክሮ ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም አመልካች ለክሱ ኃላፊ መባሉ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ የጠየቁት ዳኝነት ከውል ውጭ ኃላፊነትን መሠረት ያደረገ ሲሆን በአመልካች የተዘረጋ በኤሌክትሪክ መሥመር ምክንያት በተነሳ የእሳት ቃጠሎ ቤቱ ስለወደመ ካሣ እንዲከፍለኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች ያቀረበው መከራከሪያ ተጠሪ ለጉዳቱ ሊጋለጡ የቻሉት የአመልካች ድርጅት አሠራርና ደንብ በመጣስ ሌላ ግለሠብ ቆጣሪ ለተጠሪዎች እና ለሌሎች ግለሠቦች የኤሌክትሪክ ገመድ በመዘርጋት ኤሌክትሪክ ሀይል በመስጠታቸው እና አደጋውም ከወ/ሮ አከዛ ተስፋይ ቤት ውስጥ በራሳቸው ችግር ኤሌክትሪክ ሰርኪዩት ሾርት ምክንያት የተፈጠረ ስለመሆኑ የትግራይ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ባደረገው የፎረንሲክ ቃጠሎ ማጣራት አረጋግጧል፡፡ ተጠሪ የአመልካች ደምበኛ አይደሉም፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ/መ/ቁ. 175142

ኤሌክትሪክ ሀይል የሚጠቀሙትም በሕገ-ወጥ መንገድ በተቀጠለ ገመድ ስለሆነ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ነው፡፡

በፍ/ሕ/ቁ. 2069(1) መሠረት እንደተመለከተው አንድ ሠው ከፍተኛ ጉልበት ያለው የኤሌክትሪክ መስመር በመዘርጋት በሌላ ሠው ላይ ጉዳት ካደረሠ ለጉዳቱ ኃላፊ ነው፡፡ የኤሌክትሪክ መስመሩን የዘረጋው ሰው ጥፋት ባይኖርበትም የንብረቱ ባለቤት በመሆኑ አጥፊ ሳይሆን አላፊ ስለመሆን በተደነገገው ክፍል ስር በተመለከተው አግባብ ለጉዳቱ ኃላፊነት ይወስዳል፡፡ ከኃላፊነት ለመዳን በፍ/ሕ/ቁ. 2086(2) እንደተመለከተው ጉዳቱ የደረሠው በተበዳዩ ጥፋት መሆኑን ማስረዳት አለበት፡፡ በሥር ፍርድ ቤቶች የተወሰነውም አመልካች ለዘረጋው የኤሌክትሪክ መስመር ለሚያስከትለው ጉዳት ኃላፊነት አለበት በማለት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ በሕግ ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረበውን ፎረንሲክ ምርመራ ውጤቱን ባለመቀበል ማስረጃ መዝነው አመልካች በዘረጋው የአሌክትሪክ መሥመር ጉዳት ደርሷል በማለት ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) ሆነ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ሥልጣን አልተሠጠውም፡፡ ነገር ግን ማስረጃ ለመመዘን ሥልጣን የተሠጠው ፍርድ ቤት ማስረጃ ሲቀበል የተከራካሪዎችን እኩል የመደመጥ መብት ካላከበረ፣ የማስረዳት ሸክም የማን ነው የሚለውን ካልለየ፣ የማስረጃ ተቀባይነትና ተገቢነት ላይ መከተል የሚገባውን ሥርዓት ካልተከተለ ወይም በምዘና ጊዜ የሁሉንም ተከራካሪዎች ማስረጃ አብሮ ካልመዘነ፤ በመሠረታዊ ሕግ ሆነ በሥነ-ሥርዓት ሕግ ያሉትን የማስረጃ ሕጎችና መርሆች ካላከበረ ጉዳዩ የማስረጃ ምዘና ሳይሆን የሕግ አተረጓጎም ስህተትና ፍርድ ቤት ያለበትን ኃላፊነት አለመወጣት ስለሚሆን የሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚመለከተው ጉዳይ ይሆናል፡፡

ጉዳት ያደረሠው ተጠሪ እና ሌሎች ግለሠቦች ከአመልካች ደምበኛ ሳይፈቀድላቸው ስበው በወሰዱትና ቤታቸው ወስጥ በዘረጉት የኤሌክትሪክ መሥመር ሀይል ስለመሆኑ በትግራይ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን በባለሙያ በተደረገ የፎረንሲክ ቃጠሎ ምርመራ ውጤት ተረጋግጧል፡፡ የባለሙያ ማስረጃ በቀረበ ጊዜ በዋናነት የሚመረመረው የባለሙያው ገለልተኛነት እና ሙያዊ ብቃት ሲሆን ሁለቱን መስፈርቶች ካሟላ

ማስረጃው የፍሬ ነገሩን መኖር ወይም አለመኖር ለማረጋገጥ ከፍተኛ ግምት የሚሠጠው (high probative value) ማስረጃ እንደሆነ ተቀባይነት ካላቸው የማስረጃ ምዘና መርሆዎች የምንረዳው ነው። የሥር ፍርድ ቤቶች ከኤሌክትሪክ አደጋ ጋር በተያያዘ የሚደርስ ጉዳት የአደጋውን መንሥዔ ለማወቅ ሙያ የሚጠይቅ ሆኖ እያለ ለባለሙያ ማስረጃው ውጤት ሳይሰጡ የፎረንሲክ ምርመራ ውጤቱን አለመቀበላቸው የማስረጃ ምዘና መርህ ስህተት ነው። የፎረንሲክ ምርመራ ውጤቱ ቃጠሎ ሊያስነሳ የሚችሉ ሁኔታዎች እንዳልነበሩ፣ የቃጠሎው ምክንያት በኤሌክትሪክ ሰርኪዩት ሾርት ምክንያት አቀጣጣይ ሀይል መሆኑን፣ ቃጠሎው ከወ/ሮ አከዛ ቤት ተነስቶ ወደ ሌሎች ቤት እንደተሸጋገረ እና በአመልካች በዘረጋው ፖል ገመድ ላይ ቃጠሎው ጉዳት አድርሶ የተበጠሰ ስለመሆኑ በተመሳሳይ የቃጠሎ አደጋ ይሕ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 175139 ውሳኔ በሠጠበትና በተያዘው መዝገብ የተረጋገጠ ነው። ይህም ጉዳት ያደረሠው አመልካች የዘረጋው የኤሌክትሪክ መሥመር አለመሆኑን ያሳያል።

አመልካች ራሱ ለዘረጋው የኤሌክትሪክ መሥመር ኃላፊነት ይወስዳል እንጂ ግለሠቦች በቤታቸው ለዘረጉትና ባለቤት ላልሆነበት የኤሌክትሪክ መሥመር አጥፊ ሳይሆኑ ኃላፊ ስለመሆን በተደነገገው የውል ውጭ ኃላፊነት የፍትሐ ብሔር ሕግ ክፍል (ከፍ/ሕ/ቁ. 2066 - 2086) ስር ኃላፊ ሊሆን አይችልም። የፍ/ሕ/ቁ. 2069(1) ኃላፊነትን በግልጽ ያቋቋመው የኤሌክትሪክ መሥመሩን የዘረጋው ሠው ላይ ነው። ይህም አጥፊ ሳይሆኑ ኃላፊ ስለመሆን ከውል ውጭ የፍትሐ ብሔር ኃላፊነት የሚከተለው የኤሌክትሪክ መሥመሩን ባለቤት እንጂ የኤሌክትሪክ ሀይሉን ባለቤት አለመሆኑን ያሳያል። የኤሌክትሪክ ሀይሉ ባለቤት ኃላፊነት ሊኖርበት የሚችለው ማድረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ካላደረገና ጥፋት ከፈጸመ ብቻ ነው።

አመልካች በዘረጋው ከቆጣሪው በመለስ ባለው መስመር ላይም ላደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የሚኖርበት ቆጣሪ ለሠጠው ደምበኛ ላይ ለደረሠ ጉዳት ነው። ተጠሪ የአመልካች ደምበኛ እና ፈቃድ ወስደው የኤሌክትሪክ መሥመር ያስገቡ አይደሉም። ከአመልካች ፈቃድ ውጭ ተጠሪ እና ወ/ሮ አካዛ ተስፋይ በራሳቸው በዘረጉት የኤሌክትርክ መሥመር ምክንያት ለደረሠ ጉዳት አመልካች ኃላፊነት የለበትም። ስለሆነም አመልካች ለጉዳቱ ከውል ውጭ የፍትሐ ብሔር ኃላፊነት ሳይኖርበት ኃላፊ እንዲሆን የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል።

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ/መ/ቁ. 175142

ውሳኔ

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 110766 ጥር 10 ቀን 2011 ዓ/ም እና የምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሑመራ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 15158 መስከረም 22 ቀን 2011 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች ለጉዳት ካሣው ኃላፊነት የለበትም ተብሎ ተወስኗል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ አመልካች የራሱን እንዲችል ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰ/መ/ቁ. 175838

መጋቢት 29 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች- አቶ ሾሻይ አበበ

ተጠሪ- ወ/ሮ አፀደ ገ/ተንሳይ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ክርክሩ የጀመረው በትግራይ ክልል ማእከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ እኔና ባለቤቴ በትዳር በጋራ ያፈራነውና በአክሱም ከተማ ንግስተ ሳባ ቀበሌ የሚገኘውን 175 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያረፈ ባለ ስምንት ክፍል ቤት እኔ ከሌሎች አምስት ሰዎች ጋር በነበረኝ የአፈፃፀም ክርክር በሀራጅ ሊሸጥ ሲል ከነልጆቼ ጎዳና ላይ እንዳልወጣ በሚል የአፈፃፀም ካሰሾቼ ከተወሰነላቸው ገንዘብ ውስጥ ብር 100,000.00 ሊተውልኝ፣ ተከሳሽ ደግሞ ብር 122,000.00 ልትከፍልልኝና እኔ የቤቱን ስመ ንብረት በስሟ ለማዞር ተስማምቼ ስመ ንብረቱ ወደ እሷ ዞሮ የአፈፃፀሙን ጉዳይ ያየው ፍርድ ቤት ስምምነቱን አፅድቆታል፡፡ ይሁን እንጂ አሁን ላይ ተከሳሽ የከፈለችልኝን ገንዘብ መልሼ ሰጥቻት ቤቱን እንድትመልስልኝ ብጠይቃት ፍቃደኛ አልሆነችም፡፡ ስለዚህ ገንዘቡን ተቀብላ ቤቱን እንድትመልስ ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ተጠሪ በበኩሏ በሰጠችው መልስ ከሳሽ በማዕካዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 21917 በነበረበት የአፈፃፀም ክርክር ያለበትን እዳ ብር 122,000.00 ልከፍልለት፣ ከሳሽ ደግሞ ከባለቤቱ ጋር በመሆን ወደው እና ፈቅደው የቤቱን ስመ ንብረት በስሜ ሊያዞሩ ተስማምተን ፍርድ ቤቱም ስምምነቱ ለህግና ለሞራል የማይቀረን መሆኑን አረጋግጦ በቀን 08/05/2009 ዓ.ም ካፀደቀ በኋላ በሰጠዉ ትዕዛዝ መሠረት የቤቱ ስመ ንብረትም በስሜ ዞሯል፡፡ በመሆኑም ስምምነቱ በፍርድ ቤት ፀድቆ የውሳኔ አካል ሆኖ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ በድጋሚ የቀረበ ክስ ነዉ በማለት ተከራክራለች፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር ከሰማ በኋላ ለክሱ መነሻ የሆነውን ቤትና ቦታ ከሳሽ ወደ ተከሳሽ ስም

ሊያዞር ተከሳሽ ደግሞ የአመልካችን እዳ እንድትከፍል እንደተስማሙ፣ይህም ስምምነት በፍርድ ቤቱ ፀድቆ የውሳኔ አካል ሆኖ ከመዝገቡ ጋር ከተያያዘ በኋላ በዚሁ መነሻነት ስመ ንብረቱ ወደ ተከሳሽ እንዲዞር በተሰጠ ትዕዛዝ መሠረት ስመሀብቱ ወደ ተጠሪ ዞሯል፡፡ አንድ ስምምነት በፍርድ ቤት ከፀደቀ እንደ ውሳኔ የሚቆጠር በመሆኑ በዛው ጉዳይ ዳግመኛ ሌላ ክስ ሊቀርብበት አይገባም በማለት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 5(1) መሠረት የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበዉ ይግባኝም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 337 መሰረት ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች በቀን 11/08/2011 ዓ.ም በተፃፈ 03 ገፅ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ተፈፅመዋል ያላቸውን ስህተቶች ዘርዝሮ ያቀረበ ሲሆን፣ ይዘቱም በአጭሩ ተጠሪ ቤቱን እንድትመልስ ስትጠየቅ በሽያጭ ተላልፎልኛል ትበል እንጂ ሽያጭን የሚመለከት፣ እንዲሁም ቤቱ በስሟ የሚዞርበት ምክንያት በግልፅ ያልተጠቀሰ ሲሆን በደፈናው በስሟ ይዙር የሚል ነው፡፡ ስምምነቱ በፍርድ ቤት መፅደቁ እንዲፈርስ የሚቀርብ ጥያቄን የሚያስቀር አይደለም፡፡ በስር ፍርድ ቤት በእኔና በተጠሪ መካከል በየትኛውም ደረጃ ክርክር ያልነበረ ሲሆን ተጠሪ ወደ ክርክሩ የገባቸው የባለቤቱ እህት ስለሆነች እዳውን ለፍርድ ባለመብቶቹ ለመክፈል ሲባል ነው፡፡ ምንም እንኳን በስምምነት ሰነዱ ላይ ባይጠቀስም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው ስምምነት ተጠሪ ለከፈለችልኝ እዳ ቤቱን መያዣ እንድታደርገው ነው፡፡ ይህንንም በምስክሮች ማረጋገጥ ሲቻል የስር ፍ/ቤት መቃወሚያውን ተቀብሎ ክሱን ውድቅ ማድረጉ ተገቢነት ስለሌለው ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤቶች ግራ ቀኙ አፈፃፀምን በሚመለከት ያደረጉትን ስምምነት መሠረት በማድረግ ጉዳዩ ከዚህ በፊት በፍርድ ያለቀ ነው በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረጉበትን አግባብ ለማጣራት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቧል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪ መልስ እንድትሰጥበት ተደርጎ በጠበቃዋ አማካኝነት በቀን 30/01/2012 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በስር ፍርድ ቤት ካቀረበችው መከራከሪያ በተጨማሪ የቤቱ ስመ-ንብረት ወደ እኔ እንዲዞር የተስማማሁት ገንዘብ እንድታበድረን በመያዣነት እንድትይዘው ነው ቢልም ስምምነቱ ብድር ወይም መያዣ ስለመሆኑ አይገልጽም፡፡ አመልካች ስምምነቱ ህጋዊ አይደለም ብሎ ከመከራከር ባለፈ ስምምነቱ ምን እንደጎደለው በግልፅ አላመላከተም፡፡ የቤቱ ስመ ንብረት በስሜ ለማዘዋወር አመልካች ያለበትን የአባይ ባንክ እዳ ብር 356,313.16፣ የሊዝ ክፍያ ብር 50,000.00 እንዲሁም ለሳይት ፕላን ማውጫ ብር 23,720.27 ከፍያለሁ፡፡ ስለሆነም በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይን ሊፀና ይገባዋል በማለት ተከራክራለች፡፡ አመልካችም ባቀረበው የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታውን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ከተያዘው ጭብጥና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለዉ፣ በሌላ መዝገብ የፍርድ ባለመብት የሆኑት እነ ንጉስ ወንድም (5-ሰዎች) በአመልካች ላይ የአፈፃፀም ክስ ካቀረቡ በኋላ ከአመልካች ከሚፈልጉት ዕዳ ዉስጥ ብር 100,000.00 ትተዉለት

ቀሪዉን ዕዳ ብር 122,000.00 ደግሞ ተጠሪ ከፍላ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የአመልካች ቤት ስመ ሀብቱ በስሟ እንዲሆን የተደረገዉ ስምምነት ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ መጽደቁና በዚህም መሠረት ተጠሪ ገንዘቡን ለአፈፃፀም ከሳሾች ከፍላ የቤቱም ስመ-ሀብት ወደ ተጠሪ ስም መዛወሩ አላከራከረም፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክስ ለጠየቀዉ ዳኝነት መሠረት ያደረገዉ ገንዘቡን ከፍሎ ቤቱን ለመረከብ ሲጠይቃት ተጠሪ ፍቃደኛ ባለመሆኗ ስምምነቱ ተሰርዞ የቤቱ ስመ-ሀብት በስሙ እንዲሆን እንዲወሰንለት ሲሆን፣ ከላይ እንደተመለከተዉ የስር ፍርድ ቤት ክሱን ዉድቅ ያደረገዉ በፍርድ ቤት የጸደቀዉ ስምምነት እንደዉሳኔ ስለሚቆጠር ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነዉ በማለት ነዉ፡፡ በርግጥ አንድ ክርክር በመሰማት ላይ እያለ ተከራካሪዎቹ ጉዳያቸዉን በእርቅ ከጨረሱ እና ጉዳዩን በማየት ላይ የሚገኝ ፍርድ ቤትም እርቁን ተቀብሎ ያጸደቀ እንደሆነ የፍርድ ያህል ዉጤት እንደሚኖረዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 277 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ ይህ በመሆኑም በጉዳይ ላይ በድጋሚ የሚቀርብ ክስ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 5(1) እና 244(2)(ሐ) መሠረት ተቀባይነት አይኖረዉም፡፡ ይህ ድንጋጌ የስረ ነገር ክርክሮች ሊቋረጡ ከሚችሉባቸዉ መንገዶች አንዱ መሆኑንም መገንዘቡ ተገቢ ነዉ፡፡

በሌላ በኩል፣ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ በተያዘዉ ጉዳይ ለክርክሩ ምክንያት ለሆነዉ ስምምነት መሠረቱ በአመልካች እና በሌሎች ሰዎች መካከል የነበረ የአፈፃፀም ክርክር ሲሆን፣ ተጠሪ የቤቱን ስመ-ሀብት በስማቸዉ ለማድረግ ምክንያት የሆነዉን ብር 122,000.00 የከፈሉትም አመልካች ገንዘቡን ለአፈፃጸም ከሳሾች እንዲከፍል በሚል ምክንያት ስለመሆኑ ከስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሠረቱ የፍርድ አፈፃፀም ፍርድ ቤቶች ወይም ሌላ የዳኝነት ስልጣን በህግ የተሰጣቸዉ አካላት የሚሰጧቸዉ ዉሳኔዎች ወደ ተግባር እንዲለወጡ የሚደረግበበት ሥርዓት ሲሆን፣ ሂደቱ የሚመራዉ እራሱን በቻለ ሥነ-ሥርዓት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 371 እና ተከታዮቹ ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ የፍርድ አፈፃፀም ሂደት የፍርድ ባለዕዳ በተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረት ለፍርድ ባለመብት መፈጸም የሚገባዉን ነገር የፈጸመ መሆን ያለመሆኑ በቅድሚያ ተጣርቶ እንደ ዉሳኔዉ ያልተፈጸመ መሆኑ ከተረጋገጠ አፈፃፀሙን የያዘዉ ፍርድ ቤት በዉሳኔዉ መሠረት እንዲፈጸም የሚያስችሉ የተለያዩ እርምጃዎችን በመዉሰድ በመጨረሻም እንደዉሳኔዉ መፈጸሙን አረጋግጦ መዝገቡን ዘግቶ ግራ ቀኙን የማሰናበት ኃላፊነት ያለበት ሲሆን፣ ከዚህ ዉጪ በተከራካሪ ወገኖች ወይም በሌላ ሦስተኛ ወገን ላይ አዲስ መብትና ግዴታን ሊፈጥር የሚችል ዉሳኔ መስጠት እንደማይችል በተለይም በህጉ ከአንቀጽ 378 ጀምሮ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻል ነዉ፡፡ ስለሆነም አመልካች የአፈፃፀም ተከሳሽ የሆነበት የአፈፃፀም መዝገብ በሂደት ላይ እያለ በተደረገ ስምምነት ወይም ድርድር ከአመልካች የሚፈለግ ገንዘብ ለፍርድ ባለመብቶች የተከፈለ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ገንዘቡ መከፈሉንና በዚህም እንደ ዉሳኔዉ መፈጸሙን ያረጋገጠ እንደሆነ የአፈፃፀም መዝገቡን ዘግቶ ማሰናበት ሲገባዉ፣ ከዚህ በላይ ሄዶ ለገንዘቡ መከፈል ምክንያት የሆነዉን ስምምነት ተቀብሎ ያጸደቀዉ ሥነ ሥርዓታዊ ባለመሆኑ አንድን በሂደት ላይ ያለ የስረ ነገር ክርክርን ለማቋረጥ ምክንያት በሆነዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 277 ላይ በተመለከተዉ አግባብ ዉሳኔ ነዉ ሊባል የሚችል አይደለም፡፡

በመሆኑም በአፈፃፀም ክርክር ሂደት በፍርድ ቤት ፀደቀ የተባለዉ እና ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነዉ ስምምነት የፍርድ ወይም የውሳኔ ውጤት የሌለዉ በመሆኑ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 5(1) ተጠቅሶ መቃወሚያ ሊቀርብበት የሚገባ ባለመሆኑ ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው በማለት የስር የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የትግራይ ክልል ማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20766 በቀን 04/04/2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ እንዲሁም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 113618 በቀን 13/06/2011 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. የትግራይ ክልል ማእከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን በፍሬ ነገር ላይ ካከራከረ በኋላ የመሰለዉን እንዲወስን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 341 መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡

3. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/አ

የሰ.መ.ቁ.177968

መስከረም 28 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካቾች፡-1. የናዝሬትና አርሲ ሳሙና ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ┐ ነ/ፈጅ ባህር

2. ናዝራዊ ቅባ-ኑግ ኃዋየተ/የግ/ማህበር ┘ ጠይቦ ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ሚሊዮን መኮንን ┐

2.አቶ ዮሐንስ ዓለሙ

3. አቶ ፀጋዬ ዓለሙ

4. አቶ ተፈሪ ዓለሙ ጠበቃ ሀብታሙ አበበ ቀርበዋል፡፡

5. አቶ ዳንኤል ዓለሙ

6. ወ/ሪት ሔለን ዓለሙ

7. አቶ ቅዱስ ዓለሙ

8. አቶ ሚኪያስ ዓለሙ ┘

9. ወ/ሮ የሺ አለማየሁ - የቀረበ የለም

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የማህበር አበልነት ክርክር የተጀመረዉ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካቾች የሥር ተከሳሾች፣ የአሁን ተጠሪዎች የሥር ከሳሾች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካቾች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.169919 በ12/07/2011 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካቾች በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ እነዚህ ሁለቱ የተከሳሾች ፋብሪካዎች/ማህበራት በሁለት ግለሰቦች አቶ መኮንን አባተ እና አቶ አለሙ ገብሩ የተመሰረቱ ሲሆን፣ ከዚህ ቀደም አቶ መኮንን አባተ በመሞታቸዉ ወራሾቻቸዉ 16 ሰዎች ወራሽነታቸዉን አረጋግጠዉ በፋብሪካዎቹ የመተዳደሪያ ደንብ መሰረት በአባልነት የተመዘገቡ ሲሆን፣ ቀጥሎ አቶ አለሙ ገብሩ በመሞታቸዉ 1ኛ ከሳሽ ወ/ሮ የሺ አለማየሁ ሚስትነቴን እና ከ2ኛ-9ኛ ያሉት ከሳሾች የሚች አባታችን አቶ አለሙ ገብሩ ወራሾች መሆናችንን በወረዳዉ ፍ/ቤት አረጋግጠን፣ ሚች በእነዚህ ፋብሪካዎች [ማህበራት] የነበራቸዉን የአክስዮን ድርሻ በስምምነት ተከፋፍለን በእያንዳንዳችን የአክስዮን ድርሻ መሰረት በአባልነት እንዲንመዘገብ ብንጠይቅም በጋራ አንድ ሰዉ

ካልወከላችሁ በስተቀር ለየግላችሁ ሊትመዘገቡ አትችሉም በማለት ሊመዘግበን ስላልቻሉ፣ በንግድ ሕጉ እና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት እያንዳንዳችን የአክስዮን ድርሻ መሰረት በአባልነት እንዲንመዘገብ እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቋል። ይህን ክርክራቸዉን ለማስረዳት ማስረጃ አያይዘዉ ማቅረባቸዉን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል።

የሥር ተከሳሾች በዚህ ክስ ላይ ባቀረቡት መልስ የከሳሾች የዳኝነት ጥያቄ ሲታይ በንግድ ሕግ አንቀጽ 328 እና በማህበራቱ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 4 [2] መሰረት ከሳሾች አንድ ሰዉ በመወከል የተከሳሾች ማህበራት አባል መሆን ይችላሉ እንጂ እያንዳንዳቸዉ አባል ሊሆኑ አይችሉም፤ አሁን በሥራ ላይ ያለዉ የመተዳደሪያ ደንብ ሆነ የንግድ ሕግ አንቀጽ 524 ድንጋጌ የከሳሾችን ክርክር የሚደግፍ አይደለም፤ የአቶ መኮንን አባተ ወራሾች በመጀመሪያ መተዳደሪያ ደንብ በእያንዳንዳቸዉ አክስዮን ድርሻ አባል እንደሆኑ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለዉም፤ ከሳሾች የዉርስ ንብረት ክፍፍል አድርገን ቃለ ጉባኤ በፍ/ቤት ዉሳኔ ተሰጥቶበታል ይባሉ እንጂ ዉሳኔዉ ተሽሯል። ስለሆነም ከሳሾች ያቀረቡት ክስ የሕግ ድጋፍ ስለሌለዉ ዉድቅ እንዲደረግልን በማለት መከራከራቸዉን የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል። ይህን ክርክራቸዉን ለማስረዳት የሰነድ ማስረጃዎችን አያይዘዉ መቅረባቸዉን መዝገቡ ያሳያል።

ከዚህ በኋላ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በማከራከርና የቀረበዉን የሰነድ ማስረጃዎች በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ እኒዚህ የተከሳሾች ፋበሪካዎች በመንግስት ተወርሶ በመንግስት እጅ ቆይቶ በ2000 ዓ.ም አቶ መኮንን አባተ እና አቶ ዓለሙ ገብሩ ተገቢዉን ክፍያ ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ከፍለዉ ያስመለሱ ሲሆን፣ አቶ መኮንን አባተ ሲሞቱ ወራሾች 16 ሰዎች በአቶ ዓለሙ ገብሩ ፍላጎት በበፊቱ የመተዳደሪያ ደንብ መሰረት በማህበር በአባልነት የተመዘገቡ ስለሆነ በዚህ ረገድ ከሳሾች ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለዉም። እነዚህ ማህበራት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበራት ስለሆኑ ካላቸዉ ልዩ ባህርይ የተነሳ በጋራ ቤተሰብ በሆኑት እና ግንኙነትና ትልቅ አመኔታ ባላቸዉ ሰዎች መካከል የሚመሰረት ስለሆነ፣ የእነዚህ ማህበራት አባል ለመሆን በማህበሩ አባላት እና በመተዳደሪያ ደንቡ በስምምነት እንጂ በሕግ እና በሌላ አካል ዉሳኔ መሆን የለበትም፤ ከሳሾች የሚች አባታቸዉን የአክስዮን ድርሻ በመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 3.1 እና 4.4 መሰረት ለመዉረስ የወራሽነት መብት ያላቸዉ ቢሆንም ይህን መብታቸዉን እንዴት እንደሚጠቀሙ በተመለከተ የማይከፋፈልና የጋራቸዉ ስለሆነ ወራሾች ከ2ኛ-9ኛ ከሳሾች ድርሻ እያንዳንዳቸዉ ተለይቶ የተወሰነ ቢሆንም እነዚህ ማህበራት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበራት በመሆናቸዉና ካላቸዉ ጸባይና አመሰራረት የተነሳ ከሳሾች ወራሾች ስለሆኑ ብቻ በአባልነት የመመዘገብ መብት የሌላቸዉ ስለሆነ በወራሽነት መብት ሊይዙት የሚገባቸዉ አክስዮን ድርሻ መሰረት አንድ ሰዉን ብቻ በመወከል የሚጠበቅባቸዉን የሚያስረዳ ስለሆነ በየግላቸዉ እንመዝገብ በማለት ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለዉም፤ 1ኛ ከሳሽ ወ/ሮ የሺ አለማየሁ ሚች ሚስት ስለሆኑ በሚስትነት ድርሻቸዉ ለመጠቀም ሌላ ሰዉ በመወከል ለመጠቀም የሚያስገድድ ነገር የለም ከሳሽዋ የአክስዮን ክፍፍል ድርሻ በኋላ አጣርታ ተላይቶ የሚታወቅ በሁለቱም ማህበራት በቀጥታ ለመሳተፍ መብቷን ማስከበር ትችላለች በማለት ወስኗል።

የሥር ከሳሾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ከሳሾች ሚች አቶ

ዓለሙ ገብሩ በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.996 መሰረት ሚስት 50% እና ወራሾች 50% እንደሚገባቸዉ በፍ/ቤት በተሰጠ ዉሳኔ አረጋግጠዋል፤ ይህ ዉሳኔ አልተሻረም። ከሳሾች በእነዚህ ማህበራት የሚደርሳቸዉ የአክስዮን ድርሻ የሚስትነት ድርሻ እና ወራሽነት ድርሻቸዉን በስምምነት ተከፋፍለዉ በፍ/ቤት ያጸደቁበት ዉሳኔ የተሻራ መሆኑን የቀረበ ማስረጃ የለም። የማህበራቱ የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 4.4 ወራሾችን የሚመለከት ሳይሆን መጀመሪያዉኑ አባል የሆነ ሰዉ የጋራ ባለአክስዮን ያላቸዉን ነዉ፤ ወራሾችን የሚመለከተዉ የማህበራቱ አንቀጽ 3.1 የወራሽነት ማስረጃ ይዞ የቀረበ ወራሽ ካለምንም ቅደመ ሁኔታ የማህበሩ አባል እንደሚሆን የሚያረጋግጥ ነዉ። የሥር ከሳሾች የአባታቸዉን የአክስዮን ድርሻ በስምምነት በመከፋፈል እና እያንዳንዳቸዉ በሚደርሳቸዉ የአክስዮን ድርሻ አባል ከመሆን የሚከለክላቸዉ ሕግ በሌለበት፣ የማህበራቱ የመተዳደሪያ ደንብ በእነዚህ ነጥቦች ላይ በአጠቃቀሙ መሰረት ያስቀመጡት ነገር በሌለበት እና የንግድ ሕጉ አንቀጽ 328 በዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት የሌለዉ ሆኖ ሳለ፣ የሥር ፍ/ቤት ከሳሾች የማህበራቱ አባል መሆን አይችሉም፣ አንድ ሰዉ በመወከል ሊጠቀሙ ይቻላሉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ስህተት ነዉ፤ የሥር 1ኛ ከሳሽ ወ/ሮ የሺ አለማየሁ የሚች ሚስት በመሆንዋ ከባለቤቷ ጋር የነበራትን ግማሽ ድርሻ የማትጠቀምበት አግባብ የለም፣ ስለሆነም ሚች በ1ኛ ተከሳሽ ማህበር የነበረዉ የአክስዮን ድርሻ 9,136 ስለሆነ የሥር 1ኛ ከሳሽ የሚስትነት ድርሻዋን 4,568፣ ወራሾች ከ2ኛ-9ኛ ከሳሾች እያንዳንዳቸዉ 571፣ በሥር 2ኛ ተከሳሽ ማህበር ሚች የነበረዉ የአክስዮን ድርሻ 2,900 ሲሆን የሥር 1ኛ ከሳሽ የሚስትነት ድርሻዋ 1,450 ሲሆን፣ 7ቱ ወራሾች ደግሞ እያንዳንዳቸዉ 181 አክስዮኖች፣ አቶ ዳንኤል አለሙ 183 አክስዮኖች ድርሻ ስለሚደርሳቸዉ በዚህ መሰረት በሥር ተከሳሾች ፋብሪካዎች [ማህበራት] አባል እንዲሆኑ በማለት ወስኗል። ይህ ጉዳይ በይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን በትዕዛዝ በመሰረዝ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔና ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ።

የአሁን አመልካች በ22/9/2011 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ አመልካቾች የአሁን ተጠሪዎች የአባታቸዉ ወራሾች ሲሆኑ አዉራሻቸዉ የነበራቸዉን አክስዮችን ሲወርሱ የማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 4 [ሀ፣ ለ፣ ሐ] በሚያዘዉ መሰረት አንድ እንደራሴ በመሾም መሆን እንዳለበት ተመልክቶ እያለ የሥር ፍ/ቤት እንደራሴ መሾም ያለባቸዉ ወራሾች ሳይሆኑ ሌሎች በጋራ የአክስዮን ድርሻ የሚይዙትን እንደሆነ በመተርጎም የሰጠዉ ዉሳኔ የመተዳደሪያ ደንቡን እና የንግድ ሕጉን አንቀጽ 328 [1፣ 2] እና 524 [1] ድንጋጌ ጋር የሚጋጭ ነዉ፤ የሥር ፍ/ቤት እነዚህ የፋብሪካዎቹ የመተዳደሪያ ደንቦች ድንጋጌዎች ወራሽ በመሆኑ ሰዎች ላይ ተፈጻሚነት እንደሌላቸዉ አድርጎ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ። የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤ የሰጠዉ ትርጉም የመተዳደሪያ ደንቡ ለተለዩ ሰዎች የተደነገገ ሳይሆን አንድን አክስዮን በጋራ ለሚይዙ ባለአክስዮኖች በምን ሁኔታ ሊሰሩ እና መብታቸዉን ሊጠቀሙ እንደሚገባ የሚያዛቸዉ ሆኖ ሳለ ፍ/ቤቱ የሰጠዉ ዉሳኔ ግን የመተዳደሪያ ደንቡን እና የንግድ ሕጉን ድንጋጌዎች የጣሰ ስለሆነ እንዲሻርልን፣ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲጸናልን በዚህ ምክንያት የደረሰብን ኪሳራ እንዲከፍሉን በማለት በዝርዝር አመልክቷል።

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣ተጠሪዎች ባላቸዉ የአክስዮኖች ድርሻቸዉ መሰረት አመልካቾች በየራሳቸዉ ይመዝግቡአቸዉ የተባለበትን አግባብ ከንግድ ሕጉ አንቀጽ 328 እና ከመተዳደሪያ ደንብ አኳያ መጣራት ያለበት ጉዳይ ነዉ፣ በማለት የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት በ10/2/2012 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ የአሁን 9ኛ ተጠሪ የሚች ሚስት እና የተጠሪዎች አባት በአመልካቾች ፋብሪካዎች ያላቸዉን የአክስዮኖችን ድርሻ ወራሾች ስለሆኑ 9ኛ ተጠሪ በሚስትነት ድርሻዋ እና ሌሎች ከ1ኛ-8ኛ ተጠሪዎች በወራሽነት ድርሻቸዉ በሚደርሻቸዉ የአክስዮኖች ድርሻ በአባልነት እንዲንመዘገብ የሥር የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ምንም ዓይነት የህግ ስህተት የሌለበት ስለሆነ እንዲጸናልን ወጪና ኪሳራ ከጠበቃ አበል ጋር እንዲወሰንልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል። የአሁን አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክርና ለቅሬታዉ ምክንያት የሆኑትን ዉሳኔዎች አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ የአሁን 9ኛ ተጠሪ ባለቤት እና የአሁን 1ኛ-8ኛ ተጠሪዎች አባት የሆኑት አቶ አለሙ ገብሩ የሆኑት የአመልካቾች ማህበራት [ፋብሪካዎች] አባል መሆናቸዉ እና የአክስዮኖች ድርሻ እንዳላቸዉ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም። እነዚህ ማህበራት ኃላፊነታቸዉ የተወሰኑ የግል ማህበራት መሆናቸዉም የልተካደ ጉዳይ ነዉ። አቶ አለሙ ገብሩ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸዉ የአሁን 9ኛ ተጠሪ ሚስትነታቸዉን እና ከ1ኛ-8ኛ ተጠሪዎች የሚች ልጆች እና ወራሾች መሆናቸዉን በፍ/ቤት ያረጋገጡ መሆናቸዉን ከሥር ፍ/ቤቶች የዉሳኔዎች ግልባጭ የሚንገነዘበዉ ነዉ። የአሁን አመልካቾችም በዚህ ረገድ ክርክር እንደሌላቸዉ መገንዘብ ይቻላል። ከዚህም በላይ የአሁን አመልካቾች እና ተጠሪዎች ያላከራከራቸዉ ሌላዉ ጉዳይ አቶ አለሙ ገብሩ በሕይወት በነበሩ ጊዜ በአመልካቾች ማህበራት ዉስጥ የነበራቸዉ አክስዮኖች ለተጠሪዎች መተላለፍ እንደሚገባ፣ 9ኛ ተጠሪ የሚስትነት ድርሻ እና ከ1ኛ-8ኛ ተጠሪዎች ደግሞ የወራሽነት ድርሻ እንደሚገባቸዉ እና መብት እንዳላቸዉ አሁንም ያላከራከረ ጉዳይ ነዉ። ነገር ግን ግራ ቀኙን ያከራከረዉ ጉዳይ ተጠሪዎች ይህን መብታቸዉን እንዴት መጠቀም እንደሚገባቸዉ በሚል ላይ ነዉ። በዚህ ረገድ የአሁን አመልካቾች እያቀረቡ ያሉት ክርክር ተጠሪዎች መብት ያገኙት ከአንድ የማህበራቱ አባል ከሆኑት ከአቶ አለሙ ገብሩ ስለሆነ በማህበራቱ የመተዳደሪያ ደንብ እና በንግድ ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት አክስዮኖቹን በጋራ በአንድነት አንድ ሰዉ እንደራሴ ወክለዉ በዉክልና ከሚይዙት በስተቀር እያንዳንዳቸዉ የማህበራቱ አባላት ሆኖ የሚመዘገቡበት አግባብ የለም የሚል ሲሆን፣ የአሁን ተጠሪዎች በበኩላቸዉ 9ኛ ተጠሪ በሚስነት ድርሻቸዉ እና ሌሎች ተጠሪዎች ደግሞ ባለን በወራሽነት ድርሻ የሚደርሳንን የአክስዮኖችን ድርሻ በእያንዳንዳችን ስም ተመዝግቦ በማህበራቱ በአባልነት ሊንመዘገብ ይገባል እንጂ በጋራ አንድ እንደራሴ ወክለን በዉክልና እንዲንጠቀምበት የሚያስገድደን የመተዳደሪያ ደንብ ድንጋጌም ሆነ የንግድ ሕግ ድንጋጌ የለም በማለት ተከራክሯል።

ከዚህ አንጻር የአመልካቾች ማህበራት ኃላፊነታቸዉ የተወሰኑ የግል ማህበራት እንደመሆናቸዉ መጠን መታየት ያለበት የንግድ ሕጉ አንቀጽ 510 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሆናቸዉ መገንዘብ ያስፈልጋል። በዚህ ሕግ አንቀጽ 510 ሥር

እንደተመለከተዉ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ትርጎም ጸባይ ምን እንደሆነ የተመለከተ ሲሆን፣ ይህ ማህበር የሚያስከትለዉ የኃላፊነት መጠን እና የአባላቱ ቁጥር ምን ያህል መሆን እንዳለበት እና የሚተላለፉ የንግድ ወረቀቶችን ማዉጣት እንደማይችል ተመልክቷል። እንዲሁም በሕጉ አንቀጽ 524 መሰረት ደግሞ በዚህ ማህበር ያለዉን የአክስዮን ድርሻ ለወራሽ በምን አግባብ እንደሚተላለፍ የሚደነግግ ነዉ። የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደሚያመለክተዉ በማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ በሌላ አግባብ ካልተመለከተ በቀር የአንድ ማህበርተኛ ወራሾች ለሚቹ አክስዮኖች በደንብ ወራሾች እንደሚሆኑ ይደነግጋል። እንግዲህ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በተመለከተ አንድ የማህበሩ አባል የሞተ እንደሆነ የሚቹ የአክስዮኖች ድርሻ በምን አግባብ ወደ ወራሾች እንደሚተላለፍ የማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ እና የዚህ ሕግ ድንጋጌ መሰረት የሚፈጸም መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ከዚህ አንጻር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ስለማህበራቱ የመተዳደሪያ ደንብ እንዳመለከተዉ አንቀጽ 4.4 የጋራ ባለአክስዮኖች መብታቸዉን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸዉ የሚያመለክት እና መብታቸዉን ለአንድ ሰዉ በመወከል መጠቀም እንደሚችሉ እንደሚደነግግ ነዉ። ሌላዉ የመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 3.1 ድንጋጌ ደግሞ የወራሽነት መብት ያለዉ መሆኑን የሚያረጋገጥ ማስረጃ ይዞ የቀረበ ወራሽ ካለምንም ቅድመ ሁኔታ የማህበራቱ አባል የሚሆንበትን የሚያረጋግጥ መሆኑን እንደሚያመለክት ገልጾዋል። ይህን የንግድ ሕጉን ድንጋጌ እና የመተዳደሪያ ደንቡን ድንጋጌ በጣምራ ሲታይ የማህበራቱ አባል በሞት የተለየ እንደሆነ በማህበራቱ የነበረዉ የአክስዮን ድርሻ ለወራሾች የዉርስ መብታቸዉን መሰረት በማድረግ እንደሚተላለፍ የሚደግፍ እንጂ ምንም ዓይነት ክልከላ የሌለዉ መሆኑን ነዉ። ይህ ከሆነ ደግሞ ሟች አቶ አለሙ ገብሩ በአመልካቾች ማህበራት የነበራቸዉ የአክስዮኖች ድርሻ ለአሁን 9ኛ ተጠሪ እና ለሌሎች ተጠሪዎች በምን አግባብ ሊተላለፍና ሊጠቀሙበት እንደሚገባ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ።

ከዚህ አንጻር የአሁን አመልካቾች ባቀረቡት ክርክር ተጠሪዎች በማህበራቱ ዉስጥ መብት ያገኙባቸዉን አክስዮኖችን በምን አግባብ እንደሚጠቀሙበት የማህበራቱ የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 4.4 እና የንግድ ሕጉ አንቀጽ 328 ድንጋጌ መሰረት ሲታይ አንድ ሰዉ በመወከል ሊጠቀሙ ይገባል እንጂ እያንዳንዳቸዉ የማህበራቱ አባላት መሆን አይችሉም ሲሉ፤ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ በማህበራቱ ዉስጥ ባገኘነዉ የአክስዮኖች ድርሻ መሰረት እያንዳንዳችን አባላት ሆነን ለመመዝገብ የሚከለክለን ነገር ስለሌለ በአባልነት ሊንመዘገብ ይገባል የሚለዉ ነዉ።

ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ ኃለፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሁለት ዓይነት ባህርያት ያሉት ሲሆን አንዱ በአባላቱ መካከል ካለዉ ግንኙት አንጻር የሽርክና ማህበር ባህርይ እና ከሚያስከትለዉ ኃላፊነት አንጻር የኩባንያ ባህርይ ያለዉ መሆናቸዉ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል። ስለሆነም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የሚመለከቱት የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች የማይሸፍናቸዉ ጉዳዮች ካሉ እንደየአግባብነታቸዉ መታየትና ተፈጻሚ መደረግ የሚገባቸዉ የሽርክና ማህበር እና ኩባንያን የሚመለከቱት የንግድ ሕጉን ድንጋጌዎች መሆናቸዉን መገንዘብ አስፈላጊ ነዉ።

በዚህ መሰረት የአሁን የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ የማህበራቱ የመተዳደሪያ ደንብ እና የንግድ ሕጉ አንቀጽ 328 ድንጋጌ ማየቱ ተገቢ ነዉ። ይህ የመተዳደሪያ ደንቡም ሆነ የንግድ ሕጉ ድንጋጌ ይዘትና ዓላማ እንደሚያመለክተዉ የጋራ ባለአክስዮኖችን

የሚመለከቱ ናቸዉ። የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 4.4 መሰረት የጋራ ባለአክስዮኖች ያላቸዉን መብታቸዉን ለአንድ ሰዉ በመወከል መጠቀም ከሚችሉ በስተቀር እያንዳንዳቸዉ የማህበሩ አባላት ሆኖ መመዝገብ እንደማይችሉ የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያመለክታል። የንግድ ሕጉ አንቀጽ 328 [1] ድንጋጌ መሰረት አክስዮኖቹ የማይከፋፈሉ መሆናቸዉን የሚያመለክት ሲሆን፣ ንዑስ አንቀጽ 2 ደግሞ ብዙዎች ሰዎች የአክስዮኖች የጋራ ባለሀብት የሆኑ እንደሆነ የማህበርተኛነትን መብት ሊሰራባቸዉ እንዲችል ለሁሉም እንደራሴ የሚሆን መሾም አለባቸዉ በማለት ይደነግጋል። ከዚህ ድንጋጌ ይዘትና ዓላማ መረዳት እንደሚቻለዉ ብዙ ሰዎች ብዙ አክስዮኖችንም ቢሆን ለእያንዳንዳቸዉ አንድ አንድ አክስዮን የማይደርሳቸዉ እንደሆነ ወይም አንድ አክስዮን በጋራ የያዙ እንደሆነ፣ እነዚህን አክስዮኖች ወይም አንዱን አክስዮን ለእያንዳንዱ የጋራ ባለአክስዮኖች ማከፋፈል የማይቻል ስለሆነ በጋራ መያዝ ስለሚገደዱ፣ እነዚህ ሰዎች መብታቸዉን መጠቀም የሚገባቸዉ አንድ ሰዉ በመወከል ከሚሆን በስተቀር እያንዳንዳለቸዉ በአባልነት መመዝገብ እንደማይችሉ የሚያስገነዝብ ነዉ።

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ ሚች ከአመልካቾች ማህበራት የነበሩት የአክስዮኖች ድርሻ አንጻር የአሁን 1ኛ ተጠሪ በሚስነትነት መብታቸዉ የሚደርሳቸዉ የአክስዮኖች ድርሻ እና ከ1ኛ-8ኛ ተጠሪዎች ባላቸዉ የወራሽነት መብታቸዉ የሚደርሳቸዉ የአክስዮኖች ድርሻ ሲታይ አክስዮኖቹ ሊከፋፈሉ የማይችሉ እና ተጠሪዎች ሰዉ በመወከል በጋራ ለመያዝ የሚገደዱበት አግባብ ያለ መሆኑን የሚያሳይ ነገር የለም። ምክንያቱም ሚች አቶ አለሙ ገብሩ በአመልካቾች ማህበራት የነበራቸዉ አክስዮኖች ብዛት ሲታይ ተጠሪዎች ባላቸዉ መብት አክስዮኖቹ ለእያንዳንዳቸዉ ተከፋፍለዉ በስማቸዉ ተመዝግቦ እነርሱም በማህበራቱ በአባልነት ለመመዝገብ የሚከለክላቸዉ ምንም ነገር የለም።

ተጠሪዎች በእነዚህ አክስዮኖች ላይ ካላቸዉ መብት አንጻር ለእያንዳንዳቸዉ ተከፋፍለዉ ብይዙ ከፍ ሲል ከተጠቀሱት የማህበራቱ የመተዳደሪያ ደንብ እና የንግድ ሕግ ድንጋጌ የሚከለክላቸዉ አይሆንም። ሚች በእነዚህ ማህበራት የነበራዉ የአክስዮኖች ድርሻ ብዛት ለተጠሪዎች ባላቸዉ መብት ከመከፋፈል የሚከለክላቸዉ እና የጋራ ባለአክስዮኖች ሆኖ አንድ ሰዉ በመወከል መብታቸዉን እንዲጠቀሙበት የሚገደዱበት የህግ አግባብ የለም። ሚች አቶ አለሙ ገብሩ በአሁን 1ኛ አመልካች ማህበር 9,136 አክስዮኖች ድርሻ እንደነበራቸዉ እና በአሁን 2ኛ አመልካች ማህበር ደግሞ 2,900 አክስዮኖች ድርሻ እንደነበራቸዉ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ። በዚህ መሰረት የአሁን 9ኛ ተጠሪ ከእነዚህ አክስዮኖች የሚስትነት ድርሻቸዉ በአሁን 1ኛ አመልካች ሚች ከነበራቸዉ የአክስዮኖች ድርሻ ግማሹ የእሳቸዉ በመሆኑ 4,568 አክስዮኖች እንደሚደርሳቸዉ፣ በአሁን 2ኛ አመልካች ደግሞ ሚች ከነበራቸዉ የአክስዮኖች ድርሻ ግማሹ 1,450 እንደሚደርሳቸዉ፤ ከ1ኛ-8ኛ ተጠሪዎች የሚች ወራሾች በመሆናቸዉ በ1ኛ አመልካች ከሚደርሳቸዉ አክስዮኖች ለእያንዳንዳቸዉ 571 አክስዮኖች እንደሚደርሳቸዉ እና በ2ኛ አመልካች ደግሞ ለአሁን 5ኛ ተጠሪ ለአቶ ዳንኤል አለሙ 183 አክስዮኖች እና ለሌሎች ተጠሪዎች ደግሞ 181 አክስዮኖች እንደሚደርሳቸዉ የሥር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠዉ ጉዳይ ነዉ። ስለሆነም የአሁን ተጠሪዎች የአክስዮኖች ድርሻቸዉ በአመልካቾች ማህበራት በአባልነት ከመመዝገብ የመተዳደሪያ

ደንብ ድንጋጌም ሆነ የንግድ ሕጉ ድንጋጌ የሚከለክላቸዉ ሆኖ አልተገኘም። በንግድ ሕጉ አንቀጽ 534 [2] ሥር እንደተመለከተዉ እያንዳንዱ ማህበረተኛ በማህበሩ ዉስጥ ባሉት አክስዮኖች ልክ የድምጽ ብዛት እንዳለዉ ከደነገገዉ አንጻር ሲታይ ተጠሪዎች በየስማቸዉ በማህበራቱ በአባልነት የተመዘገቡ እንደሆነ፣ ድምጽ የሚሰጡት ባላቸዉ የአክስዮኖች ድርሻ መጠን ስለሆነ በአመልካቾች ላይ የሚያመጠዉ ችግር መኖሩን የተመለከተ ነገር የለም። እንዲሁም የማህበራቱ አባላት ብዛትም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 510 [2] ሥር ከተመለከተዉ ቁጥር በላይ እስካልሆነ ድረስ፣ በዚህ ረገድም ችግር ይፈጥራል ተብሎ አይገመትም። በመሆኑም ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 [3፣ ሀ] እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ከተሰጠዉ ስልጣን አንጻር አመልካቾች ያቀረቡት የሰበር ቅሬታም ሆነ አቤቱታ ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህን ዉሳኔ በማጽናት የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን የማያመልክት ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም ብለናል።ከዚህ አንጻር ይህ ችሎት በሰ.መ.ቁ.41526 [ቅጽ 9] ግንቦት 2 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ችሎቱ የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ለማየት ስልጣን እንደሌለዉ የወሰነዉን ማየት ይቻላል።

ሲጠቃለል የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች ባላቸዉ መብት መሰረት በአመልካቾች ማህበራት እያንዳንዳቸዉ በስማቸዉ በሚደርሳቸዉ የአክስዮኖች ድርሻ መጠን በአባልነት ተመዝግበዉ የመጠቀም መብት አላቸዉ በማለት የሰጡት ዉሳኔ በሕግ አግባብ የተሰጠ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ የሚከተለዉ ተወስኗል።

ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.169919 በ12/07/2011 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 [1] መሰረት ጸንቷል።
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ።
3. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሰ/መ/ቁ 178185

ሚያዚያ 26 ቀን 2012 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡-ጆር ኃ/የተ/የግ/ማህበር

ተጠሪ፡- ዓለም ብረታብረት ኃ/የተ/የግ/ማህበር

መዝገቡንመርምረንየሚከተለውንፍርድሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 218994 በቀን 25/03/2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 169918 በቀን 12/07/2011 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቀ ነው፡፡ ጉዳዩ የንግድ ምልክትን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ የአሁን ተጠሪ ባቀረበው አቤቱታ ነው፡፡

ተጠሪ ባቀረበው አቤቱታ፡- በአለም አቀፍ ምድብ 06 ለሚካተቱ ምርቶች መለያነት ለመጠቀም ፀሐይ የንግድ ምልክትን እንዳስመዘገበ፤ ነገር ግን የንግድ ምልክት እና ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት ዋና የስራ ሂደት ጨረር የሚል የቃል እና የምስል ንግድ ምልክት በጽ/ቤቱ ውስጥ በተከሳሽ ስም የመዘገበ በመሆኑ እንደተገለጸላቸው ጠቅሰው ይህ በተከሳሽ ስም የተመዘገበው የንግድ ምልክት ከእኛ የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ ፈራሽ ሊደረግ ይገባል፤ ምርታችን በገበያ ላይ ባለጨረሩ እየተባለ የሚጠራ በመሆኑና ጨረር ከሚለው ቃል ውጭ ያለው ምስል ስለሚመሳሰል እንዲሁም ምልክቱ ለተመሳሳይ ምርቶች በመሆኑ መሳከርን እየፈጠረ ስለሚገኝ ተከሳሽ ንግድ ምልክታቸው ላይ ማሻሻያ ሊ ያደርጉ ይገባል በማለት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

የአሁን አመልካች (ተከሳሽ) በበኩሉ በሰጠው መልስ የእኛ ንግድ ምልክት ከከሳሽ ንግድ ምልክት የተለየ ነው፤ ከቀዳሚ ንግድ ምልክት ጋር አንድ አይነት የሆነ ወይም መሳከርን ሊስከትል የሚችል ባለመሆኑ በጽ/ቤቱ ተመዝግቧል፤ ምልክቶቹ በያዙት ምስል፣ ቅርጽ እና ቃል የሚዛመድ ገጽታ የላቸውም፤ የእኛ ንግድ ምልክት ምስል ከእልፍ አዕላፍ ከዋክብት የሚመነጭ ጨረርን ሊወክል የሚችል እንጂ የፀሐይ ጨረር ነው ለማለት የሚያስችል እውነታ የለበትም፤ ህብረተሰቡንም ግራ የሚያጋባ አይደለም፤ ከሳሽ ምርታችን በህብረተሰቡ ዘንድ ባለጨረሩ እየተባለ ነው የሚጠራው ላሉት ባለጨረሩ

ብለው ያስመዘገቡት የንግድ ምልክት በሌለበትና ማስረጃ ባላቀረቡበት ሁኔታ መከራከሪያቸው አግባብነት የለውም ብሏል።

በቃል ክርክር ወቅት ደግሞ ከሳሽ የእኛ ክርክር በቃሉ ላይ ሳይሆን በምስሉ ነው። ህብረተሰቡ ምርቱን የሚገዛው ጨረሮችን አይቶ እንጂ ስሙን አውቆ አይደለም። መሳከርን በተመለከተ የአዋጁ አንቀጽ 26(2)(ሀ) እና (ለ) ይታይልን ሲሉ ተከሳሽ በበኩሉ የከሳሽ ምልክት ፀሐይን የሚወክል ሲሆን የተከሳሽ ምልክት ግን ጨረር በመሆኑ ምልክቶቹ መሳከርን አይፈጠሩም። ተጠሪ የፀሐይን ባህርያት በሞኖፖል አልያዘም በማለት ተከራክሯል።

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት ኮሚቴው በተከሳሽ ስም በማመልከቻ ቁጥር LTM/3547/08 ተመዝግቦ የሚገኘው የንግድ ምልክት ፈራሽ መሆን አለበት? ወይስ የለበትም? የሚል ጭብጥ በመያዝ በከሳሽ ስም ተመዝግቦ ከሚገኘው የማመልከቻ ቁጥር LTM/0919/2006 መዝገብ ጋር በማያያዝ ከመረመረ በኋላ የውሳኔ ሃሳብ አቅርቧል። ባቀረበው የውሳኔ ሃሳብ የአመልካችም ሆነ የተጠሪ የንግድ ምልክት በዕቃዎች ምድብ 06 ለቆርቆሮ ምርቶች ተብሎ የቀረበ ነው። ከሳሽ የእኛ ባለጨረሩ እየተባለ በተለምዶ ይጠራል በማለት የተከራከሩ ሲሆን ከንግድ ምልክቱ መዝገብ ላይ ማጣራት እንደተቻለው ከሳሽ ባለጨረሩ በሚል ያስመዘገቡት ምልክት የሌለ በመሆኑ እና ለይግባኝ ሰሚ ኮሚቴውም ይህን ክርክራቸውን የሚደግፍ ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ በዚህ ረገድ በከሳሽ የቀረበው መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም። የንግድ ምልክቶቹ ከተመዘገቡበት የቆርቆሮ ምርት ባህሪ አንጻር ማንኛውም ምክንያታዊ ሸማች ቆርቆሮ ሲገዛ በገበያ ላይ ያሉትን የቆርቆሮ ምርቶችን በተመለከተ መረጃ በደንብ ሳይሰበስብ አይገዛም። እንደ ዝቅተኛ የሸቀጥ እቃዎች ያምንም የገበያና የጥራት መረጃ ሊገዛ የማይቻል በመሆኑ ህብረተሰቡ በዚህ በኩል ሊገዛ ያሰበውን ሳይሆን የተሳሳተውን ይገዛል ተብሎ አይታሰብም። በመሆኑም በሁለቱ ንግድ ምልክቶች መካከል መመሳሰል አለ ቢባል እንኳን መመሳሰሉ ዝቅተኛ ሲሆን ሸማቹ ማህበረሰብም ምርቶቹን በሚገዛበት ጊዜ ጥናት አድርጎ እና መረጃን መሰረት አድርጎ በመሆኑ የንግድ ምልክቶቹ መሳከርን የሚፈጥሩ ባለመሆናቸው በከሳሽ በኩል የቀረበው የንግድ ምልክት ፈራሽነት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም። የንግድ ምልክት ጥበቃና ልማት ዋና የስራ ሂደት ጨረር የሚለውን የተከሳሽን የቃልና ምስል ንግድ ምልክት መመዝገቡ የሚነቀፍ አይደለም በማለት የውሳኔ ሃሳብ አቅርቧል። የአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ዋና ዳይሬክተርም በውሳኔ ሃሳቡ መሰረት እንዲፈፀም ወስነዋል።

የአሁን ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ በሰጠው ውሳኔ ከክርክሩና ከቀረበው ማስረጃ መገንዘብ እንደተቻለው የሁለቱም ተከራካሪዎች የንግድ ምልክት አገልግሎት ላይ የዋለው ለተመሳሳይ የቆርቆሮ ምርት ሲሆን የአሁን ተጠሪ የንግድ ምልክት አስቀድሞ የተመዘገበ መሆኑ አላከራከረም። የቀረበው ማስረጃም ይህን ያሳያል። የተጠሪ ንግድ ምልክት የፀሐይ ምልክት ከነጨረሩ ሲሆን በውስጡ ፀሐይ የሚል ቃል የተጻፈበት ነው። የአሁን አመልካች በበኩሉ የብርሃን ጨረር ያለው ምስል ሆኖ በውስጡ ጨረር የሚል ቃል የተፃፈበት መሆኑን የቀረበው የምስል ማስረጃ ያሳያል። አመልካች በኮሚቴው ባደረጉት ክርክርም የንግድ ምልክቱ በግልጽ ያልተለየ የኮከብ ጨረር መሆኑንና ከተጠሪ የፀሐይ ጨረር ጋር ግንኙነት እንደሌለው ተከራክረዋል። የተጠሪ የንግድ ምልክት የፀሐይን ጨረር የሚያሳይ የፀሐይ ምስል ያለበት

ከመሆኑ አንፃር ተጠቃሚው በምስሉ ምክንያት ባለጨረሩ በማለት በተለምዶ ይጠራዋል የሚል ክርክር ከመቅረቡ አንፃር ኮሚቴው ሊያየው የሚገባ የተጠሪ የንግድ ምልክት በእይታ ባለጨረሩ ሊያስብል ይችላል ወይ የሚል መሆን ነበረበት፡፡ ኮሚቴው መመሳሰሉ ዝቅተኛ ነው ያለውን በተመለከተም መመሳሰሉ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት አልተገለፀም በተለይም ምልክቶቹ በአንድ ምክንያታዊ ሰው ቅጽበታዊ እይታ ልዩነት ስለመኖሩ በግልጽ ይታያል አይታይም የሚለውን የሚያትት አይደለም፡፡ ፍርድ ቤቱ ከሁለቱ የንግድ ምልክቶች እንደተገነዘበው በአንድ ምክንያታዊ ሰው እይታ ጨረርን የሚያሳዩ ናቸው፤ የይ/ባይ ምስል ውስጥ ፀሐይ የሚለው ጽሁፍ ቢኖርም ከምስል የተነሳ ባለጨረሩ ቆርቆሮ ተብሎ ሊገለጽ እንደሚችል የሚያስገነዝብ ነው፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 5(1) ባለስልጣኑ የንግድ ምልክት ሲመዘግብ የአንድ ሰው ምርቶች እና አገልግሎቶች ከሌላው ለመለየት በግልጽ የሚያስችል መሆን እንዳለበት በቅድሚያ እንዲያጣራ የሚያስገድድ በመሆኑ የማጣራት ሀላፊነት ያለበት በመሆኑ ኮሚቴው ማስረጃ አልቀረበም በማለት የሰጠው ምክንያት ተገቢአይደለም፡፡ ከዚህም ሌላ ኮሚቴው የሁለቱ የንግድ ምልክቶች መሳከርን አይፈጥርም የሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰው የምርቱ አይነት ቆርቆሮ ስለሆነ ተጠቃሚው ሳያጣራና መረጃ ሳይሰበስብ አይገዛም በሚል ሲሆን በመርህ ደረጃ አንድተ ጠቃሚ መረጃ የሚሰበስብና ጥንቃቄ የሚያደርግ እንዲሁም በማንኛውም አይነት እቃዎችና አገልግሎቶች ላይ ያለውን ልዩነት አንጥሮ የማውጣት ብቃት ያለው ቢሆንም ህጉ ይህንን የማጣራት ሸክም ወደ ተጠቃሚ የጣለ ሳይሆን አቅራቢው ምርቱን ከሌላው እንዲለይ በሚያስችል መልኩ የንግድ ምልክቱን እንዲያዘጋጅ ሸክም የጣለ በመሆኑ ኮሚቴው በዚህ ረገድ የደረሰበት ድምዳሜም አግባብ አይደለም፡፡ ስለሆነም የአመልካች ጨረር የሚለው ቃል እና የምስል ምልክት መመዝገቡ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም በማለት የተሰጠው ውሳኔ በአዋጅቁጥር 501/1998 አንቀጽ 17(1) እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፤ የአመልካች ምልክት ሊሰረዝ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ቅሬታው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ተሰርሟል፡፡ የሰበ ርአቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡

አመልካች በቀን28/09/2011 ዓ/ም ባቀረበው ማመልከቻ ከፍተኛው ፍ/ቤት የተጠሪ ንግድ ምልክት ጨረር ነው የሚል አቋም ከመነሻው በመያዙና የኮሚቴው ውሳኔ ግድፈት ላይ በማተኮሩ መሰረታዊ ሥህተት ፈጽሟል፤ ምልክቶቹ ተመሳሳይነት አላቸው ቢባል እንኳን ዝቅተኛ ነው፤ ሁለቱ የንግድ ምልክቶች ሲታዩ ህግ ባልፈቀደው ደረጃ እንደማይመሳሰሉ ተጠሪም ሙግት ያላነሳበት ነው፤ የተጠሪ ምልክት በምስልና በፅሁፍ ፀሐይን ከመላ ተፈጥሯዊገ ጽታዎቿ የሚያሳይ ሲሆን የአመልካች ምልክት ጨረር ስለሆነ ብቻ ምልክቱ ከሚገልጸው የፀሐይ ባህርያት ጨረርን ነጥሎ ተቃውሞ ሊያነሳ አይችልም፤ ፀሐይንና ከፀሐይ ጋር የተገናኘ ማንኛውንም ነገር በሞኖፖል መስጠት ተቀባይነት የለውም፡፡ ተጠሪ ባለጨረሩ በሚል ያስመዘገበው ምልክት ባለመኖሩ የኮሚቴው ውሳኔ አግባብ ነበር፤ ተጠሪ ለዚህ ክርክሩ ማስረጃ ሊያቀርብ አይገባም ሲል የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔም ከግራቀኙ ክርክር፣ ከህግና አመክንዬ የሚቃረን እንዲሁም የማስረዳት ሸክምን በተመለከተ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን የጣሰ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ኮሚቴ በንግድ ምልክቶች መካከል የሚኖር ተመሳሳይነት መሳከርን የሚፈጥረው በተጠቃሚው ላይ በመሆኑ የመመሳሰሉ ደረጃ ተጠቃሚው በምርቱ ላይ ባለው መረጃና እውቀት ላይ እንደሚወሰን እንዲሁም በምልክቶቹ መካከል ያለው መመሳሰል ዝቅተኛ መሆኑን በማረጋገጥ የደረሰበት

መደምደሚያ ተቀባይነት እንደሌለው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ትችትም አላግባብ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴው ውሳኔ እንዲጸናልን በማለት ጠይቋል፡፡

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የፍርድ ቤቶቹ ውሳኔ ከአዋጅ ቁጥር 501/98 አንጻር መጣራት ያለበት በመሆኑ ለሰበር ችሎቱ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን 06/02/2012 ዓ.ም ባቀረበው መልስ የንግድ ምልክቱ በአመልካች ስም ከተመዘገበ በኋላ ተጠሪ መቃወሚያ አቅርቦ ምልክቱን የማሻር መብት ያለው መሆኑን፤ አመልካች ያስመዘገበው የንግድ ምልክት የኮከብ ምስል ያለበት ስላለመሆኑ፤ የአመልካች የንግድ ምልክት ከተጠሪ ንግድ ምልክት ጋር ማሳከርን የሚፈጥር ስለመሆኑ፤ ተጠሪ ‹‹ጨረሩ›› የሚል ንግድ ምልክት አስመዘገብኩ ያላለ ስለመሆኑና ምልክቱ ግን በተጠቃሚው ዘንድ ‹‹ባለጨረሩ ቆርቆሮ›› የሚል መለያ ስም ያሰጠው ስለመሆኑ ፤ እንዲሁም የንግድ ምልክቶቹ በአዋጁ አንቀጽ 7(1) በግልጽ እንደተመለከተው መሳከርን ሊያስከትል የሚችል ተመሳሳይነት ካለው ሊመዘገብ እንደማይገባና፤ የቆርቆሮ ምርትን የተማረውም ያልተማረውም የህብረተሰብ ክፍል የሚገዛው በመሆኑ የጨረር ምስሉን ብቻ በማየት ሊደናገር የሚችል በመሆኑ ምልክቱ መሳከርን የሚያስከትል ተመሳሳይነት አለው በማለት የስር ክርክሩን በማጠናከር አቅርቧል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከፍሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ በበኩላችን የግራቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች በተሰጠው ውሳኔና ትዕዛዝ የተፈፀመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

አንደመረመርነው ተጠሪ ለአመልካች በሰርተፍኬት ቁጥር LTM/3547/08 የተመዘገበው የንግድ ምልክት ፈራሽ እንዲሆን የጠየቀ ሲሆን በምክንያትነት የጠቀሰው የንግድ ምልክቱ አስቀድሞ ካስመዘገብነው ከእኛ የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይ ነው፤ መመሳሰሉም በቃሉ ላይ ሳይሆን በምስሉ ነው፤ ህብረተሰቡ የቆርቆሮ ምርታችንን የሚገዛው ጨረሮችን አይቶ እንጂ ስሙን አውቆ አይደለም የሚሉ መከራከሪያዎችን በምክንያትነት በማንሳት ነው፡፡

በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀጽ 36 የንግድ ምልክት ምዝገባን ፈራሽ ስለማድረግ የሚደነግግ ሲሆን በንዑስ ቁጥር (1) ስር ምዝገባው በአዋጁ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ከመሰረቱ ያላሟላ መሆኑ ሲረጋገጥ ፈራሽ ሊደረግ እንደሚችል ይገነግጋል፡፡ በአዋጁ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ደግሞ በክፍል ሁለት ከአንቀጽ 5 እስከ 7 ድረስ ተዘርዝረዋል፡፡ ከድንጋጌዎቹ መረዳት እንደሚቻለው ማንኛውም የንግድ ምልክት የአንድን ሰው ዕቃዎች ከሌሎች ዕቃዎች በግልፅ ለመለየት የሚያስችል ከሆነ (capable of clearly distinguishing) ሊመዘገብ እንደሚችል፤ ነገር ግን ከአንድ አይነት ዕቃዎች ጋር የተያያዘ የሌላ ሰው ቀዳሚ የንግድ ምልክት ጋር አንድ አይነት የሆነ ወይም መሳከርን ሊያስከትል የሚችል ተመሳሳይነት ያለው ከሆነ (where it is identical ……. Or if it so nearly resembles such a trademark as to be likely to deceive or cause confusion) ሊመዘገብ እንደማይገባ ተመልክቷል፡፡ (የአዋጁን አንቀጽ 5(1) እና 7(1) ይመለከቷል)፡፡ ከዚህም ሌላ በአዋጁ አንቀጽ 2(12) የተሰጠው ትርጉም እንደሚያመለክተው “የንግድ ምልክት” ማለት

የአንድን ሰው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ከሌሎች ሰዎች ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ለመለየት የሚያስችል የሚታይ ምስል ነው፡፡ ምልክቱ ቃላቶችን፣ ዲዛይኖችን፣ ፊደሎችን፣ ቁጥሮችን፣ ቀለሞችን ወይም የዕቃዎችን ወይም የመያዣዎቻቸውን ቅርጽ ወይም የእነዚህኑ ቅንጅት ሊይዝ ይችላል፡፡

ከፍሲል ከተጠቀሱት የአዋጁ ድንጋጌዎች እና ከአዋጁ ጠቅላላ ይዘት እንዲሁም በዘርፉ ከዳበረው ዕውቀት መገንዘብ እንደሚቻለው የአንድን አስቀድሞ በማመልከቻ በምዝገባ የገባ የንግድ ምልክት መሰረተዊ ባህሪ (essential feature) በመውሰድ ወይም የንግድ ምልክቱን እንዳለ ወስዶ በምልክቱ ላይ የተወሰነ ጭማሪ ወይም ለውጥ በማድረግ የቀረበ የንግድ ምልክት መሳከርን ሊያስከትል የሚችል ተመሳሳይነት ያለው ነው ሊባል ይችላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የአእምሯዊ ጽ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ባቀረበው የውሳኔ ሃሳብ በአመልካችና በተጠሪ የንግድ ምልክቶች መካከል መመሳሰል መኖሩን ጠቅሶ ዝርዝር መምክንያት ሳይሰጥ መመሳሰሉ ዝቅተኛ ነው ብሏል፡፡ በሌላ በኩል ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክርክርና ፍሬ ነገሩን በማጣራት የሁለቱን የንግድ ምልክቶች ይዘት መርምሮ ሁለቱም የንግድ ምልክቶች የጨረር ስለመሆናቸውና አንድ ምክንያታዊ ሰው የጨረር ምልክቶችን በቅጽበታዊ እይታ ተመለክቶ መለየት በማያስችለው ደረጃ ተመሳሳይ መሆናቸውን በማረጋገጥ ወስኗል፡፡ ይህ የፍሬ ነገር መደምደሚያ ተጠሪ አስቀድሞ በመዝገብ ያስገባው የንግድ ምልክት መሰረተዊ ባህሪ (essential feature) በአመልካች የንግድ ምልክት መወሰዱን የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላም በኩል በተጠሪ የንግድ ምልክት በክቡ ምስል ውስጥ ያለው ‘ፀሐይ’ የሚል ቃል በአመልካች የንግድ ምልክት በክቡ ምስል ውስጥ ‘ጨረር’ በሚል መተካቱ የንግድ ምልክቱን ወስዶ የተወሰነ ለውጥ እንደማድረግ የሚቆጠር ነው፡፡

በአጠቃላይ የአመልካች ጨረር የሚለው ቃል እና የምስል ምልክት በተጠሪ አስቀድሞ የተመዘገበውን የንግድ ምልክት መሰረታዊ ባህሪ በመውሰድ የተወሰነ ለውጥ የሚያደርግ በመሆኑና የሁለቱ ንግድ ምልክቶች ተመሳሳይነት መሳከርን የሚፈጥር መሆኑ ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ተረጋግጦ የአመልካች ምልክት ሊሰረዝ ይገባል ተብሎ በመወሰኑ የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 218994 በቀን 25/03/2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 169918 በቀን 12/07/2011 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የዕግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡
3. ለሰበር ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡተዘግቷል ወደመዝገብቤትይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ዮ/መ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ 188271

ሀምሌ 27 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- መዓዛ አሸናፊ

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

አመልካቾች ፡-1ኛ. ወ/ሮ አስካለ ዘለቀ
2ኛ. ወ/ሮ ጽጌ ተስፋዬ } ጠበቃ ዋቤ ሐጂ ከ1ኛ አመልካች ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ጽጌ ዘለቀ፡- ወኪል በቀለ ጉታ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

<u>ፍ ር ድ</u>

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካቾች በቀን 24/04/2012 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 178872 በቀን 26/01/2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልን በማለት ስለጠየቁ ነው። ክርክሩ የጀመረው በስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካቾችና በዚህ ፍርድ ቤት ተከራካሪ ያልሆኑት ዋና ሳጅን ደረሰ ዘለቀ ከሳሾች ነበሩ፤ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ።

ከሳሾች በቀን 07/03/2010 ዓ.ም በተፃፈ የውርስ ይጣራልን አቤቱታ የሟቾች አቶ ዘለቀ በቀለ እና ወ/ሮ ደደፌ ዱጉማ የመጀመሪያ ደረጃ እና ተተኪ ወራሾች መሆናቸውን፤ በመግለጽ ውርስ እንዲጣራላቸው

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ዳኝነት ጠይቀዋል። በማስረጃነትም ሟች አቶ ዘለቀ በቀለ በ16/01/1996 ዓ.ም እና ወ/ሮ ደደፌ ዱጉማ በ14/03/2008 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውን የሚገልፅ የወራሽነት ማስረጃ አቅርበዋል።

ተጠሪ ለክሱ ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቶ ዘለቀ በቀለ የሞቱት ከሳሾች እንደጠቀሱት በ1996 ዓ.ም ሳይሆን በ1991 ዓ.ም ነው፤ ከዚህ አንፃር የሟች አቶ ዘለቀ በቀለ ውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ ከ19 አመት በኋላ የቀረበ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1000(1) መሰረት በይርጋ የሚታገድ ነው፤ በሌላም በኩል ወ/ሮ ደደፌ ዱጉማን በሚመለከት አቶ ዘለቀ ከመሞታቸው በፊት ለረጅም አመታት ተለያይተው የነበረ መሆኑንና የውርስ ሃብት ነው በሚል በተጠቀሰው ቤት ውስጥም ኖረው የማያውቁ መሆኑን በመግለጽ የቀረበው የውርስ ይጣራልኝ አቤቱታ በሙሉ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን በማንሳት ተከራክረዋል።

የስር ፍርድ ቤት የይርጋ ክርክሩንና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ሟች አቶ ዘለቀ የሞቱበትን ጊዜ በተመለከተ በከሳሶች በኩል በወራሽነት ማስረጃቸው ላይ በ1996 ዓ.ም በሞት የተለዩ ስለመሆኑ ከሚገልጸው ውጭ ሌላ ማስረጃ አልቀረበም፤ በአንፃሩ ተከሳሽ የወራሽነት ማስረጃን ጨምሮ የቀብር ስርዓቱ ከተፈፀመበት ቤተክርስቲያን የተፃፈ ደብዳቤ እና ምስክሮችን በማቅረብ ሟች አቶ ዘለቀ በ1991 ዓ.ም የሞቱ ስለመሆኑ አስረድተዋል። ይርጋውም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሊቆጠርይገባል። ስለሆነም ሟች አቶ ዘለቀን በተመለከተ በአመልካቾች የቀረበው የውርስ ይጣራልኝ አቤቱታ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1000 (1) መሰረት በ 3 ዓመት ውስጥ ያልቀረበ ከመሆኑም በላይ ይህንን የይርጋ ጊዜ የሚያቋርጥ ምክንያት ስላላቀረቡ ጥያቄው በይርጋ የሚታገድ ነው። ከዚህም ሌላ ወ/ሮ ደደፌ ዱጉማን በተመለከተ በሞት የተለዩት በ14/03/2008 ዓ.ም መሆኑ አከራካሪ ባይሆንም አሁን የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ የቀረበበት ከሟች አቶ ዘለቀ ጋር የተፈራ መሆኑ የተገለጸውን ንብረት በሚመለከት በህጉ በተቀመጠው ግዜ ውስጥ ከሟች አቶ ዘለቀ ጋር ከተለያዩ በኋላ በ10 አመት ግዜ ውስጥ ሳይጠይቁ የቆዩ መሆናቸውን የቀረበው ማስረጃ የሚያረጋግጥ በመሆኑ የሟች መብት ቀድሞውኑ በይርጋ ቀሪ የሆነ በመሆኑ አመልካቾች በዚሁ መነሻነት ያቀረቡት የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ ቀድሞውኑ ሟች ባላረጋገጡበት መብት ላይ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ብይን ሰጥቷል።

በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት አመልካቾች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቅርበዋል። ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የሟች ወ/ሮ ደደፌ ዱጉማ ውርስን በሚመለከት በንብረቱ ላይ ኖረው የሚያውቁ ስለመሆናቸው ባለመረጋገጡ፤ ሟች አቶ ዘለቀ በቀለ ከመሞታቸው በፊት ተለያይተው የኖሩ መሆኑ በማስረጃዎች በመረጋገጡ፤ እንዲሁም በህይወት እያሉ ንብረቱ ላይ ያላቸውን መብት ያላስከበሩ መሆኑ በመረጋገጡ ሟች የሌላቸውን መብት ከሳሾች ሊያገኙ የማይገባ ከመሆኑ አኳያ የስር ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የቀረበውን ክስ በይርጋ

ቀሪ ማድረጉ ህጉን የተከተለ ነው በማለት ይህን የውሳኔ ክፍል አፅንቷል። በሌላ በኩል ሟች አቶ ዘለቀ በቀለን በሚመለከት የአሁን አመልካቾች አውራሽ ሟች ወ/ሮ ብዙነሽ ዘለቀ ከዚህ ቀደም በፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 23047 ተመሳሳይ ጥያቄ አቅርበው የነበረ በመሆኑ ይህ ጥያቄያቸው ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1851(2) ድንጋጌ አንፃር የክርክሩ መዝገብ እስከተቋረጠበት ጥር 2000 ዓ.ም ድረስ የይርጋ ጊዜውን አቆጣጠር የሚያቋርጥ ነው፤ ከጥር 2000 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው አቤቱታ 10 ዓመት ከመሙላቱ በፊት ህዳር 2010 ዓ.ም የቀረበ ነው፤ ውርስ እንዲጣራና ድርሻ ክፍፍል ኢንዲፈፀም የሚቀርብ ክስ የይርጋ ጊዜ የሚወስወነው የፍ/ብ/ህ/ቁ 1080(3) ሟች ከሞቱበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር 10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ጥያቄው ውድቅ ይሆናል በማለት ይደነግጋል፤ ስለሆነም የአሁን አመልካቾችን በተመለከተ ጥያቄያቸው በይርጋ ሊታገድ አይገባም በማለት በዚህ ረገድ የተሰጠውን ብይን ሽሮ በፍሬ ነገሩ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት መልሷል።

ይህን በመቃወም ተከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ይግባኝ ለጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበዋል። ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ለግራ ቀኙ ክርክር አግባብነት ያለው የይርጋ ድንጋጌ የፍ/ብ/ህ/ 1000(1) እንጂ 1080 (3) አይደለም፤ የአመልካቾች አውራሽ ከሞቱ ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ ሲቆጠር 3 አመት ያለፈ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1000(1) ክሱ በይርጋ ሊታገድ የሚገባ ነው፤ በመ/ቁ 23047 ቀርቦ የነበረው ክርክር መቋረጡ ከተረጋገጠበት ጥር 2000 ዓ.ም ጀምሮ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው ጥያቄ በስር ፍ/ቤት እስከቀረበበት ህዳር 2010 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ ሲቆጠርም 3 አመት ያለፈ በመሆኑ ጥያቄው ከዚህ አንጻርም ሲታይ በይርጋ የሚታገድ ነው፤ በመሆኑም ይ/ሰሚው ከፍተኛው ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት የሰጠው ውሳኔ ክፍል ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ሽሮ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በውጤት ደረጃ አጽንቷል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው። አመልካቾች ባቀረቡት ማመልከቻ ተፈፀመ የሚሉትን የህግ ስህተት ዘርዝረው ውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ እንዲሻርና ንብረት ማጣራቱ በተጠየቀበት አግባብ እንዲፈጸምልን በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል።

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የአመልካቾች የውርስ መብት በይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ የተወሰነበትን አግባብ ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1000 እና 1852 እንዲሁም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 31185 እና 17937 ከሰጠው ትርጉም ጋር በማገናዘብ ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል።

ተጠሪ ባቀረቡት መልስ የስር ክርክራቸውን አጠናክረው የአመልካቾች የውርስ ይጣራልን ጥያቄ በህጉ አግባብ በይርጋ የታገደ በመሆኑ የጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲጸና ጠይቀዋል። አመልካቾችም የመልስ መልስ አቅርበዋል።

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ለሰበር ችሎቱ የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በውሳኔው የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል።

እንደመረመርነው የአመልካቾች ቀዳሚ ቅሬታ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 23047 ምን እንደተሰራ ማጣራት ሲገባው ሳያጣራ በዝምታ ማለፉን የታዘበው የከፍተኛው ፍ/ቤት ስህተት ነው ብሎ ተችቶ በተጠቀሰው መዝገብ ውስጥ የውርስ ንብረትን ለማጣራት ከተካሄደው ርቀት አኳያ ተፈጻሚነት ያለው አንቀጽ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1080(3) ነው ማለቱ ትክክል ሆኖ እያለ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ተፈጻሚነት ያለው አንቀጽ 1000(1) ነው ማለቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፤ እንዲሁም የሟች አቶ ዘለቀ የውርስ ንብረት ማጣራት ይርጋ በመ/ቁ 23047 ላይ በተደረሰው እንቅስቃሴ መቋረጡን ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ተቀብሎ ነገር ግን ከዚያ በኋላ ቀጥሎ አዲሱ የይርጋ ዘመን 3 አመት ነው ያለው የፍ/ብ/ህ/ቁ 1852(1)ን ጠቅሶ ነው፤ ይሁንና የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) አዲሱ የይርጋ ዘመን 10 አመት ነው እያለ ጠ/ፍ/ቤቱ የሁለቱን ንዑስ አንቀጾች ተያያዥነት ባለማጤን የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው በሚል እየተከራከሩ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

ተጠሪ በበኩላቸው በመ/ቁ 23047 እንዲጣራ ከተሰጠው ትዕዛዝ ውጭ ምንም አይነት የውርስ ማጣራት ባልተካሄደበትና የውርስ አጣሪ ሪፖርት ባልቀረበበት ግራ ቀኙም ባለመቅረባቸው መዝገቡ ተዘግቷል በተባለበት ሁኔታ በዚህ መዝገብ የውርስ ድርሻ እንደተለየና ሪፖርት እንደቀረበ በማስመሰል አሁን ያቀረቡት መከራከሪያ ሀሰተኛ፣ የህግና የማስረጃ ድጋፍ የሌለው እንዲሁም አዲስ መከራከሪያ በመሆኑ ውድቅ እንዲደረግ፤ እንዲሁም አመልካቾች ያቀረቡት የ10 አመት የይርጋ ክርክር በፍ/ብ/ህ/ቁ 1846፣ 1852(1) እና 1000(1) መሰረት ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት ተከራክረዋል።

እንደተመለከትነው የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ሟች አቶ ዘለቀ በቀለን በተመለከተ የአሁን አመልካቾች አውራሽ ሟች ወ/ሮ ብዙነሽ ዘለቀ አስቀድመው በመ/ቁ 23047 ጥያቄ አቅርበው የነበረ በመሆኑ ይህ ጥያቄያቸው ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1851(2) ድንጋጌ አንፃር የክርክሩ መዝገብ እስከተቋረጠበት ጥር 2000 ዓ.ም ድረስ የይርጋ ጊዜውን አቆጣጠር የሚያቋርጥ ስለመሆኑ፤ ከጥር 2000 ዓ.ም ጀምሮ ሲታሰብ ደግሞ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው አቤቱታ 10 ዓመት ከመሙላቱ በፊት ህዳር 2010 ዓ.ም መቅረቡን፤ ውርስ እንዲጣራና

ድርሻ ክፍፍል ኢንዲፈፀም የሚቀርብ ክስ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1080(3) መሰረት በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊቀርብ እንደሚችል በመዘርዘር የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ በይርጋ ሊታገድ እንደማይገባ ወስኗል።

ይሁንና የፍ/ብ/ህ/ቁ 1080(3) የውረስ መከፋፈሉን አሰራር በሚደነግገው ክፍል ውስጥ የተካተተ ሲሆን የውርስ ክፍፍልን በሚመለከት በወራሾች መካከል በተደረገው ስምምነት ወይም የክፍያ ሃሳብ ያልተስማማ ወራሽ ይህን ለማስፈረስ የሚያቀርበው ጥያቄ በይርጋ የሚታገድበትን ጊዜ የሚደነግግ እንጂ የውርስ ማጣራት ጥያቄን የሚመለከት የይርጋ ጊዜ አይደለም። የውርስ ማጣራትን ጥያቄ የሚመለከተው የይርጋ ደንብ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1000(1) ስር የተመለከተው ሶስት አመት ጊዜ ሲሆን በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 25567 እና በሌሎችም መዛግብት የሰጠው ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 መሰረት ለተያዘው ጉዳይም በተመሳሳይ ተፈጻሚነት ያለው ነው። ስለሆነም ይኸው ተጠቅሶ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ በጠቅላይ ፍርድ ቤት መታረሙ በአግባቡ ነው ብለናል።

የሟች አቶ ዘለቀ የውርስ ንብረት ማጣራት የይርጋ ጊዜ መቆጠር በመ/ቁ 23047 ላይ በተደረገው እንቅስቃሴ ተቋርጦ ነበር መባሉን በተመለከተም ከመነሻው የአመልካቾች አውራሽ በመ/ቁ 23047 ጥያቄ አቅርበው የነበረ ከሆነ አዲስ ፋይል ከማስከፈት ይልቅ በክርክሩ ተተክተው ማስቀጠል የሥነ ሥርዓት ህጉን የተከተለ ይሆን የነበረ ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶች በመ/ቁ 23047 የተደረገውን ክርክር በይርጋ ማቋረጫነቱ የተቀበሉት ስለሆነና በዚህ ረገድ የቀረበ ቅሬታ ባለመኖሩ በዚህ ላይ ይህ ችሎት ውሳኔ የሚሰጥበት አይሆንም። ይሁንና ይኸው መዝገብ የይርጋ ጊዜ መቆጠርን ያቋርጣል ከተባለ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1852(2) መሰረት አዲሱ የይርጋ ዘመን 10 አመት ሊሆን ይገባል በማለት አመልካቾች መከራከራቸው ተገቢ መሆን አለመሆኑን መርምረናል። የውርስ ህጉ የውርስ ጉዳይን የተመለከቱ ልዩ የይርጋ ድንጋጌዎች የያዘ ሲሆን በሌላ በኩል በህጉ ላይ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ሲቋረጥ እንደ አዲስ ስለሚቆጠረው የይርጋ ጊዜ የውርስ ህጉ አይደነግግም። ይህ ጉዳይ በውርስ ህጉ ካልተሸፈነ ደግሞ የጠቅላላ ህጉ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ እንደሚሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1677 መገንዘብ ይቻላል። በዚህ መሰረት የይርጋ መቋረጥ ውጤትን የሚደነግገው ጠቅላላ ድንጋጌ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1852 ሲሆን በንኡስ (2) ስር የአዲሱ ይርጋ ዘመን 10 አመት እንደሆነ ይደነግጋል። የዚህን ድንጋጌ ተፈጻሚነት በተመለከተ ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 31185 እና በሌሎችም ተመሳሳይ መዛግብት በሰጠው ትርጉም "ድንጋጌው የሚገኘው ጠቅላላ የውሎች ህግ በሚለው ክፍል ከመሆኑም በላይ ውልን አስመልክቶ የሚቀርብ ክስ በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ እንደሚሆን በፍ/ብ/ህ/ቁ 1845 ላይ ስለተመለከተ ከዚሁ ከጠቅላላ ውል ጋር በተያያዘ አንድ የይርጋ ጊዜ ሲቋረጥ ሌላ አዲስ የ10 ዓመት ይርጋ ጊዜ ሊኖር እንደሚችል ከሚያስገነዝብ በስተቀር በልዩ

ህግ የይርጋ ጊዜው ከ10 ዓመት ዝቅ ብሎ የሚገኘው ሁሉ ተቋርጦ በሚገኝበት ወቅት አዲሱ የይርጋ ጊዜ 10 ዓመት ነው ማለት እንደማይቻል" ትርጉም ሰጥቷል። ከዚህ አንጻር በተያዘው ጉዳይ የይርጋ ጊዜ መቆጠር ይቋረጣል ከተባለ በኃላ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1852(2) መሰረት አዲሱ የይርጋ ዘመን 10 አመት ሊሆን ይገባል በማለት አመልካቾች የሚያቀርቡት መከራከሪያ ህግ አውጭው ለተለያዩ ክሶች የወሰነውን የተለያየ የይርጋ ጊዜ መሰረት ያላደረገና በሰበር ችሎቱም የተሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም ያላገናዘበ በመሆኑ ክርክራቸው ተቀባይነት የለውም።

በአጠቃላይ በግራቀኙ መካከል ያለው ክርክር በወራሾች መካከል መሆኑን በማረጋገጥና ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የፍ/ብ/ህ/ቁ 1000(1) መሆኑን መሰረት በማድረግ የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ ነው ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩን ወስነናል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 178872 በቀን 26/01/2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል።
2. በዚህ ፍርድ ቤት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል። ይጻፍ።
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ።
4. የስር ፍርድ ቤት መዛግብት በመጡበት መልኩ ይመለሱ።
5. ውሳኔው ዛሬ ነሐሴ 3/2013 ዓ.ም ተነቧል።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ 190228

ቀን ሀምሌ 26 2013ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፡ 1ኛ. አቶ ቶፊቅ መሀመድ
2ኛ. አቶ ሽኩር ረዲ } **ጠበቃ ወንድወሰን ሂርጳ ቀረቡ**

ተጠሪ፡ የኢፌዲሪ የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን፡- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካቾች የፌደራል የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 00027 በ26/4/11ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 169910 በ30/4/12ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ19/5/12ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ተጠሪ በስር የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የዳኝነት ችሎት በአመልካቾች ላይ ባቀረበው ክስ የግል ተበዳይ የሆነው P.K.C.J **ካምፓኒ ወኪል ጆሽ ወንድማማቾች ኃ/የተ/የግ/ማህበር የድርጅቱን እቃዎች ከሌሎች ለመለየት የሚያስችል** EVEREST (**ኤቨረስት**) **የሚል የማይዳሰስ ንብረት ምስል ባለቤት ነው፡፡** EVEREST **የንግድ ምልክት በቃላት ብቻ ያልተገደበ የቅርጽና የምስል ነጻነትን ምናባዊ ይዘት በመፍጠር ከምርትና አገልግሎት ጋር ካለው ጥምረት አንጻር ከ**1982ዓ.ም **ጀምሮ በተለያዩ የሀገሪቱ መገበያያ**

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ስፍራዎች በመግባት በገነባው መልካም ስም የሸማቹ ማህበረሰብን ምርጫ የመምራት አቅም ፈጥሯል። ሆኖም የኤቨረስት የንግድ ምልክትና የአመልካቾች የምርት ማሸጊያ መጠን፤ በማሸጊያው ላይ ባረፈው የሴት ምስል እና በአብዛኛው ደረጃ አደናጋሪ ሆኖ እያለ በኢትዮጵያ ውስጥ ጥበቃ ያልተደረገለትን የምርት ማሸጊያ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት 1ኛ አመልካች ከ2006ዓ.ም ጀምሮ ተስመስ ቆንጆ የሚባል የምርት ማሸጊያ ዲዛይን አመሳስሎ በማምረት እንዲሁም 2ኛ አመልካች የዚሁን አይነት ተመሳሳይ ምርት ከ2008ዓ.ም ጀምሮ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ሸማቹ ማህበረሰብን የሚያደናግር ምርት በመሸጥ ላይ የሚገኙ በመሆናቸውና የምርት ማሸጊያው እቃው ምልክት እና የሚኖረው አገልግሎት ተመሳሳይና አደናገሪ በመሆኑ ምክንያት አመልካቾች እየፈጸሙ የሚገኘው ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ተግባራቸውን እንዲያቆሙ ትእዛዝ እንዲሰጥልን እንዲሁም አመልካቾች ለፈጸሙት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ተግባር ከአመታዊ ሽያጭ ገቢያቸው 10% እንዲቀጡ ውሳኔ እንዲሰጥልን በማለት ዳኝነት ጠይቋል። የሰነድ እና የሰው ማስረጃዎችንም አያይዞ አቅርቧል።

አመልካቾች ባቀረቡት መልስ በK.C.J ካምፓኒ ተመዝግቧል የተባለው EVEREST (ኤቨረስት) የተሰኘው የቃል የንግድ ምልክት ነው። በክሱ በምስልና በቃል ብቻ ያልተገደበ የቅርጽ ነጻነትንም ያካተተ ነው በሚል የቀረበው በማስረጃ ያልተደገፈ ነው። የምዝገባ የምስክር ወረቀቱ ላይ ምስልና ቅርጹ ጥበቃ አልተሰጠውም። በንግድ ምልክትና ጥበቃ አ/ቁ 501/98 አንቀጽ 4 መሰረት የንግድ ምልክት ባለቤትነት የሚገኘውና በ3ኛ ወገን ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው ሲመዘገብና የምስክር ወረቀት ሲሰጥ ነው። K.C.J ካምፓኒ የተጣሰበት የጸጉር ማቅለሚያ ሂና ማሸጊያ ምስልና ቅርጽ ላይ መብት የለውም። በአ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 8(1)፤ 8(2) ሀ እና ለ መሰረት ያልተገባ የንግድ ውድድር አለ የሚባለው ከሀቀኝነት ውጪ የማታለል ስራ፤ የተወዳዳሪን ጥቅም ሊጎዳ የሚችል ተግባር መፈጸም ፤የማደናገር ተግባር እንዲሁም የማደናገር ድርጊት ወይም የሌላውን ነጋዴ መረጃ ማውጣት እንደሆነ ተደንግጓል። ሆኖም አመልካቾች በህጋዊ የምዝገባ ሂደት ባገኙት ህጋዊ የንግድ ምልክት እቃዎችን ከመሸጥ ባለፈ የፈጸሙት ህገወጥ ድርጊት ስለመኖሩ ማስረጃ አልቀረበም። የቀረበው ክስ አመልካቾች በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ ለማድረግና ተጠሪ በመስኩ ብቸኛ ነጋዴ ሆኖ ለመቆየት አልሞ ያቀረበው በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል። ክስ የተነሳበት ምርት በማሸጊያው ላይ ያለው ምስል እና ቅርጽ ለጥበቃ ብቁ አይደለም። በአመልካቾች የንግድ እቃዎች ጥቅም ላይ የዋሉት ተስመስ ቆንጆ እና መልካማ የተሰኙት የንግድ ምልክቶች የምዝገባ የምስክር ወረቀት ያገኙና ህጋዊ ጥበቃ ያላቸው ናቸው። ተስመስ ቆንጆ፤ ኤቨረስት እና መልካማ በሚሉት የንግድ ምልክቶች መካከል የአጻጻፍም ሆነ በትርጉም ሊያሳስት የሚችል ተመሳሳይነት የለም። የጸጉር ማቅለሚያ ሂናዎችን የሚጠቀሙ አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ያላቸውና የሚፈልጉትን የምርት አይነት ለይተው የሚያውቁ እንደሆኑ ይገመታል። ስለሆነም በንግድ ምልክቶቹ መካከል መመሳሰል የሌለ በመሆኑ ሸማቹን አያደናግርም። ተጠሪ ያቀረበው የውጪ ሀገር የምዝገባ ምስክር ወረቀት በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት እስካልተመዘገበ ድረስ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም። የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የሰጣቸው ማብራሪያዎች በአዋጁ እንዲያስፈጽመው ከተሰጠው ስልጣን ጋር የማይሄድ ከመሆኑም በተጨማሪ የንግድ ምልክቶች ያደናግራሉ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ወይም አያደናግሩም ብሎ የመወሰን ስልጣን የአንድ አስፈጻሚ ስልጣን ሳይሆን የፍርድ ቤቶች ስልጣን ነው። የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በመ.ቁ 145383 በ24/8/10ዓ.ም አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ በመሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ጠይቀዋል። የሰነድ እና የሰው ማስረጃዎችንም አያይዘው አቅርበዋል።

ችሎቱም 1ኛ. አመልካቾች አ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 8(1) እና 8(2)(ሀ) እና (ለ)ን በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ፈጽመዋል ወይስ አልፈጸሙም? 2ኛ. አመልካቾች ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ፈጽመዋል የሚባል ከሆነ ሊሰጥ የሚገባው ዳኝነት ምን መሆን አለበት? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ግራቀኙን በቃል ካከራከረ፤ የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ በንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ አ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 8(1) ማንኛውም ነጋዴ በንግድ ስራ ሂደት ውስጥ ማናቸውም ሀቀኛ ያልሆነ፤ አሳሳች ወይም አታላይነት ያለበትና የተወዳዳሪን የንግድ ጥቅም የሚጎዳ ወይም ሊጎዳ የሚችል ተግባር መፈጸም እንደማይችል ከደነገገው አንጻር በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የግል ተበዳይ ብሎ ያቀረበው የK.C.J ካምፓኒ ወኪል ጆሽ ወንድማማቾች ኃ/የተ/የግ/ማህበር የጸጉር ማቅለሚያ ምርቶችን ከውጪ እያስመጣ የሚሸጥ ሲሆን ለምርቱ የንግድ ምልክት የቃል ጥበቃ ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በ1/9/08ዓ.ም ተሰጥቶታል። በተመሳሳይ 1ኛ አመልካች TSMSSKONJO የሚል የቃልና የምስል የንግድ ምልክት ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በ22/9/08ዓ.ም እንዲሁም 2ኛ አመልካች MELKAMA የሚል የቃል የንግድ ምልክት በ4/10/08ዓ.ም ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ጥበቃ ተሰጥቷቸዋል። በአሁኑ ወቅት የንግድ ስራቸውን እያከናወኑ ያሉትም ይህንኑ የንግድ ስማቸውን እየተጠቀሙ መሆኑን አመልካቾች ያቀረቡ ሲሆን ተጠሪም ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ ይህንኑ የሚያረጋጋጥ በመሆኑ ከዚህ አንጻር አመልካቾች ተጠሪ ጥበቃ ያገኘበትን EVEREST የሚል የንግድ ምልክት እንዳልተጠቀሙ ያስገነዛባል።

ግራቀኙ ካቀረበት ክርክር አንጻር ተጠሪ በተባለው የምርት ማሸጊያ ላይ ሌሎች እንዳይጠቀሙበት ለመከልከል እና በብቸኝነት ለመጠቀም የሚያስችል መብት አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚለው ነጥብ ሲታይ በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አ/ቁ 501/98 መሰረት የንግድ ምልክት ምዝገባ ያገኘ ማንኛውም ባለመብት ሌላ 3ኛ ወገን በንግድ ምልክቱ እንዳይጠቀም ለማገድ መብት እንደሚያስገኝለት ከደነገገው አንጻር በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ለምርቱ መለያ በንግድ ምልክትነት ያስመዘገበው የምርቱን ስያሜ የሚያመላክት Everest የሚል ቃል እንጂ የምርት ማሸጊያውን ዲዛይን እና በምርቱ ላይ ያለውን ምስል አይደለም። ምንም እንኳ የተጠሪ ምስክሮች የማሸጊያ ዲዛይኑና ምስሉ ተመዝግቦልናል ያሉ ቢሆንም ተጠሪ ይህን የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ አላቀረበም። ተጠሪ ያቀረበው ማስረጃም Everest የሚል የቃል ጥበቃ ያገኘበትን የምዝገባ የምስክር ወረቀት ነው። ሌላው ተጠሪ ያቀረበው ማስረጃ ከህንድ ሀገር የተሰጠ የጥበቃ ሰርተፍኬት በኢትዮጵያ ውስጥ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ቀርቦ ያልጸደቀ በመሆኑ ህጋዊ ማስረጃ ነው ተብሎ አይወሰድም። በአንጻሩ አመልካቾች እና የአመልካቾች ምስክሮች ማሸጊያው የወል ወይም የጋራ መጠቀሚያ መሆኑን መስክረዋል። ስለሆነም ተጠሪ በ3ኛ ወገኖች ላይ ክስ ሊያቀርብ የሚችለው ጥበቃ ያገኘበት የቃል የንግድ

ምልክት ተጥሶ ሲገኝ ነው። ከዚህ አንጻር ተጠሪ አመልካቾች Everest የሚለውን የቃል የንግድ ምልክት እየተጠቀሙ የጸጉር ማቅለሚያ ምርትን ለገበያ እያቀረቡ ስለመሆኑ አላስረዳም፤ በሌላ በኩል አመልካቾች ለምርቱ እየተጠቀሙ የሚገኙት TSMSSKONJO እና MELKAMA የሚሉ መጠሪያዎችን በመጠቀም መሆኑን የተጠሪ እና የአመልካቾች ምስክሮች አስረድተዋል።

የአመልካቾች ድርጊት ሸማቹን ያደናግራል ወይስ አያደናግርም የሚለውን ነጥብ በተመለከተ በዋናነት የጸጉር ማቅለሚያ የሚጠቀመው የህብረተሰብ ክፍል የትኛው ነው የሚለው ሲታይ የተጠሪ ምስክሮች ሁሉም አይነት ሸማች ምርቱን ይጠቀመዋል ያሉ ሲሆን የአመልካቾች ምስክሮች የጸጉር ማቅለሚያ መሰረታዊ የሚባል ሳይሆን የቅንጦት እቃ ነው፤ ምርቶቹንም የሚጠቀሙት የህብረተሰብ ክፍሎች በአብዛኛው የተሻለ የግንዛቤ ደረጃ ያላቸውና ምርቶችን በማሸጊያው ብቻ አይተው የሚገዙ ሳይሆን በስም ለይተው የሚገዙ ናቸው የሚል መከራከሪያ አቅርበዋል። በዚህ ረገድ ምርቱን የሚጠቀሙት የህብረተሰብ ክፍሎች ወይም ሸማቾች የትኞቹ ናቸው የሚለው ሲታይ የጸጉር ማቅለሚያ መሰረታዊ ፍላጎትን ለማማላት የሚውል ምርት ሳይሆን ለተጨማሪ ውበት መጠበቂያነት የሚውል እንደመሆኑ ምርቱን የሚጠቀሙት የህብረተሰብ ክፍሎች በሚጠቀሙት ምርት ምንነት ላይ ግንዛቤ ያላቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ የሚፈልጉትን ምርት በስም ለይተው ለመግዛትና ለመጠቀም የሚችሉ ናቸው። ተጠሪም ቢሆን የአመልካቾች ድርጊት ሸማቹን የሚያደናገር ነው ከማለት በስተቀር ያቀረበው ማስረጃ የለም። ስለሆነም የአመልካቾች ድርጊት ሸማቹን የሚያደናግር ድርጊት ነው የሚባል ባለመሆኑ አመልካቾች የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ አ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 8(2)(ሀ)ን በመተላለፍ የፈጸሙት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር የለም፤ በመሆኑን ወደ ሁለተኛው ጭብጥ መግባት ሳያስፈልግ ተጠሪ አመልካቾች ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ፈጽመዋል በሚል ያቀረበውን ክስ በማስረጃ ስላላስረዳ በማለት ክሱን ውድቅ በማድረግ ወስኗል።

ተጠሪ ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራል የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የግራቀኙ ክርክርን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ ከአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያለው የጽ/ቤቱ የንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪ ንድፍ ልማት ጥበቃ ዳይሬክቶሬት የንግድ ምልክት ምርመራ ከፍተኛ ባለሙያ እንዲቀርብ በማድረግ ምዝገባ ሳያደርግ የመጠቀም መብትን በሚመለከት ሙያዊ ምስክርነት እንዲሰጥ ከፍ/ቤቱ ለቀረበለት የማጣሪያ ጥያቄ ባለሙያው የሰጠውን ምላሽ ተቀብሎ እንዲሁም በስር ፍ/ቤት በማስረጃ ዝርዝር ፊደል (ለ) ላይ የተገለጸው ኤግዚቢት በፍ/ቤት ቀርቦ እንዲታይ ካደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍ/ቤት የተጠሪን ክስ ውድቅ በማድረግ ለደረሰበት ድምዳሜ መነሻው ተጠሪ የንግድ ምልክት ጥበቃ ያገኘው ኤቨረስት በሚል ስም ሲሆን በተመሳሳይ የንግድ ዘርፍ ተሰማርተው ማደናገር ፈጽመዋል የተባሉት የአመልካቾች ድርጅት ስም ደግሞ ቆንጆ እና መልካማ የሚል መጠሪያ ነው ያላቸው፤ ስለዚህ ስማቸው ኤቨረስት ከሚለው ስም ጋር ምንም አሳሳች ነገር የለውም፤ በተጨማሪም ይህን የጸጉር ማቅለሚያ ምርት የሚጠቀሙ ሸማቾች ከመደበኛ ማህበረሰብ የተሻለ ግንዛቤ እና አቅም ያላቸው በመሆኑ የሚገዙትን ምርት በሚገባ የተረዱ ናቸው። ስለዚህ በምርቱ ዙሪያ መደናገር አይገጥማቸውም፤ የምርቱ ማሸጊያ መልክና ቀለም ምዝገባ ያልተሰጠው በመሆኑ

ጥበቃ አለው ሊባል አይችልም በሚል ነው፡፡ በስር ፍ/ቤቱ የተሰሙት የተጠሪ ምስክሮች የኤቨረስት የጸጉር ቀለም ማሸጊያ ከቆንጆና መልካማ የጸጉር ቀለም ማሸጊያ ጋር በጣም የሚመሳሰል በመሆኑ በሸማቾች ላይ ማደናገር እያስከተለ መሆኑን እንደ አንድ ሸማች ጭምር እንደሚያውቁ እና ሸማቾችም ችግር እንደገጠማቸው እንደገለጹላቸው መስክረዋል፡፡ በሌላ በኩል ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በቁ. አጠ28/662-11 በ26/12/08ዓ.ም ለአዲስ አበባ ፓሊስ እንዲሁም በቁ. አጠ28/119-660/08 በ26/12/08ዓ.ም እና በቁ. አጠ28/560-104/08 በ1/11/08ዓ.ም ለንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ዋና ባለስልጣን በዋና ዳይሬክተሩ የተጻፉት ደብዳቤዎች የኤቨረስት የጸጉር ቀለም ማሸጊያ ከቆንጆና መልካማ የጸጉር ቀለም ማሸጊያ ጋር አብሮ ቀርቦ ቢታይ በአብዛኛው በሚባል ደረጃ የመጠን፤ የፊደላት ቀለማትና በአጻጻፍ ዘይ በመደቦች ቀለማት፤ በማሸጊያው ላይ ባረፈው የሴት ምስል... እንዲሁም በአጠቃላይ የቀለም ቅንጅት ተመሳሳይ በመሆኑ በገበያ ውስጥ ቢገባ ሸማቹን ሊያደናግር እንደሚችል በዚህም ምክንያት የአንድ ድርጅት ምርት እንደሚመስሉ ይገልጻሉ፡፡

ተጠሪ ባቀረበው ክስ በአ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 8(2)(ሀ) መሰረት መደናገር በስም ብቻ ሳይሆን በማናቸውም ሁኔታ ስለመሆኑ፤ እንዲሁም ኤቨረስት የጸጉር ቀለም የምርቱን ማሸጊያ ከ1982ዓ.ም ጀምሮ ከቆንጆ እና መልካማ በፊት በቀደምትነት የሚጠቀምበት በመሆኑ በመጠቀም የጥበቃ መብት አለኝ በማለት የተከራከረ ሲሆን በአመልካቾች በኩል ደግሞ ጥበቃ የሚገኘው በአ/ቁ 501/98 አንቀጽ 4 መሰረት በማስመዝገብ ስለሆነ ያልተመዘገበ የንግድ ምልክት ሌላው እንዳይጠቀምበት ለመከላከል የሚያስችል መብት አይሰጥም በሚል ተከራክሯል፡፡ ሆኖም በስር ፍ/ቤቱ በጽሁፍ ማስረጃነት ከአእምሯዊ ንብረት ምዝገባ ጽ/ቤት በቁ. አጠ28/560-104/08 በ1/11/08ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በንግድ ምልክት ላይ ያለ መብት በመሰረታዊ ደረጃ ከመመዝገብ የሚመነጭ ቢሆንም ሳይመዘገብ ለረጅም ግዜ ግልጋሎት ላይ የዋለ የንግድ ምልክትም ቢሆን ለባለቤቱ መብትን የሚያጎናጽፍ መሆኑ በንግድ ምልክት አዋጁ ላይ የተለያዩ ቦታዎች ተጠቅሶ እንደሚገኝ እና የንግድ ምልክት ህግ ሳይንስም ይህን እንደሚያረጋግጥ የተመለከተ መሆኑን ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በማጣሪያ ምስክርነት የቀረቡት ባለሙያ ይህንኑ ሃሳብ በሚያጠናክር መልኩ የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ አንጻር የኤቨረስት የጸጉር ቀለም ማሸጊያ ባለቤት K.C.J ካምፓኒ ከ1982ዓ.ም ጀምሮ በማሸጊያው ይጠቀም እንደነበር ሲታይ በ2006ዓ.ም እና 2008ዓ.ም የኤቨረስት ባለቤት K.C.J መብት እንዳለው ያስገነዝባል፡፡ በኤግዚቢትነት ለፍ/ቤቱ የቀረቡት የኤቨረስት፤ የመልካማ እና የቆንጆ የጸጉር ቀለም መያዣ ምርቶች ማሸጊያዎች ፍ/ቤቱ እንደተመለከተው ከስማቸው መለያየት በስተቀር በሌላው ይጎውም በማሸጊያው መጠን፤ የፊደላት ቀለማት፤ የመደቦች ቀለማት፤ የማሸጊያው ቀለም፤ በማሸጊያው ላይ ያረፈው ፎቶ... ተመሳሳይነት እንዳለው እና አንዱን ከአንዱ ለመለየት አስቸጋሪ መሆኑን ያስገነዛባል፡፡

የአመልካቾች ምስክሮች የጸጉር ማሸጊያ ቢመሳሰሉም የፈለጉትን የምርት አይነት በስሙ ለይተው መግዛት እንደሚቻል የገለጹ ሲሆን 3ኛ ምስክራቸው የተጠሪ የጸጉር ቀለም ማሸጊያ ከአመልካቾች የጸጉር ቀለም ማሸጊያ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የሚመሳሰሉ እና በዚሁ ምክንያትም ሊያደናግሩ እንደሚችሉ እንደሚያደናግሩ የገለጹ ከመሆኑም በተጨማሪ ከላይ የተገለጹት የአእምራዊ ንብረት ጽ/ቤት በተለያዩ ቀናት

በጻፋቸው ደብዳቤዎች ላይ የአመልካቾች የምርት ማሸጊያ ከተጠሪ የምርት ማሸጊያ ሙሉ በሙሉ የሚመሳሰሉ እና ሸማቹንም የሚያናግሩ፤ ሊያደናግሩ የሚችሉ መሆኑን ዝርዝር ማብራሪያ ገልጿል፡፡ ሆኖም የስር ፍ/ቤት ይህን የጽሁፍ ማስረጃ ለምን እንዳልመዘነው ወይም እንዳልተቀበለው በውሳኔው ላይ አልገለጸም፡፡ በአመልካቾች በሰነድ ማስረጃነት የቀረቡትን በወንጀል ጉዳይ የተሰጡትን ውሳኔዎች በተመለከተ የወንጀልና የአስተዳደራዊ ጉዳዮች የማስረጃ ምዘና የሚለያይ ከመሆኑም በተጨማሪ በወንጀል ነጻ መባል ከአስተዳደራዊ ተጠያቂነት ነጻ እንደማያደርግ የወንጀል መርህ ከደነገገው አንጻር ማስረጃው ሚዛን የሚደፋ ሆኖ አልተገኘም፡፡

የስር ፍ/ቤቱ የምርቱ ተጠቃሚዎች የተሻለ ግንዛቤ ያላቸው ያላቸው በመሆኑ በምርቱ ማሸጊያ መመሳሰል መደናገር አይኖርም የሚለው መደምደሚያ የሀገሪቱን ማህበረሰብ ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘበ እና በጥናት ላይ ያልተመሰረተ በግለሰብ ሀሳብ ላይ ብቻ የተመሰረተ ከመሆኑ አንጻር፤ የተሻለ አረዳድ ያለው የመንግስት መስሪያ ቤት የሰጠውን መረጃ ሳይመዝን የደረሰበት በመሆኑ እንዲሁም የአ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 8(2)(ሀ)ን ድንጋጌ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ተጠሪ ክሱን በሚገባ አላስረዳም ሲል የሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለሆነም በተጠሪ በስር ፍ/ቤት በቀረቡት የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በኤግዚቢትነት ባስቀረባቸው ምርቶች እና የባለሙያ ምስክርነት አመልካቾች በአ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 8 (1) እና 2(ሀ) የተደነገገውን በመጣስ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር የፈጸሙ መሆናቸውን ተጠሪ በበቂ ማስረጃ ያስረዳ ስለሆነ አመልካቾች ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ተግባር ፈጽመዋል በማለት እንዲሁም አመልካቾች ጥፋተኞች ናቸው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም የስር የዳኝነት ችሎቱ የተጠሪን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኋላ በአ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 42(3) መሰረት አመልካቾች እያንዳንዳቸው የአመታዊ የሽያጭ ገቢያቸውን 5%(አምስት በመቶ) የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጡ በማለት ወስኗል፡፡ እንዲሁም የአመልካቾች ድርጅቶች የሚጠቀሙበት የጸጉር ቀለም ማሸጊያዎች ከኤቨረስት የጸጉር ቀለም ማሸጊያ በመጠን፤ በፊደላት፤ ቀለማትና በአጻጻፍ ዘይ፤ በመደቦች ቀለማት፤ ማሸጊያው ላይ ባረፈው የሴት ምስል .... በአጠቃላይ የቀለሞች ቅንጅት ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ በገበያ ውስጥ ሸማቾችን የሚያደናግርና ሊያደናግር ስለሚችል እንዳይጠቀሙ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ስሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ በንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ አ/ቁ 813/2006 መሰረት አመልካቾች የማደናገር ሁኔታ ያስከተለ ተግባር ፈጽመዋል አልፈጸሙም የሚለው የማስረጃ ጉዳይ በመሆኑ የባለስልጣኑ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በቁ. አጠ28/662-11 በ26/12/08ዓ.ም ፤ በቁ. አጠ28/119-660/08 በ26/12/08ዓ.ም እና በቁ. አጠ28/560-104/08 በ1/11/08ዓ.ም የተጻፉትን ደብዳቤዎች፤ ከንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪ ንግድ ልማት ጥበቃ ዳይሬክቶሬት ባለሙያ የሰጠውን ምስክርነት እና ምርቶችን በኤግዚቢትነት በማስቀረብ የ EVEREST የጸጉር ቀለም ማሸጊያ ከቆንጆና መልካማ የጸጉር ቀለም ማሸጊያ በአብዛኛው ደረጃ የመጠን፤ የፊደላት፤ ቀለማትና የአጻጻፍ ዘይ በመደቦች ቀለማት

በማሸጊያው ላይ ባረፈው የሴት ምስል... ተመሳሳይ መሆናቸውን ያረጋገጠ መሆኑን ከችሎቱ ውሳኔ መረዳት የተቻለ በመሆኑ የባለስልጣኑ ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካቾች የአ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 8(1) እና 8(2) ሀ እና ለን በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ፈጽመዋል በማለት የአመታዊ ሽያጭ ገቢያቸውን 5%(አምስት በመቶ) የገንዘብ ቅጣት እና አመልካቾች የሚጠቀሙበትን የጸጉር ቀለም ማሸጊያዎች እንዳይጠቀሙ መወሰኑ አግባብ ነው በማለት የስር የፌደራል የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ የተገለጹትን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ ተጠሪ አላግባብ ተበዳይ ነኝ ያለው የኬሲጄ ካምፓኒ ያስመዘገበውን EVEREST በሚለው የጸጉር ቀለም ምርት ላይ የተረጋገጠለትን መብት የስር ፍ/ቤት ሳያረጋግጥ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ፈጽማችኋል በማለት የሰጠው ውሳኔ፤ ለክርክር መነሻ የሆነውን ምስል እና ማሸጊያ እንዳንጠቀም እንዲሁም አመልካቾች እያንዳንዳችን የአመታዊ ሽያጫችንን 5% እንድንቀጣ የተሰጠው ውሳኔ ተሽሮ የስር የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የዳኝነት ችሎት የሰጠው ውሳኔ እንዲጸናልን፤ ወጪና ኪሳራም እንዲከፈለን እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡

ይህ አቤቱታቸው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካቾች አከራካሪው የንግድ ምልክት በህጋዊ አካል ተመዝግቦላቸው ባለበት እና ምንም ተቃውሞ ባልቀረበበት ሁኔታ፤ የንግድ ስራቸውን እየሰሩ ባለበት ሁኔታ፤ ከሌላው ተመሳሳይ የንግድ ምልክት ካለው በተለየ እነሱ ብቻ ተለይተው የንግድ ስራ መስራት አትችሉም የተባለበት ከአዋጁ አንቀጽ 2፤ 12 እና 4 እንዲሁም ከህገመንግስቱ አንቀጽ 41(1) አንጻር ለማጣራት ለሰበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ15/11/12ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ በ17/2/13ዓ.ም በተጻፈ ባቀረበው መልስ የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ አ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 8(2)(ሀ) ማንኛውም ነጋዴ በሌላው ነጋዴ ወይም በነጋዴው ተግባራት በተለይም ነጋዴው ከሚያቀርበው የንግድ እቃ ጋር በተገናኘ ሁኔታ ማደናገርን ያስከተለ ተግባር ወይም ሊያስከትል የሚችል ማንኛውም ድርጊት መፈጸም እንደማይችል ከደነገገው አንጻር የስር የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካቾች የ K.C.J ካምፓኒ ለረዥም አመታት ሲጠቀምበት የነበረውን ማሸጊያ ሆን ብለው በምስልና በዲዛይን በማሳሰል ማቅረባቸውን በስር የዳኝነት ችሎቱ ከቀረቡት ከተሰሙት የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች፤ በባለስልጣኑ የይግባኝ ሰሚ ችሎት ዘንድ በኤግዚቢትነት ከቀረቡት ምርቶች እና የባለሙያ ምስክርነት በማረጋገጥ ይህም ሀቀኛ ያልሆነ አሳሳችና የተወዳዳሪን ጥቅም የሚጎዳ ሸማቹንም የሚያሳስት ተግባር ነው በማለት አመልካቾች ከዚህ ተገቢ ካልሆነ የንግድ ውድድር ድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ሲል የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ በማለት ጠይቋል፡፡

አመልካቾች በ17/3/13ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ፤ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር የፌደራል የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍ/ቤት

እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ስሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

1ኛ አመልካች የምዝገባ የምስክር ወረቀት ያገኘበት ተስመስ ቆንጆ(TSMSSKONJO) የተሰኘው የጸጉር ቀለም የንግድ ምልክት እና 2ኛ አመልካች የምዝገባ የምስክር ወረቀት ያገኘበት መልካማ(MELKAMA) የተሰኘው የጸጉር ቀለም የንግድ ምልክት ብቻ ሆኖ ሳለ ለጸጉር ቀለማቱ የሚጠቀሙት ማሸጊያዎች በተጠሪ በተወከለው የግል ተበዳይ K.C.J ካምፓኒ ካስመዘገበው EVEREST ከተሰኘው የጸጉር ቀለም ማሸጊያ በሁሉም መልኩ ይጎውም በቅርጽ፤ በመጠን፤ በፊደላት፤ በቀለማትና በአጻጻፍ ዘዴ እንዲሁም በማሸጊያው ላይ ባለው የሴት ምስል የሚመሳሰሉ እና ሸማቹን ህብረተሰብ የሚያደናግሩ እና ሊያደናግሩ የሚችሉ መሆናቸውን በዚህም የተነሳ የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 8(1) ማንኛውም ነጋዴ በንግድ ስራ ሂደት ውስጥ ማንኛውም ሀቀኛ ያልሆነ፤ አሳሳች፤ ወይም አታላይነት ያለበት እና የተወዳዳሪን የንግድ ጥቅም የሚጎዳ ወይም ሊጎዳ የሚችል ድርጊት ለመፈጸም የማይችል ስለመሆኑ የደነገገውን እንዲሁም የአዋጁ አንቀጽ 8(2) ሀ እና ለ በሌላው ነጋዴ ወይም በነጋዴው ተግባራት በተለይም ነጋዴው ከሚያቀርበው የንግድ እቃ ወይም አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሁኔታ ማደናገርን ያስከተለ ወይም ሊያስከትል የሚችል ማንኛውም ድርጊት፤ የመረጃው ባለቤት ከሆነው ነጋዴ ፈቃድ ውጪ ከሀቀኛ የንግድ አሰራር ተጻራሪ በሆነ ሁኔታ የሌላውን መረጃ የማውጣት፤ የመያዝ ወይም የመጠቀም ማናቸውም ድርጊት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ሆነው እንደሚቆጠሩ የደነገጉትን በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር የፈጸሙ ስለመሆናቸው ማስረጃዎችን የመስማት፤ የመመርመር እና የመመዘን በህግ ስልጣን የተሰጠው የፌደራል የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍ/ቤት በስር የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የዳኝነት ችሎት ዘንድ የተሰሙትን የግራቀኙን ምስክሮች ቃል፤ ከሌሎች የሰነድ ማስረጃዎች በተጨማሪ ኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በቁ. አጠ28/662-11 በ26/12/08ዓ.ም፤ በቁ. አጠ28/119-660/08 በ26/12/08ዓ.ም እና በቁ. አጠ28/560-104/08 በ1/11/08ዓ.ም የጻፋቸውን ደብዳቤዎች በመመርመር እና በመመዘን እንዲሁም አከራካሪዎቹን EVEREST፤ ተስመስ ቆንጆ እና መልካማ የተሰኙትን የጸጉር ቀለም ምርቶች ማሸጊያዎች በኤግዚቢትነት በማስቀረብ እና በመመልከት የምርቶቹ ማሸጊያዎች ከስማቸው መለያየት በቀር በማሸጊያው መጠን፤ የፊደላት ቀለማት፤ የመደቦች ቀለማት፤ የማሸጊያው ቀለም፤ በማሸጊያው ላይ ያለው ፎቶ... ተመሳሳይነት ያለው እና አንዱን ከአንዱ ለመለየት የሚያስቸግሩ መሆናቸውን ግንዛቤ በመውሰድ፤ በተጨማሪም ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያለውን የጽ/ቤቱን የንግድ ምልክት እና ኢንዱስትሪ ንድፍ ልማት ጥበቃ ዳይሬክቶሬት የንግድ ምልክት ምርመራ ከፍተኛ ባለሙያ በማስቀረብ እና ምዝገባ ሳያደርግ የመጠቀም መብትን በሚመለከት የሙያ ምስክርነቱን እንዲሰጥ በማድረግ የሰጠውን የምስክርነት ቃል በመመርመር እና በመመዘን አመልካቾች ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር የፈጸሙ መሆናቸውን በፍሬነገር ደረጃ በማረጋገጥ ፤ የስር የዳኝነት ችሎቱ የተጠሪን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጠውን ውሳኔ በመሻር አመልካቾች ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ፈጽመዋል፤ ጥፋተኞች ናቸው በማለት የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አ/ቁ 813/2006 አንቀጽ

42(3) የአዋጁን አንቀጽ 8 ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም ነጋዴ የአመታዊ ሽያጭ ገቢውን ከ5% እስከ 10% የገንዘብ ቅጣት የሚቀጣ ስለመሆኑ በደነገገው መሰረት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኋላ እያንዳንዳቸው አመልካቾች የአመታዊ ሽያጭ ገቢያቸውን 5% የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጡ በማለት የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የአመልካቾች ድርጅቶች የሚጠቀሙት የጸጉር ቀለም ማሸጊያ ከኤቨረስት የጸጉር ቀለም ማሸጊያ በመጠን፤ በፊደላት፤ በቀለማት እና በአጻጻፍ ዘዴ፤ በመደቦች ቀለማት፤ በማሸጊያው ላይ ባረፈው የሴት ምስል... በጥቅሉ በቀለሞች ቅንጅት ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ በገበያ ውስጥ ሸማቾችን የሚያደናገርና ሊያደናገር ስለሚችል እንዳይጠቀሙ በማለት የሰጠውን ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማጽናት የሰጠውን ውሳኔ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የፌደራል ፍ/ቤቶች አ/ቁ 1234/2013 አንቀጽ 10(1) እና የኢፌዲሪ ህገመንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) ከደነገጉት አንጻር መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘውም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 00027 በ26/4/11ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 169910 በ30/4/12ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ የሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. በሰበር አጣሪ ችሎቱ በ15/11/12ዓ.ም የኢፌዲሪ የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን በቁጥር አ/ም/ክስ/አ/ዳ/199/2012 ጥር 26 ቀን 2012ዓ.ም ለጉምሩክ ኮሚሽን የሰጠው ትእዛዝ ከመፈጸም ለግዜው ታግዶ እንዲቆይ የሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
5. በዚህ የሰበር ችሎት በ12/12/12ዓ.ም በንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ዳኝነት ችሎት በመ.ቁ 000103 የተጀመረው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
6. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

ሠሰ/መ/ቁ. 190307

ህዳር 29 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- መዓዛ አሸናፊ

ሰለሞን አረዳ

ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች- የካ ክ/ከተማ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤት

ተጠሪዎች-

1. አቶ አበበ በቀለ
2. ሻለቃ ደሳለኝ ኃይሌ
3. ፱ አለቃ ሻሜ አስቻለዉ
4. ፱ አለቃ ኃ/ስላሴ አደራ
5. አቶ አሰፋ ክፍሌ
6. አቶ መንግስቱ ይታፈሩ
7. አቶ ሁንዴሳ ጎሌ
8. አስር አለቃ አራርሳ ደገፉ
9. አቶ ቡልቶ ስሜ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ፍርድ

ጉዳዩ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የሚቀርብ አቤቱታ የሚስተናገድበትን አግባብ የሚመለከት ነዉ። የጉዳዩም አመጣጥ ሲታይ ተጠሪዎች በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 01 አስተዳደር ጽ/ቤት ላይ ባቀረቡት ክስ ቤትና ንብረታቸዉን ያላግባብ አፍርሶ በመዉሰድ ጉዳት ያደረሰባቸዉ መሆኑን ጠቅሰዉ ካሳ እንዲከፈላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል። ጉዳዩን የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩን መርምሮ የተለያዩ ንብረቶች ዋጋ ብር 443,215.00 ንብረቱ ከተወሰደበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ተከሳሽ እንዲከፍል ዉሳኔ ሰጥቷል። ይህ ከሆነ በኋላ ተከሳሽ በነበረዉ በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 01 አስተዳደር ጽ/ቤት ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ ሊሻር ይገባዋል በማለት አመልካች አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የመቃወም አቤቱታ የሚቀርበዉ ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ዉሳኔ ያረፈዉ የክርክሩ ምክንያት በሆነዉ ንብረት ላይ ሆኖ በክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ ወገንን መብትና ጥቅም የሚነካ መሆኑ ሲረጋገጥ ሲሆን፣ በተያዘዉ ጉዳይ ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ ክርክሩን ማሰማት ባለመፈለጉ ምክንያት በሌለበት ዉሳኔ በተሰጠበት ሁኔታ አመልካች ተከሳሹ ክርክሩን አላሳወቀንም የሚል ምክንያት በመጥቀስ ዉሳኔዉ ይሻርልን በማለት ያቀረበዉ አቤቱታ የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉን አንቀጽ 358 ዓላማ ያገናዘበ አይደለም በማለት ዉድቅ አድርጎታል፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህንኑ በትዕዛዝ አጽንቶታል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚሁ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች የካቲት 02 ቀን 2012 ዓ.ም አዘጋጅቶ ያቀረበዉ አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአፈፃፀምና ማዘጋጃ አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋም በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 35/2004፣ አዋጅ ቁጥር 64/2011 ላይ በተመለከተዉ መሠረት አመልካች የከተማ አስተዳደሩ ነዋሪዎችን መብትና ጥቅም ለማስከበር በማናቸዉም ዳኝነት አካል ዘንድ የመቃወሚያ አቤቱታ የማቅረብ መብት አለዉ፤ ተከሳሽ የነበረዉ ተቋም እና አመልካች በአንድ መንግስታዊ መዋቅር ስር መገኘታቸዉ ብቻ አከራካሪዉን ጉዳይ በተመለከተ ተመሳሳይ ጥቅምን የሚወክሉ አካላት ናቸዉ ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ አይደለም፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 37502 ላይ በሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ይህንኑ አረጋግጧል፤ ይህ ሆኖ እያለ አመልካች በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት ያቀረበዉን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነዉ።

የሰበር አቤቱታዉ በአጣሪ ችሎት ተመርምሮም አመልካች የመቃወም አቤቱታ አቅርቦ የከተማ አስተዳደሩን መብትና ጥቅም ማስከበር እንደሚችል በህግ ስልጣን ተሰጥቶት እያለ አቤቱታዉን ዉድቅ በማድረግ የተሰጠዉን ዉሳኔ አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች በተደረገላቸዉ ጥሪ መሠረት ጥቅምት 27 ቀን 2013 ዓ.ም አዘጋጅተዉ በሰጡት መልስ አመልካች በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ያቀረበውን የመቃወም አቤቱታ ውድቅ በማድረግ በተሰጠ ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለመኖሩን ጠቅሰዉ ጸንቶ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታዉን ለማስቀረብ የተያዘዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካች በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት ላቀረበዉ የመቃወም አቤቱታ መሠረት ያደረገዉ ተጠሪዎች በስር ተከሳሽ በነበረዉ የየካ ክ/ከተማ ወረዳ 01 አስተዳደር ጽ/ቤት ላይ ያቀረቡትን ክስ መሠረት በማድረግ ብር 443,215.00 ከወለድ ጋር ለተጠሪዎች እንዲከፈል ፍርድ ቤቱ የሰጠዉ ዉሳኔ የአስተዳደሩ ነዋሪዎችን መብትና ጥቅም የሚነካ በመሆኑ እና አመልካች በፍርድ ቤት ክርክር አቅርቦ ይህን መብት ለማስከበር በህግ ስልጣን የተሰጠዉ መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ በእርግጥ አመልካች በፍርድ ቤት ክርክር አቅርቦ የክፍለ ከተማ አስተዳደሩንና የነዋሪዎችን መብትና ጥቅም የማስከበር ስልጣን በህግ የተሰጠዉ መሆኑ አላከራከረም፡፡ አከራካሪዉ እና የዚህን ችሎት እልባት የሚያሻዉ ጭብጥ አመልካች በፍርድ ቤት ክርክር በማድረግ የከተማዉ ነዋሪዎችን/የህዝብና የመንግስትን መብትና ጥቅም ለማስከበር ያለዉ መብት/ስልጣን ተመሳሳይ መብትና ጥቅምን ለማስከበር ስልጣንና ኃላፊነት ባለዉ ሌላ የከተማዉ አስተዳደር አካል ክርክር ተደርጎበት ዉሳኔ ያረፈበት ጉዳይ በድጋሚ እንዲታይ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የመቃወም አቤቱታ ለማቅረብ ያስችለዋል ወይ? የሚለዉ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ ፍርድ ቤቶች የቀረበላቸዉን የጽሑፍ ክርክር መርምረዉ፣ በቃል የሚቀርቡ ክርክሮችን አዳምጠዉ፣ ማስረጃዎችን መዝነዉ እና መሠረታዊ ህጎችን ተርጉመዉ ዉጤት ላይ መድረስ ይችሉ ዘንድ ሥርዓት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ክርክሮች የሚመሩባቸዉ ሥርዓት እና ደንቦች በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ተቀርጸዉ ስራ ላይ እንዲዉሉ የሚደረግበት ምክንያትም ይሄዉ ነዉ፡፡ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ የፍትሐብሔር ክርክሮችን አስመልክቶ የምንከተለዉ ስርዓት ሲሆን አጠቃላይ ዓላማዉም የፍትሐብሔር ጉዳዮችን ፍትሐዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ቀልጣፋ በሆነ ሁኔታ በመምራት ፍትሐዊ ዉሳኔ እንዲያገኙ ማስቻል ነዉ፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድም የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ የተለያዩ ደንቦች እና መርሆዎችን ይደነግጋል፡፡ ክርክሮች በዘፈቀደ ሳይሆን ሥርዓት ባለዉ ሁኔታ እንዲመሩ በማድረግ የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት መብትን፣ ብሎም ክርክሮች ባነሰ ወጪ እና ጊዜ መቋጫ እንዲያገኙ በማድረግ በፍርድ ቤት እና በተከራካሪ ወገኖች ላይ ያላግባብ የሚደርሰዉን የገንዘብ እና የጊዜ ብክነት በማስቀረት የክርክሩ ሂደትም ሆነ ዉጤቱ ፍትሐዊ እንዲሆን በማድረግ ረገድ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ የሚኖረዉ ሚና ከፍተኛ በመሆኑ በህጉ ላይ የተመለከቱትን ደንቦች እና መርሆዎች በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲዉሉ የማድረጉ አስፈላጊነትም የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡

በዚህ ረገድ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጋችን ዕዉቅና ከተሰጣቸዉ ደንቦች ዉስጥ አንዱ በከሳሽነት እና በተከሳሽነት ከተሰየሙት ወገኖች ዉጪ ያሉ ሦስተኛ ወገኖች የክርክር ተሳታፊ

የሚሆኑበትን ሁኔታ የሚመለከተዉ ደንብ ነዉ። በከሳሽነት እና በተከሳሽነት ከተሰየሙት ተከራካሪዎች ዉጭ የሆነ ሦስተኛ ወገን በክርክሩ ተሳታፊ ካልሆነ ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊ ዉሳኔ ለመስጠት የማይችል ዓይነት (indispensable party) ከሆነ በፍርድ ቤቱ አነሳሽነት ወይም መብት ባለዉ ሰዉ አቤቱታ አቅራቢነት፣ እንዲሁም ዉጤቱ መብቱን ሊነካ ይችላል በሚል ወገን (interested party) አቤቱታ አቅራቢነት ሦስተኛ ወገን በተጀመረ ክርክር ተሳታፊ የሚሆንበትን ሥርዓት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ ይዘረጋል (አንቀጽ 40 እና 41 ይመለከቷል)። ዓላማዉም የጉዳዩ አመራር ፍትሐዊ እንዲሆንና በሥርዓት እንዲከናወን ለማስቻል ሲባል ነዉ ተብሎ ይታመናል። ይሁንና በተለያዩ ምክንያቶች ከላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ክርክሩ በሂደት ላይ እያለ በክርክሩ ተሳታፊ ሆኖ መብቱን ማስከበር ይችል የነበረ ሰዉ ተሳታፊ ባልሆነበት መብቱን የሚነካ ዉሳኔ ሊሰጥ የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ስለሆነም በፍርድ ቤት ወይም በህግ የዳኝነት ስልጣን ባለዉ አካል በተሰጠ ዉሳኔ መብቱ ተነክቷል የሚል ሦስተኛ ወገን አቤቱታዉን በማቅረብ ዉሳኔዉን በመቃወም መብቱን ሊያስከብር የሚችልበትን ሥርዓት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 ላይ የተመለከተ ሲሆን፣ የድንጋጌዉ ሙሉ ይዘትም፡-

> በክርክሩ ዉስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባዉ ወይም በክርክሩ ዉስጥ ለመግባት የሚችልና እንዲሁም ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠዉ ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማናቸዉም ሰዉ ራሱ ወይም ጠበቃዉ ወይም ነገረ ፈጁ ተካፋይ በልሆነበት ክርክር የተሰጠዉ ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት መቃወሚያዉን ለማቅረብ ይችላል የሚል ሲሆን የዚህ ድንጋጌ የእንግሊዝኛዉ ቅጅም Any person who should or could or could have been a party to a suit and whose interests are affected by a judgment in the suit may, if he was not a party to such suit either in person or through a representative, file an opposition to such judgment at any time before such judgment is executed በማለት ይደነግጋል።

ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለዉም ክርክሩ መጀመሩን ሳይረዳና ሳያዉቅ በከሳሽነትና በተከሳሽነት በተሰየሙት ወገኖች መካከል የተደረገዉ ክርክር ተጠናቆ መወሰኑ እንኳ ቢታወቅ ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ ይረዳ ዘንድ በዉሳኔዉ መብቱ ተነክቷል የሚለዉ የክርክሩ ተካፋይ ያልነበረዉ ሰዉ ይህንኑ ዉሳኔ መቃወም የሚችል መሆኑን ነዉ። በተለይም በድንጋጌዉ ማናቸዉም ሰዉ ራሱ ወይም ጠበቃዉ ወይም ነገረ ፈጁ ተካፋይ ባልሆነበት ወይም በእንግሊዝኛዉ if he was not a party to such suit either in person or through a representative በሚል የተገለጸዉ የሚያሳየዉ ሦስተኛ ወገን የሚያቀርበዉ አቤቱታ ተቀባይነት የሚኖረዉ አቤቱታ አቅራቢዉ ለአቤቱታዉ በምክንያትነት የጠቀሰዉ ጉዳይ በቀደመዉ የክርክር ሂደት በመቃወም አመልካቹ በእራሱ ወይም በወኪሉ ወይም ተመሳሳይ መብትና ጥቅም ለማስከበር ስልጣን ባለዉ ሰዉ ክርክር ያልቀረበበት ሲሆን ነዉ። በሌላ አገላለጽ የመቃወም አመልካቹ ለአቤቱታዉ መሰረት ያደረገዉ ክርክሩ በሂደት ላይ በነበረበት ወቅት ጉዳዩ የሚያገባዉ ሰዉ የክርክሩ ተሳታፊ በሆነበት ታይቶ ዉሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ ከሆነ እና የመቃወም አመልካቹ ዉሳኔዉ '*በግል*' መብቱን የሚነካ መሆኑን በአቤቱታዉ

ካላሳየ በስተቀር አቤቱታዉ ተቀባይነት የሚኖረዉ አይደለም፡፡ የመቃወም አመልካች ለመቃወሚያዉ ምክንያት የሆኑትን ዝርዝር ምክንያቶች እና የሚጠይቀዉን ዳኝነት በአቤቱታዉ በዝርዝር መግለጽ እንዲሁም አቤቱታዉ ለሌሎች ተከራካሪ ወገኖች እንዲደርስ ተደርጎ ክርክሩም የሚሰማዉ የመጀመሪያዉ ክርክር በተሰማበት ሂደት ስለመሆኑ በህጉ አንቀጽ 359 እና 360 ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎችም የሚያሳዩት ለመቃወም አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ዉሳኔ የመቃወም አመልካቹን መብትና ጥቅም በግል የሚነካ መሆን ያለመሆኑ ጉዳይ የመቃወም አመልካቹ እና በክርክሩ ተሳታፊ የሆኑ ሌሎች ተከራካሪ ወገኖች የሚያቀርቡትን ክርክር እና ማስረጃ መሠረት በማድረግ ታይቶ ዉሳኔ የሚሰጥበት መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም በፍርድ ቤት ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠዉ የዳኝነት አካል የተሰጠን ዉሳኔን መቃወም የሚቻልበትን ሥርዓት አስመልክቶ በሥነ ሥርዓት ህጉ የተመለከተዉ ድንጋጌ በዉሳኔዉ መብቱ ‘በግል’ የተነካበት ሰዉ መቃወሚያዉን አቅርቦ መብቱን ለማስከበር እንዲችል እንጂ አንድን መብትና ጥቅም ለማስከበር የተለያዩ ሰዎች ተፈራርቀዉ የሚያቀርቡትን አቤቱታ ለማስተናገድ ያለመሆኑን መገንዘቡ ተገቢ ነዉ፡፡ ይልቁንም የመቃወም አቤቱታ የሚቀርብበትን ሁኔታ አስመልክቶ በድንጋጌዉ ላይ ከተመለከቱት መስፈርቶች አንፃር ሲታይ የድንጋጌዉ ዓይነተኛ ዓላማ በአንድ በኩል በከሳሽነት እና በተከሳሽነት በተሰየሙ ወገኖች መካከል በተደረገ ክርክር መነሻነት የተሰጠ ዉሳኔ መብቱን የሚነካበት ሰዉ ዉሳኔዉን በመቃወም ተከራክሮ መብቱን እንዲያስከብር በማድረግ ፍትሕ የማግኘት መብቱን በማረጋገጥ፣ በሌላ በኩል በከሳሽነት እና በተከሳሽነት በተሰየሙት ወገኖች መካከል ክርክር ተደርጎበት እልባት ባገኘ ጉዳይ ላይ በድጋሚ ክርክር በማቅረብ ተመሳሳይ መብትና ጥቅም ለማስከበር በሚል በሦስተኛ ወገን የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት እንዳይኖረዉ በማድረግ በአንድ ጉዳይ ላይ ወይም ተመሳሳይ መብትና ጥቅምን ለማስከበር በሚል ክርክሮች በተደጋጋሚ ሊቀርቡ የሚችሉበትን ሁኔታ በማስቀረት ክርክሮች በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጪ መቋጫ እንዲያገኙ ብሎም የፍርድ ሂደቱም ሆነ ዉጤቱ ተገማች እንዲሆን ማድረግ ነዉ፡፡ ስለሆነም በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የቀረበ የመቃወም አቤቱታ ተቀባይነት ያለዉ መሆን ያለመሆኑን አስመልክቶ በፍርድ ቤቶች የሚሰጠዉ ትርጉም ይህንኑ ያገናዘበ ሊሆን ይገባል፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ፣ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ፣ በተጠሪዎች ከሳሽነት በስር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት የተሰየመዉ የየካ ክ/ከተማ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት ሲሆን ለቀረበዉ ክስ ምክንያት የሆነዉም የተጠሪዎችን ቤት አፍርሶ ንብረታቸዉንም ያላግባብ በመዉሰድ ጉዳት ያደረሰባቸዉ መሆኑ ነዉ፡፡ ተጠሪዎች ይህ ድርጊት በስር ተከሳሽ መስሪያ ቤት የተፈጸመ እና ለጉዳቱ ኃላፊነቱን የሚወስደዉም መስሪያ ቤቱ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 33(3) እና 92 መሠረት አረጋግጠዉ ክስ ያቀረቡ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ በመሆኑም አመልካች በህጉ አንቀጽ 33(3) መሠረት በቀጥታ ተከሳሽ ሆኖ ሊቀርብ የሚችልበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ በተከሳሽነት የተሰየመዉ የወረዳዉ አስተዳደር ጽ/ቤት ቀርቦ ባለመከራከሩም ዉሳኔ በሌለበት ተሰጥቷል፡፡ አመልካች የህግ ሰዉነት የተሰጠዉ ተቋም በመሆኑ የህግ ሰዉነት የተሰጠዉ የመንግስት ወይም የግል ተቋም እንደሚያደርገዉ ሁሉ በቀጥታ ተቋሙን በሚመለከተዉ ጉዳይ ላይ በከሳሽነት፣ በተከሳሽነት፣ በጣልቃ ገብነት ወይም በመቃወሚያ አቤቱታ አቅራቢነት በፍርድ ቤት

ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠዉ የዳኝነት አካል ቀርቦ የክርክሩ ተሳታፊ በመሆን እንደ ተቋም ያለዉን መብት የማስከበር መብትም ግዴታም አለዉ። ይሁንና በተያዘዉ ጉዳይ ላይ አመልካች በተጠሪዎች የቀረበዉ ክስ ይመለከተኛል ወይም በህጉ አንቀጽ 33(3) መሠረት በተከሳሽነት መጠራት የነበረብኝ እኔ ነኝ የሚል ክርክር የለዉም፤ ይልቁንም በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 ያቀረብኩት የመቃወም አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረዉ ይገባል በማለት የሚከራከረዉ በስር ተከሳሽ የነበረዉ የየካ ክ/ከተማ ወረዳ 01 አስተዳደር እንዲከፍል የተወሰነበት ገንዘብ የክፍለ ከተማዉን ነዋሪዎች መብትና ጥቅም የሚነካ መሆኑን እና የክፍለ ከተማዉን ነዋሪዎች መብትና ጥቅምን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የመቃወም አቤቱታ አቅርቦ መከራከር እንዲችል በህግ ስልጣን የተሰጠዉ መሆኑን ነዉ። በእርግጥም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀጽ 5 የዐቃቤ ሕግ ቢሮ የተከተማዉ አስተዳደር መስሪያ ቤቶች የአስተዳደሩና የነዋሪዉ መብትና ጥቅም ወኪል ሆኖ እንደሚከራከር የተመለከተ ሲሆን፣ አመልካች የክፍለ ከተማ አቃቤ ሕግ ጽ/ቤት በመሆኑ ስለ ክፍለ ከተማ የሥልጣን አካላት ሥልጣንና ተግባር በሚደነግገዉ ክፍል አንቀጽ 78 መሠረት የክ/ከተማዉንና የክፍለ ከተማዉን ነዋሪዎችን መብትና ጥቅም በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ወኪል ሆኖ ለፍርድ ቤት ወይም በህግ የዳኝነት ስልጣን በተሰጠዉ አካል ቀርቦ ክርክር የማቅረብ ስልጣን ይኖረዋል።

በዚህም መሠረት በክፍለ ከተማዉ እና በስሩ የተደራጁት መስሪያ ቤቶች ከክፍለ ከተማዉ ነዋሪዎች መብትና ጥቅም ጋር በተያያዘ በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት ተሳታፊ በሆኑበት ጉዳይ ላይ አመልካች ወኪል ሆኖ መከራከር ይችላል። እንዲሁም እነዚህ መስሪያ ቤቶች የክርክሩ ተሳታፊ መሆን ሲገባቸዉ ተሳታፊ ባልሆኑበት የተሰጠ ዉሳኔ ሲኖር እና ዉሳኔዉም የክ/ከተማዉን ነዋሪዎች መብትና ጥቅም የሚጎዳ ከሆነ የሚመለከተዉን የክፍለ ከተማዉን መስሪያ ቤት በመወከል በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የመቃወም አቤቱታ ማቅረብ ይችላል። ይህ እንዳለ ሆኖ በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት ወይም በጣልቃ ገብነት ወይም በመቃወም አመልካችነት የክርክር ተሳታፊ ሲሆን መስሪያ ቤቱ በእራሱ የህግ ባለሙያ ወይም ነገረ ፈጅ ክርክሩን ማቅረብ የሚችልበት ሁኔታ እንዳለ የሚታወቅ ነዉ። ይህም የሚያሳየዉ በፍርድ ቤት ክርክር አድርጎ አንድን መብትና ጥቅም በማስከበር ሂደት አመልካች (ዐቃቤ ህግ) እና ጉዳዩ የሚመለከተዉ መስሪያ ቤት ተሳታፊ ሊሆኑ የሚችሉበት ዕድል መኖሩን ነዉ። ይህ ማለት ግን ሁለቱ ተቋማት አንድን መብትና ጥቅም ለማስከበር በጋራ ተከራካሪ በመሆን ይቀርባሉ ወይም ከሁለቱ አንደኛዉ መስሪያ ቤቱን በመወከል ክርክር አድርጎ ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ ሌላኛዉ ወገን ተመሳሳይ መብትን የማስከበር በህግ ስልጣን/መብት ስላለዉ ብቻ ዉሳኔዉን ለመቃወም አቤቱታ ያቀርባል ማለት እንዳልሆነ መገንዘቡ ተገቢ ነዉ። ይልቁንም የከተማዉን/የክፍለከተማዉን ነዋሪዎች መብትና ጥቅም ከማስከበር ጋር በተያያዘ ክርክር ሲኖር የሚመለከተዉን መስሪያ ቤት ወክሎ ክርክሩን ማቅረብ የሚችል አካል ከአቃቤ ህግ እና ከመስሪያ ቤቱ የህግ ባለሙያ ማን መሆን እንዳለበት የአቃቤ ህግ መስሪያ ቤት እና መስሪያ ቤቱ ተነጋግረዉ የሚወስኑት ነዉ። በዚህ መልኩ ተነጋግረዉ ጉዳዩን አቃቤ ህግ እንዲይዝ ከተወሰነ ሌላ የተለየ ዉክልና እንዲያቀርብ ማድረግ ሳያስፈልግ ጉዳዩን የሚመለከተዉ ፍርድ ቤት አቃቤ ህግ የሚያቀርበዉን ክርክር መቀበል እንዲችል

የተመለከተ ድንጋጌ ነዉ። ከዚህ ዉጪ ዐቃቤ ህግ ጉዳዩ የከተማዉ ነዋሪዎችን መብትና ጥቅም የሚመለከት በመሆኑ ብቻ የሚመለከተዉ መስሪያ ቤት የክርክሩ ተሳታፊ በመሆን በተደረገ ክርክር መሠረት ዉሳኔ ያገኘዉን መብትና ጥቅም ለማስከበር ስልጣን አለኝ በሚል ብቻ ተመሳሳይ መብትና ጥቅም ማስከበርን መሠረት ያደረገ አቤቱታ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የመቃወም አቤቱታ ማቅረብ አይችልም። ዐቃቤ ህግ ክርክር በማቅረብ የነዋሪዎችን መብትና ጥቅም ማስከበር እንደሚችል ስልጣን የሚሰጠዉ ከላይ የተመለከተዉ የአዋጁ ድንጋጌ አተገባበርም ይህን እዉነታ ባገናዘበ መልኩ ሊሆን ይገባል።

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት ክሱ የቀረበበት የየካ ክፍለከተማ ወረዳ 1 አስተዳደር ጽ/ቤት ለፍርድ ቤት ቀርቦ ባለመከራከሩ በሌለበት ጉዳዩ ታይቶ ዉሳኔ የተሰጠ ሲሆን፣ ክርክር ሳይደረግ የተሰጠ ዉሳኔ የክፍለ ከተማዉን ነዋሪዎች መብትና ጥቅም የሚጎዳ ነዉ የሚል ከሆነ እና ተከሳሹ መስሪያ ቤት ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ ክርክሩን ሊያቀርብ ያልቻለበት በቂ እና አሳማኝ ምክንያት አለዉ የሚል ከሆነ ከተከሳሽ መስሪያ ቤት ጋር በመነጋገር አቤቱታዉ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 78 መሠረት ማቅረብ ይችል ነበር። አመልካች ይህን ሳያደርግ እና በዚህም ምክንያት በተከሳሽነት የተሰየመዉ መስሪያ ቤት በሌለበት ክርክሩ እንዲቀጥል ተደርጎ የተሰጠ ዉሳኔ ሥነ ሥርዓታዊ ነዉ ተብሎ በሚገመትበት ሁኔታ ዉሳኔዉን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት ያቀረበዉ አቤቱታ ተቀባይነት ያለዉ አይደለም።

ሲጠቃለል በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የሚቀርብ አቤቱታ የክርክሩ ተሳታፊ ባልሆነበት በተደረገ ክርክር የተሰጠ ዉሳኔ መብቱን የሚነካበት ሦስተኛ ወገን የመቃወም አቤቱታዉን አቅርቦ የክርክሩ ተሳታፊ በመሆን ተከራክሮ መብቱን ማስከበር እንዲችል ታስቦ የተዘረጋ ነዉ። በመሆኑም አቃቤ ህግ ወኪል ሆኖ ሊከራከር የሚችልበት መብትና ጥቅም ክርክር በማድረግ ተመሳሳይ መብትና ጥቅም ለማስከበር ስልጣን ባለዉ ጉዳዩ በሚመለከተዉ መስሪያ ቤት ክርክር ቀርቦበት ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ አቃቤ ህግ ዉሳኔዉን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት ሊቃወም የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም። በዚህ አግባብ ለመወሰን ለክርክሩ ምክንያት ከሆነዉ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሁለቱም (ዐቃቤ ህግ እና ጉዳዩ የሚመለከተዉ መስሪያ ቤት) የሚያስከብሩት መብትና ጥቅም አንድ እስከሆነ ድረስ የአቃቤ ህግ መስሪያ ቤት እና በክርክሩ በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት የተሰየመ መስሪያ ቤት የየራሳቸዉ ስልጣንና ኃላፊነት ያላቸዉ መሆን ያለመሆኑ ጉዳይ በጭብጥነት ሊያዝ የሚገባዉ ጉዳይም አይደለም። ስለሆነም ከዚህ ጋር በተያያዘ አመልካች የሚያቀርበዉ ክርክር ተገቢነት የለዉም። በእርግጥ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 37502 በቅጽ 8 ላይ በታተመዉ ዉሳኔ ሁለት ራሳቸዉን የቻሉና የህግ ሰዉነት ያላቸዉ ተቋሞች በአንድ የመንግስት መዋቅር ሥር የሚገኙ በመሆናቸዉ ብቻ ተመሳሳይ ጥቅምን የሚወክሉ አካላት ናቸዉ ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ አለመሆኑን በመጥቀስ ከከተማ አስተዳደሩ አንዱ አካል የክርክሩ ተሳታፊ በሆነበት ክርክር ተደርጎ ዉሳኔ መሰጠቱ የአመልካች መስሪያ ቤት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የመቃወም አቤቱታ እንዳያቀርብ የሚከለክል አይደለም የሚል ይዘት ያለዉ የህግ ትርጉም ሰጥቷል። ይሁንና ይህ የህግ ትርጉም በሦስተኛ ወገን አቤቱታ የሚቀርብበትን

ሁኔታ አስመልክቶ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 ላይ የተመለከተዉን ድንጋጌ ዓላማ ያገናዘበ ባለመሆኑ ሊለወጥ የሚገባዉ የህግ ትርጉም ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የአመልካችን የመቃወም አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 210662 ላይ ሐምሌ 02 ቀን 2011 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 181686 ላይ ታህሳስ 24 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሰረት ጸንተዋል፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 37502 (ቅጽ 8 ላይ እንደታተመዉ) የሰጠዉ የህግ ትርጉም ተለዉጧል፡፡
3. የአዲስ አበባ ከተማ ዐቃቤ ህግ ቢሮ (በየደረጃዉ ያሉ ዐቃቤ ህግ ጽ/ቤቶችን ይጨምራል) ወኪል ሆኖ ክርክር በማቅረብ የነዋሪዉን መብትና ጥቅም እንዲያስከብር በአስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጁ ስልጣን የተሰጠዉ ቢሆንም፣ ይህ ስልጣኑ ብቻዉን ተመሳሳይ መብትና ጥቅምን ለማስከበር ስልጣን ያለዉ የሚመለከተዉ የከተማዉ አስተዳደር አካል የክርክሩ ተሳታፊ በሆነበት ታይቶ ዉሳኔ የተሰጠበትን ጉዳይ መሠረት አድርጎ እንደገና ክርክር ለማድረግ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የመቃወም አቤቱታ እንዲያቀርብ ምክንያት አይሆንም፡፡
4. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
5. የሰበር አጣሪ ችሎት የካቲት 17 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማ/አ **የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት**



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰበር መ/ቁጥር 191095

ሐምሌ29/2013 **ዓም**

ዳኞች፡- **እትመት አሰፋ**

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱአለም

አመልካች/ቾች፡- **አቶ ከተማ ኑኔ**

ተጠሪ/ዎች፡- **ወ/ሮ መረጠች ለማ**

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ በሊዝ ውል የተገኘ ይዞታ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ህዝቦች እና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ/14021 ላይ ታህሳስ 17/2012 ዓም በዋለው ችሎት የስር ፍቤቶችን ውሳኔ የሻረበትን የመጨረሻ ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የክርክሩ ስረ ነገር አመጣጥ እንዲህ ነው፡፡ አቶ ባላይ ላጲሶ የተባሉት የአሁን ተጠሪ የቀድሞ ባለቤት ከተጠሪ ጋር የነበራቸውን ጋብቻ በፍቺ መፍረሱ ተከትሎ ቦታ እና አዋሳኙ በክስ አቤቱታው ውስጥ የተዘረዘረውን እና ጋብቻቸው ፀንቶ በነበረበት ወቅት በሊዝ ውል ያገኙትን 4000 ካሬ ሜትር ይዞታ ለመካፈል በሆሳና ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡ የአሁን ተጠሪም ቀርበው ንብረቱ የጋራ በመሆኑ ቢካፈሉ አልቃወምም የሚል መልስ በመስጠታቸው የተጠቀሰው ይዞታ የጋራ ንብረት መሆኑ ተጠቅሶ እንዲካፈሉ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ይህ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ከሆነ በኋላ የአሁን አመልካች ባልና ሚስቱ እንዲካፈሉ ተብሎ ውሳኔ ያረፈበት ይዞታ ተጠሪና ባለቤታቸው በጋብቻ አብረው በነበሩበት ወቅት ተጠሪ ለባለቤታቸው በሰጡት ውክልና መሰረት መጋቢት 29/2008 ዓም በተደረገ የሽያጭ ውል ያስተላለፉላቸው መሆኑን፤ በውሉ መሰረት ጉዳዩ በሚመለከተው አስተዳደር ክፍል ቀርቦ ተገቢውን ክፍያ ፈፅመው በስም ዝውውር ደረጃ ላይ ያለ መሆኑን በመግለፅ ንብረቱን ባልና ሚስቱ በሽያጭ ያስተላለፉት በመሆኑ እንዲካፈሉ የተሰጠው ውሳኔ ሊሻር ይገባል በሚል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 መሰረት የመቃወም አቤቱታ ያቀርባሉ፡፡

በዚሁ የመቃወም አቤቱታ ላይ ተጠሪ እና ባለቤታቸው መልስ እንዲሰጡ በታዘዘው መሰረት ሁለቱም ቀርበው የተጠሪ ባለቤት ይዞታውን በሽያጭ ሲያስተላልፍ ይህንን ለማድረግ የሚያስችላቸው ተገቢን የውክልና ስልጣን የሌላቸው በመሆኑ ውሉ ፈራሽ ነው፤ የሽያጭ ውሉም በአዋጅ ቁጥር 721/2004 የተመለከተውን የሊዝ ውል ማስተላለፊያ ስርአትን ያልተከተለ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ለክርክር ምክንያት የሆነው የሊዝ ይዞታ የተሸጠበት ውል በተፈረመበት መጋቢት 29/2008 ዓም የአሁን ተጠሪ ባለቤት ውክልና አለኝ ብለው በውሉ የፈረሙ ቢሆንም የነበራቸው ውክልና ውሉን ለመፈረም የሚያስችላቸው ያልነበረ መሆኑን፤ በወቅቱ የአሁን ተጠሪ ወልደው ተኝተው የነበረ በመሆኑ እና የሽያጭ ውሉም ለክፍሉ አስተዳደር ከቀረበ በኋላ የተጠሪ ባለቤት ተገቢ ውክልና የላቸውም በመባሉ ምክንያት ተጠሪ ሚያዚያ 03/2008 ዓም ሙሉ ውክልና ለባለቤታቸው ሰጥተው አስተዳደራዊ ሂደቱ የቀጠለ መሆኑን፤ በዚሁ ተጠሪ እና ባለቤታቸው በሽያጭ ውሉ ተጎድተናል በማለት ይዞታው ቀድሞ ከተሸጠበት ዋጋ በተጨማሪ ብር 100.000(አንድ መቶ ሺህ) ከአመልካች የተቀበሉ መሆኑን፤ አመልካችም ይዞታውን እና ይዞታውን የሚመለከቱ ሰነዶችን በሙሉ ተረክበው በእጃቸው አድርገው የሚገኙ መሆኑን እና በአስተዳደር አካል ተጀምሮ የነበረው የስም ዝውውር ሂደትም በአሁን ተጠሪ ተቃውሞ የቆመ ስለመሆኑ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ ማረጋገጡን ጠቅሶ የሽያጭ ውሉ እና የውክልና ውሉ ፊትና ኋላ ቢሆኑም ተጠሪ ስለ ሽያጩ ሙሉ እውቀት እና ፈቃድ የነበራቸው በመሆኑ የአመልካች መብት የሚያሳጣ አይደለም፤ የሽያጭ ውሉ በሊዝ አዋጁ መሰረት አልተከናወነም የሚባል ከሆነም ድርጊቱን መቃወም እና ማስቆም የሚገባው የሚመለከተው አስተዳደር አካል ነው፤ ሆኖም የክፍሉ መሬት አስተዳደር የሽያጭ ውሉን ተቀብሎ እና አስፈላጊውን ክፍያ አስፈፅሞ ሂደቱን የጀመረ በመሆኑ ከተጠሪ እና ባለቤታቸው በኩል የቀረበው ክርክር ከቅን ልቦና ውጭ የቀረበ ነው፤ ቀደም ሲል ተጠሪ እና ባለቤታቸው እንዲካፈሉ የተባለው ይዞታው በሽያጭ ለአሁን አመልካች ባስተላለፉት ይዞታ ላይ የተሰጠ ውሳኔ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ

ቁጥር 360(2) መሰረት ሽረዋል። በዚሁ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የሃድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት ይግባኙን ዘግቷል።

የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ የግራቀኙ ክርክር ከሰማ በኃላ በሰጠው ውሳኔ በሊዝ ውል በተገኘ ይዞታ ላይ ያለ የሊዝ መብት ሊተላለፍ የሚችለው በሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 24(2) ስር በተመለከተው አግባብ ግልጽ የሽያጭ ውል ከአሁን ተጠሪ እና ባለቤት ተላልፎልኛል ቢሉም ውሉ በአዋጁ በተመለከተው ሥርዓት የተፈፀመ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ነገር የለም፤ ውሉም የተደረገው በባዶ መሬት ላይ ሲሆን ባዶ መሬትን መሸጥ በህገ መንግስቱ የተከለከለ በመሆኑ ውሉ ህጋዊ ውጤት የለውም ሲል የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ሽሯል።

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው። አመልካች በጠበቃቸው በኩል የካቲት 13/2012 በተጻፈ ዘጠኝ ገፅ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል። መሰረታዊ ይዘቱም የአሁን ተጠሪ ባለቤታቸው ያለህጋዊ ውክልና ለክሱ ምክንያት የሆነውን የሊዝ ይዞታ መብትን አስመልክቶ ከአሁን አመልካች ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውሉ እዲፈርስላቸው በሃድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ15511 ላይ ክስ አቅርበው ያለፍርድ ቤቱ ፈቃድ ክሱን ያነሱ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 279 እና 5 መሰረት የውሉን ህጋዊነት አስመልክቶ ድጋሚ ክርክር ሊያቀርቡ አይችሉም አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነውን ይዞታ እላዩ ላይ ከነበረው ጅምር ቤት ጋር ገዝተው ግንባታውን ያፈረሱ እንጂ ባዶ መሬት አልገዙም፣ የክፍሉ አስተዳደርም የሽያጭ ውሉን ህጋዊነት አረጋግጦ እላዩ ላይ የነበረውን ግንባታ ግምት በማስላት አመልካች መክፈል የሚገባቸውን ክፍያ አሳውቆ በማስከፈል ከአመልካች ጋር የሊዝ ውል የፈረመ በመሆኑ ውሉ ህጋዊ ነው፤ስልጣን ያላቸው የስር ፍርድ ቤቶችም ይኽው ለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጠው ወስነው እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በህግ ባልተሰጠው ስልጣን ማስረጃን መዝኖ ውሳኔዎቹን መሻሩ የኢ/ፌ/ድ/ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 80/3/ለ/ እና ይኽው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 32220 ላይ የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተላለፈ ነው፤ የሽያጭ ውሉም የተደረገው በሊዝ ውል በተገኘ መብት ላይ በመሆኑ እና ይህም በህግ መንግስቱ አንቀፅ 40/6/ እና በሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀፅ 14 መሰረት የተፈቀደ ሆኖ እያለ ውሉ ከመነሻው ፈራሽና እንዳልተደረገ ይቆጠራል ተብሎ መወሰኑ አግባብ አይደለም፤ ስልጣን ያለው የክፍሉ አስተዳዳር ውሉን ተቀብሎ የመዘገበ በመሆኑ ሽያጩ በአዋጁ መሰረት አልተደረገም ሊባል አይችልም፤ በአዋጁ መሰረት አልተደረገም ቢባል እንኳን ውሉ ጉድለት ያለበት ውል ነው ከሚባል በቀር ከመነሻው እንዳልተደረገ የሚያስቆጥር ባለመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የውሉ ህጋዊነት የተረዳበት እና የተረጎመበት መንገድ

የፍ/ብ/ህ/ቁ 1716፣1717 እና 1718 እንዲሁም ይኸው ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ ጉዳይ አስመልክቶ በመ/ቁ 43226 ላይ የሰጠው አስገዳጁ የህግ ትርጉም የተከተለ አይደለም፤ የሽያጭ ውሉ ጉድለት የለበትም እንጂ ቢኖርበት እንኳን በአዋጁ መሰረት አልተደረገም የሚለውን መቃወሚያ ማቅረብ ያለበት እና የሚችለው ጉዳዩ የሚመለከተው የክፍሉ አስተዳደር እንጂ መብታቸውን በሽያጭ ያስተላለፉት ተጠሪ አይደሉም፤ ውሉ ከተደረገ ከአራት ዓመት በላይ በመሆኑ እና ከውሉ በኋላም አመልካች በቦታው ላይ ከፍተኛ መሻሻል ያደረጉ በመሆኑ ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት ሊመለሱ የሚችሉበት ሁኔታ የለም፤ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ውሉ ህጋዊ አይደለም ውሉ ከመወሰን ውጭ በውጤቱ ላይ ውሳኔ ያልሰጠ እንዲሁም ከውሉ በኋላ በቦታው ላይ ስለተደረገው መሻሻል ሳይወሰን ማለፉ ከህግ አግባብ ውጭ በመሆኑ የሰበር ሰሚ ችሎቱ ውሳኔ ውድቅ ተደርጎ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሊፀና ይገባል የሚል ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የክልሉ የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ የኢ/ፌ/ድ/ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 80/3/ለ/፣ 40 /6/፣ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀፅ 14/2/ ድንጋጌዎችን በተገቢው ያገናዘበ ስለመሆኑ ግራቀኙ በተገኙበት በዚህ ችሎት እንዲመረመር በአጣሪ ችሎት በመታዘዙ ተጠሪ የፅሁፍ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል።

በዚህ መሰረት ተጠሪ በጠበቃቸው አማካኝነት ጥቅምት 13/2013 ዓ.ም የተፃፈ ሁለት ገፅ መልስ አቅርበዋል። ፍሬ ቃሉም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሊዝ ውል የተገኘ ባዶ መሬት ሽያጭ የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀፅ 24/2/ እና /3/ ድንጋጌን የተከተለ መሆን ስላለመሆኑ በጭብጥነት ይዞ በመመርመር ውሉ በአዋጁ መሰረት ያልተደረገ መሆኑን አረጋግጦ የወሰነ በመሆኑ ውሳኔው የሚነቀፍ አይደለም፤ በሽያጭ ውሉም የተላለፈው ባዶ መሬት በመሆኑ ከህግ መንግስቱ አንቀፅ 40/6/ ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም፤ ይልቁንም ውሉ በባዶ መሬት ላይ የተደረገ እና የሊዝ አዋጁንም ድንጋጌ ያልተከተለ ስለመሆኑ ተረጋግጦ የተወሰነ በመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ የሚነቀፍበት መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ሊፀና ይገባል የሚል ነው። የአመልካች ጠበቃም ህዳር 10/2013 በተፃፈ የመልስ መልስ የሰበር ቅሬታቸውን የሚያጠናክር መከራከሪያ በማከል የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ሊሻር ይገባል በማለት ሞግተዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ማስቀረቢያ ነጥብ አኳያ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል።

በመሠረቱ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራልም ሆነ የክልል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን የሚመነጨው ከፌደራሉ ህገ መንግስት ስለመሆኑ የህገ መንግስቱ አንቀፅ 78 ይደነግጋል። በህገ መንግስት አንቀፅ 80/3/ መሠረት በፌደራልም ሆነ በክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሥር ለማቋቋም የሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ውስጥ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞ ሲገኝ በሰበር አይቶ የማረም ሥልጣን ነው። ህገ መንግስቱን መሠረት አድርገው በፌደራልም ሆነ በየክልሉ የታወጁት የፍር ድ ቤት ማቋቋሚያ

አዋጆችም በህግ መንግስቱ በተገለፀው አግባብ ተመሳሳይ የዳኝነት ስልጣን ለሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡ ለመሆኑ ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10 ድንጋጌ እንዲሁም አሁን ለቀረበው ጉዳይ አግባብነት ካለው ከተሻሻለው ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ 43/1994 አንቀጽ 5/3 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

በፌዴራልም ሆነ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሥር የተቋቋመው የሰበር ሰሚ ችሎት በህገ መንግስቱ እና ህገ መንግስቱን ተከትለው በወጡ አዋጆች የተሰጣቸው የሰበር ሰሚነት ስልጣን ተግባራዊ ሲያደርጉ ፍሬ ነገርን በተመለከተ በዋናነት መነሻ የሚያደርጉት ስልጣን ባላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች በማስረጃ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ነው፡፡ እናም የሰበር ችሎት ቀዳሚ ተግባር የሚሆነው የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ በማስረጃ የተረጋገጠውን መሠረት በማድረግ በሰጡት የህግ ትርጉም ውስጥ የፈፀሙት መሠረታዊ የህግ ስህተት ካለ ለይቶ በህግ አግባብ ማረም ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ ሰበር ሰሚ ችሎት በሥር ፍርድ ቤት ተመዝኖ አቋም የተያዘበትን ጉዳይ በተመለከተ በዝምታ በማለፍ አልያም በራሱ ማስረጃውን መዝኖ ውሳኔ ለ መስጠት የሚያስችለው የህግ አግባብ የለም፡፡

ይህ ማለት ግን የበታች ፍርድ ቤቶች የቀረቡላቸውን ማስረጃዎችን ይዘት በአግባቡ ሳይመለከቱ ሲቀሩ፤ ወይም በማስረጃ የተረጋገጠው እና ፍርድ ቤቱ የደረሰበት ድምዳሜ የተለያዩ ሆኖ በተገኝ ጊዜ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንን መሰል ጉዳይ ማየት አይችልም ማለት አይደለም፡፡ የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ጉዳዩ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ሳይሆን ማስረጃን እና ህግን በማዋሃድ ረገድ የሚፈፀም ግድፈት በመሆኑ ጉዳዩ የማስረጃ ሳይሆን የህግ ነጥብ በመሆኑ ስልጣን ያለው የሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን አይቶ ከማረም የሚከለክለው አይደለም፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ወሳኔ ለመሻር የጠቀሰው ሁለት ምክንያቶችን ነው፡፡ አንዱ ውሉ በራሱ በባደ መሬት ላይ የተደረገ በመሆኑ ከመነሻውም ውሉ ኢ-ህገ መንግስታዊ ነው የሚል ሲሆን ሌላው ደግሞ የሽያጭ ውሉ በሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀፅ 24/2/ እና /3/ መሠረት አልተደረገም የሚል ነው፡፡ እንግዲህ በሥር ፍርድ ቤቶች ከተደረገው የግራ ቀኙ ክርክር መረዳት እንደሚቻለው የውሉ ጉዳይ በሊዝ ውል የተገኘ መብትን በሽያጭ ማስተላለፍ ስለመሆኑ ከመገለፁ ውጭ በሽያጭ የተላለፈው ባዶ መሬት ይሁን

አልያም ግንባታ ያለበት መሆኑ የክርክር ጭብጥ አልነበረም ፡፡ የሽያጭ ውሉ በባዶ መሬት ላይ የተደረገ ነው የሚለው ጉዳይ የተነሳው በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ነው፡፡ ከወሉ ህጋዊነት አኳያ በአሁን ተጠሪ አና ባለቤታቸው ሲቀርቡ የነበረው መከራከሪያዋ ውሉ በባልና ሚስት የጋራ መብት ላይ ያለተጠሪ ፈቃድ እና ህጋዊ ውክልና የተደረገ ነው፤ እንዲሁም በሊዝ አዋጁ መሠረት የተደረገ አይደለም የሚል ነው፡ ከዚህ ባለፈ ውሉ በባዶ መሬት ላይ የተደረገ ነው በሚል የቀረበ ክርክር የለም፡፡

በእርግጥ በተዋዋይ ወገኖች መካከል የመዋዋል ነፃነት ከሚገደብባቸው ልዩ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ የውሉ ጉዳይ ህጋዊ መሆን እንደ ሆነ እና በውጤት ደረጃም ለህግ ተቃራኒ የሆነ ውል ፈራሽ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ/1711 እና 1716 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ አንፃር በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግንት አንቀፅ 40/3/ የገጠርም ሆነ ከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት መብት

የመንግስትና የህዝብ ብቻ መሆኑን እና መሬት የማይሸጥ የማይለዋጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት መሆኑ ተደንግጓል። እናም በፍርድ ቤት በቀረበ ክርክር በተከራካሪ ወገኖች የቀረበው ውል የውሉ ጉዳይ የህገ መንግስቱን እና የመሠረታዊ ህግ መንግስታዊ ህግ ድንጋጌን የሚቃረን መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ስለ ውሉ ህጋዊነት ከተከራካሪዎች የሚቀርብ መቃወሚያን መጠበቅ ሳያስፈልግ ፍርድ ቤት በራሱ ጊዜ አንስቶ መመርመር ያለበት ጉዳይ ነው። ከዚህ አኳያ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሽያጭ ውሉን ህጋዊነት አንስቶ መመርመሩ የሚነቀፍ ተግባር አይደለም።

ሆኖም በግራ ቀኙ መካከል ተደረገ የተባለው ውል የውሉ ጉዳይ በእርግጥም በህግ የተከለከለ ስለመሆኑ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው። እንግዲህ ግራ ቀኙ የሚከራከሩት የሊዝ መብት ከማስተላለፍ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ጉዳዩ የሚመለከተው የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 ነው። በዚህ አዋጅ መሠረት የሊዝ ባለመብት የሆነ ሰው በአዋጁ በተመለከተው ሥርዓት መሠረት የሊዝ መብቱን በሽያጭ ለማስተላለፍ አልያም በዋስትና ለማስያዝ የሚችል ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 24 ተመልክቷል። መብቱም ግንባታ ከመጀመሩ አልያም በግማሽ ከማጠናቀቁ በፊት ሊተላለፍ የሚችል ስለመሆኑ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ 2 ሥር ተመልክቷል። በእርግጥ በዚህ መልኩ የሚተላለፈው የሊዝ መብት አግባብ ባለው አካል በሚደረግ ቁጥጥር መፈፀም የሚገባው ስለመሆኑ ተመልክቷል። እናም ከአፈፃፀም አኳያ የተቀመጠው ሥርዓት እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የሊዝ በላመብት የሆነው የሊዝ መብቱን ግንባታ ከመጀመሩ በፊትም ቢሆንም ማስተላለፍ እንደሚችል የተፈቀደ በመሆኑ የዉሉ ጉዳይ በህግ የተከለከለ ነው ሊባል የሚችል አይደለም። ከዚህ አንፃር የክልሉ ሰበር ሲሚ ችሎት ጉዳዩን የተረዳበት መንገድ በሊዝ ባለመብቶች የተረጋገጠውን የመብት አድማስ ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም።

የሽያጭ ውሉ በሊዝ አዋጁ በተመለከተው አግባብ አልተፈፀመም የተባለውን በተመለከተ ጉዳዩ በመጀመሪያ የዳኝነት ሥልጣኑ የተመለከተው የከተማው መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሉ ጉዳዩ ለሚመለከተው ለክፍሉ አስተዳደር ቀርቦ እና አስተዳደሩም ውሉን ተቀብሎ በውሉ መሠረት አስፈላጊ ክፍያዎችን አስከፍሎ በስም ዝውውር ሂደት ላይ እያለ የአሁን ተጠሪ ተቃውሞ በማቅረባቸው ምክንያት ሂደቱ የቆመ ስለመሆኑ ማረጋገጡን በፍርድ ሀተታው ውስጥ በግልፅ አስፍሯል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው በሊዝ ውል በተገኘ ይዞታ ላይ ግንባታ ከመጀመሩ አልያም ግንባታው በግማሽ ከመጠናቀቁ በፊት የመብት ማስተላለፍ ሂደቱን የመከታተል እና የመቆጣጠር ሥልጣን የተሰጠው አስተዳደር ክፍል በውሉ ይዘትና አፈፃፀም ላይ ተቃውሞ የሌው መሆኑን ነው። ከውሉ ሂደት እና አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ጉድለት ቢኖር እንኳን ውሉን አልቀበልም ብሎ የመመለስ አልያም አስፈላጊው ቅድመ ሁኔታ ተሟልቶ እንዲቀርብ የማዘዝ ስልጣን ያለው ይኸው አካል። ሆኖም ከዚህ አኳያ ውሉ የተነቀፈ ስለመሆኑ የቀረበ ክርክርም ሆነ የተረጋገጠ ነገር የለም። ይህ ከሆነ ደግሞ ውሉ በአዋጁ በተመለከተው ሥርዓት አልተፈፀመም የሚባልበት ምክንያት የለም። የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ቢሆን የሽያጭ ውሉ በሊዝ አዋጁ በተመለተው አግባብ አልተከናወነም ከማለት በዘለለ የሥር ፍርድ ቤቶች ከዚህ አንፃር በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጡትን እና ያን መሠረት አድርገው የደረሱበትን ድምዳሜ ያልተቀበሉበትን ምክንያት አልገለፀም። ወሉ በአዋጅ መሠረት አልተፈፀመም በሚል በጥቅሉ ከመገለፁ ውጭም ምን ማሚላት ሲገባ እንዳልተፈፀመ በግልፅ ተጠቅሶ የተሰጠ ትችት የለም። ይህ በሌለበት የሥር ፍርድ ቤቶች ወሳኔን መሻሩ

በእርግጥም የሚነቀፍ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ ተከታዩ ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ ተሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

1. የደቡብ ብሔር ፣ ብሔረሰቦች እና ህዝባች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 14021 ላይ ታህሳስ 17/2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሆሳዕና ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 25402 ላይ ሰኔ 28/2011 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔን በማፅናት የሃድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 20174 ላይ መስከረም 13/2012 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1. የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

<u>የልዩነት ሃሳብ</u>

ስማችን በተቁ. 1 እና 3 ላይ የተገለጸው ዳኞች አብላጫው ድምጽ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ ለመሻር በሰጠው ምክንያት ስላልተስማማን የሀሳብ ልዩነታችንን እንደሚከተለው አስፍረናል፡፡

ከመዝገቡ ይዘት በግልጽ መገንዘብ እንደሚቻለው የተጠሪ የቀድሞ ባለቤት የነበሩት አቶ በላይ ላጲሶ ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ ጸንቶ በነበረበት አከራካሪ የሆነውን ንብረት ለአሁን አመልካች ሸጡ የተባሉት መጋቢት 29 ቀን 2008 ዓ.ም. ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ደግሞ ግለሰቡ ጠቅላላ የአስተዳደር የውክልና ስልጣን የነበራቸው ቢሆንም ንብረቱን በሽያጭ ለማስተላለፍ የሚያስችል የውክልና ስልጣን እንዳልነበራቸው በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ የተጠሪ ባለቤት የነበሩት ግለሰብ ንብረቱን በሽያጭ ለአሁን አመልካች ባስተላለፉበት ጊዜ የውክልና ስልጣን ካልነበራቸው ከመነሻውም ቢሆን ስልጣን ሳይኖራቸው የተደረገ የሽያጭ ውል በመሆኑ ውሉ ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም፡፡ ስለሆነም ይህን ህጋዊ ውጤት የሌለውን የሽያጭ ውል በመያዝ ስመ ሀብቱን ለማዘዋወር በሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ጽ/ቤት ሲቀርቡ ግለሰቡ ይህንኑ ለማድረግ የሚያስችል የውክልና ስልጣን የሌላቸው መሆኑ ተነግሮአቸው የሽያጭ ውሉ ከተደረገ በኋላ ሚያዝያ 03 ቀን 2008 ዓ.ም. የተሰጣቸው የውክልና ስልጣን ወደኋላ ተመልሶ አስቀድሞ መጋቢት 29 ቀን 2008 ዓ.ም. የተደረገውን የሽያጭ ውል ህጋዊ የማድረግ ውጤት አይኖረውም፡፡

ምንም እንኳን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሉ የተደረገው በባዶ መሬት ላይ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ የሻረ ቢሆንም ከላይ በጠቀስነው ሕጋዊ ምክንያት የሽያጭ ውሉ ህጋዊ ውጤት ሊኖረው አይገባም የሚል እምነት ያለን በመሆኑ በውጤት ደረጃ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባ ነበር በማለት በሐሳብ ተለይተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማነታወሸ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

ሰ/መ/ቁ፡-191430
ቀን፡-30/02/2014ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ሕዳሴ ቴሌኮም አክሲዮን ማህበር - አልቀረቡም

ተጠሪዎች ፡- 1ኛ. አቶ ታምሩ ደብሩ } አልቀረቡም

2ኛ. አቶ አንተነህ ደበበ }

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ክርክሩ የአክሲዮን ድርሻ ትርፍ እንዲከፈል የቀረበ ክስን መሰረት ያደረገ ሲሆን ጉዳዩ በተጀመረበት የምእራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ ከሳሽና 1ኛ የከሳሽ ተከሳሽ፣ አመልካች ተከሳሽና የተከሳሽ ከሳሽ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ 2ኛ የተከሳሽ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ ጥቅምት 23 ቀን 2009 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው ክስ በአመልካች ኩባንያ ውስጥ በልዩ ቁጥር 1457 የተመዘገበ የአክሲዮን ድርሻ ያለኝ ሲሆን በዓመቱ መጨረሻ ሒሳብ ተሰርቶ ሊከፈለኝ ሲገባ ከ2006 እስከ 2008 ያልተከፈለኝ የአክሲዮን ትርፍን ፍርድ ቤቱ ሂሳቡን በማስመርመር በግምት ብር 30,000 እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች ህዳር 13 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ እና የተከሳሽ ክሳሽነት ክስ አቅርቧል፡፡ በመከላከያ መልሱ 1ኛ ተጠሪ የኩባንያው ባለአክሲዮን ስለመሆኑ ያቀረበው የድርሻ ሰርተፊኬት ወይም የአክሲዮን ድርሻ ስለመግዛቱ የሚገልፅ ማስረጃ ስለሌለ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33 መሰረት ክስ የማቅረብ መብት የለውም፡፡ ዳኝነት የተጠየቀበት ገንዘብም ከምን ያህል የአክሲዮን ድርሻ ላይ እና በእያንዳንዱ አመት ምን ያህል የአክሲዮን ትርፍ እንደተገኘ ስለማይገልፅ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 216 መሰረት ተቀባይት የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ በፍሬ ጉዳይ ላይ በሰጠው መልስ 1ኛ ተጠሪ የሚከፈለው የአክሲዮን ትርፍ የለም እንጂ አለ እንኳ ቢባል የባለ አክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የካቲት 9 ቀን 2007 ዓ.ም ያሳለፈውና በፌደራል ሰነዶች ምዝገባ እና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የተመዘገበውን ውሳኔ መሰረት በማድረግ የኩባንያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ሐምሌ 29 ቀን 2011 ዓ.ም በቁጥር HT/FIND/245/15 ባወጣው መመሪያ መሰረት የሚከፈለው ገንዘብ የለም፡፡ 1ኛ ተጠሪ በኩባንያው ምስራቅ ዲስትሪክት ጭሮ አካባቢ ፅ/ቤት በሽያጭ ሰራተኝነት ሲሰራ ብር 301,792.50 ለግል ጥቅሙ ያዋሉ ስለሆነና በእጁ ያለውን ሰነድ አስረክቦ ክሊራንስ እስካላቀረበ ድረስ የሚከፈለው ክፍያ እንደሌለ እያወቀ ያቀረበው ክስ የህግ መሰረት የለውም ተብሎ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በተጠሪዎች ላይ ባቀረበው የተከሳሽ ክሳሽነት ክስ 1ኛ ተጠሪ በድርጅቱ ከሰኔ 12 ቀን 2003 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 2007 መጨረሻ በሽያጭ ሰራተኝነት ተቀጥሮ ሲሰራ ከተረከበው መጠናቸው የተለያዩ የሞባይል ካርዶች እና ዲምላይት የሚባል የሶላር መብራት ሽያጭ በኩባንያው የባንክ ሒሳብ ማስገባት ሲገባው ብር 301,972.50 ለግል ጥቅሙ በማዋል ማጉደሉ ሐምሌ 6 ቀን 2007 ዓ.ም በተደረገ የኦዲት ምርምራ ተረጋግጧል፡፡ 2ኛ ተጠሪም ጥቅምት 21 ቀን 2004 ዓ.ም በተፈረመ የዋስትና ውል 1ኛ ተጠሪ በአመልካች ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት እስከ ብር 100,000 ለመክፈል ተስማምቷል፡፡ ስለሆነም 1ኛ ተጠሪ ይህን ገንዘብ ወለድን ጨምሮ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ በገባው ዋስትና መሰረት ወለድን ጨምሮ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በአንድነት እና በነጠላ እንዲከፍሉ እንዲወሰን እንዲሁም የ1ኛ ተጠሪ አክሲዮን በጫረታ ተሸጦ ለእዳው ለአከፋፈል እንዲውል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በተከሳሽ ክሳሽነት ክሱ ላይ ህዳር 23 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ በመልሱም ያጎደልኩት ሒሳብ የለም፡፡ በ1ኛ ተጠሪ እጅ ያሉ የተለያዩ ደረሰኞች ሳይመረመሩ በአመልካች ፍላጎት ብቻ የተሰራው የውስጥ ኦዲት ተቀባይነት የለውም፡፡ ከዚህ በፊት በወረዳው ፍርድ ቤት በነበረን ክርክር ተቀባይት ያጣ ስለሆነ በገለልተኛ የሂሳብ ባለሞያ ተጣርቶ በነፃ ልሰናበት ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

2ኛ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ተጠሪን የተለያዩ ክፍያዎችን ከፍሎ ከስራ ሲያሰናብተው እዳ ካለበት ተቀናሽ ሊያደርግ ይገባ ነበር፡፡ 1ኛ ተጠሪ ያጎደለው ንብረት የለም፡፡ አለ እንኳ ቢባል በቂ ንብረት ያለው በመሆኑ አኔ ላይ የቀረበው ክስ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክርና የሰው ማስረጃ ከሰማ በኋላ 1ኛ ተጠሪ በአመልካች ኩባንያ የአክሲዮን ድርሻ ያለው መሆን አመሆኑንና ያለው ከሆነ ሊያገኝ ሲገባው የቀረበት ጥቅም እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ ያጎደለው

ሒሳብ ካለ በባለሞያ ተጣርቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህም መሰረት በቁጥር wmm00606 ግንቦት 16 ቀን 2009 ዓ.ም የቀረበው ሪፖርት 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ኩባንያ ከተቀበለው ጠቅላላ መጠኑ ብር 9,848,456 የሆነ የሞባይል ካርድ እና ዲምላይት ዋጋ በላይ ብር 10,194,395.25 ገቢ ማድረጉን ገልጿል፡፡ አመልካች 1ኛ ተጠሪን ያለአግባብ ከስራ በማሰናበቱ ምክንያት 1ኛ ተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎችን ለማስከፈል በመ/ቁጥር 29811 ክስ ሲያቀርብ አመልካች 1ኛ ተጠሪ ገንዘብ ያጎደለ መሆኑን ገልፆ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ የ1ኛ ተጠሪ ምስክሮች እና የአመልካች 1ኛ ምስክር ተጠሪው ገንዘብ ማጉደሉን አናውቅም በማለት የመሰከሩ በመሆኑ 2ኛ የአመልካች ምስክር ተጠሪው ገንዘብ አጉድሏል በማለት የሰጠውን ምስክርነት ተዓማኒነት የሚያሳጣው ሲሆን የቀረበው የባለሞያው ማስረጃም ተጠሪው በብልጫ ብር 347,939.25 መክፈሉን የሚያረጋግጥ ስለሆነ በአመልካች የቀረበው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተገቢነት የለውም፡፡ የቀረበው የባለሞያ ሪፖርትም በ2006 እና 2007 ዓ.ም 1ኛ ተጠሪ ያልተከፈለው ብር 25,804.33 የአክሲዮን ድርሻ ትርፍ ያለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ስለሆነ እና የካቲት 9 ቀን 2007 የተደረገው የባለአክሲዮኖች ስብሰባ እና የን/ሕ/ቁጥር 452 አክሲዮን ድርሻ ክፍያን ስለማይከለክል ይህን ገንዘብ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ይግባኙን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱ አመልካች በስር ፍ/ቤት የቀረበው የኦዲት ሪፖርት የአዲት ስርዓትን ጠብቆ ያልተሰራ እና አንድ ደረሰኝ ለሒሳብ ስሌቱ ሁለት ጊዜ በመያዝ የተፈጸመ ነው ይህንንም ቅሬታ በስር ፍ/ቤት አቅርቤ መታለፉ ተገቢ አይደለም በማለት ያቀረበውን ቅሬታ መነሻ በማድረግ የምእራብ ሀረርጌ ዞን የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ፅ/ቤት በድጋሜ ኦዲት አድርጎ ውጤቱን እንዲገልጽ ያሳወቀ ሲሆን ፅ/ቤቱም የባንክ እስቴትመንት እና የባንክ እስሊፕን መሰረት በማድረግ አጣርቶ በቁጥር WMMDO06/06/2/85 መጋቢት 4 ቀን 2011 ዓ.ም ባቀረበ ውጤት የብር 198,719.25 ጉለት በ1ኛ ተጠሪ ላይ መገኙትን ሰላረጋገጡ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን ክስ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም ይህን ገንዘብ 1ኛ ተጠሪ ይክፈል፤ 2ኛ ተጠሪም ዋስ እስከሆነበት የገንዘብ መጠን ብር 100,000 ድረስ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በአንድነት እና በነጠላ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ጉዳዩን በመጀመሪያ በተመለከተው ፍ/ቤት ከጠየኩት ዳኝነት ላይ ብር 103,253 ተቀናሽ ተደርጎ መወሰኑ አግባብ አይደለም፤ በኦዲት ሪፖርት ተቀናሽ የተደረገው ብር 292,125 ገቢ ስለመደረጉ በባንክ እስቴትመንቱ የማይታይ እና ደረሰኞቹ ላይ በእጅ የተፃፈው እና በባንኩ ማህተም ላይ የተገለፀው ቀን ልዩነት የሚታይበት በመሆኑ ትክክለኛነቱ ከባንኩ እንዲጣራ ያቀረብኩት አስተያየት ታልፎ ዳኝነት ከጠየቀበት የገንዘብ መጠን ብር 103,253 አለመወሰኑ አግባብ አይደለም በሚል ይግባኙን ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ባይ ዳኝነት ከጠየቀበት የገንዘብ መጠን ብር 198,719.25 እንዲከፈለው የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ በማሻሻል ሲወስን አሁን ይግባኝ የተጠየቀበትን ቀሪውን ብር 103,253 በተመለከተ የከፍተኛ ፍ/ቤት ከወሰነው ጋር ተመሳሳይ አቋም መያዙን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ የክልሉ ፍ/ቤቶች በውክልና ስልጣናቸው የሰጡት ውሳኔ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተመሳሳይ በሆነበት በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 9 አመልካች የተሰጠው ሌላ የይግባኝ መብት የለም በማለት ቅሬታውን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

አመልካች የካቲት 20 ቀን 2012 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው ይህን የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ የክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ሙሉ ለሙሉ ውድቅ በማድረግ ሲወስን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሒሳቡን በገለልተኛ የሂሳብ ባለሞያ እንዲመረመር አድርጎ 1ኛ ተጠሪ የሚታይበትን ጉለት ብር 198,719.25 እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ በገባው ዋስትና መሰረት በአንድነት እና በነጠላ እንዲከፍል የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ ሙሉ ለሙሉ በመሻር ወስኖ እያለ ውሳኔዎቹ ተመሳሳይ ናቸው በሚል የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታውን ለ2ኛ ጊዜ የቀረበ ይግባኝ ነው በሚል ውድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ በተጨማሪም የምስራቅ ሀረርጌ ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ፅ/ቤት ኦዲተሮች ምርመራው የተሰራበትን አግባብ በሚመለከት የአመልካች የባንክ ሒሳብ 1000014402091፣ 1000032664176 እና 1000024461468 መሰረት አድርገው ምርመራ ከተደረገበት የባንክ እስቴትመንት ላይ የማይታይ ብር 292,125.00 1ኛ ተጠሪ ገቢ ያደረጉበት ደረሰኝ ላይ ይታያል በሚል ተቀናሽ ማድረጋቸው ተገቢ አይደለም በሚል ያቀረብነው መቃወሚያ ሳይታይ ታልፎ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ጉዳዩ የተጀመረው በዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የዞኑን ውሳኔ ሙሉ ለሙሉ ሽሮታል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሲያቀርብ የስር ፍ/ቤቶች ሁለቱም ተመሳሳይ ውሳኔ እንደሰጡበት ተደርጎ ለ2ኛ ጊዜ ይግባኝ ማቅረብ አይቻልም ተብሎ መዘጋቱ ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 9(2) አንፃር ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ታዟል፡፡

ተጠሪዎች በጋዜጣ ጥሪ ተደርገው መልስ ባለማቅረባቸው መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፏል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካች ይግባኝ አቤቱታ ለ2ኛ ጊዜ የቀረበ ነው ብሎ ውድቅ የማድረጉን እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች በስር ፍ/ቤት ዳኝነት ከጠየቀበት የገንዘብ መጠን ብር 301,792.50 ውስጥ ብር 198,719.25 ብቻ እንዲከፈለው የመወሰኑን አግባብነት በስር ፍ/ቤት ከተደረጉ ክርክሮች፣ በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ከፌደራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 9 እና ሌሎች ለጉዳዩ ተገቢነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመጀመሪያም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች የይግባኝ መብቱን ስለጨረሰ ይግባኝ ማቅረብ አይችልም የማለቱን አግባብነት ስንመለከት በኢፌድሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 80(2)(4) መሰረት የክልል ፍርድ ቤቶች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቁ ጉዳዮችን በውክልና ስልጣን መመልከት የሚችሉ መሆኑ፤ የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶችም የዞን ፍ/ቤቶች በውክልና

የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ውሳኔን በይግባኝ የሚመለከት መሆኑ ተገልጿል፡፡ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌደራል ጉዳዮችን በተወካይነቱ በይግባኝ ሰሚ ስልጣኑ ተመልክቶ ክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ የሠጠ እንደሆነ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ የመመልከት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 9 ላይ ተመላክቷል፡፡

አመልካች በፌደራል መንግስት የተመዘገበ ተቋም በመሆኑ የምእራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የተመለከተው በውክልና ስልጣኑ መሆኑ አላከራከረም፡፡ በዚህ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ በመሰረተው ክስ በአመልካች ኩባንያ ውስጥ በልዩ መዝገብ ቁጥር 1457 የተመዘገበ የአክሲዮን ድርሻ ያለው መሆኑን ገልጾ ከ2006-2008 ዓ.ም ያልተከፈለ የአክሲዮን ድርሻ ትርፍ ብር 30,000 እንዲከፈለው ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አመልካች ክሱን ክዶ የተከራከረ ሲሆን በአንጻሩ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርቧል፡፡ በዚህም ክስ ተጠሪ በአመልካች ኩባንያ የምስራቅ ዲስትሪክት በሽያጭ ሰራተኝነት ተቀጥሮ ባገለገለበት ጊዜ ብር 301,792.50 ማጉደሉን ገልጾ ይህንን ገንዘብ 1ኛ ተጠሪ እንዲከፍል እንዲወሰንለት ጠይቋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ምስክር ከሰማ በኋላ በጉዳዩ ላይ የባለሞያ ሪፖርት እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ ተጠሪ ገንዘብ አለማጉደሉን ይልቁንም በብልጫ ብር 347,939.25 ለአመልካች ኩባንያ ገቢ ማድረጉ እንዲሁም ያልተከፈለው የአክሲዮን ድርሻ ትርፍ ብር 25,804.3 መኖሩን አረጋግጦ የአመልካችን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ውድቅ አድርጎ አክሲዮን ድርሻ ትርፉን ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ አመልካችም በስር ፍ/ቤት የቀረበውን የባለሞያ ሪፖርት በመቃወም ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ጉዳዩ በድጋሚ በባለሞያ እንዲጣራ ተደርጎ ተጠሪ ብር 198,719.25 ማጉደሉ በመረጋገጡ በዚሁ አግባብ ተጠሪዎች ኃላፊነት አለባቸው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህም ምክንያት አመልካች ቀድሞ ዳኝነት ከጠየቀበት ብር 301,792.5 ውስጥ ውሳኔ ባልተሰጠበት ብር 103,253 ላይ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን አቅርቦ በዚህ ገንዘብ ላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ከዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ ለ2ኛ ጊዜ የቀረበ ይግባኝ ነው በሚል ውድቅ አድርጎታል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ውድቅ ሲያደርግ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከፍተኛ ፍ/ቤቱ ዳኝነት ከተጠየቀበት የገንዘብ መጠን ውስጥ ውድቅ ያደረገውን እና አመልካች ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበበትን የገንዘብ መጠን ብር 103,253 ትክክል ነው በሚል ተቀብሎ መጉደሉ የተረጋገጠው ገንዘብ ብር 198,719.25 እንዲከፈለው ወስኗል፡፡ ይህም በሁለቱም ደረጃ ያሉት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ብር 103,253 በሚመለከት በአመልካች የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸውን የሚያሳይ ነው ወይም ይህን ገንዘብ በሚመለከት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ከዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ጋር በውጤት ደረጃ ልዩነት የለውም ወይም አፅንቶታል የሚያስብል ነው፡፡ በመሆኑንም አመልካች በክልሉ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታው የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ካለ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ከሚያቀርብ በቀር ለ2ኛ ጊዜ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሚያቀርብበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አግባብ ስለሌለ መዝገቡ መዘጋቱ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 9 ን መሰረት ያደረገ ስለሆነ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበውን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

በመቀጠል አመልካች የምእራብ ሐረርጌ ዞን የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት በድጋሜ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በላከው ሪፖርት ላይ ቅሬታ አቅርቤ እያለ ተገቢነት ባለው ማስረጃ እንዲጣራ ሳይደረግ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በሚል የሚያቀርበውን መቃወሚያ ስንመለከት አመልካች በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበውን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ማጣራት እንዲቻል ለባለሞያ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ባለሞያው ተጠሪ ሒሳብ አለማጉደሉን ይልቁንም በብልጫ ለአመልካች ገቢ ያደረገ መሆኑን ገልጿል፡፡ በአንጻሩ አመልካች ይህን የባለሞያ ሪፖርት መሰረት ተደርጎ የተሰጠውን ውሳኔ የኦዲት ስርዓትን የተከተለ አይደለም በማለት በመቃወሙ በድጋሜ እንዲጣራ ትዕዛዝ ተሰጥቶ የምእራብ ሐረርጌ ዞን ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ፅ/ቤትም የባንክ እስቴትመንት እና ደረሰኝን መሰረት አድርጎ በማጣራት ተጠሪ ብር 198,719.25 ማጉደሉን በማረጋገጡ በዚሁ አግባብ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ ይህም ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ ትክክለኛ ውሳኔ መስጠት እንዲቻለው ተገቢውን ማጣራት ያደረገ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ሰበር ችሎት ኢ.ፌ.ድ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ መሰረት የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸውን ውሳኔዎች ማረም ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ማስረጃን መዝነው የሚደርሱበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ የማስረጃ አቀባበል እና ምዘና መርህ ጥሰት እስካልተፈጸመበት ድረስ ይህ ችሎት የማረም ስልጣን አልተሰጠውም፡፡ አመልካች ከባንክ እስቴትመንት እና ከባንክ እስሊፕ አንጻር የሚያነሳው ክርክር የማስረጃ ምዘናን የሚመለከት የፍሬ ነገር ክርክር በመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የኦዲት ሪፖርቱን መርምሮ የደረሰበትን ድምዳሜ እንዳለ የሚቀበለው ይሆናል፡፡በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምስራቅ ምድብ ቋሚ ችሎት በመ/ቁጥር 276775 በቀን 01/09/2011 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሂ/መ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁ. 193168
ቀን ፡- ሕዳር 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- 1. ወ/ሮ መሠለች ደስታ
2. ወ/ሮ ወሰንየለሽ መንክር
3. አቶ ቀደሰ መንክር
4. አቶ አክሊሉ መንክር
5. ወ/ሪት ፎቶ መንክር
6. ወ/ሮ ፀሐይ መንክር
7. ወ/ሮ ሒሩት መንክር
8. አቶ ናርዶስ መንክር
9. አቶ ነብዩ መንክር

ተጠሪ ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዐቃቤ ሕግ ቢሮ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካቾች የስር ከሳሾች ሲሆኑ የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 አስተዳደር ጽ/ቤት

ተከሳሽ እና ተጠሪ የመቃወም አመልካች ነበሩ፡፡ አመልካቾች በዚህ ችሎት ደረጃ ተከራካሪ ባልሆነው የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 አስተዳደር ጽ/ቤት ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 የቤት ቁጥር 582 በሆነ ይዞታ ላይ ያላቸው ካርታ እንዲያስተካክልና የፈጠረው ሁከት እንዲወገድ ሲሉ የጠየቁት ዳኝነት በፍርድ ቤቱ ውደቅ በመደረጉ ይግባኝ አቅርበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ተመልክቶ አመልካቾች በዕጃቸው በሚገኘው 783.82 ካሬ ሜትር ይዞታ በመሆኑ ካርታውን እንዲያስተካክልና የፈጠረው ሁከት እንዲወገድ ወስኗል፡፡

ተጠሪ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ፍርዱን በመቃወም ማመልከቻ ያቀረበ ሲሆን ይዙቱም ተከሳሽ የነበረው የወረዳ አስተዳደር ካርታ የማስተካከል ሥልጣን የለውም፣ በዚህም የከተማው አስተዳደር ሆነ የነዋሪዎች መብትና ጥቅም ተነክቷል፡፡ አመልካቾች በ773 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ ዳኝነት ጠይቀው ባልተጠየቀ ዳኝነት በ783.82 ካሬ ሜትር ላይ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ ይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጠኝ በማለት በፍርድ ቤት ዳኝነት የሚጠየቅበት አይደለም ተብሎ ፍርዱ እንዲሰረዝ የሚል ነው፡፡ አመልካቾች ባቀረቡት መልስ የወረዳውን አስተዳደር ወክሎ ዐቃቤ ሕግ ሲከራከር ስለነበር ተጠሪ ባለው አደረጃጀት ጉዳዩን ቀድሞ የሚያውቀው ነው፡፡ ሁለት ጊዜ ታይቶ ውሳኔ ካገኘና ከጸና በኋላ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1/1195፣ 2/1995፣ 18/1997፣ 4/2000 እና 64/2011 እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 37502 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንጻር ተጠሪ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት መቃወሚያ የማቅረብ መብት አለው፡፡ ቀደም ሲል የተሰጠውን ፍርድ በማሻሻል የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 አስተዳደር ጽ/ቤት የፈጠረውን ሁከት እንዲያስወግድ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በማጽናትና ካርታው እንዲስተካከል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ግን የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 አስተዳደር ጽ/ቤትን የሚመለከት ባለመሆኑና በፍርድ ቤት ቀርቦ ዳኝነት የሚጠየቅበት ባለመሆኑ ፍርዱ በከፊል ሊሰረዝ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካቾችን ይግባኝ ባለመቀበል ሠርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘትም የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 አስተዳደር ጽ/ቤትን ወክሎ የክፍለ ከተማው ዐቃቤ ሕግ ሲከራከር የነበረ በመሆኑ በአንድ አደረጃጀት ሥር ያለው ተጠሪ ተቃዋሚ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም፣ ተጠሪ ጉዳዩን በአስተዳደራዊ አቤተታ ሆነ በፍርድ ቤት ክርክር ሂደት የሚያውቀው ነው፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎቱም በመዝገብ ቁጥሮች 165372 እና 165750 ላይ ትርጉም የሠጠበት ነው፡፡ ተጠሪ ያነሳው የፍሬ ነገር ክርክርም ቀደም ሲል ክርክር ተደርጎበት ውሳኔ የተሰጠበትና ተጠሪን መብትና ጥቅም የሚነካ አይደለም የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ይዞታው የአመልካቾች መሆኑ በተረጋገጠበት እና መስተዳድሩ ፈቃደኛ እንዳልሆነ ባልተካደበት

ሁኔታ የሥር ፍርድ ቤት ካርታን አስመልክቶ ውሳኔ ያልሰጠበት አግባብ ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ በማዘዙ ተጠሪ ያቀረበው መልስ የወረዳ ሆነ በክፍለ ከተማ ደረጃ ያለ ዐቃቤ ሕግ እና ተጠሪ የተለያየ ነው፤ በአንድ መዋቅር የተደራጀም አይደለም፤ የተለያየ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ነው። የተጠቀሱት የሰበር ውሳኔዎች ለጉዳዩ አግባብነት የላቸውም። ተጠሪ መብትና ጥቅሙ በመነካቱ ተቃዋሚ ሆኖ መከራከሩ ተገቢ ነው፤ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማለት ክርክሩን አቅርቧል። አመልካቾች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል።

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ተጠሪ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ተቃዋሚ ሆኖ ማመልከቻ ማቅረቡ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ መሆን አለመሆኑን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል።

እንደመረመረውም ተጠሪ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት ላቀረበው የመቃወም አቤቱታ መሠረት ያደረገው አመልካቾች በስር ተከሳሽ በነበረው የአዲስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 አስተዳደር ጽ/ቤት ላይ ያቀረቡትን ክስ መሠረት በማድረግ ካርታ እንዲያስተካክልና ሁከት እንዲያስወግድ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሳኔ የአስተዳደሩ ነዋሪዎችን መብትና ጥቅም የሚነካ በመሆኑ እና ተጠሪ በፍርድ ቤት ክርክር አቅርቦ ይህን መብት ለማስከበር በህግ ስልጣን የተሰጠው መሆኑን በመጥቀስ ነው። በእርግጥ ተጠሪ በፍርድ ቤት ክርክር አቅርቦ የከተማ አስተዳደሩን ነዋሪዎች መብትና ጥቅም የማስከበር ስልጣን በህግ የተሰጠው መሆኑ አላከራከረም። አከራካሪው እና የዚህን ችሎት እልባት የሚያሻው ጭብጥ አመልካች በፍርድ ቤት ክርክር በማድረግ የከተማው ነዋሪዎችን/የህዝብና የመንግስትን መብትና ጥቅም ለማስከበር ያለው መብት/ስልጣን ተመሳሳይ መብትና ጥቅምን ለማስከበር ስልጣንና ኃላፊነት ባለው ሌላ የከተማው አስተዳደር አካል ክርክር ተደርጎበት ውሳኔ ያረፈበት ጉዳይ በድጋሚ እንዲታይ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የመቃወም አቤቱታ ለማቅረብ ያስችለዋል ወይ? የሚለው ነው።

እንደሚታወቀው ፍርድ ቤቶች የቀረበላቸውን የጽሑፍ ክርክር መርምረው፣ በቃል የሚቀርቡ ክርክሮችን አዳምጠው፣ ማስረጃዎችን መዝነው እና መሠረታዊ ህጎችን ተርጉመው ውጤት ላይ መድረስ ይችሉ ዘንድ ሥርዓት ያስፈልጋቸዋል። ክርክሮች የሚመሩባቸው ሥርዓት እና ደንቦች በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ተቀርጸው ስራ ላይ እንዲውሉ የሚደረግበት ምክንያትም ይሄው ነው። የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ የፍትሐብሔር ክርክሮችን አስመልክቶ የምንከተለው ስርዓት ሲሆን አጠቃላይ ዓላማውም የፍትሐብሔር ጉዳዮችን ፍትሐዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ቀልጣፋ በሆነ ሁኔታ በመምራት ፍትሐዊ ውሳኔ እንዲያገኙ ማስቻል ነው። ይህን ዓላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድም የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ የተለያዩ ደንቦች እና መርሆዎችን ይደነግጋል። ክርክሮች በዘፈቀደ ሳይሆን ሥርዓት ባለው ሁኔታ እንዲመሩ በማድረግ የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት መብትን፣ ብሎም ክርክሮች ባነሰ ወጪ እና ጊዜ መቋጫ እንዲያገኙ በማድረግ በፍርድ ቤት እና በተከራካሪ ወገኖች ላይ ያላግባብ የሚደርሰውን የገንዘብ እና የጊዜ ብክነት በማስቀረት የክርክሩ ሂደትም ሆነ ውጤቱ ፍትሐዊ እንዲሆን በማድረግ ረገድ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ የሚኖረው ሚና

ከፍተኛ በመሆኑ በህጉ ላይ የተመለከቱትን ደንቦች እና መርሆዎች በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ የማድረጉ አስፈላጊነትም የሚያጠያይቅ አይደለም።

በዚህ ረገድ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጋችን ዕውቅና ከተሰጣቸዉ ደንቦች ዉስጥ አንዱ በከሳሽነት እና በተከሳሽነት ከተሰየሙት ወገኖች ዉጪ ያሉ ሦስተኛ ወገኖች የክርክር ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ የሚመለከተዉ ደንብ ነዉ። በከሳሽነት እና በተከሳሽነት ከተሰየሙት ተከራካሪዎች ዉጭ የሆነ ሦስተኛ ወገን በክርክሩ ተሳታፊ ካልሆነ ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊ ዉሳኔ ለመስጠት የማይችል ዓይነት (indispensable party) ከሆነ በፍርድ ቤቱ አነሳሽነት ወይም መብት ባለዉ ሰዉ አቤቱታ አቅራቢነት፣ እንዲሁም ዉጤቱ መብቱን ሊነካ ይችላል በሚል ወገን (interested party) አቤቱታ አቅራቢነት ሦስተኛ ወገን በተጀመረ ክርክር ተሳታፊ የሚሆንበትን ሥርዓት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ ይዘረጋል (አንቀጽ 40 እና 41 ይመለከቷል)። ዓላማዉም የጉዳዩ አመራር ፍትሐዊ እንዲሆንና በሥርዓት እንዲከናወን ለማስቻል ሲባል ነዉ ተብሎ ይታመናል። ይሁንና በተለያዩ ምክንያቶች ከላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ክርክሩ በሂደት ላይ እያለ በክርክሩ ተሳታፊ ሆኖ መብቱን ማስከበር ይችል የነበረ ሰዉ ተሳታፊ ባልሆነበት መብቱን የሚነካ ዉሳኔ ሊሰጥ የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ስለሆነም በፍርድ ቤት ወይም በህግ የዳኝነት ስልጣን ባለዉ አካል በተሰጠ ዉሳኔ መብቱ ተነክቷል የሚል ሦስተኛ ወገን አቤቱታዉን በማቅረብ ዉሳኔዉን በመቃወም መብቱን ሊያስከብር የሚችልበትን ሥርዓት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 ላይ የተመለከተ ሲሆን፣ የድንጋጌዉ ሙሉ ይዘትም በክርክሩ ዉስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባዉ ወይም በክርክሩ ዉስጥ ለመግባት የሚችልና እንዲሁም ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠዉ ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማናቸዉም ሰዉ ራሱ ወይም ጠበቃዉ ወይም ነገረ ፈጁ ተካፋይ በልሆነበት ክርክር የተሰጠዉ ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት መቃወሚያዉን ለማቅረብ ይችላል የሚል ነው።

ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለዉም ክርክሩ መጀመሩን ሳይረዳና ሳያዉቅ በከሳሽነትና በተከሳሽነት በተሰየሙት ወገኖች መካከል የተደረገዉ ክርክር ተጠናቆ መወሰኑ እንኳ ቢታወቅ ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ ይረዳ ዘንድ በዉሳኔዉ መብቱ ተነክቷል የሚለዉ የክርክሩ ተካፋይ ያልነበረዉ ሰዉ ይህንኑ ዉሳኔ መቃወም የሚችል መሆኑን ነዉ። በተለይም በድንጋጌዉ ማናቸዉም ሰዉ ራሱ ወይም ጠበቃዉ ወይም ነገረ ፈጁ ተካፋይ ባልሆነበት ወይም በእንግሊዝኛዉ if he was not a party to such suit either in person or through a representative በሚል የተገለጸዉ የሚያሳየዉ ሦስተኛ ወገን የሚያቀርበዉ አቤቱታ ተቀባይነት የሚኖረዉ አቤቱታ አቅራቢዉ ለአቤቱታዉ በምክንያትነት የጠቀሰዉ ጉዳይ በቀደመዉ የክርክር ሂደት በመቃወም አመልካቹ በእራሱ ወይም በወኪሉ ወይም ተመሳሳይ መብትና ጥቅም ለማስከበር ስልጣን ባለዉ ሰዉ ክርክር ያልቀረበበት ሲሆን ነዉ። በሌላ አገላለጽ የመቃወም አመልካቹ ለአቤቱታዉ መሰረት ያደረገዉ ክርክሩ በሂደት ላይ በነበረበት ወቅት ጉዳዩ የሚያገባዉ ሰዉ የክርክሩ ተሳታፊ በሆነበት ታይቶ ዉሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ ከሆነ እና የመቃወም አመልካቹ ዉሳኔዉ '*በግል*' መብቱን የሚነካ መሆኑን በአቤቱታዉ ካላሳየ በስተቀር አቤቱታዉ ተቀባይነት የሚኖረዉ አይደለም። የመቃወም አመልካች ለመቃወሚያዉ ምክንያት የሆኑትን ዝርዝር ምክንያቶች እና የሚጠይቀዉን ዳኝነት በአቤቱታዉ በዝርዝር መግለጽ እንዲሁም

አቤቱታው ለሌሎች ተከራካሪ ወገኖች እንዲደርስ ተደርጎ ክርክሩም የሚሰማው የመጀመሪያው ክርክር በተሰማበት ሂደት ስለመሆኑ በህጉ አንቀጽ 359 እና 360 ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎችም የሚያሳዩት ለመቃወም አቤቱታው ምክንያት የሆነው ዉሳኔ የመቃወም አመልካቹን መብትና ጥቅም በግል የሚነካ መሆን ያለመሆኑ ጉዳይ የመቃወም አመልካቹ እና በክርክሩ ተሳታፊ የሆኑ ሌሎች ተከራካሪ ወገኖች የሚያቀርቡትን ክርክር እና ማስረጃ መሠረት በማድረግ ታይቶ ዉሳኔ የሚሰጥበት መሆኑን ነው።

ስለሆነም በፍርድ ቤት ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠው የዳኝነት አካል የተሰጠን ዉሳኔን መቃወም የሚቻልበትን ሥርዓት አስመልክቶ በሥነ ሥርዓት ህጉ የተመለከተው ድንጋጌ በዉሳኔው መብቱ 'በግል' የተነካበት ሰው መቃወሚያውን አቅርቦ መብቱን ለማስከበር እንዲችል እንጂ አንድን መብትና ጥቅም ለማስከበር የተለያዩ ሰዎች ተፈራርቀው የሚያቀርቡትን አቤቱታ ለማስተናገድ ያለመሆኑን መገንዘቡ ተገቢ ነው። ይልቁንም የመቃወም አቤቱታ የሚቀርብበትን ሁኔታ አስመልክቶ በድንጋጌው ላይ ከተመለከቱት መስፈርቶች አንፃር ሲታይ የድንጋጌው ዓይነተኛ ዓላማ በአንድ በኩል በከሳሽነት እና በተከሳሽነት በተሰየሙ ወገኖች መካከል በተደረገ ክርክር መነሻነት የተሰጠ ዉሳኔ መብቱን የሚነካበት ሰው ዉሳኔውን በመቃወም ተከራክሮ መብቱን እንዲያስከብር በማድረግ ፍትሕ የማግኘት መብቱን በማረጋገጥ፣ በሌላ በኩል በከሳሽነት እና በተከሳሽነት በተሰየሙት ወገኖች መካከል ክርክር ተደርጎበት እልባት ባገኘ ጉዳይ ላይ በድጋሚ ክርክር በማቅረብ ተመሳሳይ መብትና ጥቅም ለማስከበር በሚል በሦስተኛ ወገን የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት እንዳይኖረው በማድረግ በአንድ ጉዳይ ላይ ወይም ተመሳሳይ መብትና ጥቅምን ለማስከበር በሚል ክርክሮች በተደጋጋሚ ሊቀርቡ የሚችሉበትን ሁኔታ በማስቀረት ክርክሮች በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጪ መቋጫ እንዲያገኙ ብሎም የፍርድ ሂደቱም ሆነ ዉጤቱ ተገማች እንዲሆን ማድረግ ነው። ስለሆነም በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የቀረበ የመቃወም አቤቱታ ተቀባይነት ያለው መሆን ያለመሆኑን አስመልክቶ በፍርድ ቤቶች የሚሰጠው ትርጉም ይህንኑ ያገናዘበ ሊሆን ይገባል።

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ፣ ከፍ ሲል እንደተመለከተው፣ በአመልካቾች ከሳሽነት በስር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት የተሰየመው የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 03 አስተዳደር ጽ/ቤት ክርክር ተደርጎ ውሳኔ ተሰጥቶበታል። ተጠሪ የህግ ሰዉነት የተሰጠው ተቋም በመሆኑ የህግ ሰዉነት የተሰጠው የመንግስት ወይም የግል ተቋም እንደሚያደርገው ሁሉ በቀጥታ ተቋሙን በሚመለከተው ጉዳይ ላይ በከሳሽነት፣ በተከሳሽነት፣ በጣልቃ ገብነት ወይም በመቃወሚያ አቤቱታ አቅራቢነት በፍርድ ቤት ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠው የዳኝነት አካል ቀርቦ የክርክሩ ተሳታፊ በመሆን እንደ ተቋም ያለዉን መብት የማስከበር መብትም ግዴታም አለው። ይሁንና በተያዘው ጉዳይ ላይ ተጠሪ በአመልካቾች የቀረበው ክስ ይመለከተኛል ወይም በህጉ አንቀጽ 33(3) መሠረት በተከሳሽነት መጠራት የነበረብኝ እኔ ነኝ የሚል ክርክር የለውም፤ ይልቁንም በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 ያቀረብኩት የመቃወም አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል በማለት የሚከራከረው በስር ተከሳሽ የነበረው የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 03 አስተዳደር ጽ/ቤት ላይ የተወሰነው ውሳኔ የከተማ አስተዳደሩን ሆነ የከተማውን ነዋሪዎች መብትና ጥቅም የሚነካ መሆኑን እና የነዋሪዎች መብትና ጥቅምን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የመቃወም አቤቱታ አቅርቦ መከራከር እንዲችል በህግ ስልጣን

የተሰጠዉ መሆኑን ነዉ፡፡ በእርግጥም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀጽ 5 የዐቃቤ ሕግ ቢሮ የከተማዉ አስተዳደር መስሪያ ቤቶች የአስተዳደሩና የነዋሪዉ መብትና ጥቅም ወኪል ሆኖ እንደሚከራከር የተመለከተ ሲሆን፣ ተጠሪ የከተማ አስተዳደሩ ዐቃቤ ሕግ ቢሮ በመሆኑ የከተማ አስተዳደሩን አካላት ሆነ የነዋሪዎችን መብትና ጥቅም በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ወኪል ሆኖ ለፍርድ ቤት ወይም በህግ የዳኝነት ስልጣን በተሰጠዉ አካል ቀርቦ ክርክር የማቅረብ ስልጣን ይኖረዋል፡፡

ተጠሪ የሚከራከረው በሥር ፍርድ ቤት ተከሳሽ የነበረው የወረዳ አስተዳደር ካርታ ለማስተካከል ሥልጣን የለውም፣ ካርታ ይስተካከል የሚለው በፍርድ ቤት ዳኝነት ሊጠየቅበት አይችልም የሚል በመሆኑ ከተከሳሹ መብትና ጥቅም አኳያ የቀረበ ክርክር ነው፤ የተለየ ሳይሆን ተመሳሳይ መብትና ጥቅም ወክሎ እየተከራከረ መሆኑንም ያስገነዝባል፡፡ ተመሳሳይ መብትና ጥቅም ለማስከበር ስልጣን ባለዉ ጉዳዩ በሚመለከተዉ መስሪያ ቤት ክርክር ቀርቦበት ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ አቃቤ ህግ ዉሳኔዉን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት ሊቃወም የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሠረት ያደረገው የሠበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 37502 የተሰጠው የሕግ ትርጉምም በሰበር መዝገብ ቁጥር 190307 የተለወጠ እና መሥሪያ ቤቱ ተከራክሮ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ተመሳሳይ መብትና ጥቅም ወክሎ ዐቃቤ ሕግ ሊከራከር እንደማይችል አስገዳጅ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ በተጨማሪም በተያዘው ጉዳይ ተከሳሽ የነበረውን የወረዳ አስተደዳር በዐቃቤ ሕግ ተወክሎ ሲከራከር የነበረ ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት የተረዳን ሲሆን የወረዳ ዐቃቤ ሕግ፣ የክፍለ ከተማ ዐቃቤ ሕግ ሆነ በቢሮ ደረጃ ያለው ዐቃቤ ሕግ በተመሳሳይ አደረጃጀት ያለ እና አንዱ ለአንዱ ተጠሪ ሆኖ የተዋቀረ በመሆኑ የተለያየ የሕግ ሰውነት አለን በሚል ምክንያት ብቻ ተመሳሳይ መብትና ጥቅምን ወክለው አንድን ጉዳይ ሁለትና ከዚህ በላይ ጊዜ ክርክር እንዲደረግበት መብት የሚሰጥ አይደለም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ያቀረበውን ተቃውሞ መሠረት ተደርጎ ቀደም ሲል ተሰጠው ፍርድ መሻሻሉ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተዘረጋውን ሥርዓት ያልተከተለና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ዉሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 188696 የካቲት 13 ቀን 2012 ዓ/ም እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 196817 ሕዳር 30 ቀን 2012 ዓ/ም የሰጡት ዉሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዝግቷል ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ 193443

ሀምሌ 30 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- አቶ ሙሉጌታ ሲሳይ፡- ጠበቃ ዳንኤል ደጉ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ ጌትነት አለማየሁ

2ኛ. ደስታዬ አለማየሁ ጠበቃ መብራቱ ማሞ ቀረቡ

3ኛ. አቶ ፍቃዱ አለማየሁ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች በቀን 28/11/2012 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 83577 በቀን 09/11/2011 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 243422 በቀን 01/07/2012 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቁ ነው። ክርክሩ በስር ፍርድ ቤት ሲጀመር የአሁን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪዎች ደግሞ ከሳሾች ነበሩ።

ተጠሪዎች በቀን 02/04/2010 ዓ.ም ባቀረቡት የክስ አቤቱታ እህታችን ወ/ሮ አልማዝ አለማየሁ የካቲት 03/2009 ኣ.ም በሞት ተለይተዋል፤ በህይወት በነበሩበት ጊዜ ልጅ አልወለዱም፤ እናትና አባታችንም ከሟች ቀድመው ሞተዋል፤ ሟች ኑዛዜም አላደረጉም፤ ከሳሾች የሟች እህታችን ምትክ ወራሾች ስንሆን ተከሳሽ ሟች እህታችን ስለተናዘዘችልኝ የኑዛዜ ወራሽ ነኝ በማለት ከሳሾች በመ/ቁ 74433 አቅርበን በነበረው ውርስ ይጣራልኝ አቤቱታ ላይ ጠልቃ ልግባ በማለት ባቀረቡት አቤቱታ ምክንያት ተከሳሽ ሟች ተናዛልኛለች ማለታቸውን ለማወቅ ችለናል፤ ተከሳሽ ሟች ተናዛልኛለች ከሚሉበት ጥር 21/2009 ዓ.ም ቀደም ከአንድ ሳምንት በፊት ጀምሮ ከዚህ አለም በሞት እስከተለየችበት እለት ድረስ ህይወቷን ስታ የኑዛዜ ቃል ለመስጠት የማትችል በመሆኑ ምክንያት ሟች ሰጥታለች የተባለው የኑዛዜ ቃል በፍ/ብ/ህ/ቁ 881 መሰረት ሟች የኑዛዜውን ቃል እየተናገረች የተጻፈ ወይም በሟች የእጅ ጽሁፍ የተጻፈ ለመሆኑ የሚያረጋግጥ አይደለም፤ ስለሆነም ሟች ሰጥታለች የተባለው የኑዛዜ ቃል በግልጽ ስለሚደረግ ኑዛዜ የተመለከተውን ፎርም የማያሟላ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 881 መሰረት ፈራሽ ነው እንዲባልልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሽ በሰጡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው በብይን ውድቅ የተደረገ ሲሆን በፍሬ ነገር መልሳቸው የተከሳሽ አሳዳጊ ሟች ወ/ሮ አልማዝ የካቲት 03/2009 ዓ.ም ሞተው በማግስቱ መቀበራቸው እውነት ነው፤ ሟች ተከሳሽን ከህጻንነቱ ጀምሮ በመውሰድ ያሳደገችኝ እና ስታስተምረኝ የቆየች ሲሆን ከመሞቷም በፊት ይህንኑ ኑዛዜ ላይ በግልጽ እንዳስቀመጠችው የማደጎ ልጇ ነኝ፤ ከሳሾች ምትክ ወራሽ ነን በማለት የማደጎ ልጅ የመጀመሪያ ደረጃ እና የኑዛዜ ወራሽ የሆንኩት ተከሳሽ እያለሁ ለተከሳሽ የተደረገ ኑዛዜ ይፍረስልን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፤ ሟች በህይወት እያለች ያላትን ቤትና የቤት ቁሳቁስ በሙሉ ተናዛልኝ ሞታለች፡፡ ሟች ኑዛዜ ባደረገችበት ወቅት ብዙም ህመም ያልነበራት መንቀሳቀስ ሆነ መናገር የምትችል በትክክለኛ አእምሮ ላይ የነበረች የምትሰራውንና የምታደርገውን የምታውቅ ነበረች፡፡ ሟች ለተከሳሽ በትክክለኛ አእምሮዋ ማንም ሳያስገድዳት በራሷ አነሳሽነት የንስሀ አባቷ እና ምስክሮች ባሉበት ኑዛዜውን ያደረገች ሲሆን እነሱም ሟች የሰጠችውን የኑዛዜ ቃል እሷ እየተናገረች በጽሁፍ ካሰፈሩ በኋላ ሟች የሰጠችው ቃል ወዲያው በኮምፒውተር በመጻፍ አምጥተውላት ካነበቡላት በኋላ በምስክሮች ፊት የፈረመችና ምስክሮችም ይህ ኑዛዜ ሲደረግ በቦታው ሆነው ያዩ መሆኑን አረጋግጠው የፈረሙበት ስለሆነ በፍ/ብ/ህ/ቁ 881 መሰረት ኑዛዜው ሊከተል የሚገባውን ፎርም አሟልቶ የቀረበ ኑዛዜ በመሆኑ ሊፈርስ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ክርክሩንና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የኑዛዜው ሰነድ ሲመረመር በኑዛዜው ላይ አራት ምስክሮች የፈረሙ ሲሆን ተደረገ የተባለው ኑዛዜ

ግን በምስክሮች ፊት ስለመነበቡና ይኸው ስርአት ስለመፈጸሙ የሚገልጽ አይደለም፤ ሟች በህይወት እያሉ በፍላጎታቸው ኑዛዜ ያደረጉ መሆናቸው በተከሳሽ ምስክሮች የተረጋገጠ ቢሆንም ሟች ያደረጉት የኑዛዜ ቃል በህጉ ላይ የተቀመጠውን መስፈርት ያሟላ አይደለም። ስለሆነም ሟች ጥር 21 ቀን 2009 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ የፍ/ብ/ህ/ቁ 881 ስር የተቀመጡትን መስፈርቶች (ስርአቶች) ያላሟላ በመሆኑ ፈራሽ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል። በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተከሳሽ ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ውሳኔው ጸንቷል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው። አመልካች በቀን 28/11/2012 ዓ/ም ባቀረቡት ማመልከቻ ሟች አልማዝ አለማየሁ ለአመልካች ጥር 21/2009 ዓ.ም ያደረገችው ኑዛዜ አናዛዥር በሆኑት ምስክሮች የተነበበላት ስለመሆኑ በግልጽ ተጠቅሶ ያለ ከመሆኑም ውጪ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት እነዚህን በኑዛዜው ላይ ያሉትን ምስክሮች በችሎት አስቀርቦ ኑዛዜው ለሟች በምስክሮች ፊት ስለመነበቡ አረጋግጦ እያለ ኑዛዜው በምስክሮች ፊት ስለመነበቡና ይኸው ስርአት ስለመፈጸሙ ሰነዱ አያመላክትም በማለት ፈራሽ ማድረጉና ከፍተኛ ፍ/ቤቱ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ እንዲታረምልኝ በማለት ጠይቀዋል።

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት ሟች ለአመልካች ያደረጉት ኑዛዜ ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ አግባብነት ከፍ/ብ/ህ/ቁ 881 እና በሰበር መ/ቁ 17429 ከተሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ አንጻር ለመመርመር በሚል ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል።

ተጠሪዎች በቀን 20/02/2013 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ ሟች ሰጠች የተባለውን ኑዛዜ በኮምፒውተር ለማጻፍ የወሰዱት ምስክሮች ሳይሆኑ አመልካች ናቸው፤ ከወሰዱ በኋላ በህግ ባለሙያ ታግዘው ሟች ከሰጠችው ቃል ውጭ አስጨምረው በማጻፍ ያመጡ መሆኑን አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቧቸው ምስክር በመስቀለኛ ጥያቄ ላይ አረጋግጠው መልስ ሰጥተዋል፤ ይህም የኑዛዜው ቃል ከመጀመሪያውኑም ከአጻጻፍ ጀምሮ የፍ/ብ/ህ/ቁ 881 እና 882 ላይ የተደነገገውን የግልጽ ኑዛዜ አጻጻፍን ያላሟላ ስለነበር ከጅምሩም የፈረሰ ነው፤ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 70057 በሰጠው ትርጉም ኑዛዜው ለተናዛዥር እና ምስክሮች ስለመነበቡ በሰነዱ ላይ ያለመገለጹ ብቻ የኑዛዜ ሰነዱ በፍ/ብ/ህ/ቁ 881(2) እና 882 ስር የተመለከተውን ፎርማሊቲ አያሟላም ተብሎ ፈራሽ እንዲሆን የግድ የሚል ውሳኔ ሰጥቷል። በዚህም መሰረት ኑዛዜው በግልጽ ስለመነበቡ ኑዛዜው ላይ የተገለጸ ቃል ባለመኖሩ የስር ፍ/ቤቶች ኑዛዜው ፈራሽ ነው በማት የሰጡት ውሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት ባለመኖሩ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲጸና በማለት ተከራክረዋል። አመልካችም በመልስ መልሳቸው አቤቱታቸውን በማጠናከር አቅርበዋል።

ከፍሲል ባጭሩ የገለጽነው የክርክሩን አመጣጥ ነው። በበኩላችን የግራቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔና ተገቢነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማያያዝ መርምረናል።

እንድመረመርነው የፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የኑዛዜውን ሰነድ ይዘት መርምሮ ሟች ወ/ሮ አልማዝ አለማየሁ ለአመልካች ጥር 21/2009 ዓ.ም አደረጉት የተባለው ኑዛዜ በግልጽ የሚደረግ የኑዛዜ አይነት መሆኑን መገንዘብ መቻሉን፤ በኑዛዜው ላይ አራት ምስክሮች የፈረሙበት መሆኑን፤ ነገር ግን ኑዛዜው በምስክሮች ፊት ስለመነበቡና ይኸው ስርአት ስለመፈጸሙ የሚገልጽ አለመሆኑን፤ በአጠቃላይ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በህጉ ላይ የተቀመጠውን መስፈርት ያሟላ አለመሆኑን በማረጋገጥ ወስኗል። ይህ መደምደሚያ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ተቀባይነት አግኝቷል።

በመሰረቱ በግልጽ ስለሚደረግ ኑዛዜ ፎርም ከሚደነግገው የፍ/ብ/ህ/ቁ 881 ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለው በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ ተናዛዡ እየተናገረ ማናቸውም ሌላ ሰው ወይም ተናዛዡ ራሱ የሚጽፈው ነው። ኑዛዜው በተናዛዡ እና በአራት ምስክሮች ፊት ካልተነበበና ይህም ስርዓት (ፎርማሊቲ) መፈፀሙንና የተፃፈበትንም ቀን የሚያመለክት ካልሆነ በቀር ፈራሽ ነው። በእርግጥ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 17429 እና ሌሎችም ተመሳሳይ መዛግብት በሰጠው ትርጉም መሰረት በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ ኑዛዜው መነበቡን የሚያመለክት ከሆነ በግልፅ "ተነቧል" የሚል ቃል አለመኖሩ ኑዛዜውን ፈራሽ የሚያደርግ ስላለመሆኑ ወስኗል።

በተያዘው ጉዳይ ግራቀኙ የሚከራከሩበት ወ/ሮ አልማዝ አለማየሁ ትተውት አልፈዋል የተባለው ኑዛዜ በግልጽ የሚደረግ የኑዛዜ አይነት መሆኑና አራት ምስክሮች የፈረሙበት መሆኑን የሚያሳይ ቢሆንም ኑዛዜው በምስክሮች ፊት መነበቡን የሚያመለክት እንዳልሆነ በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል። የስር ፍርድ ቤት ይኸን የማስረጃና የፍሬ ነገር መደምደሚያ በማረጋገጥ ኑዛዜው በፍ/ህ/ቁ 881 የተመለከተውን ፎርም የተከተለ ስላለመሆኑ ወስኗል።

አመልካች በቅሬታቸው በኑዛዜው ላይ ያሉት ምስክሮች በስር ፍርድ ቤት ቀርበው ኑዛዜው ለሟች በምስክሮች ፊት ስለመነበቡ አረጋግጠው እያለ ኑዛዜው በምስክሮች ፊት ስለመነበቡና ይኸው ስርአት ስለመፈጸሙ ሰነዱ አያመላክትም ተብሎ መወሰኑ አላግባብ ነው በማለት ተከራክረዋል። ይሁንና የማስረጃውን አይነት በተመለከተ በፍ/ብ/ህ/ቁ 897 ስር እንደተደነገገው በግልጽ የተደረገ ኑዛዜ የሚረጋገጠው የኑዛዜውን ጽሁፍ በማቅረብ ሲሆን ኑዛዜውን ለማስፈፀም በማናቸውም ሌላ መንገድ ለማስረዳት አይቻልም በማለት የሚደነግግ በመሆኑ ክርክራቸው ህጉን መሰረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም። ከዚህም ሌላ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 17429 በሰጠው ትርጉም

በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ ኑዛዜው መነበቡን የሚያመለክት ከሆነ በግልፅ "ተነቧል" የሚል ቃል አለመኖሩ ብቻ ኑዛዜውን ፈራሽ የሚያደርግ ስላለመሆኑ የተወሰነበት እንጂ ይህ ትርጉም ኑዛዜው ከመነሻው በምስክሮች ፊት መነበቡን የሚያመለክት እንዳልሆነ በተረጋገጠበት እንደተያዘው ጉዳይ ባለ ሁኔታ ላይ ተፈፃሚነት የሚኖረው አይደለም፡፡

በአጠቃላይ ወ/ሮ አልማዝ አለማየሁ ትተውት አልፈዋል የተባለው ኑዛዜ በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ ፎርምን ተከትሎ የተሰጠ አለመሆኑን የስር ፍርድ ቤቶች በማጣራትና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ የወሰኑ በመሆኑ ውሳኔው የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 83577 በቀን 09/11/2011 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 243422 በቀን 01/07/2012 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ዕግድ ካለ ተነስቷል፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሠበር መዝገብ ቁጥር 195656

ሀምሌ 29 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንከር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ከሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1ኛ ወ/ሮ የጌራወቅ አንጋጋው

2ኛ ወ/ሮ ትዕግስት አንጋጋው

3ኛ ወ/ሮ በለጡ አንጋጋው

4ኛ አቶ አንበርብር አንጋጋው

5ኛ አቶ ናኦድ አንጋጋው

6ኛ ወ/ሮ አስቴር አንጋጋው

7ኛ አቶ ምኒልክ አንጋጋው

8ኛ አቶ አግደው አንጋጋው

9ኛ ወንደወሰን አንጋጋው

ተጠሪዎች፡- 1ኛ የካ /ክ/ከ ወረዳ 06 አስተዳደር

2ኛ ሲስተር ብርሃኔ ሰማኝ

3ኛ አቶ አስራት ገብረ ቃል

4ኛ ወ/ሮ አሰገደች ደበበ

5ኛ አቶ አምባቸው ታረቀኝ

6ኛ አቶ ደበበ ዘውገ

7ኛ አቶ ተክላይ ካሳ

8ኛ አቶ ገዛኸኝ ሽጉጤ

9ኛ አቶ ካሳ ፍሰሃ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚህ አግባብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የከተማ ይዞታ የሚመለከት ነው። የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 251007 በቀን ሰኔ 15/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሥር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማጽናት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ያደረገበትን ትዕዛዝ በመቃወም ነው።

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የካ ምድብ ፍታብሄር ችሎት ባቀረቡት ክስ አውራሻችን ቦታውና አዋሳኙ በክሱ ውስጥ የተገለፀዉን 513 ካ.ሜ የሆነው የቤት ቁጥር 390 ጎን ያለውን ይዞታ በውል ከባለቤቶቹ በመግዛት ለቤተሰቦቻቸው መኖሪያ እንዲሆን አንድ ጣራ ግርግዳ የሚጋሩትን እና በአንድ ግቢ ውስጥ የሚገኙትን ቤቶች በመሥራት እስከ 1969 ዓ.ም ድረስ አምስቱን ደጃፍ ቤቶች ለተለያዩ ሰዎች ሲያከራዩ ቆይተው እነዚህን ቁጥራቸው ከ391-395 ድረስ ያሉ ቤቶች 1ኛ ተጠሪ ትርፍ ነው በማለት በመውረስ በህገ-ወጥ መንገድ በመውሰድ ከ2ኛ-6ኛ ላሉ ተጠሪዎች በማከራየት እንዲሁም ቤቱን በእነዚህ ተከራዮች ስም ለማዛወር በእንቅስቃሴ ላይ የሚገኝ በመሆኑ፣ 1ኛተጠሪ ቁጥሩ 391Aኤ የሆነው ለልጆች መኝታ ቤት የምንጠቀምበትን አንድ ክፍል ቤት በ1981 ዓ.ም በሩን በመስበር ለ9ኛ ተጠሪ አከራይቶ ያለግባብ ጥቅም እያገኘ መሆኑ፤ እንዲሁም 7ኛ ተጠሪ የ9ኛ ተጠሪ ልጅ በቤቱ እየኖረ የሚገኝ በመሆኑ፤

8ኛ ተጠሪ ደግሞ ለጥበቃ ሠራተኛ የተሠራውን የቤት ቁጥር 39 B በማያውቁት መንገድ በመያዝ እየተገለገለ የሚገኝ መሆኑን በመጥቀስ የቀበሌው መስተዳደር አምስት አባላት ያሉት ቡድን ጥቅምት 20 ቀን 1968 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ 11 ክፍል ቤቶች ለአውራሻችን የተፈቀደ መሆኑን ገልፆ ነገር ግን ጋራዥና የእንጀራ መጋገሪያ ቤቶች በጋራ እንድንጠቀም በመወሰኑ አውራሻችን ውሳኔውን በመቃወም ለመስተዳደሩ የንዑስ ወረዳ 04 አዝማች ቡድን በማቅረብ ኮሚቴው ህዳር 23 ቀን 1968 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔም ትርፍ ናቸው የተባሉት ከመኖሪያ ቤቱ ጋር የተያያዙት አራት ክፍል ቤት ከነሰርቪሱ ስለሆኑ በትርፍነት ስለማይቆጠሩ በይዞታቸው ሥር እንዲቆዩ ሌላ ትርፍ ሆኖ የተገኘውን አራት ክፍል ከነሰርቪሱ እንዲያስረክቡ በማለት የወሰነ ቢሆንም 1ኛ ተጠሪ ሊያስረክበን ስላልፈቀደ ቤቱን ለቀው እንዲወጡና ያላግባብ ያገኙትን ገቢ እንዲከፍሏቸው አመልክተዋል፡፡

ተጠሪዎች ከ9ኛ ተጠሪ ውጭ መልሳቸውን ያቀረቡ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ በቀን ሐምሌ 5/2010 ዓ. ም በተጻፈ መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቀወሚያ በማለት አመልካቾች ቤቱ አላግባብ በትርፍነት ተወስዶብኛል የሚሉ ከሆነ ለኘራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 110/87 መሠረት በሰዓቱ ከሚያቀርቡ በስተቀር ለፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ሊያቀርቡ ስለማይገባ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፤ ክርክር የቀረበባቸውን ቤቶች መንግስት ከ1969 ዓ.ም ጀምሮ እያስተዳደራቸው የሚገኝ በመሆኑ አመልካቾች ክስ የማቅረብ መብትና ጥቅም የላቸውም በማለት ተከራክሯል ። ከ2ኛ-6ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎች በበኩላቸው አመልካቾች ቤቶቹ በአዋጅ ቁጥር 47/67 ለአመልካቾች አባት ተፈቅዶላቸው ባለንብረት የሆኑባቸውን ማስረጃዎች ስላላቀረቡ ክሱን ለማቅረብ መብትና ጥቅም የላቸውም ፤ አመልካቾች ቤቶቹ የተወረሱ መሆናቸውን የሚያምኑ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 110/87 በአንቀፅ 3/1/ አግባብ ቤቶቹ የተወረሱት በቀላጤ በመመሪያ ወይም ደግሞ በቃል ትዕዛዝ መሆኑን በማስረዳት ውሳኔ በማሰጠት ያልቀረቡ በመሆኑ ክሱ የክስ ምክንያት የለውም ተበሎ ውድቅ ይደረግልን በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማቅረብ ተከራክረዋል፡7ኛ ተጠሪ ደግሞ የቤት ቁጥር 391A አመልካቾች 7ኛ ተጠሪን ሊከሱ የማይገባቸው መሆኑን፤ ቤቱ ውስጥ የሚኖረው በጥገኝነት መሆኑን፤ አሁን 9ኛተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ አስረክቦ የታሸገ መሆኑን ገልጸ ተከራክሯል፡፡ 8ኛ ተጠሪ በበኩሉ የቤት ቁጥር 391B ቤቱን ያገኘው በስጦታ ውል ከአመልካቾች አባት መሆኑን በመጥቀስ ክሱ የቀረበው ከ40 ዓመት በኋላ በመሆኑ በይርጋ ሊታገድ የሚገባ መሆኑን ፤ የቤቱ ግምት በአግባቡ ያልተገመተ መሆኑን ጠቅሰው ክሱ በማስረጃ የተደገፈ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክር ተመልክቶ ህዳር 5 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ብይንም ቤቶቹ ከ1969 ዓ.ም ጀምሮ ትርፍ ናቸው በሚል በ1ኛ ተጠሪ ተወርሰው

መያዛቸው በአመልካቾች የታመነ መሆኑን ፤ በመንግስት እጅ ለረጅም ጊዜ የተያዘ ቤት ይመለስልኝ ጥያቄ ለፍ/ቤት የሚቀርበው በአዋጅ ቁጥር 47/67 ተጠቅሶ ከሚመለከተው አካል የተረጋገጠ ከሆነ ወይም በአዋጅ ቁጥር 110/87 መሠረት በኘራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቀርቦ ባለመብትነቱ ተረጋግጦ የተወሰነ ከሆነ ለዚህ ማስረጃ ሲቀርብ መሆኑን አመልካቾች ግን ከሚመለከተው አካል ተረጋግጦ የተሰጣቸው ካርታ መኖሩን ወይም በአዋጅ ቁጥር 110/87 መሠረት ባለመብት የሆኑበትን ውሳኔ አለማቅረባቸውን በመጥቀስ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም በማለት በብይን ዘግቶታል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤቱም የሥር ፍ/ቤቱን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው አመልካች መስከረም 8/2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሠረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎቱ እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም 1ኛ ተጠሪ በሰጠው መልስ ክርክሩ ቁጥራቸው 391-395 እና 390 ኤ፣ 390 ቢ ቤቶችን በተመከተ መሆኑን ገልጾ አቅርቦ እያለ ፍ/ቤቱ የቤት ቁጥር 391 ኤ እና 391 ቢ በሆኑ ቤቶች ላይ ምንም አይነት ክርክር ባልቀረበበት ብይን መስጠቱ ስህተት መሆኑን፣ ክስ የቀረበባቸው ቤቶች የአመልካቾች እንደሆኑ በማስረጃ አስደግፈን አቅረበን እያለ የስር ፍ/ቤት በአዋጁ ቁጥር 47/67 መሰረት ያልተፈቀደ በመሆኑ በፍ/ቤቱ ከሰው ሊጠይቁ አይችሉም ማለቱ ስህተት መሆኑን፣ ጥያቄው ያላግባብ ተወረሰብን ሳይሆን ያላግባብ የተወሰዱ ቤቶች እንዲመለሱ የመፋለም ዳኝነት ሆኖ እያለ፣ በቅፅ 003 ላይ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን የወረሰው ከአውራሻቸው ሳይሆን አውራሽ አባታቸውን አስረው ከእናታቸው በማስገደድ መሆኑን በመጥቀስ ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ለፍ/ቤቱ ያመለከትን ቢሆንም ማስረጃዎቹ ሳይሰሙ መወሰኑ አግባብ አለመሆኑን፣የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉዳዩ በፕሪቬታይዜሽን ኤጀንሲ ሊታይ ማለቱ ኤጀንሲው የፈረሰ በመሆኑ ጉዳዩን ያለ ፍትህ የሚያስቀር በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፣ የስር ፍ/ቤት አዋጅ ቁጥር 47/67ን የተረጎመበት አግባብ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በስር ፍ/ቤት አላግባብ የተያዘባቸው ቤት እንዲለቀቅላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት የዳኝነት ስልጣን የለኝም በማለት የወሰነበትን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 47/67 እና 110/87 እንዲሁም በሰ/መ/ቁ 31682 በሆነ መዝገብ ከተሰጠ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

1ኛ ተጠሪ በቀን ታህሳስ 24/2013 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት መልስ በስር ፍ/ቤት የቀረበው ክስ በፍ/ቤቱ ሊታይ የማይችል ስለመሆኑ በተመሳሳይ ጉዳይ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 45161

ቅፅ 10 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት መሆኑን፣ሁሉንም ብይን የተሰጣባቸውን ቤቶች በቃል ክርክር ወቅት አንስተው የተካራከሩበት መሆኑን፣ ለክርክር የቀረቡት ቤቶች በአዋጁ ስላለመወረሳቸው አመልካቾች ማስረጃ ያላቀረቡና 1ኛ ተጠሪ ግን ማስረጃ ያቀረበ መሆኑን፣ የቤት ቁጥር 391 በአዋጁ 47/67 ከተወረሰ በኋላ ቤቱን ሀእና ለ በማለት በመከፍፈል እያስተዳደረው የሚገኝ መሆኑ ቤቶቹ በመንግስት እንደተወረሰ አመልካቾች ያመኑ መሆኑን በመግለፅ የስር ፍ/ቤት ብይን ሊፀና ይገባል በማለት የተከራከረ ሲሆን ከ 2ኛ-6ኛ ያሉ ተጠሪዎች በበኩላቸው የካቲት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ቤቶቹ ከተወረሱ 40 ዓመት ስለሆናቸው በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተወረሱ ንብረቶች የባለቤትነት ሁኔታ አጣርቶ የመወሰን ስልጣን የተሰጠው በአዋጅ ቁጥር 110/87 አንቀፅ 4/1/2/ መሰረት ለኢትዮጲያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ መሆኑን፣ ቤቶቹ በአንድ ጣራና ግድግዳ ስር የተሰሩ 5 ደጃፍ ቤቶች መሆናቸውንና የአመልካቾች አውራሽ ትርፍ ቤት ስላለው መርጦ በመውሰድ ሌሎቹ በህጉ መሰረት የተወረሱ መሆናቸውን በመጥቀስ የስር ፍ/ቤት ብይን ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

8ኛ ተጠሪ ጥር 21 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካቾች ቤቱ ከአዋጅ ውጭ ያላግባብ ተወርሶ ከሆነ መብታቸውን ተጠቅመው ስልጣን ለነበረው አካል ያላቀረቡና ያልጠየቁ መሆኑን፣ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት መ/ቁ 31682 በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተወርሰዋል ተብለው በመንግስት ተቋማት ቁጥጥር ስር ያሉ ቤቶች ጋር በተያያዘ ይመለሱልኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መሰረት በማድረግ ፍ/ቤቶች መውረስና አለመውረስን በተመለከተ ማስረጃዎችን መርምሮ ውሳኔ ለመስጠት ስልጣን ያልተሰጣቸው መሆኑን፣ 8ኛ ተጠሪ የያዙት ቤት አባታቸው አቶ ሽጉጤ ቡሌ ከአመልካቾች አባት በስጦታ ያገኙት መሆኑ በቀበሌው ማስረጃ መቀበያ መረካከቢያ ደረሰኝ ላይ በማህተም ተረጋግጦ ማህደር ላይ የተቀመጠ መሆኑን፣ ስለሆነም የሚጠየቁበት አግባብ እንደሌለ ተከራክረዋል፡፡ 7ኛ እና 9ኛ ተጠሪ በፍ/ቤቱ መጥሪያ ቢላክላቸውም መልስ ያላቀረቡ በመሆኑ ችሎቱ በቀን መጋቢት 16 ቀን 2013 በዋለው ችሎት መልስ የማቅረብ መብት ቀሪ በማድረግ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች የመልስ መልስ በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ እና የክርክር ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመለከት ችሎቱም ከሰበር ቅሬታው አኳያ እና ከስር ፍ/ቤት መዝገብ ይዘት አንፃር አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ ተመርምሮአል፡፡ በመሰረቱ ለረዥም ጊዜ በመንግስት ቁጥጥር ስር የነበረን ቤት ይለቀቅልኝ በሚል አቤቱታ የሚያቀርብ ወገን ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተፈቀደለት ስለመሆኑ ወይም ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ለሚመለከተው አካል ጥያቄውን አቅርቦ ውሳኔ

አግኝቶ ባለመብት መሆኑን ማስረዳት ያለበት ስለመሆኑ ከመስረዳት ሸክም ከመክሰስ መብት አንፃር በሰ/መ/ቁ 14094 እና 45161 አስገዳጅ ውሳኔ ተሰጥቷል። ይህንን ማስረጃ የሚሰጠውን በጉዳዩ ላይ የዳኝነት ስልጣን ያለውን አካል በተመለከተ አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ከአዋጁ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ወገኝ ጉዳዩን ማቅረብ ያለበት ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 110/87 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጡት አዋጅ ቁጥር 193/92 እና 572/2000 የሚያሳዩ ሲሆን በዋነኛነትም የአዋጅ ቁጥር 110/87 አንቀፅ 4/2/ /ሐ/ ከአዋጁ ውጪ የተወሰደን ንበረት ባለቤትነት በተመለከተ በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ መረጃዎችን እያጣራ ተገቢውን ውሳኔ የሚሰጠው ይኸው አካል መሆኑ በግልፅ ተመልክቷል።

በዚህ አግባብም በሰበር መዝገብ ቁጥር 30631፤30701 እና በተመሳሳይ መዝገቦች በተሰጠው አስገዳጅ ውሳኔም ለረዥም ጊዜ በመንግስት ቁጥጥር ስር የነበረን ቤት ከአዋጅ ውጪ ወይም በህገ ወጥ መንገድ በመንግስት የአስተዳዳር አካል ተወስዶብኛል በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎችን እንዲሁም ከምርጫ ቤት ጋር በተያያዘ የምርጫ ቤቱን፤ በቀላጤ፣በቃል ትዕዛዝ ወይም በመመሪያ ከህግ ውጪ ተወሰደብኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎች መርምሮ የመወሰን ስልጣን ያለው የፕራይቬታዜሽን ኤጀንሲ ለመሆኑ አስገዳጅ ውሳኔ ተሰጥቷል። አሁን በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች ክሳቸውን ያቀረቡት 1ኛ ተጠሪ ቁጥራቸው ከ391-395 ድረስ ያሉ ቤቶችን ትርፍ ነው በማለት በመውረስ በእገ-ወጥ መንገድ በመውሰድ ከ2ኛ እስከ 6ኛ ለተመለከቱት ተጠሪዎች ማከራየቱን የቤት ቁጥር 391Aን በተመለከተም ከ1981 ዓም ጀምሮ በህገወጥ መንገድ በመውሰድ ለ9ኛ ተጠሪ በማከራየት እየተጠቀመ መሆኑን በመግለፅ ሲሆን አመልካቾች አውራሽ አባታችንን በማሰር እናታችንን በማስፈረም የተዘጋጀ ነው ቢሉም ቁጥራቸው ከ391-395 ያሉት ቤቶች የተረከበበትን በ24/03/1968 ዓም የተዘጋጀውን ቅፅ 003 በማቅረብ ቤቶቹ ለረዝም ጊዜ በአስተዳደር አካሉ ቁጥጥር ስር የቆዩ መሆኑን አሳይቷል።ይህ ከሆነ ደግሞ የስር ፍርድ ቤት አከራካሪዎቹን ቁጥራቸው ከ391-395 የተመለከቱትንና ቁጥሩ 391A የሆነው ቤት አስመልክቶ ለፕራይቬሽን ኤጀንሲ ቀርቦ ባለመብትነታቸው ተረጋግጦ ወይም በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት በወቅቱ በተቋቋመው አካል ተረጋግጦ የተሰጠው ውሳኔ በሌለበት በቀጥታ ቤቶቹ በህጉ አግባብ ተወርሰዋል ወይስ አልተወረሱም በማለት የመወሰን ስልጣን የለኝም በማለት የአመልካቾችን ክስ ከነዚህ ቤቶች አንፃር ውድቅ ማድረጉ የሚነቅፍ ሆኖ አልተገኘም።

በ8ኛ ተጠሪ ቁጥጥር ስር የሚገኘውን የቤት ቁጥር 391B በተመለከተ በሰበር መዝገብ ቁጥር 37281 በተሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ አግባብ ቤቱ ተወርሶ ለረዝም ጊዜ በመንግስት የአስተዳደር አካል ቁጥጥር ስር ለመሆኑ አመላካች ማስረጃዎች ያአልቀረቡ በመሆኑና አመልካቾች ክስ ሲያቀርቡም

ሆነ 1ኛ ተጠሪ መልስ ሲሰጥ በዚሁ አግባብ ያልተከራከረ ሆኖ እያለ 8ኛ ተጠሪም የአመልካቾች አውራሽ ለአባታቸው በስጦታ የሰጧቸው የግል ቤታቸው መሆኑን ጠቅሰው እየተከራከሩ የስር ፍርድ ቤት ይህንን ቤት አስመልክቶ የቀረበውን ክርክር ከላይ ከተመለከቱት ቤቶች ክርክር ለይቶ በማየት የግራቀኙ የመፋለም ክርክር በመመርመር ተገቢውን ውሳኔ ሊሰጥ ሲገባ ከላይ ከተመለከተው ክርክር ጋር አጠቃልሎ በማየት የአመልካቾችን በቤትቁጥር 391B ላይ ያቀረቡትን ክስ ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት በኮመ/ቁ 134862 በ05/03/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት አከራካሪዎቹን የቤት ቁጥራቸው ከ391-395 የተመለከቱትንና ቁጥሩ391A የሆነውን ቤት አስመልክቶ የሰጠውና እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ251009 በቀን 15/10/2012 ዓም በዋለው ችሎት ይህንን የውሳኔ ክፍል በማፅናት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል

2. አመልካቾች በየካ ክ/ከ/ወረዳ 06 የሚገኘውን የቤትቁጥር 391B የሆነውን ቤት አስመልክቶ በ8ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበውን ክስ ጥያቄው ለፕራይቬታዜሽን ኤጀንሲ ቀርቦ ባለመብትነታቸው ተረጋግጦ ወይም በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት በወቅቱ በተቋቋመው አካል ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ በሌለበት በቀጥታ ቤቱ በህጉ አግባብ ተወርሰዋል ወይስ አልተወረሱም በማለት የመወሰን ስልጣን የለኝም በማለት የግራቀኙን የመፋለም ክርክር ውድቅ ማድረጉና ይህ ውሳኔ በከፍተኛው ፍርድ ቤት መፅናቱ መሰረታዊ የህግ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይኸው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡ የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የጉዳዩን መዝገብ በማንቀሳቀስ አመልካቾችና 1ኛ ተጠሪ አከራካሪውንቤት አስመልክቶ ያቀረቡት የመፋለም ክርክር 8ኛ ተጠሪ ካቀረቡት መቃወሚያ በመነሳት መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ341(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡

3. የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ በመጣበት አኳኃን ይመለስ፡፡

4. ሚያዝያ 04 ቀን 2013 ዓም በዋለው ችሎት በየካ ክ/ከ/ወ/06 የቤ/ቁ391A እና392 የሚገኙ ቤቶች አስመልክቶ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሳ ታዟል፡፡

5. ግራቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ

<u>ጉዳዩ ተገቢውን እልባት ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡</u>

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 195919

ቀን ፡- ጥቅምት 01 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኘ

አመልካች ፡- 1. ወ/ሮ ጌጤ ዶሪ

2. ወ/ሮ አበራሽ ዶሪ

3. ወ/ሮ ባዩ ዶሪ

4. ወ/ሮ ዘሪቱ ዶሪ

ተጠሪ ፡- 1. አቶ ዶሪ ሻሎ

2. አቶ ዓለሙ ጉጆ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ከሳሾች ሲሆኑ ተጠሪዎች ተከሳሾች ነበር፡፡ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ወላጅ እናታችን ወ/ሮ ማሬ በዳኔ በ21/08/1990 ዓ/ም የሞቱ ሲሆን አመልካቾች የሟች ልጆችና ወራሾች ነን፤ በይርጋ ጨፌ ወረዳ በአዳሜ ቀበሌ አስተዳደር ክልል ሥር ከአባታችን ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በጋራ ያፈሩት ቤት አላቸው፡፡ ንብረቱን ወራሾች በማናውቀው ሁኔታ በ15/05/2010 ዓ/ም በተጻፈ ውል 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ በሽያጭ መኖሪያ ቤቱን ከነይዞታው አስተላልፏል፡፡ በፍ/ሕ/ቁ. 1715(2) መሠረት ውሉ ፈርሶ ንብረቱን ለወራሾች እንዲመልሱ እንዲወሰንልን ሲሉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ የሠጡት መልስ ይዘት ውሉ የተደረገው በ21/09/2009 ዓ/ም ነው፡፡ የተሸጠውም 20 በ17 ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ መኖሪያ ቤት ነው፡፡ የሽያጭ ውሉ ከባለቤቱ ወ/ሮ ምትኬ ደሮ እና ከሌሎች ሦስት ወራሾች ጋር በብር 50,000.00 የተደረገ ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪም ንብረቱን ከገዛ በኋላ ማሻሻያ ሥራ ሰርቶበታል፡፡ የእናታቸው ድርሻ ከተሸጠ ውርሱ ተጣርቶና ድርሻ ተለይቶ ሊቀርብ ሲገባ በዚህ አግባብ ያልቀረበ ክስ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ንብረቱን ገዝቻለሁ፡፡ የኔ ባይ ከመጣ ለመከራከርና ለማስቀረት ተዋዋዮች ግዴታ ገብተዋል፡፡ ንብረቱን የማደስና የማሻሻያ ሥራ ሰርቻለሁ፡፡ አመልካቾች ድርሻቸውን ከሻጮች ይጠየቁ እንጂ ውሉ ሊፈርስ አይገባም ብለዋል፡፡ የይርጋ ጨፌ ወረዳ ፍርድ ቤት ግራቀኙን አከራክሮ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 41857 እና 47378 ላይ በቅጽ 10 እንደታተመ በሠጠው ትርጉም መሠረት ጠንቃቃ ገዥ ያደረገው የሽያጭ ውል ሊፈርስ አይገባም፡፡ ወራሾች ድርሻቸውን ከሽያጭ ገንዘቡ ከሻጮች ሊቀበሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በየደረጃው የሚገኙ ፍርድ ቤቶች ውሳኔውን አጽንተዋል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘትም በተጠቀሱት የሰበር ችሎት ውሳኔዎች ወራሾች ብቸኛ ወራሽ ነን በማለት ንብረቱን በስማቸው አዛውረው ያደረጉትን ሽያጭ የሚመለከት ነው፤ በተያዘው ጉዳይ የንብረቱ ሻጭ ወራሾች ሳይሆኑ 1ኛ ተጠሪ ናቸው፡፡ የንብረቱ ሥመ-ሀብትም አልተዛወረም፤ በጋራ ስናስተዳድረው የነበረን ንብረት ነው 1ኛ ተጠሪ የሸጡት፡፡ በውል አዋዋይ ፊት የተደረገ ውል አይደለም፤ ውሉም ሕገ-ወጥ በመሆኑ ሊፈርስ ይገባል የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ የሠበር ውሳኔዎች ተጠቅሰው ውሉ ሊፈርስ አይገባም መባሉ ሕጋዊነቱን ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ አዟል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት መልስ ይዘትም በሥር ፍርድ ቤቱ የተጠቀሰው የሠበር ውሳኔ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው ነው፡፡ አመልካቾች ንብረቱ ሲሸጥ ያውቃሉ፡፡ ውሳኔው ተገቢ ነው የሚል ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ አመልካቾች ውሉ ሲፈጸም እያወቁና ንብረቱ ማሻሻያ ሥራ ሲሰራበት እያዩ ቆይተው ያቀረቡት ክስ ተገቢነት የለውም፡፡ የተሸጠው ቤት እንጂ ቦታ አይደለም፤ ውሉ ሕጋዊ ስለሆነ ሊፈርስ አይገባም፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል ብለዋል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር፣ በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘው ጭብጥ፣ በሥር ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮችና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ወላጅ እናታችን ሚች ወ/ሮ ማሬ በዳኔ ልጆችና ወራሾች ነን፤ በይርጋ ጨፌ ወረዳ በአዳሜ ቀበሌ አስተዳደር ክልል ሥር ከአባታችን ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በጋራ ያፈሩት ቤት አላቸው፡፡ ንብረቱን ወራሾች በማናውቀው ሁኔታ በ15/05/2010 ዓ/ም በተጻፈ ውል 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ በሽያጭ መኖሪያ ቤቱን ከነይዞታው አስተላልፏል፤ ውሉ ፈርሶ ንብረቱን ለወራሾች እንዲመልሱ እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ 20 በ17 ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ መኖሪያ ቤት ለ2ኛ ተጠሪ መሻጣቸውን ገልጸው ውርሱ ተጣርቶና ድርሻ ተለይቶ ያልቀረበ ክስ ተቀባይነት የለውም ብለዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ንብረቱን ገዝቻለሁ፡፡ ንብረቱን የማደስና የማሻሻያ ሥራ ሰርቻለሁ፡፡ አመልካቾች ድርሻቸውን ከሻጮች ይጠየቁ እንጂ ውሉ ሊፈርስ አይገባም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ውል ሊመሠረት የሚገባው ችሎታ ባላቸው፣ በተዋዋዮች ነጻ ፈቃድ፣ የሚቻልና ሕጋዊ በሆነ ዓላማና ጉዳይ ላይ በሕግ የተመለከተውን የውል አጻጻፍ ፎርም ተከትሎ ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ሕ/ቁ. 1678 ላይ ተመልክቷል፡፡ ውሉ የአመሠራረት ጉድለት ካለበት ተዋዋዮች/መብት ያገኙ ሰዎች ሥምምነቱ ፈራሽ እንዲሆን በፍ/ሕ/ቁ. 1808 አግባብ ክስ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ አመልካቾችም በዚህ አግባብ ውል ሰጭ የሆኑት አባታቸው በሙሉ ንብረቱ ላይ ውሉን ለመፈጸም መብት የላቸውም፣ በንብረቱ የሚች እናታችን ግማሽ ድርሻ ላይ ወራሾች ሳንፈቅድና ሳንስማማ የተደረገው ውል ፈራሽ እንዲሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪዎች የንብረቱ ግማሽ ባለድርሻ ወራሾች የሆኑት አመልካቾች አይደሉም የሚል ግልጽ ክርክር የላቸውም፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም አመልካቾች በንብረቱ ላይ ድርሻ ያላቸው መሆኑን በማረጋገጥ ከሽያጭ ገንዘቡ 1ኛ ተጠሪ ድርሻቸውን እንዲከፍሏቸው ወስኗል፡፡ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም ከሽያጭ ገንዘቡ ሳይሆን ውሉ ፈርሶ ንብረቱን መረከብ አለብን በሚል ነው፡፡

2ኛ ተጠሪ በዚህ ችሎት ደረጃ የሚከራከሩት አመልካቾች ውሉ ሲፈጸም እያወቁና ንብረቱ ማሻሻያ ሥራ ሲሰራበት እያዩ ቆይተው አሁን ያቀረቡት ክስ ተገቢነት የለውም በማለት ነው፡፡ ከዚህ ክርክር በመነሳት 2ኛ ተጠሪ መብቱ የተላለፈላቸው ጥበቃ ሊደረግለት በሚገባ ግብይት መሆን አለመሆኑን መመልከት ተገቢ ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪ ግዥ ሲፈጽሙ አንድ ጠንቃቃ ገዥ በሕግ ሆነ በአሠራር ሊያደርገው የሚገባውን ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ሕግ የተለየ ጥበቃ ስለሚያደርግ የሀብትነት ሠነድ ስለሚወጣበት፤ ሠነዱ ስለሚገኝበት የሥራ ክፍል፣ ውሉ ስለሚፈጸምበት እና ንብረቱ ስለሚተላለፍበት ሥርዓት የተገለጸውን መከተል ዴታ ይጥላል፡፡ ሽያጭ ውል የሚፈጸምበት ንብረት ላይ በሕግ መብት ያላቸው ሰዎች እነማን እንደሆኑ፣ ቦታው ላይ ቤት ያረፈበትና ስለቤቱ የሚመለከቱ ሠነዶች በቤቱ ባለሀብት ሥም በማይንቀሳቀስ ሀብት ምዘገባ ክፍል መገኘቱና ውሉ የፍ/ሕ/ቁ. 2878 በሚያዘው አግባብ ንብረቱ በሚገኝበት ሥፍራ ባለው የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዘገባ ክፍል እንዲመዘገብ ይጠበቃል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ውሉን የፈጸሙት ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ሲሆን የንብረቱ ግማሽ ባለድርሻ ወራሾች የሆኑት አመልካቾች በሽያጭ ውሉ አለመሳተፋቸው ከትክክለኛው ባለመብት ያልገዙ መሆኑን ያሳያል፡፡ አመልካቾች የሽያጭ ሂደቱን በጊዜው ያውቁ ነበር የሚለው የ2ኛ ተጠሪ ክርክርም ሌሎች ወራሾች እንዳሉ እያወቁ ተገቢውን ጥንቃቄ ሳያደርጉ የገዙት መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ውሉም በማይንቀሳቀስ ሀብት ምዘገባ ክፍል የተመዘገበ አይደለም፡፡ ስለሆነም

የተደረገው የሽያጭ ውል ተገቢውን ሕግና አሠራር ተከትሎ የተፈጸመ ባለመሆኑ ውሉ ፈራሽ ሊሆን ይገባል ብለናል፡፡

በሥር ፍርድ ቤት የተጠቀሱት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 41857 እና 47378 የሠጣቸው ውሳኔዎችና አስገዳጅ ትርጉሞች የሽያጭ ውሉ ጥበቃ እንዲደረግለት የሚያዘው ንብረቱ በሻጭ ስም ተዛውሮ የነበርና ገዥው ተገቢው ጥንቃቄ አድርጎ በሕግ በተመለከተው ሥርዓት ለተፈጸመ ግብይት ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ 2ኛ ተጠሪ ተገቢው ጥንቃቄ አድርገው የፈጸሙት የሽያጭ ውል ባልሆነበት ሁኔታ ውሉ ሊፈርስ አይገባም ተብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ውሳኔ

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 76667 የካቲት 24 ቀን 2012 ዓ/ም፣ የጌዴኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 15110 ታህሳስ 03 ቀን 2012 ዓ/ም እና የይርጋ ጨፌ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 012032 መስከረም 06 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. በይርጋ ጨፌ ወረዳ በአዳሜ ቀበሌ አስተዳደር ክልል ሥር የሚገኘው ቤት በተጠሪዎች መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል ፈራሽ ነው በማለት ወስነናል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ንብረቱን ለአመልካቾችና ለ1ኛ ተጠሪ እንዲያስረክቡ ተወስኗል፡፡

3. 2ኛ ተጠሪ የሽያጭ ገንዘቡንና ለማሻሻያ ሥራ ያወጡት ወጪን በተመለከተ 1ኛ ተጠሪን ከመጠየቅ ይሕ ውሳኔ አያግድም፡፡

4. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የይርጋ ጨፌ ወረዳ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲያስፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- በዚህ ችሎት የካቲት 17 ቀን 2013 ዓ/ም የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁ. 196128
ቀን ፡- ሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ወ/ሮ መቅደስ ወልደማርያም ፡- ጠበቃ ነብዩ ምክሩ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ታምሩ በቀለ፡- ጠበቃ ዘውዱነህ ዘኪዮስ ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች ተቃዋሚ ሲሆኑ ተጠሪ የስር አፈጻጸም ከሳሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ከወ/ሮ ኤደን ወንድይፍራው እና ኤድሰን ካርጎ ኃ/የተ/የግል ማሕበር ጋር ተከራክረው ገንዘብ እንዲከፈላቸው በመወሰኑ ምክንያት ውሳኔውን ለማስፈጸም የአፈጻጸም ክስ አቅርበዋል፡፡ ለፍርዱ ማስፈጸሚያ የሚሆን በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 የቤት ቁጥር 1137 የሆነ የ1ኛ የፍርድ ባለዕዳ ወ/ሮ ኤደን ወንድይፍራው ንብረት ነው በማለት ለእዳው መክፈያ እንዲሆን ጠይቀው አፈጻጸም ችሎቱ ንብረቱ እንዲከበር ያደረገ ሲሆን አመልካች በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት ንብረቱ እንዲለቀቅ የተቃውሞ ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአፈጻጸም የተከበረው ንብረት የሚች ወንድይፍራው መንገሻና የእኔ ያልተከፋፈለ የጋራ ሀብት ነው፡፡ የሚች የውርስ ሀብትም በፍርድ ቤት በመጣራት ላይ ያለ ስለሆነ የውርስ ድርሻ አልተለየም፡፡ በመሆኑም ንብረቱ ተሸጦ ለፍርዱ ገንዘብ ማስፈጸሚያ ሊውል አይገባም ብለዋል፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ክርክር የንብረቱ ስመ-ሀብት

ወደወራሾች ዞሯል፣ ካርታውም በስማቸው ይገኛል፤ ይሕም የውርስ ድርሻቸው መለየቱን ያሳያል፡፡ ስለሆነም በ1ኛ የፍርድ ባለዕዳ ድርሻ ላይ የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሰጠቱ ተገቢ ነው የሚል ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አከራክሮ የውርስ ንብረት ያልተከፋፈለ የወራሾች የጋራ ንብረት ነው፡፡ ንብረቱ በአመልካች እና በሌሎች ወራሾች ስም መመዝገቡ ተረጋግጧል፡፡ ይሕ በሆነበት ሁኔታ የውርስ ሀብት ማጣራት ሂደት ይጠበቅ መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ አፈጻጸሙ ንብረቱ ላይ ሊቀጥል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ ባለመቀበል ሠርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም የውርስ ሀብቱ በመጣራት ላይ ያለ ነው፡፡ የ1ኛ የፍርድ ባለዕዳ የውርስ ድርሻ አልተለየም፡፡ ስለሆነም የአፈጻጸም ክርክሩ የውርስ ማጣራት ሂደቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ሊጠብቅ ይገባል የሚል ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ የውርስ ድርሻው ተለይቶ ባልታወቀበትና አመልካች ይሕንን እየተቃወመ አፈጻጸሙ በንብረቱ ላይ መቀጠሉ ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ በማዘዙ ተጠሪ ያቀረቡት መልስ ንብረቱ ላይ የሚስትነትና የወራሽነት ማስረጃ ወጥቶ ስመ-ሀብቱ ተዛውሯል፡፡ የውርስ ማጣራት አቤቱታ ያቀረበ ሰው ካለ በራሱ የሚከራከር እንጂ አመልካች ሌሎች ሰዎችን ወክለው ሊከራከሩ አይችሉም፡፡ የፍርዱ ገንዘብ ብር 173,283.00 ነው፤ የ1ኛ የፍርድ ባለዕዳ የውርስ ድርሻ ከዚህ ገንዘብ በላይ ነው፡፡ በድርሻቸው ላይ አፈጻጸሙ መቀጠሉ ተገቢ ነው ብለዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር፣ የሠበር አጣሪ ችሎት ከያዘው ጭብጥና በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ ከወ/ሮ ኤደን ወንድይፍራው እና ኤድሰን ካርጎ ኃ/የተ/የግል ማሕበር ጋር ተከራክረው ገንዘብ እንዲከፈላቸው በመወሰኑ ምክንያት ለፍርዱ ማስፈጸሚያ የሚሆን በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 የቤት ቁጥር 1137 የሆነ የ1ኛ የፍርድ ባለዕዳ ወ/ሮ ኤደን ወንድይፍራው ንብረት ነው በማለት ለእዳው መክፈያ እንዲሆን ጠይቀው አፈጻጸም ችሎቱ ንብረቱ እንዲከበር አድርጓል፡፡ አመልካች በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት ንብረቱ እንዲለቀቅ የተቃውሞ ማመልከቻ ያቀረቡት የተከበረው ንብረት የሚች ወንድይፍራው መንገሻና የእኔ ያልተከፋፈለ የጋራ ሀብት ነው፡፡ የሚች የውርስ ሀብትም በፍርድ ቤት በመጣራት ላይ ያለ ስለሆነ የውርስ ድርሻ አልተለየም፡፡ ስለሆነም በአፈጻጸም ሊከበር አይገባም የሚል ነው፡፡ ለፍርድ ማስፈጸሚያ የተከበረ ንብረት ላይ መብቱ ተነክቷል ያለ ሰው በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት የተቃውሞ ማመልከቻ አቅርቦ በንብረቱ ላይ ያለውን መብት በማሳየት ንብረቱ ከአፈጻጸም ውጭ እንዲሆን የመጠየቅ መብት አለው፡፡ በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር 3 ላይ አመልካች የሆነው ወገን ንብረቱ ላይ የተቀዳሚነት ሆነ የባለይዞታነት መብቱን የሚያረጋግጥለትን ማስረጃ አያይዞ ማቅረብ እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 419(1) መሠረት ፍርድ ቤቱ አቤቱታውን እና ማስረጃውን መርምሮ ንብረቱ እንዲያዝ

ወይም እንዲከበር የሚያደርግ በቂ ምክንያት አለመኖሩን ሲረዳ የተያዘው ንብረት እንዲለቀቅ ትዕዛዝ ይሠጣል፡፡

አመልካች ያቀረቡትን የተቃውሞ ማመልከቻ ተከትሎ ተጠሪ ያቀረቡት ክርክር የንብረቱ ስመ-ሀብት ወደወራሾች ዞሯል፣ ካርታውም በስማቸው ይገኛል፤ ይሕም የውርስ ድርሻቸው መለየቱን ያሳያል፡፡ ስለሆነም በ1ኛ የፍርድ ባለዕዳ ድርሻ ላይ የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሰጠቱ ተገቢ ነው የሚል ነው፡፡ ከክርክሩ የተገነዘብነው በአፈጻጸም የተከበረው ቤት ባለንብረት አመልካችና አቶ ወንድይፍራው መንገሻ ነበሩ፡፡ አቶ ወንድይፍራው መንገሻ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ሥመ-ሀብቱ በአመልካች ስምና በሚች ወራሾች ስም መዛወሩን የሥር ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ፍሬ ነገር ነው፡፡ አመልካችም ንብረቱ በአመልካና በወራሾች ስም መዛወሩን ክደው አይከራከሩም፡፡ 1ኛ የፍርድ ባለዕዳ የሆኑት ወ/ሮ ኤደን ወንድይፍራው የሚች ወራሽና ባለድርሻ መሆናቸውም የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ አፈጻጸም ችሎቱ በተለይም ሐምሌ 02 ቀን 2011 ዓ/ም በሠጠው ትዕዛዝ ዕዳው የሚፈጸመው የፍርድ ባለዕዳ በንብረቱ ባላቸው የውርስ ድርሻ ልክ ስለመሆኑ ገልጿል፡፡ ንብረቱ ወደ ወራሾች ሲዛወር በቤቱ ግማሽ ሀብት ላይ መብት ያላቸው ሰዎች የተለዩ በመሆኑ የውርስ ድርሻው ላይ አፈጻጸሙን ማስቀጠል የሚያስችል ነው፡፡ አመልካች በንብረቱ ላይ ያላቸው ግማሽ ድርሻ ለዕዳው መክፈያ እንዲውል ያልተደረገ በመሆኑ አፈጻጸም ሂደቱ መብታቸውን የነካ አይደለም፡፡ ሌሎች ወራሾች ውርስ ሀብት እንዲጣራ የጠየቁ ካሉና አፈጻጸሙ መብታቸውን የሚነካ ከሆነ መብታቸው የተነካባቸው ሰዎች በራሳቸው የተቃውሞ ማመልከቻ ሲያቀርቡ የሚመረመር ይሆናል፤ አመልካች ውክልና ሳይኖራቸው በራሳቸው ስም ስለሌሎች ሰዎች ሊከራከሩ አይችሉም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት አመልካች ያቀረቡትን የተቃውሞ ማመልከቻ ያልተቀበሉት የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ተከትለው ስለሆነ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 253896 ሰኔ 24 ቀን 2012 ዓ/ም እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 267544 ታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

1. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

2. አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የመ.ቁ. 196174
መስከረም 28/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ አቶ ጋትዴት ኛቾም የቀረበ የለም

ተጠሪ፡ አቶ ኒያል ደጆክ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም የአሁን ተጠሪ ጥር 05/2012 ዓም ፅፈው በጋምቤላ ከተማ አስተዳደር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁን አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ለፍርድ ቤቱ አቅርበዉ የነበረው ክስ ጭብጥም ለአስር ተከታታይ ዓመታት በእጃቸው አድርገው ሲገለገሉበት የነበረውን ይዞታ የአሁን አመልካች በራሳቸው ሥልጣን ይዘውባቸው ቤት የሰሩበት መሆኑን በመግለፅ በፍርድ ኃይል ሁከቱ ተወግዶ ይዞታው እንዲለቀቅላቸው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት አመልካች ክስ የቀረበበት ይዞታ በከተማው ማስተር ፕላን ምክንያት በተወሰደብኝ ይዞታ ምትክ በከተማው አስተዳደር ተሰጥቶኝ የይዞታ ማረጋጋጫ ምስክር ወረቀት ጭምር ወስጄበት የያዝኩት ይዞታዬ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን ከሰማ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ክስ የቀረበበት ይዞታ የአሁን ተጠሪ ስለመሆኑ ተጠሪው ባቀረቧቸው የሰው ምስክሮች የተረጋገጠ መሆኑን፤ በአሁን አመልካች በኩል የቀረቡ ምስክሮች ደግሞ ይዞታ የከተማ አስተዳደሩ የቀበሌ 01 ምክር ቤት በኩል የተሰጣቸው እንደሆነ መናገራቸውን፤ ሆኖም የቀበሌ ምክር ቤት የከተማ ይዞታን ለመስጠት ሥልጣን ያልተሰጣቸው መሆኑን፤ አመልካች በማስረጃነት ያቀረቡት የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትም በክርክር ሂደት የተሰጠ በመሆኑ ህግ ወጥ ነው በማለት የአመልካችን መከራከሪያ ውድቅ አድርጎ ይዞታውን ለተጠሪ ሊለቁ ይገባል ብሏል።

ይህንኑ ውሳኔ በይግባኝ የተመለከተው የጋምቤላ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ ክስ በቀረበበት ይዞታ ላይ ለአሁን አመልካች የተሰጠ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቀርቦ እያለ ይህ ወደ ጎን ተደርጎ በሰው የምስክርነት ቃለ ብቻ አመልካች ይዞታውን እንዲለቁ መወሰኑ አግባብ አለመሆኑን ተችቶ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሯል። የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደግሞ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በመሻር የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን አጽንቷል። አመልካች በዚሁ ውሳኔ ላይ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም።

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው። አመልካች መስከረም 15/2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይዞታ የጋምቤላ ከተማ አስተዳደር ለአመልካች የሰጠው መሆኑን በስር ፍ/ቤት ውሳኔ በተገለፀበት ሁኔታ አመልካች ሁከት ፈጥረዋል በማለት የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ከፍ/ሀ/ቁ 1149 አኳያ በዚህ ሰበር ችሎት እንዲመረመር በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል።

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል።

እንግዲህ ከክርክሩ አጀማመር መረዳት እንደሚቻለው ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ለአስር ተከታታይ ዓመታት በእጁ አድርጌ ስለገለግለብት የነበረውን ይዞታዬን አመልካች በሥልጣኑ ይዞት ቤት የሰራበት በመሆኑ ሁከቱ ተወግዶ ይዞታው ሊለቀቅልኝ ይገባል የሚል ነው። የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለአንድ ንብረት ባለይዞታ ንብረቱን አስመልክቶ በህግ ከተረጋጡት መብቶች ውስጥ አንዱ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1149(1) ይደነግጋል። በዚህ መልኩ ክስ የሚያቀርብ ሰው ማረጋገጥ የሚጠበቅበት ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች ሁከት ተፈጠረበት የተባለውን ንብረት/ሀብት/ ባልተጭበረበረ መንገድ በእጁ አድርጎ በእውነት የሚያዝበት መሆኑን እና በዚሁ ይዞታው ላይ በተከሰሰው ሰው ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ሁከት የተፈጠረበት ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ/1140፣ 1146 እና 1149 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መረዳት ይቻላል። በዚህ አግባብ በቀረበ ክስ ላይ ሁከት ተፈጥሯል ተብሎ ውሳኔ የሚሰጠውም የተከሰሰው ሰው የሌላ ሰው ይዞታ መያዙ አልያም በይዞታው ላይ ሁከት መፍጠሩ ሲረጋገጥ እና የሁከት ክስ የቀረበበት አካልም የሥራውን አደራረግ የሚፈቅድ ለእርሱ የሚናገርለት መብት መኖሩን በፍጥነት እና በማይታበል ዓይነት ሁኔታ ሳያስረዳ ሲቀር ስለመሆኑ ከዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 1 እና 3 ይዘት መረዳት ይቻላል።

አሁን በቀረበው ጉዳይ ተጠሪ ያቀረቡትን የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማስረዳት ያቀረቡት የሰው ምስክር ብቻ ነው። የተሰሙት ምስክሮችም ቢሆኑ ይዞታው የተጠሪ ነው የሚል የምስክርነት ቃል ከመስጠታቸው ባለፈ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ይዞታ ተጠሪ በእጃቸው አድረገው በእውነት እያዘዙበት እያለ አመልካች በሁከት ተግባር የያዙባቸው ስለመሆኑ ያረጋገጡት ነገር የለም። በአንፃሩ የአሁን አመልካች በዚሁ ይዞታ ላይ የተሰጣቸውን የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ ግብር ሲገብሩበት የነበረውን ማስረጃ ስለማቅረባቸው ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ይዘት መረዳት

ይቻላል፡፡ በእርግጥ አመልካች ያረቀቡት የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ግራ ቀኙ በክርክር ላይ እያሉ የተሰጠ ነው በሚል ውድቅ ተደርጓል፡፡ ሆኖም የይዞታ ማረጋጫ ምስክር ወረቀቱ ለአመልካች የተሰጠው ህዳር 03/2012 ሲሆን ተጠሪ ክስ ያቀረቡት ደግሞ ጥር 05/2012 ዓ.ም ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት መዝገብ የሚያሳይ በመሆኑ ማስረጃው በክርክር ሂደት የተገኘ ነው የሚባል አይደለም፡፡ በክርክር ሂደት የተገኘ ነው ቢባል እንኳን ማስረጃው የተሰጠው ከህግ እና የአሰራር ደንብ ውጭ ስለመሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ ውድቅ የሚደረግበት የህግ አግባብ የለም፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪ ለክሱ መነሻ የሆነውን ይዞታ በእጃቸው አድርገው በእውነት እያዘዙበት እያለ በአሁን አመልካች በሁከት ተግባር የተያዘባቸው ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት፣ ይልቁንም አመልካች በይዞታው ላይ ቢያንስ ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ ግብር እየገበሩበት ያለ እና በይዞታው ላይም ሥልጣን ባለው አስተዳደር አካል የተሰጠ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያላቸው ስለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ አመልካች በይዞታው ላይ ሁከት ፈጥረዋል ተብሎ እንዲለቁ መወሰኑ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት ያላደረገ እና የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1149 ድንጋጌን መሰረታዊ ይዘት ያላገናዘበ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

1. የጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ፋ/መ/ቁ/02517/2012 ላይ ሐምሌ 28/2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ ውሳኔን በማፅናት የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የጋምቤላ ከተማ አስተዳደር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/007/6/12 ላይ የካቲት 27/2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. የጋምቤላ ከተማ አስተዳደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ/20105 ላይ ሚያዝያ 16/2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በውጤት ደረጃ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-196340

ቀን፡-29/02/2014ዓ.ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡- ተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃላ/የተ/የግ ማኅበር - ጠበቃ ነጋ ጌታነህ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን- ነ/ፈጂ ደመቀ ሞልዬ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኮንስትራክሽን ሥራ ዉል አፈጻጸም መሰረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በመሰረተዉ ክስ ነዉ፡፡በግራ ቀኙ መካከል በቀን 10/05/2008ዓ/ም የመገጭ ግድብ የዉሃ ማማ የመሰረት ምሰሶ ጉድጓድ ቁፋሮ ግንባታ ሥራ ዉል ተደርጓል፡፡የግንባታ ዉሉ ጠቅላላ ዋጋ ተጨማሪ እሴት ታክስ(ተ.እ.ታ) ጨምሮ ብር 57,500,9200.00 ነዉ፡፡ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች የዉሉ አካል እንዲሆን ስምምነት ተደርጓል፡፡ተጠሪ ብር 11,500,184.00 ለአመልካች ቅድመ ክፍያ ፈጽሟል፡፡አመልካች ግንባታዉን በ360 ቀናት በማጠናቀቅ ለተጠሪ ለማስረከብ ግዴታ ገብቷል፡፡ተጠሪ የግንባታ ሥራ ቦታ ለአመልካች በቀን 29/06/2008ዓ/ም አስረክቧል፡፡

ሆኖም ግንባታዉ የዘገየዉ የግንባታ ሥራዉ በሚከናወንበት ወቅት በሃገሪቱ በተለይ በአማራ ክልል ጎንደርና አካባቢ በተነሳዉ የሕዝብ አመጽ በተፈጠረ ሁከት መንግስት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያወጀበት ጊዜ ስለነበር ከቀን 30/12/2008ዓ/ም እስከ ቀን 14/02/2009ዓ/ም ለ79 ቀናት የግንባታ ሥራዉ ተቋርጧል፡፡ይህም

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1793 መሰረት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ከመሆኑም በተጨማሪ በጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች ቁጥር 18.6 መሰረት ከአመልካች ቁጥጥር ዉጭ ነዉ ተብሎ የሚወሰድ ነዉ፡፡ይህንን ምክንያት በመጥቀስ አመልካች በቀን 04/12/2008ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ የ102 ቀናት የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ለተጠሪ ቢያቀርብም ተጠሪ በዉል ጠቅላላ ሁኔታዎች አንቀጽ 18.6፣73(1/ረ እና ሸ) ከዉልና ከሕግ የመነጨ ምክንያት በመጥቀስ ለአመልካች ጊዜ ይራዘምልኝ ጥያቄ በ21 ቀን ዉስጥ ምላሽ ስላልሰጠ የማስረከቢያ ጊዜዉ በዉል ተለይቶ እንዳይሰን በማድረጉ የማስረከቢያ ጊዜዉ በአእምሮ ግምት በቂ የሆናል ተብሎ ስለሚወሰን(time at large) በዉሉ የተመለከተዉ የማስረከቢያ ጊዜ የማይፀና ሆኗል፡፡ አመልካች ለግንባታ ሥራዉ መዘግየት ተጠያቂነት ሳይኖርበት ተጠሪ ዉሉን በሕገ-ወጥ መንገድ አቋርጧል፡፡የተፈጠረዉ ከአቅም በላይ ምክንያት ከ60 ቀናት በላይ ስለቆየ በዉሉ ጠቅላላ ሁኔታዎች አንቀጽ 21.3/መ መሰረት አመልካች ዉሉን መቋረጥ መብት ቢኖረዉም አላቋረጠም፡፡ይልቁንም ግንባታዉ በተፈጠረዉ የጸጥታ ችግር ምክንያት ተቋርጦ ከቆየ በኋላ አመልካች ሥራዉን እንዲቀጥል አማካሪዉ በቀን 01/04/2009ዓ/ም ጽፎ ለአመልካች በግልባጭ አሳዉቋል፡፡ አመልካች ሥራዉን በቀን 24/12/ 2009ዓ/ም በቁጥር የኢኮስኮ/8390/09 በጻፈዉ ደብዳቤ አመልካች ሥራዉን በታቀደዉ የማስረከቢያ ጊዜ በቀን 20/07/2009ዓ/ም አላጠናቀቀም በሚል ቀኑን ወደኋላ በማድረግ ዉሉን አቋርጧል፡፡

ስለሆነም አመልካች ለዉሉ መዘግየት ተጠያቂነት ሳይኖርበት ተጠሪ ዉሉን በሕገ-ወጥ መንገድ አቋርጧል ተብሎ እንዲወሰን፡፡ ዉሉ በተቋረጠበት ጊዜ አመልካች ከሚቆፈረቱ 64 ጉድጓዶች ዉስጥ 21 የቆፈረ በመሆኑ አመልካች ለሰራዉ ሥራ ብር 12,794,644.30 ሊከፈለዉ ስለሚገባ ከዚህ ላይ በቅድመ ክፍያ መልክ የከፈለዉ ብር 11,500,184.00 ተቀንሶ የሚቀረዉን ብር 1,294,460.30 ዉሉ ሲቋረጥ መክፈል ሲገባዉ ስላልከፈለ ከቀን 22/04/2008ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል እንዲወሰንበት፡፡ዉሉ የተቋረጠዉ አመልካች ተጠያቂ በሚሆንበት ምክንያት ባለመሆኑ ተጠሪ ከአመልካች ተከፋይ ሂሳብ ላይ በቅጣት መልክ የቀነሰዉን ብር 5,750,000.00 ለአመልካች ተመላሽ እንዲያደርግ እንዲወሰንበት፡፡አመልካች ለግንባታዉ መዘግየት ተጠያቂ ነዉ የሚባል ከሆነ በዉሉ አንቀጽ 87.1 መሰረት ቅጣት የሚቀነሰዉ ላልተሰሩ ሥራዎች መጠን ብቻ ነዉ ተብሎ እንዲወሰን፡፡ተጠሪ ዉሉን ሲያቋርጥ የአመልካች የግንባታ መሳሪያዎች አግቶ በመያዝ አመልካች በንብረቱ እንዳይገለገል በማድረጉ አመልካች ከማሽኖቹ ያጣዉን ገቢ እስከ ቀን 23/10/2010 ዓ/ም ድረስ በተወሰደ የዋጋ ጥናት የተጣራዉን ከተ.እ.ታ በፊት ብር 59,136,000.00 እንዲከፍል እንዲወሰንበት፡፡ ተጠሪ ዉሉን በሕገ-ወጥ መንገድ ሲያቋርጥ ከጊዜ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ ተጨማሪ የክፍያ ጥያቄዎች በዉሉ ጠቅላላ ሁኔታዎች አንቀጽ 18.6፣69.1፣74.1/ተ መሰረት ከተ.እ.ታ በፊት ብር 8,1666,798.15 ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል እንደወሰንበት፡፡ እንዲሁም ተጠሪ በቅድመ ክፍያ ዋስትና እና በመልካም አፈጻጸም ዋስትና ላይ የማዘዝ ሥልጣን የለዉም እንዲባልና ለአመልካች እንዲሰቅ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጠዉ መልስ አመልካች በክሱ የተጠቀሰዉን የግንባታ ሥራ በብር 57,500,920.00 ለመሥራት ከተጠሪ ጋር ዉል ተፈራርሟል፡፡አመልካች በዉሉ መሰረት ቅድመ ክፍያ ብር 11,500,184

ከተጠሪ ላይ ተቀብሏል፡፡አመልካች በዉሉ መሰረት አመልካች ቅድሚያ ክፍያ በተፈጸመለት በ20 ቀናት ዉስጥ ሥራዉን ጀምሮ በ360 ቀናት ግንባታዉን አጠናቆ የማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡ለግንባታ ሥራዉ የተንተተበት ምክንያት አመልካች ባለዉ የፀጥታ ችግር ሳይሆን የአመልካች የማሽን ብልሽት እና ለፕሮጀክቱ ሥራ የሚሆን በቂ የሰዉ ኃይል እና ግብአት ባለመቅረቡ ነዉ፡፡ይሁን እንጂ ድጋሚ ጨረታ ማዉጣት የበለጠ የግድብ ሥራዉ ጊዜ ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል በሚል አመልካች ያሉበትን የአቅም እና የተለያዩ ችግሮች በአስቸኳይ እንዲያርም መግባባት ላይ በመድረስ ላቀረበዉ የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ በቀን 08/05/2009ዓ/ም የ33 ቀናት ተጨማሪ ጊዜ ተጠሪ ለአመልካች ሠጥቷል፡፡አመልካች የፀጥታ ችግር ስለመኖሩና ይህም ሥራዉን እንዳይሰራ ፍፁም እክል የሆነበት መሆኑን በማስረጃ አላስረዳም፡፡የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የግንባታ ሥራዉ በሚሰራበት አካባቢ በተፈጠረ የፀጥታ ችግር ምክንያት የታወጀ አይደለም፡፡ስለሆነም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1792 መሰረት ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ሊባል የሚችል ካለመሆኑም በተጨማሪ የግንባታ ሥራዉን ሊያስተጓጉል የሚችል የፀጥታ ችግር ባለመኖሩ አመልካች በወቅቱ ሥራዉን ሲሰራ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ግንባታዉን እንዲያጠናቅቅ በተደጋጋሚ ተጠሪ ለአመልካች ማስጠንቀቂያ የሰጠ ቢሆንም አመልካች ችግሩን ቀርፎ ግንባታዉን ማጠናቀቅ ባለመቻሉ ከጊዜና ከገንዘብ አንጻር በመንግስት ላይ ከፍተኛ ጉዳት በመድረሱ ምክንያት ተጠሪ ዉሉን መቋረጡን ለአመልካች በጽሁፍ አሳዉቋል፡፡

አመልካች በቀን 04/12/2008ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ ለወደፊት የጊዜ ማራዘሚያ እንደሚጠይቅ ገለጸ እንጂ በዚህ ቀኝ የጊዜ ማራዘሚያ አልጠየቀም፡፡የጊዜ ማራዘሚያ በቀን 09/03/2009ዓ/ም እና በቀን 03/04/2009ዓ/ም በተጻፉ ደብዳቤዎች ጠይቆ በአምስት ቀን ዉስጥ ማለትም በቀን 14/03/2009ዓ/ም መልስ በመስጠት የሥራ መርሀግብር አዉጥቶ ተጨማሪ ማሽነሪና የሰዉ ኃይል አስገብቶ በተጨማሪ 33 ቀናት ዉስጥ እንዲያጠናቅቅ ተጨማሪ ጊዜ ስለተሰጠዉ በ21 ቀን ዉስጥ ላቀረበዉ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ተጠሪ መልስ እንዳልሰጠዉ አድርጎ ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡አመልካችም ይህንን መሰረት በማድረግ ሥራዉን እስከ ቀን 16/08/2009ዓ/ም ድረስ ለማጠናቀቅ በሚያስችለዉ መልኩ የሥራ መርሀ ግብር አዘጋጅቶ አቅርቧል፡፡የ33 ቀናት ጊዜ ማራዘሚያ ስለተሰጠዉ ተጠሪ ለጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ መልስ ሳይሠጥ ዉሉን እንዳቋረጠ አድርጎ ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡በአጠቃላይ አመልካች የገነባዉ 21 ምሶሰዎች ሲሆኑ ይህም በዉሉ መሰረት ስለመገንባቱ ተሞክሮ አለመረጋገጡ እንደተጠበቀ ሆኖ አፈጻጸሙ ከ1/3ኛ ያነሰ ነዉ፡፡ይህም የአቅም ችግር እንዳለበት ስለሚያሳይ ተጨማሪ 360 ቀናት ቢጨመርለትም ቀሪዉን ሥራ ማጠናቀቅ አይችልም፡፡ስለሆነም ዉሉ የተቋረጠዉ በአግባቡ ነዉ፡፡ተጠሪ ዉሉን ከመቋረጡ በፊት ለተጠሪ የ60 ቀናት ማስጠንቀቂያ እንዲሰጥ ዉሉ ተጠሪን አያስገድደዉም፡፡በዉሉ አንቀጽ 21.2 ላይ ተጠሪ ለአመልካች የ30 ቀን ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠዉ በፈቃጅ መልክ የተቀመጠ ነዉ፡፡በዚህ መሰረት ማስጠንቀቂያ መስጠት አስፈላጊ የሚሆነዉ በዉሉ አንቀጽ 21.2/ሀ መሰረት ተጠሪ ዉሉን በራሱ አነሳሽነትና ምክንያት የሚያቋርጥ ሲሆን ነዉ፡፡ ግንባታዉን ማጠናቀቂያ ጊዜ በዉሉ በግልጽ ስለተመለከተ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1775 መሰረት ተጠሪ ዉሉን ከማቋረጡ በፊት ለአመልካች ማስጠንቀቂያ ለመስጠት አይገደድም፡፡

አመልካች የ21 ጉድጓዶች ግንባታ ስለፈጸምኩ ብር 1,294,460.03 ይከፈለኝ በማለት የጠየቀ ቢሆንም በዉሉ መሰረት ግንባታ መፈጸሙንና ለታለመለት ዓላማ የሚዉል መሆኑን አስመርምሮ ለተጠሪ ያላስረከበ በመሆኑና በዉሉ አንቀጽ 59.3 መሰረት በአማካሪ መሀንዲሱ አስመርምሮ ይሕንን የሚያሳይ በማስረጃ ባለማቅረቡ ይህንን ገንዘብ ተጠሪ ልከፍል አይገባም፡፡ተጠሪ ከአመልካች ክፍያ ላይ ብር 5,750,000.00 በቅጣት መልክ ቀንሶ ያስቀረዉ በዉሉ አንቀጽ 5 መሰረት አመልካች በዉሉ በተመለከተዉ ጊዜ ግንባታዉን ባለማጠናቀቁ ምክንያት ግንባታዉ ለዘገየበት ጊዜ በዉሉ አንቀጽ 27 መሰረት የበሰለ ጉዳት ኪሳራ(liquidated damage) በየቀኑ 0.1% የዉሉ ዋጋ 10% እስከሚሆን ድረስ ከተከፋይ ሂሳቡ ላይ ቆርጦ ለማስቀረት ዉሉ በሚሰጠዉ መብት መሰረት የተፈጸመ በመሆኑ አለአግባብ ተቀንሶብኛል ሲል ያቀረበዉ ጥያቄ ዉድቅ ሊሆን ይገባል፡፡አመልካች ግዴታዉን ሳይወጣ ሲቀር በዉሉ አንቀጽ 58 መሰረት ያስያዘዉ ዋስትና እንዲከፈለዉ ተጠሪ ዋስትናዉን ለሰጠዉ ባንክ ጥያቄ አቅርቦ ገንዘቡን የመዉረስ መብት ስላለዉ ተጠሪ አንደዋና ተቋረጭ ለፕሮጀክቱ ባለበት የግንባታ ሥራዉ ለዘገየበት በየቀኑ ብር 4,927,939.79 እየታሰበ ግንባታዉ ለዘገየባቸዉ ቀናት በቅጣት መልክ እንዲከፍል አመልካች ምክንያት ስለሆነና ተጠሪ ክፍያ እንዲፈጸምለት ለባንክ ደብዳቤ ስለጻፈ አመልካች ከዋስትና ጋር በተያያዘ ያቀረበዉ ጥያቄ ዉድቅ ሊሆን ይገባል፡፡ አመልካች ከጊዜ ጋር ተያያዥነት ላላቸዉ ተጨማሪ ወጪ ተዳሪጌያለሁ ብሎ በዉሉ ጠቅላላ ሁኔታዎች አንቀጽ 18.6፣69.1 እና 74 መሰረት የሥራ ዉሉ የተቋረጠዉ ከአቅም በላይ ሁኔታ ወይም ሥራዉን ለማስቀጠል የማያስችል ሁኔታ ገጥሞ አሠሪዉ ወይም ተጠሪ የሥራ ዉሉን ያቋረጠ እንደሆነ በመሆና በተያዘዉ ጉዳይ የሥራ ዉሉ የተቋረጠዉ በዚህ አግባብ ካለመሆኑም በተጨማሪ አመልካች ያወጣዉ ወጪ ባለመኖሩና ለወጪ መዳረጉን የሚያሳይ ማስረጃም ያላቀረበ በመሆኑ ከዚህ ጋር አያይዞ ብር 8,166,798.55 እንዲከፈለዉ ያቀረበዉ ጥያቄ ዉድቅ ሊሆን ይገባል፡፡

እንዲሁም አመልካች ተጠሪ የግንባታ መሳሪያዎችን በሕገ-ወጥ መንገድ አግቶ ስላቆየ ብር 59,136,000.00 እንዲከፈለኝ በማለት የጠየቀዉ ዳኝነት በአጠቃላይ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ መጠን ብር 80,181,307.57 ስላደረገዉ ይህም አመልካች ከዉሉ ዋጋ በላይ ዳኝነት እንደጠየቀ ስለሚያሳይና በዉሉ መሰረት ከዉሉ ጠቅላላ ዋጋ በላይ ካሳ መጠየቅ ስለማይቻል ከዚህ አኳያ የጠየቀዉ ዉድቅ ሊሆን ይገባል፡፡ተያዙብኝ ያላቸዉ ንብረቶች ንብረቶቹ እንደሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ተጠሪ አንዳች የአመልካች ንብረቶች አልያዘም፡፡በጠቅላላ የዉሉ ሁኔታዎች አንቀጽ 23 እና በዉሉ ልዩ ሁኔታ አንቀጽ 64.2 መሰት ዉሉ በሥራ ተቋራጩ ምክንያት ሲቋረጥ በግንባታ ቦታ ላይ ያሉ ሁሉም የግንባታ እቃዎች፣መሳሪያዎች እና ጊዜያዊ የግንባታ ሥራዎች የተጠሪ(የአሰሪ) ንብረት እንደሚሆኑ ስለተደነገገ አመልካች ንብረቶቹን የማስመለስም ሆነ አከራይቶ የሚያገኘዉን ጥቅም የመጠየቅ መብት የለዉም፡፡ እንዲሁም አመልካች ማሽኖቹን ወደ ግንባታ ስፍራዉ ያመጣቸዉ ተከራይጦ ይሁን በሌላ መንገድ ስለመሆኑ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ለቆሙበት ጊዜ የከፈለዉ ክፍያ ስለመኖሩ ያቀረበዉ የኪራይ ክፍያ ሰነድ የለም፡፡ሊከፈለዉ ይገባል እንኳን ቢባል መከፈል ያለበት ዉሉ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ያለዉ ነዉ፡፡ በተጨማሪም ንብረቱን ተከታትሎ በወቅቱ በመሰብሰብ ጉዳት የመቀነስ ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ በራሱ ጥፋት ጥያቄ ሳያቀርብ ለቀረበት ጊዜ ሁሉ ክሱን ከማቅረቡ በፊት ያለዉን

ወደኋላ ሄዶ መጠየቁ ተገቢነት የለውም፡፡እንዲሁም የጠየቀዉ ካሳ ተመጣጣኝ አይደለም በማለት ክሱ ዉድቅ እንዲደረግለት በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 220306 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና በግራ ቀኙ የቀረቡለትንና ራሱ ያስቀረበዉን ማስረጃዎች ሰምቶና መርምሮ በቀን 10/02/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ በግራ ቀኙ መካከል ለክሱ መነሻ የሆነዉ የመገጭ ግድብ የዉሃ መቆጣጠሪያ ማማ የመሰረት ምሰሶ ጉድጓድ ቁፋሮ የግንባታ ሥራ ዉል መፈራረማቸዉ፣የግንባተታዉ አጠቃላይ ዋጋ ከተ.እ.ታ ጋር ብር57,500,920.00 እንደሆነ፣ በጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች የተመለከቱትን የዉል ግዴታዎች ለመፈጸመ ግዴታ መግባታቸዉን እና ተጠሪ ለአመልካች ቅድመ ክፍያ ብር 11,500,184.00 መክፈሉ በግራ ቀኙ የታመነ ነዉ፡፡ግራ ቀኙ የተካካዱበትን ጭብጦች በመለየት በግራ ቀኙ መካከል ያለዉን የግንባታ ዉል ተጠሪ ያቋረጠዉ በአግባቡ ነዉ ወይስ አይደለም የሚል ጭብጥ በተመለከተ አመልካች በአካባቢዉ በገጠመዉ የፀጥታ ችግር ምክንያት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሥራ መስራት ባለመቻሉ ጊዜ መባከኑን ገልጩ የጊዜ ማራዘሚያ የጠየቅሁ ቢሆንም ተጠሪ መልስ በመንፈግ ከሕግ ዉጭ የሥራ ዉል አቋርጧል በማለት የተከራከረዉን ተጠሪ ዉሉ የተቋረጠዉ በዉሉ የተመለከተዉ ጊዜ ተጠናቆ አመልካች በጠየቀዉ መሰረት ተጨማሪ የ33 ቀን ጊዜ የተራዘመለት ቢሆንም አመልካች የመሳሪያና የሰዉ ኃይል ችግር ስላለበት በራሱ ጉድለት የግንባታዉ ጊዜ በመጓተቱ ምክንያት የሥራ ዉል በሕግ አግባብ የተቋረጠ ነዉ በማለት የተከራከረ ቢሆንም አመልካች አቅርቦ ባሰማቸዉ ምስክሮች ከቀን 19/11/2008ዓ/ም እስከ ህዳር 2009ዓ/ም ድረስ ክኘሮጀክቱ አካባቢ ጎሳን ለይቶ የማጥቃት ሁከትና ብጥብጥ በአካባቢዉ እንደተከሰተ፣በተለይም አመልካችና ሠራተኞች የተጠሪ ሠራተኞች ወደሚገኙበት ወደመገጭ ካምፕ እንዲገቡ በተጠሪ ባለመፈቀዱ ምክንያት ከሳይጡ ወጣ ብሎ በሚገኘዉ ጠዳ ከተማ ላይ አመልካች ለሠራተኞቹ ተከራይቶ በነበረዉ ቦታ ላይ ከፍ ያለ ረብሻ ተፈጥሮ ንብረቱ ተዘርፎ ሠራተኞቹ ለነፍሳቸዉ ሸሽተዉ ማምለጣቸዉን ከዚያም በኋላ ወደሥራ ተመልሰዉ ለመግባት የግርግር ጊዜ እስከሚያልፍ ሲጠበቅ የሥራ ማጠናቀቂያ ጊዜዉ እንዳለፈ ይህም በዉሉም ሆነ በፍትሐ ብሔር ሕግ መሰረት ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ አመልካች እንደገጠመዉ አመልካች ከተጠሪ የተሻለ ማስረጃ በማቅረብ አስረድቷል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ላቀረብኩት የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ተጠሪ በ21 ቀን ዉስጥ መልስ አልሰጠኝም በማለት የተከራከረ ቢሆንም አመልካች እ.ኤ.አ በቀን 18/11/2016ዓ/ም ላቀረበዉ ጥያቄ በአማካሪዉ በ5 ቀን ዉስጥ በቀን 23/11/2016 ዓ/ም በተሰጠ መልስ ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጠዉ እንደማይገባና በዉሉ በተመለከተዉ ጊዜ እንዲያጠናቅቅ ተገልጾ መልስ ተሰጥቶታል፡፡ አመልካች እ.ኤ.አ በቀን 18/11/2016ዓ/ም ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎች እንደገጠሙት ገልጾ ለወደፊት የጊዜ ማራዘሚያ እንደሚጠይቅ አሳወቀ እንጂ የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ከዝርዝር መግለጫ ጋር በዉሉ አንቀጽ 73/2 መሰረት አልጠየቀም፡፡አመልካች በአማካሪዉ ዉሳኔ ቅሬታ ካለዉ በጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች(GCC) ወይም (FIDIC) ላይ በተመለከተዉ መሰረት ደረጃዉን ጠብቆ ቅሬታ አላቀረበም፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካች እ.ኤ.አ በቀን 12/12/2016 ጽፎ ለ102 ቀናት የጊዜ ማራዘሚያዉ እንዲሰጠዉ በድጋሚ ያቀረበዉን ጥያቄ ተከትሎ ተጠሪ በቀን 08/05/2009ዓ/ም በተያዘ ቃለ ጉባኤ ለአመልካች ጠቸማሪ ጊዜ የሠጠዉ ሲሆን ይህ ጊዜ በቂ አይደለም በማለት ይግባኝ ለሥራና

ከተማ ልማት ሚኒስቴር ካለማቅረቡም በላይ በተሰጠዉ ጊዜ ግንባታዉን ለማከናወን የሥራ መርሀ-ግብር አቅርቦ ወደ ሥራ የገባ ቢሆንም በታቀደዉ ማስረከቢያ ጊዜ ባለማጠናቀቁ ተጠሪ በቀን 15/12/2009ዓ/ም ዉሉን ሊያቋርጥ ችሏል፡፡ከዚህም ፍርድ ቤቱ የተረዳዉ እስከ ቀን 08/05/2009ዓ/ም ድረስ ያለዉን ጊዜ በተመለከተ በግራ ቀኙ በተደረሰዉ ስምምነት መሰረት ለአመልካች የ33 ቀናት ተጨማሪ ጊዜ በመሰጠቱ መቋጫ አግኝቷል፡፡ ሆኖም አመልካች የተራዘመለትን ጊዜ ተጠቅሞ እስከ ቀን 16/08/2009ዓ/ም ድረስ ሥራዉን ማጠናቀቅ ይቅርና የዉል ማቋረጫ ደብዳቤ ተጽፎ እስከተሰጠበት ቀን 15/12/2009ዓ/ም ድረስ ከ7 ወር በኋላም ቢሆን ሰርቶ አጠናቅቆ አላስረከበም፡፡ ተጠሪ ለአመልካች ከቀን 08/05/2009ዓ/ም በኋላ ዉሉን ከማቋረጥ በፊት ከተከታታይ 6 ጊዜ ሲያስጠነቅቅ ቆይቶ በቀን 15/12/2009ዓ/ም ዉሉን ያቋረጠዉ አመልካች የግንባታ ሥራዉን በማዘግየቱ ምክንያት በመሆኑ ተጠሪ ዉሉን በአንቀጽ 22(2/ሀ እና መ) መሰት በሕግ አግባብ የተቋረጠ ነዉ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በዉሉ 64 የዉሃ መቆጣጠሪያ ማማ የመሰረት ምሰሶ ለመስራት ተስማምቶ የግንባታ ዉሉ ሲቋረጥ አመልካች 21 የዉሃ መቆጣሪያ ማማ የመሰረት ምሰሶ በዉሉ መሰረት መስራቱ በማስረጃ እንደተረጋገጠ ገልጾ ለዚህ ሥራዉ ለቅድመ ክፍያ የተከፈለዉ ተቀንሶ ተ.እ.ታ ጨምሮ ቀሪ ብር 1,294,460.30 ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል ወስኗል፡፡እንዲሁም ዉሉ በአመልካች ምክንያት ስለተቋረጠ በዉላቸዉ አንቀጽ 19(2 እና 3) እና 27 መሰረት ዉሉ በጊዜዉ ባለመጠናቀቁ ለሚደርሰዉ ጉዳት ተጠሪ ባልተሰራ ሥራ መጠን ልክ በየቀኑ የዉሉን ዋጋ 0.1% የዉሉ ዋጋ 10% እስከሚደርስ ድረስ ለአመልካች ከሚከፈል ክፍያ ላይ የመቀነስ መብት አለዉ፡፡በዚህ መሰረት ተጠሪ ከአመልካች ሊቀንስ የሚገባዉ የጉዳት ካሳ ብር 5,620,645.00 ነዉ በማለት ወስኗል፡፡

እንዲሁም ተጠሪ የግንባታ ዉሉን ሲያቋርጥ የአመልካችን የግንባታ መሳሪያዎች ከቀን 08/12/2009ዓ/ም ጀምሮ ይህ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ በኃይል አግቶ በመያዝ አመልካች በንብረቱ እንዳይገለገል በማድረጉ ተገቢነት የሌለዉ ዉሳኔ በመሆኑ አመልካች በንብረቶቹ ባመለመገልገል ያጣዉን ጥቅም ብር 45,000,000.00 ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል ይገባል፡፡ሆኖም ከላይ በተመለከተዉ መሰረት ተጠሪ ከአመልካች የሚፈለገዉ እዳ ብር 5,620,645.00 ሲቀነስ ብር 39,379,355 ከተጠሪ የሚጠበቅ ሲሆን አመልካች ለሰራዉ ሥራ ለአመልካች ሊከፈል ይገባል የተባለዉ ብር 1,294,460.30 ሲጨመር በድምሩ ብር 40,673,815.00 ከቀን 05/06/2010ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ሕጋዊ ወለድ ጋር ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍልና የአመልካችን መሳሪያዎች/ማሽነሪዎች እንዲሁም የቅድመ ክፍያ ዋስትና ለአመልካች ሊመለስለት ይገባል በማለት ሌሎች አመልካች የጠየቃቸዉን ዳኝነት ጥያቄዎች ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ችሎቱም በመ/ቁጥር 187031 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 25/12/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ በግራ ቀኙ መካከል በተፈጸመ ዉል መሰረት ዉሉ በአመልካች ምክንያት በዉሉ በተመለከተዉ ጊዜ ሳይጠናቀቅ በመቅረቱ ዉሉ የተቋረጠ እንደሆነ ተጠሪ የአመልካችን መሳሪያዎች/ማሽነሪዎች በባለቤትነት ተረክቦ በዉሉ የተጠቀሰዉ ሥራ

አስኪጠናቀቅ እንዲጠቀምባቸዉ መብት ተሰጥቶታል፡፡በዚህ መሰረት ተጠሪ በዉሉ የተሰጠዉ መብት ማሽኖቹን ሥራዉ እስኪያልቅ ለመጠቀም የይዞታ መብት እንጂ የባለቤትነት መብት አልተሰጠዉም በሚል አመልካች ያቀረበዉ መከራከሪያ ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡ዉሉ በአመልካች ጥፋት መቋረጡ ተጠሪ የማሽኖቹ ባለቤት እንዲሆን በዉሉ ግራ ቀኙ እንደተስማሙ የምንገነዘበዉ ጉዳይ ቢሆንም የተሰጠዉ ባለቤትነት ግን ከዉሉ አጠቃላይ ዓላማ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ በዉሉ ለተጠቀሰዉ ሥራ ማጠናቀቂያ ሰፊ መብት የሚሰጥ እንጂ በዉሉ የተጠቀሰዉ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ የሚቀጥል አይደለም፡፡ስለሆነም መሳሪያዎቹ/ማሽኖቹ የአመልካች በመሆናቸዉ በዉሉ መሰረት አመልካች ያላጠናቀቀዉን ሥራ ተጠሪ በአመልካች ማሽኖች ተጠቅሞ የማጠናቀቅ እና ካጠናቀቀ በኋላ ማሽኖቹን ለአመልካች ሊመልስ ይገባል በማለት የዉሉን ጠቅላላ ሁኔታ አንቀጽ 23.2፣21፣64.2/ሠ እና 83.3ን ጠቅሶ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካች በማሽኖች ማግኘት እየቻልኩ ተጠሪ ማሽኖቹን በመያዙ ያጣሁት ነዉ ያለዉን ገቢ ተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት ሽሮ አመልካች መክፈል ከሚገባዉ ቅጣት ከብር 5,620,645.00 ላይ አመልካች ለሰራዉ ሥራ የሚከፈለዉ ብር 1,294,460.30 ተቀንሶ አመልካች ብር 4,326,184.70 ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ አሻሽሎ ወስኗል፡፡

አመልካች የኮንስትራክሽን ሥራ ዉሉ ሲቋረጥ ተጠሪ የአመልካችን ማሽኖች ባለማስረከቡ ማሽኖቹ ያለሥራ በመቆማቸዉ አመልካች ያጣዉን ገቢ እንዲከፍልና ማሽኖቹን/መሳሪያዎቹን እንዲመልስ አመልካች የጠየቀዉን ዳኝነት በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤት የደረሰዉን ጉዳት አረጋግጦ በርትእ ብር 39,375,355.00 ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል የወሰነዉ ጉዳዩን ከጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች አንቀጽ 21.5፣83.1፣83.2፣83.3 እንዲሁም ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1205 አንጻር በመመርመር ተጠሪ ማሽኖቹን የመዉረስ መብት እንደሌለዉ ጭምር በማረጋገጥ ስለሆነ ተገቢነት ያለዉ ነዉ፡፡ሆኖም ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ተጠሪ ዉሉ ከተቋረጠ ከ3 ዓመታት በኋላ ማሽኖቹን የመዉረስ መብት አለኝ በማለት አግቶ የያዛቸዉን ጊዜያት አመልካች በንብረቶቹ ሳይገለገል የቆየበትን ጊዜያት ከግምት ዉስጥ ሳያስገባ አመልካች ያጣዉን ጥቅም ተጠሪ ሊከፍል አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በፍርድ ሀተታዉ ላይ ተጠሪ የአመልካችን ንብረቶች መያዝ የሚችለዉ አመልካች ያልጨረሳቸዉን ሥራዎች ለመጨረስ ብቻ ነዉ በማለት የአመልካችን ክርክር የሚያጠናክር ምክንያት ከገለጸ በኋላ ከዚህ አግባብ ዉጭ ተጠሪ ማሽኖቹን ከ3 ዓመት በላይ አግቶ ላቆየበት ጊዜ የታጣ ገቢ ሊከፍል አይገባም ማለቱ ዉሳኔዉ እርስ በእርስ የሚቃረንና ሚዛናዊነት የጎደለዉ ነዉ፡፡የተሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ በአመልካች ንብረት ማብቂያ ለሌለዉ ጊዜ ይዞ እንዲቆይ የሚያደርግና አግቶ ያቆየዉን ጊዜ ከግምት ያላስገባና በአመልካች ላይ የደረሰዉንና እየደረሰ ያለዉን ጉዳት ያላገናዘበ በመሆኑ ሕግንና ሞራልን የሚቃረን ስለሆነ አመልካች ያጣዉን ገቢ ተጠሪ እንዲከፍል የተወሰነዉ አለአግባብ ስለተሻረ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ይጽናልኝ በማለት አቤቱታዉን አቅርቧል፡፡

ሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ ተጠሪ የግንባታ ሥራ በዉሉ በተመለከተዉ ጊዜ ዉስጥ ባለመጠናቀቁ የቀረዉን ሥራ ሠርቶ እስከሚጨርስ ድረስ የግንባታ ሥራ መሳሪያዎችን እንዲይዙና ሥራዉ ሲጠናቀቅ እንዲመልስ ዉላቸዉ መሰረት ተደርጎ ሲወሰን በዉሉ ላይ ሥራዉን የሚጨርሱበት ጊዜ በዉላቸዉ

ባይቀመጥም ከጠቅላላ ዉል ይዘት መሰረት ተጠሪ ባለበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 01/06/2013ዓ/ም የተጻፈ የሚከተለዉን መልስ አቅርቧል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት በነበረዉ ክርክር ተጠሪ ማሽኖቹን ሊያዝ የሚገባበትን ጊዜ በተመለከተ ያደረገዉ ክርክር የለም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ማሽኖቹን ማብቂያ ለሌለዉ ጊዜ እንዲጠቀምባቸዉ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት ያቀረበዉ መከራከሪያ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 329/1 መሰረት ተቀባይነት የለዉም፡፡ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በዉሉ ጠቅላላ ሁኔታዎች አንቀጽ 23.2 እና 83.3 እንደዚሁም የዉሉ ልዩ ሁኔታ አንቀጽ 64.2/ሠ ላይ ዉሉ በሥራ ተቋራጭ/አመልካች ጥፋት ከተቋረጠ ተጠሪ የአመልካች ጥፋት ከተቋረጠ ተጠሪ የአመልካችን ማሽኖች አመልካች የጀመረዉ ሥራ እስኪጠናቀቅ ድረስ መጠቀም ይችላል የሚል በመሆኑ ዉሳኔዉ የተጠሪን ከዉል የመነጨ መብት መሰረት ያደረገ ዉሳኔ ነዉ፡፡እንዲሁም በዉሉ አንቀጽ 23.2 በግልጽ እንደተመለከተዉ ዉሉ በአመልካች ምክንያት ከተቋረጠ በግንባታ ቦታ ላይ ያሉ ማሽኖቹን ተጠሪ የመዉሰድ መብት እንጂ ተጠቅሞ የመመለስ በመሆኑ አመልካች ጀምሮ የነበረዉ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላም ቢሆን ተጠሪ የመመለስ ግዴታ የለበትም፡፡በግራ ቀኙ ዉል ጠቅላላ ሁኔታዎች አንቀጽ 83/3 ላይ ዉሉ በስር ተቋራጩ(አመልካች) ምክንያት የተቋረጠ እንደሆነ አሠሪዉ(ተጠሪ) ንብረቱን ሥራዉ እስኪጠናቀቅ ድረስ ለመጠቀም እንደሚችል ይጠቀሳል፡፡ስለሆነም ተጠሪ ማሽኖቹን የመዉረስ ከዉል የመነጨ መብት እያለዉ ይህንን መብት ባለመቀበል ሥራዉ እስኪጠናቀቅ ድረስ የመጠቀም መብት አለዉ ብሎ መወሰኑ ተጠሪን የሚጎዳ ዉሳኔ በመሆኑ ተጠሪ ለአመልካች የሚከፍለዉ የጉዳት ካሳ የለም ተብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡በይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔም አመልካች እንዳለዉ እርስ በእርሱ የሚጣረስ አይደለም፡፡ዉሉ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ የአመልካች ማሽኖች ተጠሪ የግንባታ ሥራዉን በሚያሰራበት ቦታ ላይ ያሉ ቢሆንም የማሽኖቹ ቁልፍ አመልካች እጅ ስለሚገኙና ተጠሪ ቁልፎቹ እንዲሰጠዉ በተደጋጋሚ ተጠይቆ ባለማስረከቡ ማሽኖቹ ላለፉት ሶስት አመታት ማሽኖቹ በተጠሪ ተይዘዋል ቢልም ተጠሪ ተጠቅሞባቸዉ ስለማያዉቅ እስካሁን ተጠሪ በማሽኖቹ እየተገለገለ እንደሚገኝ አድርገዉ ያቀረበዉ ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡በዚህ ምክንያት በማሽኖቹ አልተጠቀምንም እንጂ ብንጠቀም እንኳን ለአመልካች የምንከፍለዉ ክፍያ አይኖርም፡፡ስለሆነም ተጠሪ ማሽኖቹንን እንዲወርስ ዉሳኔዉ ሊሻሻል ይገባል እንጂ ለአመልካች ካሳ የሚከፈልበት የሕግ መሰረት የለም ተብሎ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ማስቀረቢያ ነጥብ ከግምት በማስገባት በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደተመረመረዉም ለግራ ቀኙ ክርክር መነሻ የሆነዉ ተጠሪ አመልካችን የመገጭ ግድብ የዉሃ መቆጣጠሪያ ማማ የመሰረት ምሰሶ ጉድጓድ ቁፋሮ የግንባታ ሥራ ለማሰራት በቀን 10/05/2008 ዓ/ም ወይም እ.ኤ.አ ጃንዋሪ 19 ቀን 2016 ዓ/ም የተፈራረሙት ዉል ነዉ፡፡የግንባታዉ አጠቃላይ ዋጋ ከተ.እ.ታ ጋር

ብር57,500,920.00 እንደሆነ፣ ግንባታውን በ360 ቀናት ውስጥ ለማጠናቀቅና በጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች የተመለከቱትን የዉል ግዴታዎች ለመፈጸም ግዴታ መግባታቸዉ በግራ ቀኙ የታመነ ነዉ፡፡እንዲሁም በዉሉ መሰረት ተጠሪ ለአመልካች ቅድመ ክፍያ ብር 11,500,184.00 በቀን 24/06/2008ዓ/ም መክፈሉ፣አመልካች ቅድመ ክፍያ ከተከፈለዉ ቀን ጀምሮ በ20 ቀን ዉስጥ ግንባታ ለመጀመር የዉል ግዴታ መግባቱን፣አመልካች ግንባታ በሚፈጽምበት አካባቢ በተፈጠረ የጸጥታ ችግር ምክንያት ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠዉ ጠይቆ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ እንደገጠመዉ ተረጋግጦ በተጠሪ የ33 ቀናት ጊዜ ተጨምሮለት ግንባታ መፈጸሚያ ጊዜ ተራዝሞለት አመልካች ወደ ሥራ እንደገባ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ በተራዘመዉ ጊዜ አመልካች የሉበትን የሰዉ ኃይልና የማሽነሪ(ግንባታ የመፈጸም አቅም)ችግር መቅረፍ ባለመቻሉ ተጠሪ በዉልና በሕግ አግባብ ዉሉን መቋረጡ፤ዉሉ በተቋረጠበት ጊዜ በዉሉ መሰረት አመልካች መገንባት ከሚጠበቅበት 64 የዉሃ መቆጣጠሪያ ማማ የመሰረት ምሰሶ ጉድጓድ ዉስጥ 21 ብቻ እንደሰራ በግራ ቀኙ የታመነና በስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸዉ፡፡እንዲሁም ዉሉ በሚቋረጥበት ጊዜ ግንባታ በሚፈጸምበት ቦታ የአመልካች ንብረት የሆኑ የግንባታ መሳሪያዎች/ማሽነሪዎች በግንባታ ቦታ በተጠሪ ይዞታ ሥር እንደቀሩም የተረጋገጡ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ግራ ቀኙን ያከራከረዉና የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ ጭብጥ ዉሉ ሲቋረጥ በግንባታ ቦታ የነበሩትን የአመልካችን መሣሪያዎች/ማሽኖች ቀሪ የግንባታ ሥራ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ተጠሪ ተጠቅሞባቸዉ ግንባታዉን የማጠናቀቅ መብት አለዉ ተብሎ መወሰኑ እና ግንባታዊ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ለሚኖረዉ ጊዜ አመልካች በማሽኖች ማግኘት እችል የነበረዉንና ያጣሁትን ገቢ ተጠሪ ሊከፍለኝ ይገባል በማለት ጠይቆ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የተወሰነለትን ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ዉደቅ በማደረጉ የተፈጸመ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል ስህተት መኖር አለመኖሩን የሚመለከት ነዉ፡፡

በኮንስትራክሽን ሕግጋትና በልማድ የዳበረዉና ተቀባይነት አግኝቶ ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች ወይም የሲቪል ሥራዎች ኮንስትራክሽን ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች (Standard conditions of contract for Construction of civil works) በሚል በሚታወቁ ደንቦች ላይ የሚታወቁ የኮንስትራክሽን ሥራ በዉሉ ላይ ተወስኖ በተቀመጠዉ የግንባታ ሥራ ማጠናቀቂያ ጊዜ ዉስጥ እንዳያልቅ ወይም ግንባታዉ ሳይጠናቀቅ እንዲዘገይ የሚያደርጉ የተለያዩ ምክንያቶች ያሉ ሲሆን እነዚህም በስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ እንደተመለከተዉ በአራት የኃላፊነት ገጽታዎችና ኃላፊነት በሚያስከትሉ ሁኔታዎች(risk) ምንጮች ላይ በመመስረት የሚታወቁ ናቸዉ፡፡እነዚህም አንደኛ ሙሉ በሙሉ አሰሪዉን በሚመለከቱ ምክንያቶች ወይም ሁኔታዎች(employer's risk event) የሚከሰት፣ ሁለተኛዉ ሙሉ በሙሉ ሥራ ተቋራጩን(ንኡስ ተቋራጩን ይጨምራል) በሚመለከቱ ሁኔታዎች (contractor's risk event) የሚከሰት፣ሶስተኛዉ አሰሪዉን፣ ሥራ ተቋራጩንና አማካሪ መሀንዲሱን በሚመለከቱ ሁኔታዎች (concurrent risk event/Common risk) የሚከሰት ሲሆን አራተኛዉ ደግሞ በግንባታ ዉሉ ተሳታፊ የሆኑ ወገኖችን በማይመለከት እና ከእነዚህ አካላት ቁጥጥር ዉጭ በሆኑ ሁኔታዎች(special risk event) የሚከሰት በሚል የሚገለጹ ናቸዉ፡፡

ግራ ቀኙ በተፈራረሙት ዉል አንቀጽ 23.2 እና በዉሉ ልዩ ሁኔታ አንቀጽ 64.2/ሠ እና አንቀጽ 83.3 ስር ዉሉ የተቋረጠዉ በሥራ ተቋራጩ ጥፋት ከሆነ ሁሉም የግንባታ ቁሶች፣መሳሪያዎች፣ጊዜያዊ የግንባታ ሥራዎች እና የግንባታ ሥራዎች የአሠሪዉ እንደሚሆኑ ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል የዉላቸዉ አካል ባደረጉት የሲቪል ሥራዎች ኮንስትራክሽን ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች (Standard conditions of contract for Construction of civil works)ላይ አንቀጽ 63(1/ሠ) ስር ባለዉ የመጨረሻ ፓራግራፍ ላይ የሥራ ተቋራጭ የዉል ግዴታዉን አለመወጣት (Default of contractor) ወይም በሥራ ተቋራጩ ጥፋት ዉሉ በሚቋረጥበት ጊዜ የሚያስከትለዉን ዉጤት በተመለከተ እንደተደነገገዉ ደግሞ አሠሪዉ ከግንባታ ቦታ ሥራ ተቋራጩን በማሰናበት ለግንባታ ሥራዉ ተብለዉ በግንባታ ቦታዉ ገብተዉ የሚገኙ መሳሪያዎችንና ማሽኖችን (construction plant)፣ ጊዜያዊ ግንባታዎችንና ቁሶችን የግንባታ ሥራዉን ለማጠናቀቅ የመጠቀም መብት እንዳለዉና ተገቢ ነዉ ብሎ ሲወስን ከሥራ ተቋራጩ ለሚፈልገዉ ከዉሉ ለመነጨ የበሰለ እዳ እነዚሁኑ ንብረቶች በመሸጥ ገንዘቡን ማስመለስ(ለዕዳዉ ማካካሻ ማድረግ) እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በዚህ አግባብ ግራ ቀኙ በተፈራረሙትና በዉሉ ጠቅላላ ሁኔታዎች ላይ የተመለከተዉ ሀሳብ በአንድ በኩል ዉሉ የተቋረጠዉ በሥራ ተቋራጩ ምክንያት(ጥፋት) የተነሳ እንደሆነ በግንባታ ቦታ ላይ ያሉ ንብረቶች ላይ አሠሪዉ የባለቤትነት መብት እንዲያገኝ በሚያደርግ መልኩ የተቀረጸ ሲሆን በሌላ በኩል በግንባታ ቦታዉ ላይ ባሉት በስራ ተቋራጩ ንብረቶች እና/ወይም በጊዜያዊነት በሥራ ተቋራጩ በተሰሩ ግንባታዎች አሠሪዉ ተገልግሎባቸዉ የቀረዉን ሥራ ያጠናቅቃል በሚል በንብረቶቹ የመገልገል መብት አሰሪዉ እንዲኖረዉ በሚያደርግ መልኩ በሚጣረስ አኳኋን የተደነገገ ነዉ፡፡በአንድ ዉል ላይ ባሉ የዉል ቃላት (Provisions) መካከል በዚህ መልኩ አለመጣጣም ሲኖር በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1732 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ የተመለከተዉን የዉል አተረጓጎም መርሆዎች ተከትሎ በመተርጎም ተፈጻሚነት ያለዉን የዉሉን ሀሳብ መለየት ይገባል፡፡

በፍ/ብሕግ ቁጥር 1734 ስር እንደተደነገገዉ የዉሉ ቃል(the provision of contract)የሚያሻማ በሆነ ጊዜ ተዋዋዮቹ ዉላቸዉን ከመዋዋላቸዉ አስቀድሞ ወይም ከተዋዋሉ በኋላ የነበሩበትን ሁኔታ በማመዛዘን የተዋዋዮቹ ሐሳብ ምን እንደነበር በመፈለግ አሻሚ ለሆነዉ የዉል ቃል ትርጉም መስጠት ይገባል፡፡እንዲሁም በዚሁ ሕግ በቁጥር 1732 ስር ደግሞ ዉሎች የቅንነት፣የመተማመንን ግንኙነት መሰረት በማድረግና በጉዳዮቹ ዉስጥ ያለዉን ልማዳዊ ሥርዓት በመከተል በቅን ልቦና ሊተረጎሙ እንደሚገባም ተመልክቷል፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገዉ ዉል ጉዳይ(object) በዉሉ የተመለከተዉን ግንባታ በዉሉ በተመለከተዉ አግባብና ጊዜ አመልካች እንዲገነባ ግዴታ የሚጥል ተጠሪ ደግሞ የዉሉን ዋጋ ለአመልካች መክፈልና በዉሉ የዉሉን ጉዳይ ለመፈጸም የተቀመጡ ሌሎች ተግባራትን መወጣት ነዉ፡፡ከጠቅላላ የዉል ሁኔታዎችና ደንቦች፣ በኮንስትራክሽን ሥራ ዘርፍ ከዳበሩ ልማዶች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አመልካች በዚህ ዉል የተመለከተዉን ግዴታዉን በዉሉ በተመለከተዉ ጊዜ ወይም በስምምነት በተራዘመዉ ጊዜ ሠርቶ በማጠናቀቅ ባያስረክብ ተጠሪ እንደ ዋና ተቋራጭ የሚኖረዉ መብት ግንባታዉ ለዘገየበት ጊዜ በዉሉ አስቀድሞ የተወሰነ ኪሳራ(liquidated damage) ማስከፈል፤ እንደነገሩ ሁኔታ በዉላቸዉና በሕግ አግባብ

ግንባታው በጊዜ ባለመጠናቀቁ ምክንያት የሚደርስበትን ሌላ ወጪ ወይም የተረጋገጠ ኪሳራ(actual damage) ማስከፈል እና/ወይም በግንባታ ቦታ ላይ ባሉት የሥራ ተቋራጩ ንብረቶች በመጠቀም ቀሪዉን የግንባታ ሥራ በሌላ ተቋራጭ አሰርቶ ለማጠናቀቅ የሚያስችል በዉል ባገኘዉ መብት መሰረት በራሱ ተግባራዊ ማድረግ ወይም በፍርድ ቤት በአመልካች ላይ እንዲወሰንለት መጠየቅ ነዉ፡፡ ይህም የሚያሳየዉ የዉሉ ጉዳይም ሆነ የሥራ ተቋራጩ የዉል ግዴታ ያለመወጣት ወይም በተቋራጩ መዘግየት ምክንያት ዉሉ በተቋረጠ ጊዜ የሚከተለዉ ዉጤት የተቋራጩን የንብረት ባለቤትነት መብት ወደ አሠሪ ወይም ወደ ዋና ሥራ ተቋራጭ ማስተላለፍ እንዳልሆነ ነዉ፡፡ከዚህ የምንገነዘበዉ ግራ ቀኙ ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በተፈራረሙት ዉል ላይም ሆነ የዉላቸዉ አካል ባደረጉት ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች የተደነገገዉን የተስማሙት በአመልካች ጥፋት ዉሉ ሲቋረጥ በግንባታ ቦታ ላይ የነበሩትን ንብረቶች ባለቤትነት መብት ለተጠሪ ለማስተላለፍ በማሰብ ሳይሆን በአመልካች ምክንያት ዉሉ በመቋረጡ ተጠሪ ቀሪዉን ሥራ በራሱ ሰርቶ ለማጠናቀቅ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ አሊያም ሌላ የሥራ ተቋራጭ አስገብቶ ለማጠናቀቅ በሚያደርገዉ እንቅስቃሴ ለሥራዉ አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎችን/ማሽኖችን እየፈለገ እና ዋናዉን ግንባታ ለማከናወን የሚያስፈልጉ ጊዜያዊ ግንባታዎችን በመገንባት ተጨማሪ ጊዜ እንዳያባክን እና በአመልካች ጥፋት ለተጨማሪ ወጪ እንዳይዳረግ ለማድረግ፤ እንዲሁም ከሥራ ተቋራጩ የሚፈልገዉ ገንዘብ ካለም እነዚሁኑ የተቋራጩን ንብረቶች እንደመያዣ (lien right) በመጠቀም ማስከፈል እንዲችል መብት ለመስጠት ነዉ፡፡ስለሆነም ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ዉሉ በተቋረጠበት ጊዜ በግንባታ ቦታ የሚገኙትን መሳሪያዎችን/ማሽኖችን ቀሪ ግንባታ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ተጠሪ ይዞ የመገልገል መብት አለዉ በማለት ለዉሉ የሰጠዉ ትርጉም የተዋዋዮችን ሀሳብና የዘርፉን ልማድ ከግምት ያስገባ በመሆኑ ከዚህ አንጻር የተፈጸመ ስህተት አላገኘንም፡፡

እንዲሁም ተጠሪ ይህንን መብት ያገኘዉ ዉሉ አመልካች ኃላፊ በሆነበት ጥፋት(ጉድለት) ምክንያት በመቋረጡ ስለሆነ ተጠሪ ዉሉ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ቀሪዉ ግንባታ እስከሚጠናቀቅ ድረስ አመልካች በማሽኖቹ/በመሳሪያዎቹ ማግኘት የሚችለዉን ገቢ ለመተካት የሚገደድበት የዉልም ሆነ የሕግ መሰረት የለም፡፡ምክንያቱም ከላይ በተመለከተዉ መሰረት ተጠሪ በመሳሪያዎቹ/በማሽኖቹ የመገልገል መብት አለዉ የሚለዉ የዉሉ ጠቅላላ ሁኔታ ዉጤት የሚኖረዉ ተጠሪ በመሳሪያዎቹ/በማሽኖቹ ያለክፍያ መገልገል ሲችል ነዉ፡፡ተጠሪ ለመሳሪያዎቹ ክፍያ እየፈጸመ እንዲገለገል በዉሉ ታስቦ የነበረ ቢሆን ኖሮ መሳሪያዎቹ/ማሽኖቹ በተጠሪ እጅ በሚቆዩበት ጊዜ ተጠሪ ስለሚከፍለዉ ክፍያ አመላካች ድንጋጌ ያስቀምጡ ነበር፡፡በዚህ መልኩ በዉሉ ተጠሪ በመሳሪያዎቹ/በማሽኖቹ በሚገለገልበት ጊዜ ለአመልካች ስለሚከፍለዉ ክፍያ የሚገልጽ የዉል ቃል አለን በማለት ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡በዚህ አግባብ በዉሉ ያልተመለከተዉ ዉሉ በአመልካች ጥፋት በተቋረጠበት ሁኔታ እንዲህ አይነት የሁለቱን ግንኙነት የሚያስቀጥል ሀሳብ በዉሉ ለማኖር ሀሳብ ነበራቸዉ ለማለት የሚያስችል አሳማኝ አመክኒዮ ባለመኖሩና በአመልካች ላይ እንዲህ አይነት ኃላፊነት የመጣበት ዉሉ በሱ ጥፋት በመቋረጡ ምክንያት ስለሆነ ነዉ፡፡

ስለሆነም ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ተጠሪ በዉሉ መሰረት በግንባታ ቦታ በሚገኙት የአመልካች መሳሪያዎች እና/ ወይም ማሽኖች ቀሪዉ ግንባታ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የመገልገል መብት ስላለዉ አመልካች

በመሳሪያዎቹ እና/ ወይም በማሽኖቹ ማግኘት እችል የነበረዉን ገቢ አጣሁኝ በማለት እንዲከፈለዉ የጠየቀዉን ተጠሪ ሊከፍል አይገባም በማለት የስር ፍርድ ቤት ከዚህ አኳያ የወሰነዉን በመሻር የሰጠዉ ዉሳኔ ዉሉንና ሕግን መሰረት ያደረገ ነዉ ከሚባል በስተቀር የተፈጸመ ስህተት አላገኘንም፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የእነዚህ መሳሪያዎች እና/ ወይም ማሽኖች ባለቤትነት መብት የአመልካች በመሆኑ ቀሪዉ የግንባታ ሥራ በተጠሪ ምክንያት ወይም በአሰሪዉ ዉሳኔ ወይም በሌላ ምክንያት እንዲቀር ከተደረገ(ከተተወ) አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክስ ላይ ዘርዝሮ ያቀረባቸዉ መሳሪያዎች እና/ ወይም ማሽኖች እንዲመለሱለት ከመጠየቅ ይህ ዉሳኔ የሚያግደዉ አይደለም ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 187031 ላይ በቀን 25/12/2012ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት የወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

1. በዉሳኔዉ መሰረት እንዲፈጽም የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡- ተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃላ/የተ/የግ ማኅበር -

ተጠሪ ፡-የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን

ተጠሪ በቀን 01/06/2013 ዓ/ም ጽፎ ያቀረበዉን መስቀለኛ የሰበር አቤቱታ መርምረን የሚከተለዉን ትእዛዝ ሰጥተናል፡፡

ት እ ዛ ዝ

የተጠሪ መስቀለኛ አቤቱታ ዉሉ ሲቋረጥ በግንባታ ቦታ የነበሩትን የአመልካችን መሳሪያዎች/ማሽነሪዎች በዉሉ መሰረት እንዲወርስ አለመወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ የሚል ነዉ፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነዉ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገዉ የኮንስትራክሽን ሥራ ዉል ተጠሪ ቀሪዉን ሥራ በመሳሪያዎቹ/በማሽኖቹ እየተገለገለ እንዲያጠናቅቅ መብት የሚሰጠዉ እንጂ በመሳሪያዎቹ/በማሽኖቹ ላይ የባለቤትን መብት የሚሰጠዉ ባለመሆኑ ከዚህ አንጻር ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በመ/ቁጥር 187031 ላይ በቀን 25/12/2012ዓ/ም እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 220306 በቀን 10/02/2012 ዓ/ም የሰጡት ዉሳኔ ጉድለት ስለሌለባቸዉ አቤቱታዉን ሰርዘናል፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

??/? /??? 196346
?? 26/11/2013 ?/?

ዳኞች ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች - አቶ በፍቃዱ ጌታቸው፡- **ጠበቃ ከፋለኝ ደጉ ቀረቡ**

ተጠሪ - 1. አቶ ዮናስ ጌታነህ 2. ወ/ሮ ብዙነሽ ጌታነህ 3. አቶ ተስፋዬ ጌታነህ
4. ወ/ሮ ሸዋዬ ጌታነህ 5. ወ/ሮ ዘነበች ጌታነህ 6. ወ/ሮ ሙሉ ብርሃን ጌታነህ
7. አቶ በየነ ደረሰ 8. አቶ አዲሱ ጌታነህ ፡- **ተወካይ ዘነበች ጌታነህ ቀረቡ**

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች መስከረም 22 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 182644 ሰኔ 12 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታውን በማቅረቡ ነው፡፡ ቅሬታውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የሚቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ ያከራከረን ቤት በእናቴ ስም የተመዘገበ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ጣልቃ ገብዎች ቤቶቹን ሰራን የሚሉት 1ኛ ጣ/ገብ አያቴ ሞግዚቴ ሆኖ ባለበት ጊዜ መሆኑ እየታወቀ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያላደረኩትን እርቅ መሰረት አደርጎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ባቀረበው አቤቱታ እናቴ ወ/ሮ ዓለምነሽ ጌታነህ በ1989 ዓ/ም ሞታለች፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ወራሽነቱን በ2009 ዓ/ም አረጋግጫለሁ፡፡ እናቴ በህይወት እያለች ያፈራችው ንብረት በን/ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ወረዳ 7 ውስጥ ያለ የቤት ቁጥር 1711 የሆነው ቤት የእናቴ ውርስ ሀብት ስለሆነና አጣርቼ ያቀረብኩት በመሆኑ እንዲጸድቅልኝ ሲል ጠይቋል፡፡ ጣልቃ ገብዎች 1. አቶ ጌትነት አበበ፣ 2. አቶ ዮናስ ጌትነት፣ 3. ብዙነሽ ጌታነህ፣ 4. አቶ ተስፋዬ ጌታነህ 5. ሸዋዬ ጌታነህ 6. ዘነበች ጌታነህ 7. ሙሉብርሃን ጌታነህ 8. ፊቴን በየነ 9. አቶ አዲሱ ጌታነህ ባቀረቡት አቤቱታ ቤቱ በሚች ወ/ሮ ዓለምነሽ ጌታነህ ስም ይመዝገብ እንጂ ቦታው ላይ ያሉት ቤቶች በጣልቃ ገብዎች የተሰሩ ናቸው፡፡ በመሆኑም አቤቱታው ውድቅ ይሁንልን በሚል ተከራክረዋል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 124770 ታህሳስ 1 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ያከራከረው የቤት ቁጥር 1171 የሆነው ቤት ቦታው በአመልካች እናት ስም የተመዘገበ መሆኑን በቀረበው የሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠ ቢሆንም በቦታው ላይ ጣልቃ ገብዎች ቤት የሰሩበትና ሲኖሩበት የነበሩ መሆኑን፣ ቤቱን ሲሰሩ የተቃወማቸው የሌለ መሆኑ በመረጋገጡና አመልካችም ያላስተባበለው በመሆኑ፣ የንብረት ባለቤት ነኝ የሚል በሀብቱ በገንዘቡ በዕውቀቱ ያፈራው ንብረት መሆኑን ማረጋገጥ የሚገባውና ይህንንም አመልካች ባለማረጋገጡ የውርስ ንብረት ነው ለማለት የሚቻል አይደለም ሲል የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ አከራክሮ በመ/ቁጥር 222293 ሐምሌ 4 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ያከራከረው የቤት ቁጥር 1171 የሆነው ቤት በአመልካች እናት ስም ተመዝግቦ የሚገኝ በመሆኑና እናቴ ስትሞት 1ኛ ጣልቃ ገብ አያቱ የአመልካች ሞግዚት መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ፣ 1ኛ ጣልቃ ገብ የአመልካች ሞግዚት ሆኖ ሀብቱንም ቁጭር ሲያስተዳድር ባለበት ጊዜ ከ2ኛ እስከ 9ኛ ያሉት ጣልቃ ገብዎች በቦታው ላይ ቤት በመስራታቸው የተቃወማቸው የለም ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም ቤቱ የውርስ ንብረት ነው፡፡ ጣልቃ ገብዎች ሰራን ለሚሉት ቤት ግምቱን መጠየቅ ይችላሉ ሲል የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር ወስኗል፡፡ ጣልቃ ገብዎች ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርበው አከራክሮ በመ/ቁጥር 182644 ሰኔ 12 ቅን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ያከራከረው የቤት ቁጥር 1171 የሆነው ቤት በአመልካች እናት ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቢሆንም ይዞታውን ያገኙት 1ኛ ጣልቃ ገብ አባቷ ናቸው፡፡ በጊዜው አባቷ 1ኛ ጣልቃ ገብ ሌላ ቤት ስለነበረው በአመልካች እናት (በልጁ) ስም ያስመዘገበ መሆኑና በይዞታው ላይ ቤቶች የተሰሩትም በጣልቃ ገብዎች መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም ግራ ቀኙ በ30/8/2002 ዓ/ም በሽማግሌዎች ባደረጉት እርቅ ይህንኑ ፍሬ ነገር በማስፈር ጣልቃ ገብዎች የሰሩት ቤት የራሳቸው ሆኖ አመልካች የሰራውን 9*16 = 144 ካ/ሜ ይዞታ እንዲወስድ የተስማሙ መሆኑንም ያሳያል፡፡ ይሁንና አመልካች የእርቁ የመጀመሪያ ገጽ ላይ አልፈረምኩም፣ ሽማግሌዎች በመጨረሻው ገጽ ላይ አልፈረሙም ከሚል ክርክር ውጪ እርቁን አላደረኩም የሚል ክርክር የለውም፡፡ በዚሁ እርቅ መሰረት መፈጸም ሲገባ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሞግዚትነቱን ሁኔታ ብቻ በማየት የሰጠው ውሳኔ ስህተት ነው ሲል የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ሽሮ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤትና ይዞታ በአሁኑ አመልካች እናት ስም ተመዝግቦ እያለ የውርስ ሃብት አይደለም ተብሎ ለተጠሪዎች የተወሰነበትን አግባብ ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪዎች ታህሳስ 21 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልን ሲሉ ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የካቲት 17 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመለከት፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን

የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ግራ ቀኙን ያከራከረው ቤት በአሁን አመልካች እናት ስም ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን፣ ቤቱ በአሁን አመልካች እናት ስም የተመዘገበው በተለያየ ምክንያት ከቦታቸው ለተነሱ ነዋሪዎች መንግስት ምትክ ቦታ ሲሰጣቸው ለስር ፍ/ቤት 1ኛ ጣልቃ ገብ የተሰጠና 1ኛ ጣልቃ ገብ ሌላ ቤት ስለነበረውና በወቅቱ ለከተማው ነዋሪ ሁለት ቤት ስለማይፈቀድ በልጁ በአሁን አመልካች እናት ስም ያስመዘገበ መሆኑን፣ እንዲሁም በይዘታው ላይ ያሉት ቤቶች በጣልቃ ገብዎች የተሰሩ መሆኑንም ማስረጃ የመስማትና የመመዘን ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት አረጋግጦ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁን አመልካች አቤቱታ ቅሬታ ያከራከረው ቤት የውርስ ንብረት መሆኑ በቀረቡት ማስረጃ ተረጋግጦ እያለ አቤቱታዬ ውድቅ መሆኑ ተገቢ አይደለም የሚል የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10(1) መሰረት ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከተሰጠው ስልጣን ውጭ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚሁ መሰረት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 182644 ሰኔ 12 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻላሉ፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የመ.ቁ.196871

ሐምሌ 27/2013 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ አቶ ሀብታሙ ዝናቡ ፡- ቀርበዋል

ተጠሪ፡ አቶ ታሪኩ አየለ ፡- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የከተማ ይዞታ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/333779 ላይ ጥቅምት 03/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔን በማፅናት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ለማስለወጥ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ ሐምሌ 05/2011 ዓ.ም ፅፈው በአሁን አመልካች ላይ በጅማ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ ፍሬ ቃሉም ቦታ እና አዋሳኙ በክሱ ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሰውን 200 ካሬ ሜትር የከተማ ይዞታ ነሐሴ 06/2011 ዓ.ም ተሰጥቷቸው አስፈላጊውን ክፍያ ፈፅመው እና የግንባታ ፈቃድ አውጥተው በቦታው ላይ ግንባታ ለማከናወን ሲሄዱ ባላወቁት መንገድ የአሁን አመልካች ትንሽ ሰርቪስ ቤት ሰርተዉበት የያዙባቸው መሆኑን በመግለፅ በፍርድ ኃይል ተገደው በቦታው ላይ የሰሩትን ቤት አፍርሰው እንዲለቁላቸው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች ለዚሁ ክስ በሰጡት መልስ ይዞታውን በ1987 ዓ.ም በሽንሻኖ ያገኘሁት ህጋዊ ይዞታዬ ነው፤ ተጠሪ ከክሳቸው ጋር ያቀረቡት ማስረጃም ይዞታውን የሚመለከት አይደለም፤ ተጠሪ ከአካባቢውም ምንም ይዞታ የሌላቸው በመሆኑ ልለቅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት እና ስለጉዳዩም ከአስተዳደር ክፍሉ ተጣርቶ እንዲቀርብለት በማድርግ እንዲሁም ይዞታው ለተጠሪ ሲሰጥ ነበሩ የተባሉትን የክፍሉ መሬት አስተዳደር ባለሙያዎች የይዞታውን ማህደር ይዘው በመቅረብ ስለይዞታው አሰጣጥ እንዲያስረዱ ካደረገ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ለክርክር ምክንያት የሆነው ይዞታ ቀደምት ይዞታነቱ የአሁን አመልካች ቢሆንም ይዞታው ከአምልካች ላይ በህጋዊ መንገድ ተወስዶ ለአሁን ተጠሪ በሽንሻኖ የተሰጠ መሆኑን፤ ይህ ሲሆንም በዞታው ላይ ዛፍ ብቻ እንጂ በአመልካች የተሰራ ቤት ያልነበረበት ስለመሆኑ አረጋግጫለሁ በማለት አመልካች በቦታው ላይ የሰሩትን ቤት አፍርሰው ይዞታውን ለተጠሪ ሊለቁ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ ይኸው ውሳኔ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ፀንቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ጥቅምት 11/2013 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለክርክር መነሻ የሆነው ይዞታ ለአሁን ተጠሪ ከመሰጠቱ በፊት የአመልካች ቤት የነበረበት መሆኑ ባልተካደበት አመልካች ቤቱን አፍርሰው ይዞታውን ለተጠሪ ያስረክቡ ተብሎ የተወሰነበት አግባብ ግራ ቀኙ በተገኙበት ለዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ይህንን ሲመስል ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ እና በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር አንፃር አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንግዲህ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ይዘት መረዳት እንደሚቻው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይዞታ ቀደምት ይዞታነቱ የአሁን አመልካች ቢሆንም ስልጣን ባለው አስተዳደር አካል ከአመልካች ተወስዶ አስተዳደር እጅ ከገባ በኋላ በህጋዊ መንገድ ለአሁን ተጠሪ በሽንሻኖ የተሰጠ ለመሆኑ ማስረጃን የመመርመር እና የመመዘን ስልጣን ባለው የወረዳው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ የይዞታውን አወሳሰድ በተመለከተም በይዞታው አካባቢ በተደረገ አሰሳ ከአንድ ሰው በቀር አመልካችን ጨምሮ በርካታ ሰዎች በአካባቢው ያለምንም ህጋዊ መብት መሬት ይዘው የነበረ በመሆኑ መንግስት ሰዎቹን በማሳመን ተቀብሏቸው በሽንሻኖ ለሌሎች ሰዎች የሰጠ መሆኑን እና በዚሁ አግባብ አሁን ክስ የቀረበበት ይዞታ ለተጠሪ የተሰጣቸው ስለመሆኑ በክፍሉ መሬት አስተዳደር ባለሙያዎች በዝርዝር መገለፁን የወረዳው ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡ በይዞታው ላይ ለተጠሪ የተሰጠውን የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ህጋዊነትን አስመልክቶ ትክክለኛው እና ህጋዊ ሰነድ በተጠሪው እጅ ያለው ሲሆን በመሬት አስተዳደሩ ጽ/ቤት በሚገኘው ቀሪ ላይ በጽ/ቤቱ ሰራተኛ ሆነ ተብሎ JU30P1 የነበረው 1 ቁጥሩን በካርቦን ፅሁፍ ወደ 4 ተለውጦ የተተካ ስለመሆኑ ተደርሶበት ሰራተኛው በስነ ምግባር የተረከሰሰ ስለመሆኑንም መረጋገጡ ተገልጿል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ከእነዚህ በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋጡት ነጥቦች በግልፅ መረዳት የሚቻለው የአሁን አመልካች ለክርክር ምክንያት በሆነው ይዞታ ላይ ቀድሞውንም ቢሆን በህግ ጥበቃ የሚደረግለት የይዞታ መብት ያላቋቋሙ ሲሆን ይዞታው ስልጣን ባለው አስተዳደር አካል ከአመልካች ላይ ተወስዶ ለተጠሪ በሰነድ ተረጋግጦ የተሰጣቸው መሆኑን ነው፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ ይህ ከተረጋገጠ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ማስረጃን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ በመሆኑም የአመልካች የሰበር ቅሬታ ውድቅ ተደርጎ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/333779 ላይ ጥቅምት 03/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔን በማፅናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-196963

ቀን፡-04/02/2014ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቶ ደሣለኝ ሲሳይ

ተጠሪ ፡- 1. ወ/ሮ ድማም ተክሉ
2. አቶ መንግስቱ አዘነ

} አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታ የቀረበው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በሚል ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ ሲሆኑ 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ እና 2ኛ ተጠሪ ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ ከባለቤቱ አቶ አዘነ በየነ ጋር የባንክና የዕቁብ ዕዳ ስለነበረብን በቡራዩ ከተማ ዉስጥ የነበረንን ቤት በቀን 24/08/1999 ዓ/ም በተደረገ ዉል ሽጠን በሱሉልታ ከተማ ቁምቡራ በተባለ ቦታ በካርታ ቁጥር ሱል/243/2005 ሆኖ የሚታወቀዉን ቤት የአሁን 2ኛ ተጠሪ ልጃችን ስለሆነ በስሙ ከአቶ ዳዊት አለሙ ላይ ገዝተናል፡፡ ይሁን እንጂ ባለቤቴ በሞት ሲለይ አመልካች ቤቱን ስለያዘብኝ ቤቱንና ሰነዱን እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ በማለት

ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት በራሴ ገንዘብ የገዛሁት እንጂ የ1ኛ ተጠሪ አይደለም ብለዋል፡፡ አመልካች በክርክሩ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 41 መሰረት ጣልቃ በመግባት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት በቀን 28/01/2011ዓ/ም በተደረገ ዉል በብር 443,594.25 ከ2ኛ ተጠሪ ላይ ገዝቼ በስሜ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ቁጥር ሱል/562/11 ከቀን 06/02/2011ዓ/ም ጀምሮ አስመዝግቤ የያዝኩት ነው፡፡ ክርክር ያስነሳውን ቤት በግዥ ያገኘሁት ስለሆነ ሊከራከሩበት አይገባም ብለዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ለጣልቃ-ገብ ማመልከቻ ባቀረቡት መልስ ቤቱን አመልካች የገዛው ክስ ካቀረብኩና እግድ እንዲሰጥ ከጠየቅሁ በኋላ ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪም ፍርድ ቤት ሳይቀርብ ነው የሸጠው፤ አመልካች መብት የሌለው መሆኑን እያወቀ የገዛው ስለሆነ ክርክሩ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ንብረቱን ለአመልካች መሸጣቸውን በመግለጽ መልስ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት የ2ኛ ተጠሪ አባት(የ1ኛ ተጠሪ ባለቤት) በ2ኛ ተጠሪ ስም ለራሳቸዉ ጥቅም በገንዘባቸዉ የገዙ ስለመሆኑ ምስክሮቻቸዉ አላስረዱም፡፡ ቤቱ የተገዛዉ በ2ኛ ተጠሪ ስም በመሆኑና ተመዝግቦ የሚገኘዉም በ2ኛ ተጠሪ ስም ስለሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1195 መሰረት 2ኛ ተጠሪ የቤቱ ባለቤት እንደሆኑ ይገመታል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ መብት ለማግኘት ቤቱ በ1ኛ ተጠሪ እና በባለቤታቸዉ ገንዘብ በአሁን 2ኛ ተጠሪ ስም መገዛቱን በማስረጃ በማረጋገጥ ግምቱን ማስተባበል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ማስረጃዉ ሲመረመር የቤቱ ባለቤት 2ኛ ተጠሪ እንደሆኑ የሚያስቆጥረዉን ግምት በማስረጃ አላስተባበሉም በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ ሚዛን በሚደፋ ሁኔታ ማስረጃዎቹ የሚያሳዩት 1ኛ ተጠሪ ከባለቤታቸዉ ጋር የነበራቸዉን እዳ ለመሰወር በማሳብ የነበራቸዉን ቤት ሸጠዉ በ2ኛ ተጠሪ ስም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት መግዛታቸዉን ነዉ፡፡ በሕብረተሰቡ ዉስጥ ባለዉ ተጨባጭ ሁኔታ አባት በልጁ ስም ቤትም ሆነ ሌላ ንብረት የሚገዛ መሆኑ የተለመደ ነዉ፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች 1ኛ ተጠሪ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1195 መሰረት ቤቱ በ2ኛ ተጠሪ ስም ሊመዘገብ የቻለበትን ምክንያት በማስረዳት ግምቱን አስተባብለዋል፡፡ አመልካች ንብረቱ በቅን ልቦና ከ2ኛ ተጠሪ አልገዙትም፤ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ላይ ክስ የመሰረቱት በቀን 23/01/2011 ዓ/ም ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ደግሞ አከራካሪዉን ቤት ለአመልካች በሽያጭ ያስተላለፉት በቀን 28/01/2011 ዓ/ም ክሱ ከተመሰረተ ከ5ቀን በኋላ እንደሆነ የቀረበዉ ማስረጃ ስለሚያሳይና አስቀድሞ ከብር አንድ ሚሊዮን በላይ በሆነ ገንዘብ የተገዛዉን ቤት 2ኛ ተጠሪ ለአመልካች በብር 445,000.00 እንደሸጡ በመግለጽ መከራከራቸዉ ሲታይ በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል በድብቅ ግንኙነት መኖሩን ያሳያል፡፡ ስለሆነም ክርክር ያስነሳዉን ንብረት 1ኛ ተጠሪ በሞት ከተለዩት ባለቤታቸዉ አቶ አዘነ በየነ ጋር ያፈሩት ንብረት ነዉ በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በመሻር አመልካች ቤቱን ለመግዛት ለ2ኛ ተጠሪ የከፈሉትን ገንዘብ ከ2ኛ ተጠሪ ላይ ከማስመለስ ዉሳኔዉ እንደማያግድ ገልጾ ወስኗል፡፡ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡትን የሠበር አቤቱታ ባለመቀበል ሠርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም 2ኛ ተጠሪ በስሙ ካርታ መያዙን፣ የሊዝ ውል መዋዋሉን አይቼ በውል አዋዋይ ፊት በተደረገ ውል ገዝቼና ስመ-ሀብት አዛውሬ የያዝኩት ንብረት ነው፡፡ የ2ኛ ተጠሪ አባት በሕይወት እያለ 2ኛ ተጠሪ የሊዝ ውል ተዋዋሎ ያዛወረውን ድብቅ ግንኙነት መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ንብረቱን በምገዛበት ጊዜ በፍርድ ቤት እግድ አልተሰጠበትም፡፡ የቤቱ ዋጋ ብር 445,000.00 የተባለው የመሐንዲስ ዋጋ ግምት ነው፤ ቤቱን የሸጠልኝ በብር 1,200,000.00 ነው፡፡ ተጠሪዎች ያላቸውን ግንኙነት አላውቅም፤ በንብረቱ ላይ ያለኝ መብት ሊከበር ይገባል የሚል ነዉ፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት 2ኛ ተጠሪ በስሙ የሚገኘውን ለአመልካች በሽያጭ አስተላልፈው ባለበት ሁኔታ ቤቱን እንዲለቁ የመወሰኑ አግባብነትን ተጠሪዎች ባሉበት እንዲጣራ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት መልስ ንብረቱ ላይ ክስ ካቀረብኩ በኋላ እገድ እንዲሰጥበት ጥያቄ አቅርቤ በእግድ ማመልከቻው ላይ 2ኛ ተጠሪ አስተያየት እንዲሰጡበት ትዕዛዝ ተሰጥቶ፤ 2ኛ ተጠሪ ትዕዛዙን አልቀበልም ካሉ በኋላ በ5 ቀናት ውስጥ ባላቸው ግንኙነት፣ 2ኛ ተጠሪን ለመርዳት በዝቀተኛ ዋጋ የተሸጠው ንብረቱን ለማሸሽ ነው፡፡ በማጭበርበርና ከቅን ልቦና ውጭ የተደረገ ሽያጭ ስለሆነ የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም ብለዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ንብረቱ የራሴ ነው፤ ውል ለመዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት የባንክ ዕዳ እና የፍርድ ቤት እግድ እንደሌለው ተረጋግጦ ለአመልካች በሽያጭ ውል የተላለፈና በስሙ አዛውሮ ባለሀብት የሆነበት ንብረት ነው ብለዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኝ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር፣ የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ማስቀረቢያ ነጥብ መሰረት በማድረግ ዉሳኔው ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በሱሉልታ ከተማ ቁምቡሬ በተባለ ቦታ በካርታ ቁጥር ሱል/243/2005 በ2ኛ ተጠሪ ስም ያለው ንብረት የ1ኛ ተጠሪና የሚኝ ባለቤቱ ስለሆነ ቤቱን ከነሰነዱ 2ኛ ተጠሪ ሊያስረክበኝ ይገባል በሚል ባቀረቡት ክርክር መነሻነት የተጠሪዎች ክርክር እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ በመዝገብ ቁጥር 196173 ሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ/ም በሠጠው ውሳኔ ንብረቱ በ2ኛ ተጠሪ ስም የተገዛ ቢሆንም የተገዛበት ገንዘብና ባለቤትነቱ የ1ኛ ተጠሪና የባለቤታቸው ስለመሆኑ በመረጋገጡ ለ2ኛ ተጠሪ በሕግ የተሰጣቸው የባለሀብትነት ግምት ስለመስተባበሉ በሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማስረጃ ተረጋግጦ ንብረቱ የ1ኛ ተጠሪና የባለቤታቸው ተብሎ የተሠጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ በዚህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ላይ አመልካች በክርክር ያልተሳተፉ በመሆኑ ንብረቱን ከ2ኛ ተጠሪ መግዛታቸው ውጤቱ በጭብጥነት ተይዞ አልተመረመረም፡፡ በዚህም ምክንያት አመልካች አሁን በተያዘው መዝገብ ላይ የሠበር አቤቱታቸውን ያቀረቡ በመሆኑ በተጠሪዎች ክርክር ንብረቱን ገዝቻለሁ በሚል ያቀረቡት የጣልቃ ገብነት ማመልከቻና ሕጋዊ ውጤቱን በቀጣይነት እንመለከታለን፡፡

በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41 መሠረት ጣልቃ የሚገባ ተከራካሪ ክርክሩ መብቱን የሚነካው እና በጉዳዩ ላይ የተረጋገጠ መብት ያለው መሆኑን ማሳየት አለበት፡፡ አመልካችም ጣልቃ የገቡት ክርክር ያስነሳውን ንብረት 2ኛ ተጠሪ በስማቸው ካርታ አውጥተው የያዙትን መስከረም 28 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገ ውል ገዝቼዋለሁ፡፡ ውሉም ሥልጣን ባለው አካል የተመዘገበና ስመ-ሀብቱ ተላልፎ የባለቤትነት ማረጋገጫ ያወጣሁበት ነው፡፡ ስለዚህ የ1ኛ ተጠሪ ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ የሚከራከሩት አመልካች ቤቱን የገዛው ክስ ካቀረብኩና እግድ እንዲሰጥ ከጠየቅሁ በኋላ ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪም ፍርድ ቤት ሳይቀርብ ነው የሸጠው፤ አመልካች መብት የሌለው መሆኑን እያወቀ የገዛው ስለሆነ ክርክሩ ተቀባይነት የለውም በሚል ነው፡፡ ክክርክሩ የተረዳነው 2ኛ ተጠሪ ቤቱን በስማቸው ከገዙ በኋላ ለአመልካች ውል ለመዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ሽያጭ ውል በማድረግ ባለሀብትነት መብትን አስተላልፈዋል፡፡

አመልካች መብቱ የተላለፈላቸው ጥበቃ ሊደረግለት በሚገባ ግብይት መሆን አለመሆኑን መመልከት ተገቢ ነው፡፡ አመልካች ግዥ ሲፈጽሙ አንድ ጠንቃቃ ገዥ በሕግ ሆነ በአሠራር ሊያደርገው የሚገባውን ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ሕግ የተለየ ጥበቃ ስለሚያደርግ የሀብትነት ሠነድ ስለሚወጣበት፤ ሠነዱ ስለሚገኝበት የሥራ ክፍል፣ ውሉ ስለሚፈጸምበት እና ንብረቱ ስለሚተላለፍበት ሥርዓት የተገለጸውን መከተል ግዴታ ይጥላል፡፡ ሽያጭ ውል ሊፈጸምበት በሚችል የከተማ ክልል ውስጥ ያለ፣ ቦታው ላይ ቤት ያረፈበትና ስለቤቱ የሚመለከቱ ሠነዶች በቤቱ ባለሀብት ሥም በማይንቀሳቀስ ሀብት ምዘገባ ክፍል መገኘቱና ውሉን የፍ/ሕ/ቁ. 1723(1) በሚያዘው አግባብ ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት ማድረግ ይጠበቃል፡፡

አመልካች ውሉን የፈጸሙት 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ገዝተው ሕጋዊ ሠነድ በቤቱ ላይ ካወጡበት በኋላ ሕጋዊ ባለቤት እንዳለው በማረጋገጥ በውል አዋዋይ ፊት መሆኑ ሲታይ ግብይቱ ሕግን መሠረት ያደረገ በመሆኑ የሕግ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ ነው፡፡ አመልካች ውሉን የማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ እንዲጸፍ በማድረግ ካርታ ያወጡበት በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 2878 እንደተመለከተው ውሉ ሦስተኛ ወገኖችን ላይም ውጤት ያለው ነው፡፡ ሕግን መሠረት ላደረገ ግብይት ፍርድ ቤት ሕጋዊ ጥበቃ በመስጠት ገበያው በሕግ እንዲመራ ሆነ የኢኮኖሚ እንቅሳቀሴው ጤናማ በሆነ ሁኔታ እንዲመራ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡ ንብረቱ በ2ኛ ተጠሪ ስም ከመመዝገቡ እና ወደ አመልካች በሽያጭ ውል በሠነድ ከመዛወሩ በፊት መብቱ የማን ነው የሚለውን አመልካች የማጣራት ኃላፊነት በሕግ የለባቸውም፡፡ ንብረቱ ላይ በፍርድ ቤት እግድ ከመሰጠቱ በፊት የተዛወረ ከመሆኑ አኳያ አመልካች ክስ ካቀረቡ በኋላ ሽያጭ ውሉ መደረጉ ሆነ የተሸጠበት ዋጋ የተደረገውን ግብይት ቀሪና ውጤት አልባ አያደርገውም፡፡ ምንም እንኳን 1ኛ ተጠሪ በንብረቱ ላይ መብት ያላቸው ስለመሆኑ በፍርድ የተረጋገጠላቸው ቢሆንም ይህ መብታቸው ከመረጋገጡ በፊት 2ኛ ተጠሪ በስማቸው የነበረውን ንብረት ለሦስተኛ ወገን ለሆኑት ለአመልካች ያስተላለፉ በመሆኑ፤ ከሦስተኛ ወገን መብት አኳያ ንብረቱን 1ኛ ተጠሪ ሊረከቡ አይችሉም ብለናል፡፡ ሥለሆነም ክርክር ያስነሳው ንብረት ሕጋዊ ባለመብት አመልካች በመሆናቸው 1ኛ ተጠሪ ንብረት ለመረከብ ያቀረቡት ክስ ውድቅ ሊደረግ ሲገባ ይሕ ታልፎ የተሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ውሳኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 333206 ነሀሴ 07 ቀን 2012 ዓ/ም እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 322981 ሚያዚያ 20 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 33894 ጥር 27 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጠው ውሳኔ በውጤት ደረጃ ጸንቷል፡፡

3. 1ኛ ተጠሪ የሽያጭ ገንዘቡን ከ2ኛ ተጠሪ ለመጠየቅ ሆነ ወይም በሕግ አለኝ የሚሉትን መብት ክስ አቅርበው ከመከራከር ይሕ ውሳኔ አያግድም ብለናል፡፡

4. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሄ/መ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-197008

ቀን፡- 05/02/2014 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- አዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን - ጠበቃ መኮንን ይማም ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ፀጋ ረታ አስመጪ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ክርክሩ የሽያጭ ውልን መነሻ ያደረገ ሲሆን ጉዳዩ በተጀመረበት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የካቲት 4 ቀን 2011 ዓ.ም ባቀረበው ክስ አመልካች የኮምፒዩተር እቃዎችን ለመግዛት ባወጣው ጨረታ ተጠሪ አሸንፎ እቃዎቹን አቅርቦ ክፍያ የተቀበለ ቢሆንም እቃዎቹን ከሰርቨሩ ጋር የሚያገናኙ ኬብሎችን ባለማቅረቡ ምክንያት እቃዎቹ የተፈለገውን አገልግሎት መስጠት አልቻሉም፡፡ በመሆኑም ኬብሎቹን እንዲያቀርብ ወይም በወቅቱ የገበያ ዋጋ የእቃዎቹን ግምት ብር 182,900 ወጪና ኪሳራን ጨምሮ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተጠሪ የካቲት 29 ቀን 2011 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች እቃዎቹ ጉድለት ያለባቸው መሆኑን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ1 አመት ውስጥ ክስ ስላላቀረበ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመቃወሚያው ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ግንኙነታቸው የሽያጭ ውልን መሰረት ያደረገ ስለሆነ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው ስለውሎች በጠቅላላው የተደነገገው የፍ/ሕ/ቁጥር 1845 ሳይሆን የሽያጭ ውልን የሚመለከተው የፍ/ሕ/ቁጥር 2298(1) ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረትም በሻጩ አጭበርባሪነት ካልሆነ በቀር ገዢው ጉድለቱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ1 ዓመት ጊዜ ውስጥ ክስ ማቅረብ አለበት፡፡ አመልካች የተጠሪ አጭበርባሪነት ያለበት ስለመሆኑ በክሱ ያልገለፀ ሲሆን ተጠሪው የእቃዎቹን ጉድለት እንዲያስተካክል ያሳወቀው ጥቅምት 7 ቀን 2009 ዓ.ም እንዲሁም ለተረከባቸው እቃዎች ክፍያ የፈጸመው ጥቅምት 25 ቀን 2009 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ የቀረበው ሁለት ኣመት ካለፈው በኂላ የካቲት 4 ቀን 2011 ዓ.ም ነው፡፡ የተጠሪ ሰራተኛ ሰኔ 10 ቀን 2009 ዓ.ም UPS 5kg ለቼክአፕ መውሰዱ ጉድለቱን በግልፅ አምኗል አያስብልም፡፡ አምኗል ቢባል እንኳ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በ1 ዓመት ውስጥ ክሱ ስላልቀረበ በይርጋ ይተጋዳል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት በማፅናቱ ጥቅምት 13 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታውን አቅርቧል፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ አመልካች በክሱ ላይ ፍሬ ነገርን ከመግለፅ በዘለለ ተጠሪው መቃወሚያ ሊያቀርብ ይችላል ብሎ በማሰብ በክስ መስማት ወቅት ሊያቀርብ የሚችለውን መከራከሪያ አስቀድሞ ማቅረብ ግዴታ በሌለበት ተጠሪው የማታለል እና የማጭበርበር ተግባር ስለመፈፀሙ አመልካች በክሱ አልገለፀም መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ተጠሪ እቃዎቹን አስተካክላለው ብሎ መውሰዱን አልካደም፡፡ የወሰደውም እቃውን ባስረከበ በአንድ ዓመት ውስጥ ሲሆን እቃውን በእምነት በመውሰድ በተግባር የማታለል እና የማጭበርበር ተግባር የፈፀመ ሲሆን እቃዎቹን አስተካክሎ የሚያቀርብበት ጊዜም ስላልተወሰነ እና እቃዎቹን አስተካክሎ እንዲያስረክብ በተደጋጋሚ በአመልካች ሲጠየቅ ከዛሬ ነገር አስተካክዬ እመልሳለው ማለቱ ስላልተካደ አስፈላጊ ከሆነም ምስክሮቻችንን በመስማት ሊጣራ ሲገባ ክሱ በይርጋ ይታገዳል መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ውሉ የሽያጭ ብቻ ሳይሆን የጥገና ማደስና መለዋወጫ ማቅረብ መሆኑ በሰነድ ተረጋግጦ እያለ ሽያጭ ብቻ ነው ተብሎ የሽያጭ ሕግ የይርጋ ድንጋጌ ተግባራዊ መደረጉ እንዲሁም እቃው በተጠሪ እጅ ያለ በመሆኑ አመልካች በማንኛውም ጊዜ ንብረቱን መጠየቅ የሚችል ሁኖ እያ ክሱ በይርጋ ይታገዳል መባሉ የፍ/ሕ/ቁጥር 1206 እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 63600 ቅፅ 10 የሰጠውን ውሳኔ የሚቃረን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ነው፡፡

አቤቱታው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ተጠሪ የእቃውን ጉድለት አምኖ መልሶ መቀበሉን ለክሱ በሰጠው መልስ አምኖ እያለ ክሱ በአንድ አመት ይርጋ ይታገዳል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ከፍ/ሕ/ቁጥር

2298(1) እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ ለመመርመር ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልሱን እንዲያቀርብ ታዟል፡፡

ተጠሪም ጥር 10 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱ ይዘት ባጭሩ ተጠሪ ለክሱ በአማራጭ በሰጠው መልስ አመልካች የመለሳቸውን እቃዎች አስመልክቶ ክትትል አላደረገም በሚል መቀመጡ አማራጭ ክርክር ከሚሆን በቀር በፍ/ሕ/ቁጥር 1851(ሀ) መሰረት እዳውን አምኗል አያስብልም፡፡ እቃው ጉድለት አለበት በሚል ማሳወቅም ሆነ ጉድለት አለ በሚል እቃ መመለሱ መታመኑ በውጤት ደረጃ አንድ ስለሆነ በፍ/ሕ/ቁጥር 2298(1) መሰረት አመልካች በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ክስ ስላላቀረበ ክሱ በይርጋ ይታገዳል መባሉ ተገቢ መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 1 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልሱን ያቀረበ ሲሆን የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን የአመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት በስር ፍ/ቤት ከተደረጉ ክርክሮች፣ በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ለጉዳዩ ተገቢነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በዋናነት የሚከራከረው ተጠሪው ክርክር ያስነሳውን እቃ መልሶ መረከቡ እና በተለያዩ ጊዜያትም ከዛሬ ነገ አስተካክዬ አስረክባለው እያለ እንደነበር ባልተካደበት አስፈላጊ ከሆነም ምስክር ሊሰማ ሲገባ እንዲሁም ውሉ ሽያጭ ብቻ ሳይሆን የጥገና እና የመለዋወጫ እቃ አቅርቦት ጭምር ሆኖ እያለ ክሱ በአንድ አመት ይርጋ ይታገዳል መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ እቃውን መልሶ መቀበሉን በአማራጭ ክርክር ማቅረቡ እዳውን አምኗል የማያስብል እና አመልካች ጉድለት አለበት በሚል ማሳወቁም ሆነ እቃውን መመለሱ በውጤት ደረጃ ልዩነት ስለሌለው ክሱ በፍ/ሕ/ቁጥር 2298(1) መሰረት በይርጋ ይታገዳል ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆኑን ገልፆ ተከራክሯል፡፡

ገዢው ክስ ማቅረቡን የከለከለው የሻጩ አጭበርባሪነት ካልሆነ በቀር እቃው እንደ ውሉ ትክክል አለመሆኑን ወይም ጉድለት ያለበት መሆኑን ካስታወቀበት ቀን አንስቶ እስከ አንድ አመት ውስጥ ክስ ያላቀረበ እንደሆነ እቃው ጉድለት አለበት ወይም እንደ ውሉ የቀረበ አይደለም በማለት ክስ ማቅረብ የማይችል መሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 2298(1) ላይ ተመላክቷል፡፡ ይህም ማለት አንድ ገዢ የገዛው እቃ ላይ ጉድለት ያለበት ከሆነ ጉድለቱ ለሻጩ ባሳወቀ በአንድ አመት ውስጥ ጉድለቱ እንዲስተካከልለት ክስ ካላቀረበ ክሱ በይርጋ ይታገዳል፡፡ ነገር ግን ገዢው በዚህ አንድ አመት ውስጥ ክስ እንዳያቀርብ የሻጩ አጭበርባሪነት ከልክሎት ከሆነ ገዢው ጉድለት መኖሩን ካሳወቀ ከአንድ አመት በኋላም ቢሆን ጉድለቱ እንዲስተካከልለት ክስ ማቅረብ ይችላል፡፡ በሌላ አባባል የሻጩ የማጭበርበር ድርጊት የአንድ አመቱን የይርጋ ጊዜ ገደብ የሚያቋርጥ ምክንያት ይሆናል፡፡ የዚህ ድንጋጌ አላማ ሻጩ በፈጸመው የማጭበርበር ተግባር የወንጀል ድርጊት በመሆኑ በአንድ አመት ውስጥ ክስ አልቀረበም በሚል በወንጀል ድርጊቱ ተጠቃሚ እንዳይሆን ለመከላከል ነው፡፡ ይህ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማለት ግን የማጭበርበር ድርጊት ከተፈጸመ ምንም አይነት የክስ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ አይኖረውም ማለት አይደለም። የማጭበርበር ድርጊቱ እንደ ይርጋ ማቋረጫ ጊዜ ተወስዶ የአንድ አመቱ የይርጋ ጊዜ የማጭበርበር ድርጊቱ ከተፈጸመ ጊዜ ጀምሮ እንደአዲስ መቁጠር የሚጀምር ይሆናል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ሌላው መታየት ያለበት የሻጩ አጭበርባሪነት የሚለው አገላለጽ ምን አይነት እና መቼ የሚፈጸም የሻጩን ድርጊት የሚያመለክት ነው? የሚለው ሊሆን ይገባል። በፍ/ህ/ቁጥር 2297 ሻጩ የሸጠውን ነገር ጉድለቶች ያለበት መሆኑን ገዢው እንዳያውቃቸው በተንኮል ደብቋቸው ከሆነ ሻጩን ከሀላፊነት የሚያድኑ የውል ቃሎች ቢኖሩ ሻጩ ከተጠያቂነት ማምለጥ እንደማይችል ያመለክታል። ይህም ማለት ሻጩ ለገዢ በሸጣቸው ነገሮች ላይ ጉድለት መኖሩን እያወቀ በተንኮል በሸያጭ ወቅት ምንም አይነት ጉድለት እንደሌለባቸው አስመስሎ ከሸጠ ወይም ከሸያጭ በኋላም ቢሆን ጉድለቱ እንዳይታወቅ ለማድረግ ሻጩ የማጭበርበር ድርጊት የፈጸመ በመሆኑ ተጠያቂ የማያደርገው የውል ቃል እንኳን ቢኖር ውሉ ተፈጻሚ እንደማይሆን እና ሻጩ በኃላፊነት እንደሚጠየቅ የሚያመለክት ነው። የፍ/ህ/ቁጥር 2298/1 የፍ/ሕ/ቁጥር 2297 ተከታይ እንደመሆኑ ተጣምረው ሲነበቡ ሻጩ እቃውን ወይም የሚሸጠውን ነገር ለገዢ በሚሸጥበት ወይም በሚያስረክብበት ወቅት እቃው ጉድለት ያለበት መሆኑን እያወቀ ጉድለት እንደሌለ አድርጎ ወይም ጉድለቱ እንዳይታወቅ አድርጎ በማጭበርበር ለገዢ መሸጡ ወይም ማስረከቡ ከተረጋገጠ ክስ የማቅረቢያ ጊዜው በአንድ አመት ይርጋ የማይገደብ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። በተቃራኒው ሻጩ በሸያጭ ወይም በርክክብ ወቅት የፈጸመው የማጭበርበር ድርጊት ከሌለ ጉድለቱን ገዢው ለሻጭ ባሳወቀ በአንድ አመት ውስጥ ክስ ካላቀረበ ክሱ በይርጋ ይታገዳል ማለት ነው።

በተያዘው ጉደይ አመልካች ተጠሪው ከዛሬ ነገ እቃውን እጠግናለው በማለት የማጭበርበር ተግባር ስለፈጸመ ክሱ በይርጋ ተቋርጧል መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት የሚከራከር ቢሆንም ከላይ እንደተገለጸው በፍ/ሕ/ቁጥር 2298(1) የተገለፀው የማጭበርበር ተግባር እቃውን ከሚመለከት ዝርዝር መግለጫ ወይም በግብይቱ ጊዜ እቃው ጉድለት ያለበት መሆኑ እየታወቀ ይህን በመደበቅ ከተፈጸመ ተግባር ጋር የሚገናኝ ነው። ተጠሪ ከዛሬ ነገ እቃውን አስተካክላለሁ እያለ ቆይቶ ቢሆን እንኳን ተጠሪ የዋቢነት ሃላፊነቱን አለመወጣቱን የሚያሳይ እንጂ በግዢ ወቅት በእቃው ላይ ያለው ጉድለት በአመልካች እንዳይታወቅ የማጭበርበር ድርጊት መፈጸሙን የሚያመለክት አይደለም። ከግብይቱ በኋላ የተጠሪ ሰራተኛ ሰኔ 10 ቀን 2009 ዓ.ም UPS 5kg ለቼክአፕ መውሰዱ ጉድለቱን በግልፅ አምኗል የሚያስብል ካለመሆኑም በላይ ተጠሪ ጉድለቱን ለማስተካከል እቃውን ተቀብሏል ቢባል እንኳ በዚህ አግባብ ባለማስተካከሉ አመልካች ተጠሪ እቃውን ለማስተካከል ከተቀበለበት ጊዜ ጀምሮ በሕግ በተገለፀው አንድ አመት ጊዜ ውስጥ ክስ በመመስረት ዳኝነት ሊጠይቅ ይገባ ነበር። ከዚህ ጋር ተያይዞ አመልካች ተጠሪው ከዛሬ ነገ እቃውን አስተካክላለው በማለት ያጭበረበረኝ ስለመሆኑ ምስክሮቼ መሰማት ነበረባቸው በማለት የሚከራከር ቢሆንም በፍትሐብሄር ክርክር ማስረጃ የሚሰማው እና ፍሬ ነገር እንዲነጥር የሚደረገው ለጉዳዩ አወሳሰን የግድ አስፈላጊ ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም አመልካች ምስክሮቼ ሊሰሙ ይገባ ነበር በማለት የሚያቀርበው ቅሬታ ተገቢነት የለውም።

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በመጨረሻም አመልካች ለክሱ መነሻ ያደረገው የገዛዋቸው እቃዎች በውሉ መሰረት ተሟልተው የቀረቡ ባለመሆኑ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት አልቻሉም የሚል ሁኖ እያለ እና ውላችን የጥገና እና የመለዋወጫ አቅርቦትን ስለሚጨምር የፍ/ሕ/ቁጥር 2298 ለጉዳዩ ተፈጻሚነት የለውም በማለት የሚያነሳው መከራከሪያ ተገቢነት ስንመለከት አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ተጠሪው ጥገና እንዲያደርግልኝ ይወሰንልኝ የሚል ግልጽ ዳኝነት አልጠየቀም፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከመለዋወጫ እና ጥገና ውል ጋር የተያያዘ ክስ ባላቀረበበት የተጠቀሰው የይርጋ ድንጋጌ ተፈጻሚ ሊሆን አይገባም በሚል የሚያቀርበው መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ክስ ያቀረበው የሽያጭ ውልን መሰረት አድርጎ በተሸጠው እቃላይ አለ የሚለው ጉድለት በገንዘብ ወይንም በአይነት እንዲስተካከልለት በመሆኑ ለጉዳዩ የፍ/ሕ/ቁጥር 2298/1 ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

በመሆኑም አመልካች ተጠሪ እቃውን እንዲያስተካክል ያሳወቀው ጥቅምት 7 ቀን 2009 ዓ.ም መሆኑ እና ክሱ የቀረበው የካቲት 1 ቀን 2011 ዓ.ም መሆኑ ተረጋግጦ በይርጋ ይታገዳል ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ብይን ላይ እና ብይኑን በማጽናት በተሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁጥር 65181 ግንቦት 16 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 239590 ሐምሌ 22 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት ሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. አመልካች ለተጠሪ እንዲስተካከል ሰጥቻለሁ የሚለውን እቃ በተመለከተ ባለበት ሁኔታ ለማስመለስ ክስ ከማቅረብ ይህ ውሳኔ አያግደውም፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሄ/መ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 197009

ሀምሌ 28 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ኃይለጊዮርጊስ ይልማ፡- አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ አዲስ እሸቱ፡- አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች እና በስር ፍርድ ቤት ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተመለከቱት ተከሳሾች አከራካሪውን ቤት ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት የስር የጣርማ በር ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች መፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ መነሻ በማድረግ ሲሆን ተጠሪ በጣርማ በር ወረዳ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩ ሲሆን አመልካች 1ኛተከሳሽ ነበሩ፡፡

ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በአመልካች እና በስር ፍርድ ቤት ከ1ኛ እስከ 3ኛ በተመለከቱት ተከሳሾች ላይ ባቀረቡት ክስም አዋሳኙ በክሱ ላይ የተመለከተውን 400 ካሜ ላይ ያረፈ መኖሪያ ቤት ከነሰርቪሱ የካቲት 27 ቀን 2011 ዓም በተደረገ የሽያጭ ውል ከ1ኛ እስከ 3ኛ ከተመለከቱት ተከሳሾች በብር 200,000.00 ገዝቼ ካርታ በስሜ የተሰጠኝ ቢሆንም ቤቱን ከአመልካች ነፃ በማድረግ ያላስረከቡኝ በመሆኑ ፣አመልካችም በአደራ ይገፉ የምጠቀመው ነው በማለት ምንም መብት ሳይኖረው ለማስረከብ ፍቃደኛ ስላልሆነ ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተመለከቱት ተከሳሾች ቤትና ይዞታውን ከ3ኛ ወገን ነፃ አድርገው

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እንዲያስረክቡኝ አመልካችም የፈጠረውን ሁከት አቁሞ ቤትና ቦታውን እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

አመልካች በሰጡት መልስም አዋሳኙ በክሱ ላይ በተጠቀሰው ቦታ ላይ ያለውን ሰርቪስ ቆርቆሮ ቤትና ለሱቅ እና ለሻይ ቤት አገልግሎት የሚውለውን ከ28 አመት በላይ ከእሸቴ ወዳጆ ጋር በቤተሰብ አባልነት ስኖር እንድሰራ ፈቅደውልኝ የሰራሁት ከመኖሪያ ቤቱ አዋሳኝ ሆኖ የተለየ መግቢያና መውጫ ያለው የቤት ቁጥራችንም ቢሆን የኔ 151 ሆኖ የሚች 153 በመሆን የተመዘገበ በመሆኑ ግንባታውን ሳከናውንም የተቃወመኝ ባለመኖሩ ፤የስር ተከሳሾች በውርስ ያላገኙትን ለተጠሪ መሸጣቸው አግባብ ባለመሆኑ ፤ለ28 አመት በእጄ በቆየው ንብረት ላይ ክስ ለማቅረብም ይርጋ ስለሚያግዳቸው በግል የያዝኩትን ቤትና ቦታ ላስረክብ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቶ ተገቢውን ማጣራት አድርጎ በሰጠው ውሳኔም ማዘጋጃ ቤቱ በሰጠው ምላሽ 400 ካሜ ላይ ያረፈው ቤትና ቦታ ስመ ንብረቱ በሚች እሸቴ ወዳጆ ስም የነበረ፤አቶ እሸቴ ከሞቱ በኋላም ከ1ኛ እስከ 3ኛ በተመለከቱት ተከሳሾች ስም የተመዘገበና ግብሩም በነዚሁ ተከሳሾች ስም የሚከፈል መሆኑን የገለፀ መሆኑ አመልካች ቤቱን በማያሻማና ግልፅ በሆነ ሁኔታ የግሌ ነው ብሎ አለመያዙንና አለመገልገሉን የሚያሳይ መሆኑን ፤ተጠሪ ቦታውንና ቤቱን ሲገዛ በስር ተከሳሾች ስም መሆኑን አረጋግጦ መሆኑን የሰነድ ማስረጃዎቹ የሚያሳዩ መሆኑን ፤ማዘጋጃ ቤቱ የሰጠው ምላሽም ሽያጩ አመልካች የግሌ ነው የሚለውን ቤትና ቦታ የሚጨምር ፤መግቢያና መውጪያውም አንድ መሆኑን የሚያረጋግጥ በመሆኑ ፤አመልካችና በስር ፍርድ ቤት ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተመለከቱት ተከሳሾች ክስ የቀረበበትን ቤትና ቦታ ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ይግባኙን በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.337 መሰረት የሠረዘው ሲሆን ፤የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር አጣሪ ችሎትም በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም ምስክሮቼ ቤቱን ወላጅ አባቴ በ1984 ዓም መስራቱን አስረድተው እያለ የተጠሪ ምስክሮች ይህንን ባላስተባበሉበት የስር ፍርድ ቤት በህጉ የተቀመጠውን የማስረጃ ምዘና መርህ ሳይከተል ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤አባቴ ከ1984 ዓም ጀምሮ አከራካሪውን ቤትና ቦታ ውሳኔው እስከተሰጠበት የካቲት 12 ቀን 2012 ዓም ድረስ በቁጥጥሩ ስር አድርጎ የሚጠቀምበት ሆኖ እያለ የይርጋ መቃወሚያው በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሳይሰጥበት መታለፉ አግባብነት የለውም፤ማዘጋጃ ቤቱ መውጪያና መግቢያው አንድ ነው በማለት የሰጠው ምላሽ እውነታውን የደበቀ በመሆኑ ሊያዝ አይገባም በማለት የተከራከርኩ በመሆኑ በግለልተኛ ባለሙያ ሊጣራ ሲገባ ጥያቄዬ ውድቅ መደረጉ አግባብ አይደለም፤ባለመሬቱ ሳይቃወም በሌላ ሰው መሬት ላይ ህንፃ የሰራ ሰው የዚህ ህንፃ ባለቤት ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1179(1)

የተመለከተ ሆኖ እያለ ሟች አባቴ ግንባታውን ያከናወኑት ሟች እሸቴ ፈቅደውለት ሆኖ እያለ ፣በሰበር መ/ቁ.96628 በተሰጠ አስገዳጅ ውሳኔበዚህ አግባብ የተገነባ ቤት የውርስ ሀብቱ አካል ሊሆን እንደማይገባ ተመልክቶ እያለ ለኔ በውርስ ሊተላለፍ የሚገባውን ሟች አባቴ በስጦታ ያገኘውን ቤትና ቦታ በማካተት የተደረገው የሽያጭ ውል የህግ መሰረት የለውም ተብሎ ሊፈርስ ይገባል ተብሎ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሸሮ አከራካሪው ቦታና ቤት ለአመልካች ሊተላለፍ ይገባል ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በስር ፍርድ ቤቶች የስር 1ኛ ፣2ና እና 3ኛ ተከሳሾች አውራሽ የአመልካችን አባት በህይወት እያለ ሳይቃወሟቸው ቤት ሰርተው ሲኖሩበት የነበረ መሆን አለመሆኑ የተረጋገጠበትን እና አመልካች ቤቱን ለቀው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የተወሰነበትን አግባብ ከማስረጃ ምዘና መሰረታዊ መርህ እና ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1179 እና ተከታታይ ድንጋጌዎች አንፃር ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

ተጠሪ በሰጡት መልስም የቀረበው አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚሉባቸውን ዝርዝር ሁኔታዎች በመዘርዘር የሰበር አቤቱታው ውድቅ ተደርጎ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፣ ከተገቢው ህግና፣ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡ በመሰረቱ አንድ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ወገኖች የተለያዩበትን የህግ ወይም የፍሬ ነገር አግባብ ምን እንደሆነ በመለየት ለጉዳዩ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችለውን ሞጉጥ መያዝ ያለበት መሆኑን የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.246(2) የሚደነግግ ሲሆን እነዚህ የተያዙ ሞጉጦችን አስመልክቶ የአንዱ ሞጉጥ መወሰን ሌሎቹንም ያጠቃልላቸዋል ብሎ ፍርድ ቤቱ ካልገመተ በስተቀር እየአንዳንዱ ሞጉጥ በህጉ አግባብ ተመርምሮ እልባት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን ከፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.182(3) ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡አሁን በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ክርክር በተነሳበት ቤት ላይ በግዢ ያገኙት መብት እንዲከበርላቸው ላቀረቡት ክስ አመልካች በህግ የተቋቋመ መብት ያላቸው መሆኑን በመግለፅ የተከራከሩ ሲሆን ለዚህም መሰረቱ ቤቱን አባታቸው የሰሩት አቶ እሸቴ ወዳጆ ፈቅደውላቸው መሆኑን የቤቱን ግንባታ ሲያከናውኑም የተቃወማቸው ሰው አለመኖሩን በመግለፅ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1179(1) አግባብ ክርክር ያቀረቡ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ክርክር የሚያሳይ ቢሆንም የስር ፍርድ ቤት በዚህ አግባብ የቀረበውን ክርክር መሰረት አድርጎ ተገቢውን ሞጉጥ በመያዝ ለግራ ቀኙ ክርክር እልባት መስጠቱን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያሳይም፡፡

የስር ፍርድ ቤት የአመልካች አባት አከራካሪውን ቤት የሰሩ መሆኑን ግንባታውን ሲያከናውኑም በስር ከ1ኛ እስከ 3ኛ ተከሳሾች አውራሽ ተፈቅዶላቸው መሆኑን ገልፀው የተከራከሩ በመሆኑ የግራ ቀኙ ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል ከዚሁ ክርክር አንፃር በመመርመር የአመልካች አባት አከራካሪውን ቤት ሰርተዋል? ወይስ አልሰሩም? ሰርተዋል ከተባለስ የሰሩት በአቶ እሸቴ ወዳጆ ተፈቅዶላቸው ነውን? ተፈቅዶላቸው ከሰሩስ ግንባታውን ተፈቅዶላቸው መስራታቸው በተለይም በግር ውል ይዞታውን ካገኙት ተጠሪ አንፃር በገነቡት ቤት ላይ የሚያገኙት መብት ይኖራልን? ተፈቅዶላቸው ያልሰሩ ከሆነስ ግንባታውን ሲያከናውኑ የቀረበ ተቃውሞ ነበርን? ውጤቱስ ምን ሊሆን ይገባል? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ለግራ ቀኙ ክርክር ተገቢውን እልባት ሊሰጥ ሲገባ የግራ ቀኙን መሰረታዊ የክርክር ነጥብ ሳያጣራ ማዘጋጃ ቤቱ በሰጠው ምላሽ 400 ካሜ ላይ ያረፈው ቤትና ቦታ ስመ ንብረቱ በሚች እሸቴ ወዳጆ ስም የነበረ መሆኑን ፣አቶ እሸቴ ከሞቱ በኋላም ከ1ኛ እስከ 3ኛ በተመለከቱት ተከሳሾች ስም የተመዘገበና ግብሩም በነዚሁ ተከሳሾች ስም የሚከፈል መሆኑን የገለፀ መሆኑን መነሻ በማድረግ አመልካች ቤቱን በማያሻማና ግልፅ በሆነ ሁኔታ የግሌ ነው ብሎ አለመያዛቸውንና አለመገልገላቸውን በመጥቀስ ፣ተጠሪ ቦታውንና ቤቱን ሲገዛ በስር ተከሳሾች ስም መሆኑን አረጋግጦ መሆኑን የሰነድ ማስረጃዎቹ የሚያሳዩ መሆኑን ፣ማዘጋጃ ቤቱ የሰጠው ምላሽም ሽያጩ አመልካች የግሌ ነው የሚለውን ቤትና ቦታ የሚጨምር መሆኑንና መግቢያና መውጪያውም አንድ መሆኑን በመጥቀስ አመልካች ከፍ/ብ/ህ/ቁ.1179 አንፃር ያቀረቡትን ክርክር በአግባቡ ሳይመረምር አከራካሪውን ቤትና ቦታ ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የጣርማ በር ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.0120263 በ12/06/2012 ዓም የሰጠው ፍርድና ይህንን ፍርድ በማፅናት የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.0133151 ግንቦት 25 ቀን 2012 ዓም እንዲሁም የአ/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.03-11754 ጥቅምት 06 ቀን 2012 ዓም የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የጣርማ በር ወረዳ ፍርድ ቤት መዝገቡን እንደገና በማንቀሳቀስ የአመልካች አባት አከራካሪውን ቤት ሰርተዋል? ወይስ አልሰሩም?ሰርተዋል ከተባለስ ቤቱን የሰሩት በአቶ እሸቴ ወዳጆ ተፈቅዶላቸው ነው? ወይስ አይደለም? ተፈቅዶላቸው ከሰሩስ ግንባታውን ተፈቅዶላቸው መስራታቸው በተለይም በግር ውል ይዞታውን ካገኙት ተጠሪ አንፃር በገነቡት ቤት ላይ የሚያገናዕፉቸው መብት ይኖራልን? ተፈቅዶላቸው ያልሰሩ ከሆነስ ግንባታውን ሲያከናውኑ የቀረበ ተቃውሞ ነበርን? ተቃውሞ ካልቀረበስ ተቃውሞ ሳይቀርብባቸው የገነቡትን ቤት ለተጠሪ ለቀው ሊያስረክቡ ይገባል?ወይስ አይገባም? የሚሉትንና ተያያዥ ጭብጦች በመያዝ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የሰነድ ማስረጃዎች አስቀርቦ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በመመርመር በህጉ አግባብ የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡

3. በጣርማ በር ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.01- 20263 በተጀመረው አፈፃፀም ላይ ጥቅምት 27 ቀን 2013 ዓም የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ እና ታህሳስ 07 ቀን 2013 ዓ.ም አከራካሪው ይዞታና ቦታ ላይ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
4. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

<u>በግራ ቀኙ መሃል ያለው ክርክር ተገቢውን እልባት ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡</u>

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ን

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-197008

ቀን፡- 05/02/2014 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- አዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን - ጠበቃ መኮንን ይማም ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ፀጋ ረታ አስመጪ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ክርክሩ የሽያጭ ውልን መነሻ ያደረገ ሲሆን ጉዳዩ በተጀመረበት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የካቲት 4 ቀን 2011 ዓ.ም ባቀረበው ክስ አመልካች የኮምፒዩተር እቃዎችን ለመግዛት ባወጣው ጨረታ ተጠሪ አሸንፎ እቃዎቹን አቅርቦ ክፍያ የተቀበለ ቢሆንም እቃዎቹን ከሰርቨሩ ጋር የሚያገናኙ ኬብሎችን ባለማቅረቡ ምክንያት እቃዎቹ የተፈለገውን አገልግሎት መስጠት አልቻሉም፡፡ በመሆኑም ኬብሎቹን እንዲያቀርብ ወይም በወቅቱ የገበያ ዋጋ የእቃዎቹን ግምት ብር 182,900 ወጪና ኪሳራን ጨምሮ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተጠሪ የካቲት 29 ቀን 2011 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች እቃዎቹ ጉድለት ያለባቸው መሆኑን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ1 አመት ውስጥ ክስ ስላላቀረበ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመቃወሚያው ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ግንኙነታቸው የሽያጭ ውልን መሰረት ያደረገ ስለሆነ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው ስለውሎች በጠቅላላው የተደነገገው የፍ/ሕ/ቁጥር 1845 ሳይሆን የሽያጭ ውልን የሚመለከተው የፍ/ሕ/ቁጥር 2298(1) ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረትም በሻጩ አጭበርባሪነት ካልሆነ በቀር ገዢው ጉድለቱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ1 ዓመት ጊዜ ውስጥ ክስ ማቅረብ አለበት፡፡ አመልካች የተጠሪ አጭበርባሪነት ያለበት ስለመሆኑ በክሱ ያልገለፀ ሲሆን ተጠሪው የእቃዎቹን ጉድለት እንዲያስተካክል ያሳወቀው ጥቅምት 7 ቀን 2009 ዓ.ም እንዲሁም ለተረከባቸው እቃዎች ክፍያ የፈጸመው ጥቅምት 25 ቀን 2009 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ የቀረበው ሁለት ኣመት ካለፈው በኂላ የካቲት 4 ቀን 2011 ዓ.ም ነው፡፡ የተጠሪ ሰራተኛ ሰኔ 10 ቀን 2009 ዓ.ም UPS 5kg ለቼክአፕ መውሰዱ ጉድለቱን በግልፅ አምኗል አያስብልም፡፡ አምኗል ቢባል እንኳ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በ1 ዓመት ውስጥ ክሱ ስላልቀረበ በይርጋ ይተጋዳል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት በማፅናቱ ጥቅምት 13 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታውን አቅርቧል፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ አመልካች በክሱ ላይ ፍሬ ነገርን ከመግለፅ በዘለለ ተጠሪው መቃወሚያ ሊያቀርብ ይችላል ብሎ በማሰብ በክስ መስማት ወቅት ሊያቀርብ የሚችለውን መከራከሪያ አስቀድሞ ማቅረብ ግዴታ በሌለበት ተጠሪው የማታለል እና የማጭበርበር ተግባር ስለመፈፀሙ አመልካች በክሱ አልገለፀም መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ተጠሪ እቃዎቹን አስተካክላለው ብሎ መውሰዱን አልካደም፡፡ የወሰደውም እቃውን ባስረከበ በአንድ ዓመት ውስጥ ሲሆን እቃውን በእምነት በመውሰድ በተግባር የማታለል እና የማጭበርበር ተግባር የፈፀመ ሲሆን እቃዎቹን አስተካክሎ የሚያቀርብበት ጊዜም ስላልተወሰነ እና እቃዎቹን አስተካክሎ እንዲያስረክብ በተደጋጋሚ በአመልካች ሲጠየቅ ከዛሬ ነገር አስተካክዬ እመልሳለው ማለቱ ስላልተካደ አስፈላጊ ከሆነም ምስክሮቻችንን በመስማት ሊጣራ ሲገባ ክሱ በይርጋ ይታገዳል መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ውሉ የሽያጭ ብቻ ሳይሆን የጥገና ማደስና መለዋወጫ ማቅረብ መሆኑ በሰነድ ተረጋግጦ እያለ ሽያጭ ብቻ ነው ተብሎ የሽያጭ ሕግ የይርጋ ድንጋጌ ተግባራዊ መደረጉ እንዲሁም እቃው በተጠሪ እጅ ያለ በመሆኑ አመልካች በማንኛውም ጊዜ ንብረቱን መጠየቅ የሚችል ሁኖ እያ ክሱ በይርጋ ይታገዳል መባሉ የፍ/ሕ/ቁጥር 1206 እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 63600 ቅፅ 10 የሰጠውን ውሳኔ የሚቃረን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ነው፡፡

አቤቱታው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ተጠሪ የእቃውን ጉድለት አምኖ መልሶ መቀበሉን ለክሱ በሰጠው መልስ አምኖ እያለ ክሱ በአንድ አመት ይርጋ ይታገዳል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ከፍ/ሕ/ቁጥር

2298(1) እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ ለመመርመር ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልሱን እንዲያቀርብ ታዟል፡፡

ተጠሪም ጥር 10 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱ ይዘት ባጭሩ ተጠሪ ለክሱ በአማራጭ በሰጠው መልስ አመልካች የመለሳቸውን እቃዎች አስመልክቶ ክትትል አላደረገም በሚል መቀመጡ አማራጭ ክርክር ከሚሆን በቀር በፍ/ሕ/ቁጥር 1851(ሀ) መሰረት እዳውን አምኗል አያስብልም፡፡ እቃው ጉድለት አለበት በሚል ማሳወቅም ሆነ ጉድለት አለ በሚል እቃ መመለሱ መታመኑ በውጤት ደረጃ አንድ ስለሆነ በፍ/ሕ/ቁጥር 2298(1) መሰረት አመልካች በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ክስ ስላላቀረበ ክሱ በይርጋ ይታገዳል መባሉ ተገቢ መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 1 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልሱን ያቀረበ ሲሆን የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን የአመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት በስር ፍ/ቤት ከተደረጉ ክርክሮች፣ በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ለጉዳዩ ተገቢነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በዋናነት የሚከራከረው ተጠሪው ክርክር ያስነሳውን እቃ መልሶ መረከቡ እና በተለያዩ ጊዜያትም ከዛሬ ነገ አስተካክዬ አስረክባለው እያለ እንደነበር ባልተካደበት አስፈላጊ ከሆነም ምስክር ሊሰማ ሲገባ እንዲሁም ውሉ ሽያጭ ብቻ ሳይሆን የጥገና እና የመለዋወጫ እቃ አቅርቦት ጭምር ሆኖ እያለ ክሱ በአንድ አመት ይርጋ ይታገዳል መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ እቃውን መልሶ መቀበሉን በአማራጭ ክርክር ማቅረቡ እዳውን አምኗል የማያስብል እና አመልካች ጉድለት አለበት በሚል ማሳወቁም ሆነ እቃውን መመለሱ በውጤት ደረጃ ልዩነት ስለሌለው ክሱ በፍ/ሕ/ቁጥር 2298(1) መሰረት በይርጋ ይታገዳል ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆኑን ገልፆ ተከራክሯል፡፡

ገዢው ክስ ማቅረቡን የከለከለው የሻጩ አጭበርባሪነት ካልሆነ በቀር እቃው እንደ ውሉ ትክክል አለመሆኑን ወይም ጉድለት ያለበት መሆኑን ካስታወቀበት ቀን አንስቶ እስከ አንድ አመት ውስጥ ክስ ያላቀረበ እንደሆነ እቃው ጉድለት አለበት ወይም እንደ ውሉ የቀረበ አይደለም በማለት ክስ ማቅረብ የማይችል መሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 2298(1) ላይ ተመላክቷል፡፡ ይህም ማለት አንድ ገዢ የገዛው እቃ ላይ ጉድለት ያለበት ከሆነ ጉድለቱ ለሻጩ ባሳወቀ በአንድ አመት ውስጥ ጉድለቱ እንዲስተካከልለት ክስ ካላቀረበ ክሱ በይርጋ ይታገዳል፡፡ ነገር ግን ገዢው በዚህ አንድ አመት ውስጥ ክስ እንዳያቀርብ የሻጩ አጭበርባሪነት ከልክሎት ከሆነ ገዢው ጉድለት መኖሩን ካሳወቀ ከአንድ አመት በኋላም ቢሆን ጉድለቱ እንዲስተካከልለት ክስ ማቅረብ ይችላል፡፡ በሌላ አባባል የሻጩ የማጭበርበር ድርጊት የአንድ አመቱን የይርጋ ጊዜ ገደብ የሚያቋርጥ ምክንያት ይሆናል፡፡ የዚህ ድንጋጌ አላማ ሻጩ በፈጸመው የማጭበርበር ተግባር የወንጀል ድርጊት በመሆኑ በአንድ አመት ውስጥ ክስ አልቀረበም በሚል በወንጀል ድርጊቱ ተጠቃሚ እንዳይሆን ለመከላከል ነው፡፡ ይህ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማለት ግን የማጭበርበር ድርጊት ከተፈጸመ ምንም አይነት የክስ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ አይኖረውም ማለት አይደለም። የማጭበርበር ድርጊቱ እንደ ይርጋ ማቋረጫ ጊዜ ተወስዶ የአንድ አመቱ የይርጋ ጊዜ የማጭበርበር ድርጊቱ ከተፈጸመ ጊዜ ጀምሮ እንደአዲስ መቁጠር የሚጀምር ይሆናል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ሌላው መታየት ያለበት የሻጩ አጭበርባሪነት የሚለው አገላለጽ ምን አይነት እና መቼ የሚፈጸም የሻጩን ድርጊት የሚያመለክት ነው? የሚለው ሊሆን ይገባል። በፍ/ህ/ቁጥር 2297 ሻጩ የሸጠውን ነገር ጉድለቶች ያለበት መሆኑን ገዢው እንዳያውቃቸው በተንኮል ደብቋቸው ከሆነ ሻጩን ከሀላፊነት የሚያድኑ የውል ቃሎች ቢኖሩ ሻጩ ከተጠያቂነት ማምለጥ እንደማይችል ያመለክታል። ይህም ማለት ሻጩ ለገዢ በሸጣቸው ነገሮች ላይ ጉድለት መኖሩን እያወቀ በተንኮል በሸያጭ ወቅት ምንም አይነት ጉድለት እንደሌለባቸው አስመስሎ ከሸጠ ወይም ከሸያጭ በኋላም ቢሆን ጉድለቱ እንዳይታወቅ ለማድረግ ሻጩ የማጭበርበር ድርጊት የፈጸመ በመሆኑ ተጠያቂ የማያደርገው የውል ቃል እንኳን ቢኖር ውሉ ተፈጻሚ እንደማይሆን እና ሻጩ በኃላፊነት እንደሚጠየቅ የሚያመለክት ነው። የፍ/ህ/ቁጥር 2298/1 የፍ/ሕ/ቁጥር 2297 ተከታይ እንደመሆኑ ተጣምረው ሲነበቡ ሻጩ እቃውን ወይም የሚሸጠውን ነገር ለገዢ በሚሸጥበት ወይም በሚያስረክብበት ወቅት እቃው ጉድለት ያለበት መሆኑን እያወቀ ጉድለት እንደሌለ አድርጎ ወይም ጉድለቱ እንዳይታወቅ አድርጎ በማጭበርበር ለገዢ መሸጡ ወይም ማስረከቡ ከተረጋገጠ ክስ የማቅረቢያ ጊዜው በአንድ አመት ይርጋ የማይገደብ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። በተቃራኒው ሻጩ በሸያጭ ወይም በርክክብ ወቅት የፈጸመው የማጭበርበር ድርጊት ከሌለ ጉድለቱን ገዢው ለሻጭ ባሳወቀ በአንድ አመት ውስጥ ክስ ካላቀረበ ክሱ በይርጋ ይታገዳል ማለት ነው።

በተያዘው ጉደይ አመልካች ተጠሪው ከዛሬ ነገ እቃውን እጠግናለው በማለት የማጭበርበር ተግባር ስለፈጸመ ክሱ በይርጋ ተቋርጧል መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት የሚከራከር ቢሆንም ከላይ እንደተገለጸው በፍ/ሕ/ቁጥር 2298(1) የተገለፀው የማጭበርበር ተግባር እቃውን ከሚመለከት ዝርዝር መግለጫ ወይም በግብይቱ ጊዜ እቃው ጉድለት ያለበት መሆኑ እየታወቀ ይህን በመደበቅ ከተፈጸመ ተግባር ጋር የሚገናኝ ነው። ተጠሪ ከዛሬ ነገ እቃውን አስተካክላለሁ እያለ ቆይቶ ቢሆን እንኳን ተጠሪ የዋቢነት ሃላፊነቱን አለመወጣቱን የሚያሳይ እንጂ በግዢ ወቅት በእቃው ላይ ያለው ጉድለት በአመልካች እንዳይታወቅ የማጭበርበር ድርጊት መፈጸሙን የሚያመለክት አይደለም። ከግብይቱ በኋላ የተጠሪ ሰራተኛ ሰኔ 10 ቀን 2009 ዓ.ም UPS 5kg ለቼክአፕ መውሰዱ ጉድለቱን በግልፅ አምኗል የሚያስብል ካለመሆኑም በላይ ተጠሪ ጉድለቱን ለማስተካከል እቃውን ተቀብሏል ቢባል እንኳ በዚህ አግባብ ባለማስተካከሉ አመልካች ተጠሪ እቃውን ለማስተካከል ከተቀበለበት ጊዜ ጀምሮ በሕግ በተገለፀው አንድ አመት ጊዜ ውስጥ ክስ በመመስረት ዳኝነት ሊጠይቅ ይገባ ነበር። ከዚህ ጋር ተያይዞ አመልካች ተጠሪው ከዛሬ ነገ እቃውን አስተካክላለው በማለት ያጭበረበረኝ ስለመሆኑ ምስክሮቼ መሰማት ነበረባቸው በማለት የሚከራከር ቢሆንም በፍትሐብሄር ክርክር ማስረጃ የሚሰማው እና ፍሬ ነገር እንዲነጥር የሚደረገው ለጉዳዩ አወሳሰን የግድ አስፈላጊ ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም አመልካች ምስክሮቼ ሊሰሙ ይገባ ነበር በማለት የሚያቀርበው ቅሬታ ተገቢነት የለውም።

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በመጨረሻም አመልካች ለክሱ መነሻ ያደረገው የገዛዋቸው እቃዎች በውሉ መሰረት ተሟልተው የቀረቡ ባለመሆኑ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት አልቻሉም የሚል ሁኖ እያለ እና ውላችን የጥገና እና የመለዋወጫ አቅርቦትን ስለሚጨምር የፍ/ሕ/ቁጥር 2298 ለጉዳዩ ተፈጻሚነት የለውም በማለት የሚያነሳው መከራከሪያ ተገቢነት ስንመለከት አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ተጠሪው ጥገና እንዲያደርግልኝ ይወሰንልኝ የሚል ግልጽ ዳኝነት አልጠየቀም፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከመለዋወጫ እና ጥገና ውል ጋር የተያያዘ ክስ ባላቀረበበት የተጠቀሰው የይርጋ ድንጋጌ ተፈጻሚ ሊሆን አይገባም በሚል የሚያቀርበው መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ክስ ያቀረበው የሽያጭ ውልን መሰረት አድርጎ በተሸጠው እቃላይ አለ የሚለው ጉድለት በገንዘብ ወይንም በአይነት እንዲስተካከልለት በመሆኑ ለጉዳዩ የፍ/ሕ/ቁጥር 2298/1 ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

በመሆኑም አመልካች ተጠሪ እቃውን እንዲያስተካክል ያሳወቀው ጥቅምት 7 ቀን 2009 ዓ.ም መሆኑ እና ክሱ የቀረበው የካቲት 1 ቀን 2011 ዓ.ም መሆኑ ተረጋግጦ በይርጋ ይታገዳል ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ብይን ላይ እና ብይኑን በማጽናት በተሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁጥር 65181 ግንቦት 16 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 239590 ሐምሌ 22 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት ሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. አመልካች ለተጠሪ እንዲስተካከል ሰጥቻለሁ የሚለውን እቃ በተመለከተ ባለበት ሁኔታ ለማስመለስ ክስ ከማቅረብ ይህ ውሳኔ አያግደውም፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሄ/መ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም